የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች

የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት

ዓመታዊ ሪፖርት

ጥራዝ 1

ግንቦት/2008

አዲስ አበባ

ማውጫ

ገጽ

1. መግቢያ 1

2. ኦዲት በተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተገኙ
   ዋና ዋና ግኝቶች የተጠቃለለ ሪፖርት /Summery Report 3

3. የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በዘርፍ የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርት

   3.1 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን 35

   3.2 የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች 109

   3.3 የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች 132

   3.4 የልማትና ማህበራዊ አገልግሎት መ/ቤቶች 196

   3.5 የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች 290

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ዓመታዊ ሪፖርት

I. መግቢያ

የዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግስተ አንቀጽ 101 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

- የፌዴራሉን መንግሥት ዕቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወጡት ሕጐች፣ በአስፈጻሚው አካል በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መሰብሰቡን፣ መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ፣
- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የፋይናንስና ህጋዊነት፣ የክዋኔና የአካባቢ ጥበቃ፣ ኦዲቶች እና ልዩ ኦዲቶችን ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩ ለክልልና ለፌዴራል መንግሥት ሠራተኞችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ የሚመረመርበትን የኦዲት ደረጃ /ስታንዳርድ/ ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

ናቸው፡፡

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲችል የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግስታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጐማዎች ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፡
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል ወይም ያስደርጋል፣
- በፌዴራል መንግሥቱ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን ኦዲት ያደርጋል ወይም ያስደርጋል፣
- ማናቸውም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት እና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊው የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ምስክርነት ይሰጣል፣
- ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥትና የክልል መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል አስፈላጊውንም ቁጥጥር ያደርጋል፣
- ከክልል መንግሥታት የኦዲት መ/ቤቶች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፣

ይህንኑ ስልጣን መሰረት በማድረግ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት ለማከናወን ለፋይናንስና የህጋዊነት ኦዲት በእንጌጅሜንት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በ4 የኦዲት ዳይሬክቶሬቶች፡- የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች፤ የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች፤ የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች እና የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች እና በ2 የክዋኔ ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች፤ እንዲሁም በክልል መንግስታት የተከናወነው

የመሰረታዊ አገልገሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲት ለማከናወን በ1 የድጋፍና ድጎማ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በመደራጀት የኦዲቱ ስራ ተከናውኗል፡፡

ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት በዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች እና ኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሳብ መዛግብት እና ሰነዶች እንዲሁም የሂሳብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

በሪፖርት ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሃሳቦች፣ ኦዲት የተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን፣ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በመገምገም በተከታታይ ኦዲት በማድረግ የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተከናወነው የኦዲት ሥራ እንዳለቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊዎች በኦዲት ግኝቶች ላይ የመውጫ ውይይት (Exit Conference) ከመደረጉ ሌላ የኦዲት ሪፖርቱ ለእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ የፌዴራል መ/ቤትና ተቆጣጣሪ መ/ቤት እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ለሥራ አመራር ሪፖርት መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን መልስና አስተያየት ያገናዘበ ነው፡፡

መ/ቤታችን በሚከተለው የኦዲት ጊዜ አቆጣጠር ከየካቲት 1/2007 እስከ ጥር 30/2008 ዓ.ም(በጊዜያዊነት የተስተካከለ) የ145 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በመከናወን የኦዲት ሪፖርቶቹ ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶችና ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል።

II. ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች

ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙት የጥሬ ገንዘብና ሌሎች የአሰራርና የአፈፃፀም ጉድለቶች በርካታ ሲሆኑ፣ እነዚህ ጉድለቶች በዚሁ ጥራዝ ከገጽ 39 ጀምሮ በየኦዲት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በተደራጁ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አንጻር የታዩት ዋና ዋና ግኝቶችና የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች ተጠቃለው ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

1. <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ኦዲት</u>

1.1 <u>የጥሬ ገንዘብ ጉድለት</u>

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ3 መ/ቤቶች ብር 196,544.65 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 3 ተመልክቷል/

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል የሚታይ ልዩነት በ6 መ/ቤቶች ቆጠራው በብር 284,971.53 በማነስ የሚታይ ሲሆን፣ በ6 መ/ቤቶች ብር 2,034,074.93 በመብለጥ የሚታይ መሆኑ ታውቋል ፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ - 4 ተመልክቷል/

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካና የታየው ልዩነትም ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.2 <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመት የታባቸው መ/ቤቶች</u>

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፤ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ26 መ/ቤቶችና ለተለያዩ መ/ቤቶች ተጠሪ የሆኑ በ12 ቅ/ጽ/ቤቶች የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡/የመ/ቤቶቹ ዝርዝር አባሪ- 5/ሀ-ሠ ተመልክቷል፡፡/

ከሚታዩት ዋና ዋና የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች፤

- የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማያደርጉና ሂሣብ ከመዝገብ (ሌጀር) ጋር የማይመሳከርና የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ያልተዘጋጀ፣

- የባንክ መግለጫ እና የባንክ ሌጀር/ሪፖርት ልዩነት በ1 ቅ/ጽ/ቤት ብር 1,288,779.61 በማነስና በ1 ሌላ ቅ/ጽ/ቤት ብር 3,532,677.21 በመብለጥ የሚታይ መሆኑ፣
- የሰበሰቡትን ጥሬ ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ወይም ለዋና ገ/ያዥ ያላስገቡ በ5 መ/ቤቶች ብር 7,343,636.39 መገኘቱ፣
- በ15 መ/ቤቶች ብር 11,286,212.23 በክፍያ መመሪያ ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ በጥሬ ገንዘብ ወይም በቼክ ወጪ የተደረገ ሂሳብ የተገኘባቸው፣
- የተጣራ ሀብት መደበኛ ያልሆነ ሚዛን የሚያሳይ /ዴቢት/ በ6 መ/ቤቶች ብር 46,860,929.52 መገኘቱ፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፤ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወቅቱ ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር፤ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በየወሩ እንዲዘጋጅ፤ እንዲሁም በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከቆጠራው ጋር በየወቅቱ ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2. <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

2.1. <u>በደንቡ መሰረት ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች</u>

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ፣ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዢ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ94 መ/ቤቶች እና በ11 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 2,078,949,440.60 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ /በዝርዝሩ በአባሪ-6 ተመልክቷል/ ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	607,800,407.15
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	886,900,744.18
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	205,888,263.11
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	378,371,326.16
ጠ/ድምር	ብር	2,078,949,440.60

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት፤የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 342,235,704.80 ፣ የትምህርት ሚኒስቴር ብር 315,133,460.41 ፣ በብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ብር 172,191,236.99 ፣ የሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 139,258,386.16፤ ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ 138,482,895.82፣ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 85,982,359.92 የግብርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጣና ማስተባበሪያ ብር 75,882,513.81 እና ሀረማያ ዩኒቨርስቲ 69,010,479.00 ይገኙበታል፡፡

ይህ የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ ከዓመት ወደ ዓመት እየተንከባለለ በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ሲሆን፤ በተወሰኑ መ/ቤቶች መሻሻል የሚታይ ቢሆንም የአንዳንዶቹ እየጨመረ የሄደና በአብዛኛው ቀደም ባሉት ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ እንዲወራረድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም ሂሳቡ እንዲወራረድ ያልተደረጉ ናቸው፡፡

በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቢን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2.2. በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች

- ለተሰብሳቢ ሂሳብ ሌጀር ያልተዘጋጀ በ4 መ/ቤቶች ብር 174,023,890.94 መገኘቱ ፣
- ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ባላንስ (Abnormal balance) የሚታይባቸው በ9 መ/ቤቶችና በ1 ቅ/ጽ/ቤት ብር 58,521,861.28 መሆኑ፣

- በ2 መ/ቤት እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን 4 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 48,100,306.61 ከማን እንደሚሰበሰብ መረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ሂሳብ በመሆኑ፣ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፣
- በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባው አላግባብ በተሰብሳቢ ሂሳብ የተያዘ በ2 መ/ቤቶች ብር 15,944,606.97 መገኘቱ፣
- በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች ብር 17,615,101.49
- በ1 መ/ቤት በማነስ ሪፖርት የተደረገ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 8,813,345.26 እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ ተሰብሳቢ ሂሳብ በ3 መ/ቤቶች ብር 67,387,848.40 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ዝርዝራቸው በአባሪ- 7 ሀ እስከ ሰ ተመልክቷል።

በመሆኑም ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ /እንዲሰበሰቡ፣ ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳቡ ማስረጃ እንዲቀርብለቸውና ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደራግላቸው፤ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. <u>የገቢ ሂሳብ</u>

3.1 <u>በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ ለመሰብሰብ በሚደነግጉ አዋጆች ደንብና መመሪያዎች መሰረት ሳይሰበሰብ የተገኘ ሂሳብ</u>

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ34 መ/ቤቶችና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስር ባሉ አስራ አራት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 118,705,272.89 በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ፣ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ያልተሰበሰበ እና በሌሎች 19 መ/ቤቶች ከህንጻ ስራ ተቋራጮችና ዕቃ አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ያልተሰበሰበ

ቅጣት ብር 502,718,693.22 ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲት $ 211,930.00 ወደ ተለያዩ ሀገራት ለትምህርት ከሄዱ ሰራተኞች በውሉ መሰረት ያልተሰበሰበ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ- 9 እና 9/1 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	108,606,404.92
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	6,936,039.66
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	805,685.08
ድምር	ብር	118,705,272.89

በአዋጁ ደንብና መመሪያው መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 38,247,446.01፣ የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ብር 27,938,793.13 ፣ ኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት ብር 8,034,322.15፣ የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 4,267,580.75፣ በባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት ብር 2,131,240.28 እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ብር 2,332,802.70 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፣ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S.Code) እና Custom Procedure Code (CPC Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በትክክለኛው የትራንስፖርት የመጫኛ፣ ማራገፊያና ኢንሹራንስና ሌሎች ወጪዎች ለቀረጥ ማስከፊያነት ባለመወሰዱ ምክንያት ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር፣ በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ በገቡ እቃዎች ላይ በህግ

የተወሰነው የመቆያ ጊዜ ያለፈበት ቢሆንም በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያልተደረገ በመሆኑ እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች ለወደፊቱ የመንግሥት ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.2 ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ሕግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በስሩ ባሉት አስራ አንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በሌላ 1 መ/ቤት ከውዝፍ ግብር፤ ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው በድምሩ ብር 205,113,732.24 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ እና በግብር ከፋዮች ለቀረበው ቅሬታ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ ባለመሰጠቱ ያልተሰበሰበ ግብር በ3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 58,036,507.02 በድምሩ ብር 263,150,239.26 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 8 እና 8/1 ተመልክቷል/

በተጨማሪም ከሰጡት አገልግሎትና ሽያጭ ላይ ውዝፍ /የዱቤ ሽያጭ ሂሳብ በ2 መ/ቤቶች ብር 426,577,775.92 በወቅቱ ያልተሰበሰበ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል።

ውዝፍ ገቢን በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት ብር 391,213,272.36 (ከተወረሱ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ሽያጭ እስከ 7 ዓመታት የቆየ)፣ ኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት ብር 109,325,214.55፣ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ብር 35,364,503.56፣ የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት ብር 35,134,372.40፣ በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት ብር 34,073,495.91፣ በጅማ ቅ/ፅ/ቤት ብር 23,745,392.55፣ አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 16,394,111.76 እና የምራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 15,338,315.92 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ የዱቤ ሽያጭን በወቅቱ አለመሰብሰብ፣ ውዝፍ

የቤት ኪራይን በወቅቱ አለመሰብሰብ፣ ውሳኔ ወጥቶላቸው በቅሬታ ሰሚ እጅ ያሉ እንዲሁም ቅሬታ ያልቀረበበት እና ቅሬታ ሰሚ ውሳኔ ሰጥቶባቸው ለበርካታ ዓመታት ያልተሰበሰበ ውዝፍ ግብር እና በመሳሰሉት የገቢ አሰባሰብ ችግሮች የተነሳ ሳይሰበሰብ የቆየ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል ፡፡

በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የኢኮኖሚ ልማት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋትና መሠረተ ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክቶች ፣ እንዲሁም ለሀገሪቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሳካት ወሳኝ ሚና የሚኖረው በመሆኑ፤ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶ የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.3 ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ሁለት ቅ/ጽ/ቤቶች እና በ3 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 7,875,053.47 እና በሌሎች 6 መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ የገቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ማረጋገጥ አልተቻለም። ዋና ዋና ምክንያቶቹም አግባብ ባለው አካል የጸደቀ የገቢ ታሪፍ/የማስከፈያ ተመን/ ባለመኖሩ ፣ የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፣ መግቢያ ደረሰኝ (ማንኛውም እቃ ሲመጣ የሚመዘገብበት) ፣ የመጋዘን መውጫ ደረሰኝ (እቃው ሲወጣ በተሽከርካሪ ከሆነ ሲሄድ የቆይታ ጊዜ እና የእቃው ጠቅላላ ክብደት የሚገለጽበት እንደዚሁም በተቀመጠው ስሌት መሰረት ተባዝቶ የሚቀመጥበት) ቅ/ጽ/ቤቱ ደረሰኞቹን የማይጠቀም በመሆኑና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የገቢ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው፤ የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4 የውስጥ ገቢን ሂሳብ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተቱ መ/ቤቶች

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 መ/ቤቶች ብር 76,700,098.25 እና ሌሎች የአምስት መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ

የሰበሰቡትን የውስጥ ገቢ ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል፡፡

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		ብር	98,557.90
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		"	76,601,540.35
	በድምር	ብር	76,700,098.25

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱ መ/ቤቶች አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ፤ ይህ አሰራር በመ/ቤቶች የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢ ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ የሚያደርግ ሲሆን፣ ለገቢ ሂሳብ ደረሰኝ አለማዘጋጀት በሂሳቡ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር በማላላት ገንዘብ እንዲጣፋ ወይም እንዲጎድል መንገድ ይከፍታል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስበቸውን የገቢ ሂሳብ በሂሳብ መግለጫዎችም በማካተት ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.5 የተሰበሰበውን ገቢ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያላደረጉ መ/ቤቶች

በመንግሥት ስም የተሰበሰበ ማናቸውም ዓይነት የቀጥታ ገቢ ሂሳብ ወይም ከልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢ በሕግ በተለየ ሁኔታ እንዲሰራበት የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር በበጀት ዓመቱ ውስጥ በየጊዜው ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ በፈሰስ /ለሚመለከተው አካል ገቢ የሚደረግ መሆኑም ለማጣራት ኦዲት

ሲደረግ፡ በ6 መ/ቤቶች ብር 4,547,250.31 ከተለያዩ ገቢዎችና ከሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ የቀረውን ሂሳብ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ወይም ለሚመለከተው አካል ገቢ /ፈሰስ ያልተደረገ ሂሳብ ተገኝቷል። /ዝርዝሩ በአባሪ- 12 ተመልክቷል/

በመሆኑም ገቢ ያልተደረገው ሂሳብ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ ፈስስ መሆን እንዳለበት፤ ለወደፊቱም በሚሰበሰቡት ሂሳቦች ዙሪያ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.6 <u>በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች</u>

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ሰልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

3.6.1 <u>በገቢዎችና ጉምሩክ ባላስልጣንና ቅ/ጽ/ቤቶች</u>

በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

- በበጀት ዓመቱ ከተስተናገዱትና ለአዲት እንዲቀርቡ ከተጠየቁት ዲክላራሲዮኖች መካከል፡-በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት 118 ፤ በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት 5 እና የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት 366 በድምሩ ብዛታቸው 489 የሆኑት ዲክላሳዮኖች ለኦዲት ሊቀርቡ ባመቻላቸው በእነዚህ ዲክላራሲየኖች የተሰበሰበውን ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባወጣው የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍፍል ግብር መመሪያ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 3.4 ላይ ከ2006 የበጀት ዓመት ጀምሮ ኩባንያዎች ትርፍ ለባለ አክሲዮኖች ያከፋፈሉ ወይም የኩባንያውን የካፒታል መዋጮ ለማሳደግ ያዋሉ መሆኑን የሚገልፅ ሪፖርት እና ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማቅረብ እንዳለባቸው በሚያዘው መሰረት

መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፦- በባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት 51 ድርጅቶች እና በጅማ ቅ/ፅ/ቤት 5 ድርጅቶች የአክሲዮን ትርፍ ለባለ አክሲዮኖች ማከፋፈላቸውን ወይም የድርጅቱን ካፒታል ለማሳደግ ያዋሉ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

- በገቢ ግብር አዋጅ 286/2002 ክፍል 1 አንቀጽ 38 በተቀመጠው የግብር አስገቢው ስልጣንና ተግባር መሰረት በተከታታይ ኪሳራ የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮች ላይ ስለሚደረገው ክትትል ለማጣራት በተሞከረበት ወቅት ፣ በምራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ለኦዲት በናሙና ከታዩት ግብር ከፋዮች መካከል ሁለት(2) ግብር ከፋዮች ከአራት ዓመት እስከ ስምንት ዓመት በተከታታይ ኪሳራ ያሳየ መሆኑንና ምንም ዓይነት ማጣራት አለመደረጉ

  ታውቋል፡፡

3.6.2 <u>ሌሎች የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች</u>

ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ተመን ያላቸው ለመሆኑና ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ሲጣራ፣

- በ5 መ/ቤቶች ለደመወዝና ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች ክፍያ ብር 7,217,491.03 የተፈጸመ ቢሆንም፣ ከክፍያው ላይ የገቢ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ፣
- የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት የገቢ ሂሳብ በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 111,476.47 መገኘቱ፣
- በሲግታክስ (ሲስተም ላይ) ያልተመዘገበ ገቢ ሂሳብ በ2 መ/ቤቶች ብር 4,051,119.70 መገኘቱ፣
- ለሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙ.ያ ትም/ ስልጠና ኮሌጅ ለሥራ ማስኬጃ በተላከውና በተመዘገበው መካከል ብር 843,465.69 ልዩነት መኖሩ፣
- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ገንዘብ የማይሰበሰቡ መ/ቤቶች- በመንግሥት ቤቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት ብር 6,167.70 እና

ብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል ከ6 ሰራተኞች ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

በኦዲቱ ተረጋግጧል።

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የገቢ አሰባሰብ፤ አፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ፣ እንዲሁም በገቢ አሰባሰብ ላይ የሚደረገው የውስጥ ቁጥጥር ሊጠናከር እንደሚገባ በሰጠነው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ አንዳንዶቹ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

4. የወጪ ሂሳብ

4.1 ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ25 መ/ቤቶች ብር 139,267,560.08 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ የተመዘገበና ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 18 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	ብር	4,903,513.07
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	47,908,489.75
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	28,048,058.67
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	58,407,498.59
ድምር	ብር	139,267,560.08

ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ከተገኘባቸው ዋና ዋናዎቹ የሃዋሳ ዩኒቨርስቲ ብር 40,150,000.00፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የሲቪል ሰራተኞች ደመወዝና አበል የተከፈለ ብር 28,653,118.45፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር 28,643,514.26 እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 26,817,229.49፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ከዚህ በተጨማሪም ያለአማካሪ ድርጅት የክፍያው ትክክለኛነት የማረጋገጥ እና የመሳሰሉት ሥራዎች በግንባታ ጽ/ቤት አማካኝነት የተከናወነ በ4 መ/ቤቶች ብር 834,655,709.74 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ተገቢውን ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ስለሚችል ባለጥቅሞቹ ገንዘቡ የደረሳቸው ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ለወደፊቱም ማስረጃዎች ወዲያውኑ እንዲቀርቡ ቢደረግ ሊያጋጥም የሚችልን ስጋትና አላስፈላጊ ወጪን ለማስቀረት ስለሚያስችል ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል::

4.2 <u>የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ</u>

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ24 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 221,879,238.59 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 17 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	1,578,135.82
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	61,518,938.44
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	145,445,269.94
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	13,336,894.39
ድምር	ብር	221,879,238.59

ሆኖ ተገኝቷል ።

ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፣ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚያሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፣ የመንግሥት ሰራተኞች የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ አንድ ሳይዘጋጅ፣ የቀረቡት ተራ ደረሰኞች ማለትም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሌላቸው እና በባንክ በኩል

ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን ወይም ለተቀባዩ ስለመድረሱ የሚገልጽ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጉላ ያሉት ናቸው፡፡

ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና ያልተሟላውም ማስረጃ እንዲሟላ በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውንና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

4.3 ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

ክፍያዎቹ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ56 መ/ቤቶችና 4 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 61,397,293.70 ከደንብና መመሪያ ውጭ አላአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-19 ተመልክቷል/ ከዚህ በተጨማሪም በ3 መ/ቤቶች የተሰበሰበውን ግብርና ታክስ በወቅቱ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባለመከፈሉ ከመ/ቤቶች የመንግስት በጀት ላይ ብር 1,145,629.42 ለቅጣት የተከፈለ ተገኝቷል፡፡

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	13,018,463.66
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	40,217,705.15
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	5,372,969.97
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	2,788,154.92
ድምር	ብር	61,397,293.70

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ከተፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤ ሀረማያ ዩኒቨርሲቲ ብር 15,062,986.00፣ የደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 9,980,512.79፣ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ ብር 6,837,046.79፤ ዲላ ዩኒቨርስቲ ብር 3,798,720.53፤ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,329,915.35፣ የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ብር 2,261,095.55 እና የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ ብር 2,087,760.45

ሲሆኑ፤ ምክንያቶቹም ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈጸም ፣ ለሠራተኞች አበል፣ ደመወዝና ማበረታቻ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ በመፈጸም፤ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈል፣ የምግብና መኝታ አገልግሎት ተከፍሎ እያለ በተጨማሪ የውሎ አበል በመክፈል፣ የሲቪል ሰርቪስ

ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የኃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ክፍያ መፈጸም እና መ/ቤቱን ከለቀቁ ሰራተኞች ለበርካታ ወራት የደመወዝ ክፍያ መፈጸምና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም አፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ ስለሆነ፣ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት ደንብና መመሪያን የተከተለ እንዲሆንና ያለአግባብ የተከፈለውም ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.4 <u>በብልጫ የተከፈለ ወጪ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፤ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ9 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች ብር 16,771,051.27 እና በ9 መ/ቤቶች ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 1,731,694.61 በጠቅላላው ብር 16,771,051.27 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-20 ተመልክቷል/ በተጨማሪም በ4 መ/ቤቶች ብር 2,133,311.01 በድጋሚ የተመዘገበ ወጪ ተገኝቷል።

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ሂደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፤ በድጋሚ ወጪ በማድረግ ወይም ከተገቢው ውል ውጭ በመክፈል፣ ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል እንዲሁም ለትርፍ ሰዓት፤ለተለያ ጥቅማ ጥቅም እና ለመኖሪያ ቤት አበል ከተፈቀደው በላይ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግና በድጋሚ መመዝገብ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱንና የወጡት ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው በብልጫ የተከፈለውም ወጪ ለመንግስት ካዝና

ተመላሽ እንዲሆንና ምዝገባውም አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.5 <u>የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች</u>

የዕቃና አገልግሎት ግዥዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ77 መ/ቤቶችና 5 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር

546,059,783.00 የመንግሥትን የግገር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግገር ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 21 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	53,079,171.88
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	338,034,098.03
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	103,657,148.90
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	49,982,635.37
ጠ/ድምር	ብር	546,059,783.00

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፣ ዋቸሞ ዩኒቨርስቲ 161,399,723.74፣ ለአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 81,187,004.35፣ ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 44,669,141.93፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 33,285,467.58፣ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ ብር 24,639,473.79 ፣ የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ብር 25,961,711.36 ፣ የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ብር 20,278,574.57፤ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 17,995,122.49 እና በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 17,052,194.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚሁ በተጨማሪ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የብር 14,519,235.75 የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ካልሆነ ድርጅት የአገልግሎት ግዥ፤ የተፈጸመ ሲሆን፣ 5 መ/ቤቶች የብር 9,267,364.24 ያለውል ስምምነት የተፈጸመ ክፍያ መሆኑ ተረጋግጧል። /ዝርዝሩም በአባሪ- 21/1 እና 21/2 ተመልክቷል፡፡/

ካልተከተሏቸው የግዥ ደንብና መመሪያዎች የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ያለጨረታ ማስታወቂያ በመግዛት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ /ፕሮፎርማ/ አማካኝነት መፈጸም ያለበትን የግዥ ውድድር ሳይደረግ መፈጸሙ እና የተለያዩ ግዥዎችን ከአንድ አቅራቢ ብቻ መፈጸም የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ከመንግስት መመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቶቹን ጥራቱን ላልጠበቀ ዕቃ ወይም ግንባታና ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም/ገቢም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዥ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፣ የመንግስትን አዋጅ በማያከብሩ የመ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ላይም ተገቢው እርምጃ ሊወሳድ ይገባል፡፡

4.6 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት</u>

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆጠረለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ13 መ/ቤቶች በብር 9,694,291.99 ተገዙ ተብሎ በወጪ ለተመዘገበ ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች እና በ7 መ/ቤቶች ብር 358,063,033.00 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ሳይቀረበላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-22 እና አባሪ- 22/1 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	7,468,458.80
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	12,238.00
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	1,713,595.19
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	<u>500,000.00</u>
ድምር	ብር	<u>9,694,291.99</u>

ከዚህም ውስጥ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 7,064,490.00፣ የምግብ መጠጥና ፋርማስቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ብር 1,424,000.05 እና የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ብር 181,760.00 ለግዥ ወጪ ሆኖ የተገዛው ዕቃና የንብረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልተቆረጡት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸውም በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ብር 512,484,298.25፣ የቀድሞው የቅድመ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት ብር 321,500,900.33፣ ትምህርት ሚ/ር ብር 17,059,131.50 እና የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 11,989,874.47 ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጣው ገንዘብ ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ መንግስት ለወጠው ወጪ ተመጣጣኝ አገልግሎት

ስለመግኘቱ ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን የተገዛው ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡን የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.7 <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 7,064,490.00 እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ብር 6,629,165.34 ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች ክፍያ በድምሩ ብር 13,693,655.34 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 27 ተመልክቷል/

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፤ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.8 <u>የወጪ የሂሣብ መደብ ሳይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች</u>

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ37 መ/ቤቶችና በሁለት ተጠሪ ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 94,500,290.37 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሳይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 25 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	6,483,691.37
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	10,729,583.62
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	8,599,994.74
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	68,687,020.64
ድምር	ብር	94,500,290.37

የወጪ ሂሣብ መደብ ሳይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 54,622,967.67፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ብር 6,730,783.42፣ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,618,133.48፣ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ብር 4,417,274.66 የዲላ ዩኒቨርስቲ ብር 3,429,450.78 እና በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ብር 2,278,381.78 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.9 <u>የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ</u>

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ16 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 21,161,998.79

የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ በ2007 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -24 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	ብር	20,378,953.54
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	566,189.00
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	216,856.25
ድምር	ብር	21,161,998.79

ሲሆን ይህም የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት አመቱ የተገኘ አገልግሎት ወጪው በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.10 በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

የውስጥ ገቢ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸውን ያወጡትን ወጪና ሌሎች ወጪዎች የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ/ ሁሉም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት የተካተተ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ4 መ/ቤቶች ብር 16,920,367.57 እና በሌሎች 4 መ/ቤቶች በገንዘብ መጠኑ ያልተገለጸ ከውስጥ ገቢ የተከፈለና የሌሎች ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ/ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-23 ተመልክቷል/

ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ ያደርገዋል፤ በተጨማሪም ትክክለኛውን የመ/ቤቶቹን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችላል፡፡

በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.11 በብድር ከተሰጡ የግንባታ ዕቃዎች ከክፍያቸው ተቀናሽ ያልተደረገ/ ያልተሰበሰበ ብድር ሂሳብ

ከግንባታዎች ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ግንባታዎች በሚያከናወኑ መ/ቤቶች፣ የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ ብር 2,597,743.62 በብድር ከተሰጡ የግንባታ ዕቃዎች ከክፍያቸው ተቀናሽ ያልተደረገ/ ያልተሰበሰበ ብድር ሂሳብ መኖሩ ታውቋል።

ለግንባታ የቀረቡ ግብዓቶች ስራ ላይ ሳይውሉ ክፍያ መፈጸሙና ተቋራጮች ክፍያ ሲፈጸምላቸው ቀደም ሲል የተሰጠቸው ብድር ሳይቀነስ ክፍያ መፈጸሙ ከውል በላይ ክፍያ እንዲፈጸም፣ የተሰጠ ብድርም እንዳይሰበሰብ ክፍተት ይፈጥራል።

በመሆኑም ያልተሰበሰበው የግንባታ ግብዓቶች ብድር እንዲሰበሰብ የወሰዱትን ግንባታ በወቅቱ በመያጠናቀቁ ተቋራጮች ተገቢው የጉዳት ካሳ በውሉ መሰረት

እንዲጠየቅና የግንባታ ስራዎች በመመሪያው መሰረት እንዲከናወኑ አስፈላጊ ክትትል እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል።

4.12 በባለስልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ

በወጪ የተመዘገቡት ክፍያዎች ስልጣን በተሰጠው ኃላፊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ9 መ/ቤቶች በኃላፊ ሳይጸድቅ ብር 22,335,349.52 እና በ1 መ/ቤቶች ደግሞ ብር 10,757,285.00 ከተሰጣቸው ውክልና በላይ ወጪ አፅድቀው መገኘቱ ተረጋግጧል። /ዝርዝሩ በአባሪ-26 እና 26/1 ተመልክቷል/

በዚህም ውስጥ ስለትክክለኝነቱ ወጪውን ባረጋገጠው ኃላፊ ያልተፈረመ፣ በጀት ስለመፈቀዱ የበጀት ሰራተኛ፣ሂሣቡን ባረጋገጠው ሰው ያልተፈረሙና ከተሰጠው ውክልና ባላይ የተፈረመ ይገኝበታል፡፡

አሰራሩ ከደንብና መመሪያ ውጭ በመሆኑና ለገንዘብ ብክነት ሊያገልጥ ስለሚችል ሊስተካከል እንደሚገባ አሳስበናል።

4.13 ሌሎች ከወጪ ሂሳብ ጋር የተያያዘ የሚታዩ ችግሮች

- **በአክሱም ዩኒቨርሲቲ** በዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች ተረጋግጦ በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ገቢ የተደረገ በቁጥር አንድ ሳውንድ ፕሩፍ ጀኔሬተር ብር 4,499,700.00 የተከፈለበት ቢሆንም ሌሎች የዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች እንደገና በረጋገጡት መሰረት ዕቃው በውሉ ላይ በተገለጸው ዝርዝር (specification) መሰረት አለመሆኑ ስለተረጋገጠ ዩኒቨርስቲው ለከፈለው ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም ማግኘቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

- **ሐረማያ ዩኒቨርስቲ፡-**

  ከምዕራብ ሐረርጌ ዞን መስተዳድር የሐረማያ ከተማ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤት ጋር በቀን 5/07/2005 በፈጸመው ውል መሰረት ለመምህራን መኖሪያነት የሚያገለግሉ 413 የመኖሪያ ቤቶች የያዙ በቁጥር 22 ህንጻዎች ግዥ ብር 38,783,544.70 የተከፈለ ቢሆንም ሕንጻዎቹ ባለመጠናቀቃቸው ለታቀዱበት ዓላማ ያልዋሉ መሆኑ፣ ተቋሙ ከሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት የቤቶች ልማት ጋር 158 የመኖሪያ ቤቶች የያዙ በቁጥር 8 ህንጻዎች ግዢ ውል የፈጸመ ሲሆን በውሉ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 3.1 ውል ሰጪ በውል ስምምነቱ መሰረት ቅድሚያ ክፍያውን እንደተቀበለ በ12 ወራት ውስጥ

የግንባታ ሥራውን አጠናቆ ለማስረከብ የግዴታ ውል የፈጸመ ቢሆንም ብር 16,824,455.55 ክፍያ የተፈጸመባቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዩኒቨርስቲው ያልተረከበ መሆኑ፣

➢ <u>የሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ የመምህራን ቤቶች ግንባታ የጨረታ ሂደትን በተመለከተ</u>

ኮሌጁ የመምሕራን መኖሪያ ቤት ግንባታ እስክንድር ታዬ የተባለ የህንጻ ሥራ ተቋራጭ እንዲገነባ በብር 2,177,208.30 ውል የገባ መሆኑ ታውቋል፡፡ ሆኖም የጨረታው ሂደት አፈጻጸም ሲታይ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ታይቷል፡፡

- በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 29 መሰረት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ መዘጋጀት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም ሰኔ 2002 ዓም በወጣው የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል አራት አንቀጽ 16.5(ሸ) መሰረት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው በጨረታው መጫረት ለሚፈልጉ ተጫራቾች የተሟላና ትክክለኛ የመጫረቻ ሰነድ እንዲያዘጋጁ በሚያስችል ዓይነት ተሟልቶ እና በዝርዝር ተዘጋጅቶ የጨረታው ሰነድ አንድ ክፍል መሆን እንዳለበት ተቀምጧል፡፡ ሆኖም የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16(5) መሰረት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ያልተዘጋጀ ከመሆኑም በተጨማሪ በግዥ አጽዳቂ ኮሚቴም የተወሰነው ውሳኔ በፋይናንሻል ግምገማ ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑ፣
- የኮንትራት ውሉ በግዥ መመሪያው ክፍል አራት አንቀጽ 16(27) መሰረት በዝርዝር መዘጋጀት ሲገባው ውል ተብሎ የተዘጋጀው በአጭሩ (በተጠቃለለ መልኩ) መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

- **<u>በበጀት ሂሳብ ላይ በወጪ እንዲመዘገብ ተደርጎ ወደ ፕሮጀክት የተዛወረ ሂሳብ</u>**

የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት በ6412 በሂሳብ መደብ ለብድር መስጠትና ማስመለስ እንዲውል ብር 50 ሚሊዮን በጀት የተፈቀደለት ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከተያዘለት በጀት ውስጥ ሳይጠቀሙበት የቀረውን ብር 50 ሚሊዮን በወጪ ሒሳብ መደብ 6412 በወጪ መዝግቦ ወደ ጽህፈት ቤቱ ፕሮጀክት ሂሳብ እንዲዞር ያደረገ ሲሆን፣ በ2004፣ በ2005 እና በ2006 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም ወደ ፕሮጀክት (ፈንድ) ሂሳብ እንዲዞር የተደረገው ሂሳብ በተሰብሳቢ ሒሳብ መያዝ እንዳለበት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በዚህ ኦዲት ወቅትም አሰራሩ የቀጠለ መሆኑ ታውቋል፡፡

5. <u>የተከፋይ ሂሣብ</u>

5.1 <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ</u>

በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ55 መ/ቤቶችና በስምንት ተጠሪ ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,039,053,017.42 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 31 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን	ብር	617,270,855.60
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	164,204,770.92
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	224,922,322.51
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	32,940,785.39
ድምር	ብር	1,039,053,017.42

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 573,375,335.26፣ ሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 140,672,253.79፤ ዲላ ዩኒቨርስቲ ብር 66,326,640.75፣ የበጎ አድራጎት

ድርጅቶች ማህበራት ኤጀንሲ ብር 29,170,083.93፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በጅማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 24,601,870.61፣ በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ብር 22,909,946.60 እና አድግራት ዩኒቨርሲቲ ብር 18,958,704.29፣ የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ ብር 17,122,223.91 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ አስገዳጅ ሕጎች መሰረት ገቢ ሰብስበው የተሰበሰበውን ገቢ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያላደረጉ በ6 መ/ቤቶች ብር 4,547,250.31 መኖሩ ተረጋግጧል።

ይህም የተከፋይ ሂሳብ ፣ ከተለያዩ ቅጣት፣ ከሰነድና መድኃኒት ሽያጭና በሌሎች የገቢ መሰብሰብ ግዴታዎች ምክንያት ተሰብስበው ለሚመለከተው አካል ያልተከፈሉትን ሂሳብ ይጨምራል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

5.2 <u>በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ድክመቶች</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የየመ/ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ በ3 መ/ቤቶችና በ6 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 78,579,156.42 መኖሩ፣
- በተከፋይ ያልተመዘገበ የመያዣ ሂሳብ፤ በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 2,995,104.05 መገኘቱ፣
- መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴብት) የሚታይ በ7 መ/ቤቶች ብር 213,309,829.63 መታየቱ፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀላቸው በ2 መ/ቤቶች ብር 6,696,197.00 መገኘቱ፣ እና ሌሎች ሌጀር አዘጋጃጀትና አያያዝ ችግሮች እንደሚታይባቸው ተረጋግጧል። /ዝርዝሩ በአባሪ-32 ሀ እስከ መ ተመልክቷል/

በዚህ አሰራር የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የተከፋይ ሂሳብ ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ምዝገባው ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ከላይ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ ደግሞ ተገቢውን ማጣራት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል።

6. <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

6.1 <u>ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ</u>

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ40 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች

ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ሥራ ላይ የዋለ ሂሳብ በመደበኛ በጀት ብር 621,319,554.74 እና ከካፒታል በጀት ብር 124,831,405.18 በድምሩ ብር 746,150,959.92 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	259,619,250.88
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	331,715,932.76
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	29,121,619.60
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	125,694,156.68
ጠ/ድምር	ብር	746,150,959.92

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች፣ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን /የተጠቃለለ ሂሳብ/ ብር 186,511,080.05፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 123,560,176.47፣ የቴ/ሙ/ት/ሥ/ኢንስቲትዩት ብር 70,488,788.00 ጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 54,131,454.48 ፣ ሚዛን -ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 43,010,493.00፣ ወለጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 39,080,757.06፣ አሶሳ ዩኒቨርስቲ ብር 35,343,027.00፣ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 35,861,587.36 እና ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 35,110,366.58 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በ7 መ/ቤቶች ብር 2,325,067.72 በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ የተፈፀሙ ክፍያዎች እና በ1 መ/ቤት ለስራው ምንም በጀት ሳይያዝ ብር 454,342.50 ወጪ መሆኑ ታውቋል፡፡

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ ከመሆኑ በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክንና በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙ የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

6.2 <u>ያልተሰራበት በጀት</u>

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት

ኦዲት ሲደረግ፣ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% ላይ የሆነውን ብቻ በመውሰድ በ111 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 1,048,894,871.46 እና ካፒታል ብር 906,148,745.79 ብር 1,955,043,617.25 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	360,069,034.03
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	352,069,616.05
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	392,847,319.52
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	850,057,647.65
ድምር	ብር	1,955,043,617.25

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች ትምህርት ሚ/ር ብር 203,452,410.13፣ የደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 156,830,658.92፣ አገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 135,989,824.52፣ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ብር 109,278,480.17፣ ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ብር 104,674,170.55፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 91,886,238.87 አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 76,526,239.04 ፣ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጄንሲ ብር 70,488,787.09፣ አዲስ አበባ

ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ብር 69,911,636.78፣ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ብር 50,944,597.96 እና የቀድሞ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ብር 49,789,189.55 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም የታቀዱ ሥራዎች ሳይከናወኑ ሊቀሩና መ/ቤቱም ዓላማውን እንዳያሳካ ሊያደርግ ስለሚችል፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

7.1 የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች፡ እንደሚገኙ በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-34 / ሀ እስከ ከ ተመልክቷል፡፡/

ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	29 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገበ ከወጪ ቀሪ ጋረ ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	24 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	15 መ/ቤቶች
ቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ	27 መ/ቤቶች
የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	12 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	24 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	55 መ/ቤቶች
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	21 መ/ቤቶች
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	13 መ/ቤቶች
በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ንብረቶች አያያዝ ችግር የሚታይባቸው	8 ቅ/ጽ/ቤቶች
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ	8 መ/ቤቶች
ዋስትና በሚያስፈልጋቸዉ የስራ መደቦች ላይ የተመደቡ ሰራተኞች ዋስትና (ተያዥ) እንዲያቀርቡ ያልተደረገ ስለመሆኑ	1 መ/ቤት
የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ መሆኑ፤	4 መ/ቤቶች
በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ሳይደረጉ ንብረት ክፍል የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው መ/ቤቶች	6 መ/ቤቶች
ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች	12 መ/ቤቶች

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው፡፡ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለአገልግሎት በየንብረት ክፍሉ ተከማችተው እያለ የተመሳሳይ ንብረቶች ግዥ የሚፈጽሙ መ/ቤቶችም መኖራቸው በኦዲታችን ወቅት ታይቷል። እንዲሁም ጊዜ ያለፈባቸውና ሊወገዱ የሚገባ የተለያዩ ለጤና ጎጂ የሆኑ ኬሚካሎች በበርካታ መ/ቤቶች ይገኛሉ፡፡

የእነዚህ የተለያዩ የንብረት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው በየዘርፍ በንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ ሌሎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች በሚል ተገልጿል ።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፣ አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንና ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችና ኬሚካሎች በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረትና በጥንቃቄ እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>ተሽከርካሪ</u>

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ32 መ/ቤቶች	313 ተሽከርካሪዎች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ21 መ/ቤቶች	218 ተሽከርካሪዎች
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣	በ6 መ/ቤቶች	15 ተሽከርካሪዎች
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	በ4 መ/ቤቶች	38 ተሽከርካሪዎች
ሊብሬ ብቻ ሲገኝ ተሽከርካሪዎቹ በአካል ያልተገኙ	በ1 መ/ቤቶች	10 ተሽከርካሪዎች
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪ ዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት	በ2 መ/ቤቶች	3 ተሽከርካሪዎች

መኖራቸው ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -35 /ሀ እስከ ረ ተመልክቷል/

በመሆኑም ም/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ፣ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳዳር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ /እንዲወገዱ፣ ሊብሬ የሌላቸው እንዲወጣላቸውና ሰሌዳ የሌላቸው እንዲወጣላቸው አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

8. <u>ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ</u>

ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

በ36 መ/ቤቶች እና 11 ቅ/ጽ/ቤቶች/ ተጠሪ ጽ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰዱ ሲሆን /ዝርዝሩ በአባሪ-36 ተመልክቷል/ እርምጃ ያልተወሰዱባቸው ነጥቦች በየመ/ቤቶቹና በየዘርፉ ዝርዝር ሪፖርት መጨረሻ ላይ ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ እርምጃ እንዲወሰድ ለሁሉም መ/ቤቶች በድጋሚ አሳስበናል።

9. <u>ልዩ ልዩ</u>

9.1 <u>የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት፣</u>

የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ፡-

- በዩኒቨርስቲው የተማሪዎች ማደሪያ አካባቢ መፀዳጃ ቤቶች የውሃ እጥረት ለባለመሰራታቸው በግቢው ውስጥ ባሉት ባህር ዛፎች አካባቢ የሚጠቀሙ በመሆኑ በአካባቢው መጥፎ ጠረን እያመጣ መሆኑን፣

- የዩኒቨርሰቲው ሀብት ከዘረፋና ከጥፋት ለማዳን ግቢው ምንም ዓይነት አጥር የሌለው መሆኑን፣

- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል በተሟላ የሰው ሃይል አለመደራጀቱ እና የሥራ ክፍሉ የአራተኛው ሩብ ዓመት ሪፖርት እስከ ነሐሴ 15/2007 መቅረብ የነበረበት ቢሆንም የመስክ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት እስከ ታህሳስ/2008 አጋማሽ አካባቢ ድረስ ያልቀረበ መሆኑ፣

በአክሱም ዩኒቨርሲቲ

- በፕሣ 9 የሥራ ደረጃዎች ላይ ያለውድድር እና የሥራ ልምዳቸው አግባብነት ሳይኖረው በመማር ማስተማር ሥራ ላይ የተሠማሩ ባለሙያዎች በአይ ቲ ዳይሬክተርነት እና በተቋማዊ ዕቅድና አፈፃፀም ግምገማ ማዕከል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተርነት መመደባቸው፣

በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ

- በመቀሌ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ስም በታተሙ የክፍያ ቫውቸሮች ተሠርቶባቸው መገኘቱ፣

በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ፡-

- ለአንድ የዕቃ ግ/ቤት ሠራተኛ እና አንድ የሬጂስትራር ሰራተኛ ከህዳር/07 አስከ ሰኔ/07 ዓ.ም በተመሳሳይ የመደብ መታወቂያ ቁጥር ደመወዝ የተከፈላቸው መሆኑ፣
- ከተቋሙ ጋር ውል በመግባት ለትምህርት ተልከው በገቡት ውለታ መሠረት ግዴታቸውን ካልተወጡ ሁለት መምህራን በድምሩ ብር 314,304.00 እና አንድ ግለሰብ ያልከፈለው የቤት ኪራይ ብር 48,000.00 ጉዳያቸው በህግ ተይዞ ገንዘቡን እንዲከፍሉ በፍርድ ቤት ብይን የተሰጠ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው እስከ አሁን ድረስ ገንዘቡን ያላስመለሰ መሆኑ፣

በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ፡-

በዩኒቨርሲቲው ድርጅታዊ መዋቅር መሠረት የዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት 9 የሰው ኃይል የሚያስፈልገው ቢሆንም በክፍሉ አንድ ኦዲት ኃላፊ በቅርብ እንደተመደበ፣

- በፌደራል መንግስት የውስጥ ኦዲት መመሪያ መሰረት የውስጥ ኦዲት ሪፖርት የጊዜ ሰሌዳውን ጠብቆ ሪፖርት ማቅረብ ሲገባው እስከ መጋቢት 30/2007 ዓ/ም ድረስ ምንም ዓይነት የኦዲት ሪፖርት ያላቀረበ መሆኑ፣
- በመዋቅሩ መሰረት ለሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አንድ ሠራተኛ ብቻ መሆን ሲገባው በአዋጅና ተፈላጊ ችሎታዎች መመሪያ መሠረት በሜሪት አፈጻጸም በሠራተኛ ተይዞ በሚገኘው መደብ ላይ ከደንብ ውጭ በተደራቢነት አካደሚሺያን /መምህር/ በቁጥር ዋዩ/ፕ/ጽ/04/169/08 በቀን 02/02/2008 ከፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ መመደቡ፣
- የሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የስራ ደረጃው የባችለር ዲግሪ እና 9 ዓመት ወይም የማስተርስ ዲግሪ እና 7 ዓመት የስራ ልምድ የሚጠይቅ ሲሆን በወቅቱ የተመደቡ ግለሰብ ያላቸው የስራ ልምድ 5 ዓመት ብቻ መሆኑ፣
- የሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬትን ጨምሮ ሌሎች መምህራን ከማስተማሩ ሥራ በተደራቢነት በመምህራን እንዲያዙ ባልተፈቀዱ የአስተዳደራዊ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ተመድበው የሚሰሩ መሆኑ፣

በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ፡-

- አንድ ሠራተኛ ከግንቦት 01/2005 ዓ/ም ጀምሮ የፕሮጀክት መሀንዲስ ሆነው የተቀጠሩ ሲሆን የስራ ደረጃው የምህንድስና ዲግሪ እና 3 ዓመት የስራ ልምድ የሚጠይቅ ሆኖ ሳለ በወቅቱ ግለሰቡ ያላቸው የስራ ልምድ 6 ወር ብቻ መሆኑ፣
- የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ኃላፊ ቦታን በጊዜያዊነት ኃላፊ ሆነው እንዲሰሩ ባለሙያ የተመደበ ሲሆን በቦታው ላይ ሃላፊ በቋሚነት መመደብ ሲገባ ያልተመደበ እና እስከአሁን በቦታው ላይ ከአንድ ዓመት በላይ በጊዜያዊነት እየሰሩ መሆኑን፣

በባህር ዳር ዩኒቨርቲ

- እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ከዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ግቢዎች በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ አገር በትምህርት ላይ ያሉ 43 መምህራን ውል ሳይገቡ ለትምህርት የሄዱ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 10 መምህራን መቼ ለትምህርት እንደሄዱ እና የሚማሩበት ተቋም የማይታወቅ መሆኑ፣ 15 መምህራን ደግሞ መቼ ለትምህርት እንደሄዱ የማይታወቅ መሆኑ፣

9.2 <u>የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ ሆነው ግዴታቸውን ባልተወጡ መምህራን ላይ በገቡት ግዴታ መሰረት ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤</u>

- በሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ለሚሰጠው የትምህርት ዕድል የግዴታ ውል የሚያስገባ፣ ዋስ የሚያስጠራ መሆኑን እና የትምህርት ዕድል ያገኙት መምህራን ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ግዴታቸውን የሚወጡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በኮሌጁ በመምህርነት ተቀጥረው ሲያገለግሉ የነበሩ 8 (ስምንት) መምህራን በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የሁለተኛ ዲግሪያቸውን እንዲማሩ የተፈቀደላቸውና ከኮሌጁም ጋር ውል የፈጸሙ ሲሆን፣ በገቡት ውል መሰረት ህጉን ካፈረሱ፡

  - ✓ ለትምህርት
  - ✓ ለምርምር

  በትምህርት ላይ ባሉበት ጊዜ ሲከፈላቸው የነበረውን ደሞዝ ታስቦ ተመላሽ እንዲያደርጉ ወይም ትምህርቱ የፈጀባቸውን ጊዜ እጥፍ አገልግሎት ለመስጠት ውል የገቡ እና ዋስትና ያስያዙ ቢሆንም መምህራኖቹ የገቡትን ግዴታ ሳይወጡ ስምንት መምህራን ሥራቸውን ለቀዋል፡፡ ሆኖም ኮሌጁ ግለሰቦቹ በገቡት ግዴታ መሰረት አስፈላጊውን እንዲፈጽሙ ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

  በመሆኑም መምህራኖቹ በገቡት ውል መሰረት አገልግሎቱን እንዲሰጡ ወይንም ገንዘቡን እንዲከፍሉ ወይም ገንዘቡን ለመክፈል ፍቃደኛ ሆነው ካልተገኙም በሕግ አግባብ እንዲጠየቁ መደረግ እንዳለበት እናሳስበናል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

የ2007 በጀት ዓመት የተጠቃለለ ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 669/2002 መሰረት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የ2007 በጀት ዓመት ሂሣብ በተጠቃለለ ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዋና መ/ቤት ፣ የአስራ አምስት ቅ/ጽ/ቤቶችንና የማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት የባለስልጣን መ/ቤቱ ባዘጋጃቸው የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ /የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

በዚህም መሰረት የባለስልጣን መ/ቤቱን፣ 15 ቅ/ጽ/ቤቶችን (ማለትም የከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ የመቀሌ፣ የምስራቅ አዲስ አበባ፣ ምዕራብ አዲስ አበባ፣ የሞያሌ፤ የድሬዳዋ፤ የኮምቦልቻ፤ የአዋሳ፤ የባህር ዳር፤ የአዳማ፣ የጂማ፤ የሞጆ ገቢዎችና ጉምሩክ እና የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ የአ.አ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤትና የጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤትን) እንዲሁም የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተጠቃለለ የ2007 በጀት አመት የሂሳብ እንቅስቃሴ ኦዲት ተደርጓል፡፡

በኦዲቱም መሰረት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ቀጥለው ቀርበዋል::

የኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የዋና መ/ቤትና የ15 ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሁም የ2007 በጀት ዓመት የማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. የጉምሩክ ገቢ ሂሳብ

1.1 የጉምሩክ ቀረጥና ታክስን በተመለከተ

ሀ/ አስመጪው ያቀረበው ዝቅተኛ የግብይት ዋጋ በመወሰዱ ምክንያት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 2,120,323.85

ግኝት

በገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 94/2006 አንቀፅ 5 የግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴ አፈፃፀም ንዑስ አንቀፅ 2 መ በአስመጪው የቀረበው የዕቃ ዋጋ እና በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ዳታ ቤዝ ውስጥ የሚገኙ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች አማካኝ ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት ከ10% በላይ ከሆነ የማነፃፀሪያ ዋጋ እንደ ትክክለኛ ዋጋ ተወስዶ ለቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ እንደሚሆን በሚያዘው መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት ብር 2,120,323.85 ቀረጥና ታክስ ልዩነት መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

በአስመጪዎች የሚቀርበው የዕቃዎች ዋጋ (ኢንቮይስ) የወቅቱ ተገቢ የዕቃዎች ዋጋ ስለመሆኑ በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ዳታ ቤዝ ውስጥ ከሚገኙ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የዕቃዎች አማካኝ ዋጋ ጋር ተነጻጽሮ በሚገኘው ውጤት መሰረት የማይፈጸም ከሆነ አነስተኛ ዋጋ ቀረጥና ታክስ ሊሰበሰብ ከመቻሉም በላይ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ለወደፊቱ በአስመጪዎች የሚቀርበው የዕቃዎች ዋጋ (ኢንቮይስ) የወቅቱ ተገቢ የዕቃዎች ዋጋ ስለመሆኑ በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ዳታ ቤዝ ውስጥ ከሚገኙ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የዕቃዎች አማካኝ ዋጋ ጋር እየተነጻጸረ በመመሪያው መሰረት እርምጃ ሊወሰድ የሚገባ ሲሆን ከላይ የተመለከተው ሂሳብ ከአስመጪዎች እንዲሰበሰብ ሊደረግ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ሥራ አመራሩም በድዕራ -ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ቡድን መተላለፉንና ተጣርቶ ማስተካከያ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

ለ) የትራንስፖርት ወጪና ሌሎች ወጪዎች በትክክል ባለመወሰዳቸው እና ደረሰኝ ባለመቅረቡ ምክንያት ብር 4,358,135.00 ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ

ግኝት

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 96 መሠረት ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ እቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ሲወሰን ለእቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ላይ እቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የትራንስፖርት፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያና፣ የኢንሹራንስ ወጪ መደመር እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በቁጥር 3.1.0/856 በ20/የካቲት/2006 በተላከው የመመሪያ ቁጥር 94/2006 አፈጻፀም ማብራሪያ መሰረት ከጅቡቲ እና ከሌሎች ክልሎች መግቢያ ወደቦች ተጓጉዞ ለሚመጡ እቃዎች ከመግቢያ ወደቦች እስከ ኢትዮጵያ የመጀመሪያው መግቢያ በር ድረስ እስከ መድረሻ የጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤቶች ወይም ደረቅ ወደቦች ያለውን ርቀት መሰረት በማድረግ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ውስጥ መካተት ያለበትን የትራንስፖርት ወጪ ተሰልቶ መካተት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር የኢንሹራንስና የትራንስፖርት ወጪ በትክክል በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ውስጥ ባለመካተቱ ምክንያት፣

- በኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት ብር 26,778.68
- በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት ብር 47,855.42
- በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 89,898.25
- በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት ብር 178,274.68
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 121,744.50
- በሞጆ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ብር 801,733.35
- የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 3,091,850.12

በአጠቃላይ ትክክለኛው የትራንስፖርት ወጪ እንዲሁም የኢንሹራንስና ሌሎች ወጪዎች ለቀረጥ ማስከፈያነት በትክክል ያልተካተቱ በመሆናቸው ምክንያት በድምሩ ብር 4,358,135.00 የቀረጥና ታክስ ልዩነት መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

ለቀረጥ ማስከፈያነት መካተት ያለበት ወጪ በትክክል የማይካተት ከሆነ መንግስት ከገቢ እቃዎች ሊሰበስብ የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበስብ ያደርገዋል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

በተፈጠረው ስህተት ምክንያት ያልተሰበሰበው የቀረጥ መጠን ብር 4,358,135.00 ከሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ትራንስፖርት እና ሌሎች ወጪዎች በትክክል የተካተተ ለመሆኑ የሚመለከታቸው የቅርንጫፍ ፅ/ቤት ሰራተኞች ተገቢውን ጥንቃቄ መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

ግኝቱን ተቀብለው ማስተካከያ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

ሐ) እቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥርና የጉምሩክ ስነ ስርአት ኮድ ባለመመደባቸው ምክንያት ብር 361,179.00 ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ፡-

ግኝት

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ምዕራፍ 2 አንቀጽ 102 መሠረት ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ ማናቸውም ዕቃዎች ላይ የሚከፈል ቀረጥ በጉምሩክ የታሪፍ ደንብ በተወሰነው ምጣኔ መሠረት እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ ለዚህም እቃዎች በሀርሞናይዝድ ሲስተም ታሪፍ አተረጓጎም አጠቃላይ ደንቦች መሰረት መመደብ ያለባቸው ቢሆንም ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር (H.S.code) እና በትክክለኛው የጉምሩክ ስነስርአት ኮድ (CPC) ባለመመደባቸው ምክንያት፡-

- በጅግጅጋ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር ባለመመደባቸው ብር 297,913.54 እና በትክክለኛው የጉምሩክ ስነስርአት ኮድ (CPC) ባለመመደባቸው ምክንያት፣ ብር 14,228.06 በድምሩ ብር 312,141.60፡-
- በሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር ባለመመደባቸው ብር 49,037.40፡-

ባጠቃላይ እቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥርና የጉምሩክ ስነስርአት ኮድ መሰረት ባለመስተናገዳቸው ምክንያት ብር 361,179.00 ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

መንግስት ከገቢ እቃዎች መሰብሰብ ያለበትን ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበስብ ያደርገዋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

እቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር እና ጉምሩክ ስነስርአት ኮድ (CPC) ባለመመደባቸው ምክንያት ያልተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ሂሳብ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም እቃዎች በሀርሞናይዝድ ሲስተም ታሪፍ አተረጓጎም አጠቃላይ ደንቦች መሰረት የተመደቡ ለመሆኑ የሚመለከታቸው ሰራተኞች አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል::

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

- ግኝቶቹ ትክክል ናቸው እርምጃ ይወሰዳል በማለት መልሰዋል፡፡

መ) <u>ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 101,225,258.50 መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

በጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ እዳ የክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ ቁጥር 69/2004 አንቀጽ 6/1 እና 2 መሰረት የገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች አያያዝ ቡድን በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ቡድን በኩል የተጠየቁ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳቸውን ተከታትሎ እያስከፈለ ስለመሆኑና ዕዳቸውን ለመክፈል ፈቃደኛ ያልሆኑ አስመጪዎችን ዝርዝር

በመያዝ የንብረት መያዝ ስነ-ስርዓት እንዲፈጸም ለሚመለከተው የስራ ሂደት እያሳወቀ መሆኑንና ተጨማሪ የግብር ውሳኔም በወቅቱ የሚሰበሰብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በከምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል የቀሪ ሂሳብ የክፍያ ማስታወቂያ የውሳኔ ማስታወቂያ ደርሷቸው በመመሪያው መሰረት በ15 ቀናት ውስጥ ቅሬታ ያላቀረቡ በመሆኑ ከ6 አስመጪዎች የሚፈለግ በድምሩ ብር 26,023,948.46 ፡፡
- በመቀሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል በጉምሩክ ቀሪ ሂሳቡ ላይ ቅሬታ ያልቀረበበት እና ቀሪ ሂሳቡን ተመላሽ ለማድረግ የንብረት መያዝ ስርአት ተፈጻሚ ያልሆነበት ያልተሰበሰበ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ብር 2,017,913.22 መገኘቱ፣
- በድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የክፍያ ማስታወቂያ ከወጣ ከ 4 ወር እስከ 6 ዓመት የሆነውና ቀሪ ሂሳቡን ተመላሽ ለማድረግ የንብረት መያዝ ስርአት ተፈጻሚ ያልሆነበት ያልተሰበሰበ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ብር 11,234,938.57
- በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ቅሬታ ያልቀረበበት እና ቀሪ ሂሳቡን ተመላሽ ለማድረግ የንብረት መያዝ ስርአት ተፈጻሚ ያልሆነበት ብር 3,663,041.74 የክፍያ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀ ድረስ ያልተሰበሰበ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ መኖሩ፣
- በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል የቀሪ ሂሳብ የክፍያ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ሳይሰበሰብ ከ 1 ወር እስከ 1 ዓመት የቆየ ውዝፍ የቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ በድምሩ ብር 35,134,372.40 በገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች ቡድን በኩል የተያዘ፣
- በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የቀሪ ቀረጥና ታክስ የክፍያ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከ 2 ወር እስከ 2 ዓመት የቆየ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ብር 2,861,054.32
- አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት 120 ዲኪላራሲዎን ብር 16,394,111.76፣

ቀሪ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል ፡፡

<u>ስጋት</u>

የገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች ቡድን በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ቡድን ውሳኔ መሰረት የቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ያለባቸውን አስመጪዎች ዝርዝር በመያዝ ዕዳቸውን

እንዲከፍሉ የማይከታተል ከሆነ የመንግስት ገቢ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በውሳኔው መሰረት ዕዳቸውን ለመክፈል ፈቃደኛ ባልሆኑ አስመጪዎች ላይ በመመሪያ 69/2004 አንቀጽ 7/1 መሰረት የንብረት መያዝ ስነ-ስርዓቱ ተፈጻሚ እንዲሆን ዝርዝሩን ለንብረት ያዥ ኮሚቴ በማስተላለፍ ያልተሰበሰበው ግብር ከሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- በኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል ከሚፈለገው ቀሪ ሂሳብ ውስጥ ብር 1,290,778.65 ተሰብስቦ ገቢ የተደረገ መሆኑን ያልተሰበሰበ ቀሪ ቀረጥና ታክስን በተመለከተ 26,132,243.86 ብር የተባለው የ12 አስመጪ ድርጅቶች ድ/ዮን ላይ ብር 7,963,356.57 ቅሬታ ዋና መ/ቤት ስለሆነ ውሳኔው ስለማይታወቅ ለብቻ መያዝ አለበት፣ ሌሎችም ከሲስተም እንዲታገዱ በማድረግ ቀሪ ቀረጥና ታክስ እንደ ሂደት መረጃዎችን በማጥራት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ለመሰብሰብ ጥረት የሚያደርጉ መሆኑን፣

ሠ) **በገቡት የክፍያ ጊዜ ስምምነት መሰረት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 205,905.49**

ግኝት

የጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ እዳ የክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ ቁጥር 69/2004 አንቀፅ 16 በዚህ መመሪያ በተሰጠው የክፍያ ጊዜ ስምምነት መሰረት በየወሩ ወይም በስምምነቱ በተገለጸው የአከፋፈል ሁኔታ እዳውን የማይከፍል ወይም መክፈል ያቋረጠ አስመጪ ወይም ላኪ ወይም ሌላ ሰው ያለተጨማሪ ማስጠንቀቂያ የክፍያ ጊዜ ስምምነቱ ተቋርጦ ቀጣይ የቀረጥና ታክስ አሰባሰብ ስነስርዓት ተፈጻሚ ይደረግበታል ብሎ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ መመሪያ አንፃር ውላቸውን ባቋረጡ አስመጪዎች ላይ የቀረጥና ታክስ ዕዳ ለማስከፈል የተደረጉ ጥረቶች እንዳሉ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ

በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት አስመጪዎች የስምምነት የጊዜ ገደባቸው ከተጠናቀቀ ከ10 ወራት እስከ 3 ዓመት የቆየ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ብር 205,905.49 መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

ስጋት

አስመጪዎች በገቡት ውል ስምምነት መሰረት ካልከፈሉ በመመሪያው መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ የማይደረግ ከሆነ ቀሪ ቀረጥና ታክስ በወቅቱ ገቢ ሳይሆን ሊቀር ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል የገቡ አስመጪዎችን ውል ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ክፍያቸውን በውሉ መሰረት እየፈጸሙ ስለመሆናቸው የተጀመረውን ክትትል በማጠናከር ክፍያቸውን ባቋረጡ አስመጪዎች ላይ ንብረታቸው ተይዞ የተወሰነባቸውን ቀረጥና ታክስ እንዲከፍሉ ሊደረግ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት ቀሪ ቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ በመመሪያው መሠረት አስፈላጊው እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ረ) ዕቃዎች በጊዜያዊነት የሚቆዩበት የጊዜ ገደብ ቢጠናቀቅም ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 86,965,661.32 መኖሩ-

ግኝት

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 117(2) መሰረት እቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ለገቡ ተመልሰው መውጣታቸውን ለማረጋገጥ ወይም ካልወጡ ቀረጥና ታክስ መከፈሉን ለማረጋገጥ እንዲቻል እቃዎች በዋስትን መግባት እንደሚችሉና በአንቀጽ 119(3) ደግሞ ባለእዳው ግዴታውን ሳይወጣ በቀረ ጊዜ ዋስትን ሰጪ ክፍያውን ወዲያውኑ መፈጸም እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ከአዋጁ አንጻር በጊዜያዊነት በሚገቡ እቃዎች ላይ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል የሚደረግ መሆኑንና በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተመልሰው ከአገር በማይወጡት እቃዎች ላይ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ የሚደረግ

መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በጊዜያዊነት ለገቡት እቃዎች በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ የተጠናቀቀ በመሆኑ ምክንያት፡-

- በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት ብር 7,943,500.00
- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 8,742,424.13
- በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 7,185,348.17
- በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 24,846,943.01 ከዚህ ውስጥ ብር 5,930,879.67 ወደ አቃቢ ህግ የተላለፈ ቢሆንም ያስያዙት ዋስትና ከዋስትና ሰጪዎች ተሰብስቦ ገቢ ያልተደረገ፣
- አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 38,247,446.01

በድምሩ በ5 ቅ/ፅ/ቤቶች ብር 86,965,661.32 በጊዜያዊነት ለገቡት እቃዎች በውሉ የተወሰነዉ የመቆያ ጊዜ የተጠናቀቀ ቢሆንም በዋስትና የተያዘዉ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያልሆነ መሆኑን ወይም ውሉ አለመታደሱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

በጊዜያዊነት በሚገቡ እቃዎች ላይ በአዋጁ መሰረት ተገቢዉ ቁጥጥር በማድረግ እርምጃ ካልተወሰደ በጉምሩክ የቀረጥና ታክስ ገቢ አሰባሰብ ላይ የሚያስከትለዉ ጉዳት ከፍተኛ ሊሆን ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በአዋጁ መሰረት በዋስትና የተያዘዉ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ መሆን አለበት፡፡ለወደፊቱም በጊዜያዊነት በሚገቡ እቃዎች ላይ በአዋጁ መሰረት ተገቢዉ ክትትል፣ቁጥጥርና እርምጃ ሊወሰድ ይገባል ፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- ከተገለጸው ሂሳብ ውስጥ የተወሰኑት ተመልሰው እንደወጡና መረጃዎች ተጣርተው እርምጃ እንደሚወሰድና ክትትል እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

ሽ) ለኦዲት ያልቀረቡ 489 የጉምሩክ ዲክላራስዮኖች መኖራቸው

ግኝት

በበጀት ዓመቱ ከተስተናገዱትና ለኦዲት እንዲቀርቡ ከተጠየቁት ዲክላራሲዮኖች መካከል ከሶስት ቅ/ጽ/ቤቶች ብዛታቸው 489 የሆኑት ዲክላሳዮኖች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው በእነዚህ ዲክላራሲያኖች የተሰበሰበውን ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም ፡፡ ዝርዝራቸውም ፣

- በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት በኩል 118 ዲክላራሲዮኖች
- በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት በኩል 5 ዲክላራሲዮኖች
- የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል 366 ዲክላራሲዮኖች

ናቸው፡፡

ስጋት

የተጠየቁት ማስረጃዎች ካልቀረቡ የሒሳቡን ትክክለኛነት አጠራጣሪ ያደርገዋል አሰራሩም ለብልሹ አሰራር በር ይከፍታል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ለኦዲት ሊቀረቡ ያልቻሉት ተፈልገው ትክክለኛነታቸው በውስጥ ኦዲት ተረጋግጦ ውጤቱ ሊገጸልን ይገባል፡ ለወደፊቱም ማስረጃዎች በሚፈለጉ ጊዜ ወዲያው እንዲገኙ አስፈላጊው የዶክመንት አያያዝ መተግበር ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- የመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት ስራ አመራር ዶክሜንቴሽን ክፍል ሰራተኛዋ በመታመሟ ምክንያት በተወከለው ሰራተኛ ተፈልጎ ሊገኝ ባለመቻሉ ሲሆን የተወሰኑትም በአሰሰሮች እጅ የነበሩ መሆናቸውን፣
- የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ስራ አመራር ያልቀረቡትን 366 ዲክላራሲዎኖችን ሂሳባቸውን አጣርተው እንደሚያቀርቡ፣

በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

ቀ) <u>የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማጣራት ያልተቻለ የመጋዘን ክፍያ ብር 2,546,643.92</u>

<u>ግኝት</u>

ወደ ሀገር የሚገቡና ከሀገር ለሚወጡ እቃዎች የመጋዘን ኪራይ ማስከፈያ ምጣኔ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 59(3) በተደነገገው መሰረት እንደዚሁም ይህን ለማስፈጸም ተሻሽሎ በወጣው መመሪያ ቁጥር76/2004 መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል የመጋዘን መግቢያ ደረሰኝ (ማንኛውም እቃ ሲመጣ የሚመዘገብበት) ሲሆን፣ የመጋዘን መውጫ ደረሰኝ(እቃው ሲወጣ በተሽከርካሪ ከሆነ ሲሄድ የቆይታ ጊዜ እና የእቃው ጠቅላላ ክብደት የሚገለጽበት እንደዚሁም
- በተቀመጠው ስሌት መሰረት ተባዝቶ የሚቀመጥበት) ቢሆንም መስሪያ ቤቱ ደረሰኞቹን የማይጠቀም መሆኑን፣
- ከላይ የተጠቀሱት መረጃዎች ቤዝ በማድረግ የጉምሩክ መጋዘን ውስጥ የገባ እቃ በተሽከርካሪ ላይ የሚፈተሸን ጨምሮ ለቆየባቸው ለእያንዳንዱ ቀን በተቀመጠው ስሌት መሰረት መሰራት ሲኖርበት ቅ/ጽ/ቤቱ ካለ ምንም የመረጃ ምንጭ ብር 2,546,643.92 የሰበሰበ ሲሆን የገቢው አሰባሰብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>ስጋት</u>

መሰብሰብ ያለበት ገቢ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡ የዚህ ዓይነት አሰራርም ለብልሹ አሰራር በር ይከፍታል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ከላይ በተገለጸው የአሰራር ክፍተት ምክንያት ያልተሰበሰበ ገቢ ተጣርቶ ከሚመለከተዉ ድርጅት መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ከላይ በተቀመጠው መሰረት መሰራት ይኖርበታል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

- ❖ እቃዎች የሚፈተሹት በጉምሩክ ግቢ ሳይሆን በመንገድ ላይ በመሆኑ የመጋዘን መውጫም ሆነ መግቢያ የተባለውን ደረሰኝ ለመጠቀም አልተቻለም፡፡
- ❖ የመጋዘን ኪራይ ብለን የምንሰበስበው በመኪና ላይ እንዳለ የሚፈተሽ እቃን ሲሆን መጋዘን ኪራይ አከፋፈል መመሪያ ቁጥር 40 እና ተሻሽሎ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 76 መሰረት ያደረገ ሲሆን ከአንድ ቀን በላይ በራሱ ጊዜ የቆየ አስመጪ በተጨማሪ ይከፍላል፡፡ በመስሪያ ቤቱ ችግር ከሆነ ግን አይከፍልም በተረፈ ሳይከፍል የሚሄድ ቢኖርም በቀጣይ እየተከታተልን እንገኛለን፡፡

<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

የተጠቀሰው መመሪያ መሰረት ለመስራት መጀመሪያ የመጋዘን ኪራይ የተከፈለበት እቃ በእቃ ገቢ ደረሰኝ እና በመጋዘን ሂሳብ ማስያ ደረሰኝ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ማስረጃን መሰረት ያላደረገ አስተያየት በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

በ) <u>የዋስትና ሂሳብን በተመለከተ</u>

<u>ግኝት</u>

የፌዴራል ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው የመንግስት ሂሳብ አያያዝ መመሪያ እንዲሁም ማኑዋል መሰረት የዋስትና ሂሳብ አሰራር በአግባቡ መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡-

<u>በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት</u>

- ➢ የሂሳብ አያያዝን በተመለከተ ወጥ የሆነ የሂሳብ መዝገብ (TR) ፣ ሌጀር እና ባንክ ማስታረቂያ የማይሰራለት መሆኑን፣
- ➢ የአመቱ ዲፖዚት ባንክ ባላንስ ፡ የገቢ ሂሳብ ቡድን ሪፖርት ላይ እና የመስሪያ ቤቱ ሪፖርት ላይ ያለው አኃዝ (የመስሪያ ቤቱ፡- ብር 578,822.96 ከገቢ ሂሳብ፡- ብር 3,475,650.12 ባንክ እስቴትመንት ብር 3,231,700.76 የሚያሳይ ሲሆን ከገቢ

ሂሳብ እና እስቴትመንት ልዩነት ብር 243,949.36 ሲሆን የመስሪያ ቤቱ እና ገቢ ሂሳብ ብር 2,896,827.16) በልዩነት የሚያሳይ መሆኑን፣

- በመመሪያ ቁጥር 37/2002 በአንቀጽ (9)እና(10) ዕቃዎች በዋስትና ስለሚለቀቁበት ሁኔታ የወጣ የአፈፃጸም መመሪያ መሠረት ቀረጥ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ እቃዎች ተመልሰው መዉጣታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በጊዜአዊነት የገቡ እቃዎች ለብቻ ተመዝግበው ያልተያዙ በመሆናቸው ተመልሶ የወጣና ያልወጣ መቆጣጠሪያ ስልት የሌለ መሆኑን፣

ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ስጋት

- የአሰራር ክፍተቱ የተሰበሰበውን የመንግስት ገቢ ለብክነት ሊዳርግ ይችላል እንዲሁም ለሪፖርቱ ተጠቃሚ አካል ትክክለኛ የሂሳብ አቋም ላይገልጽ ይችላል፣
- የዲፖዚት ሂሳቡ በመመሪያው በተወሰነለት ቀን ድረስ እቃው ካልወጣ ወደ ቀጥታ ገቢ ለማሸጋገር ሂሳቡን ውስብስብ ከማድረጉም በተጨማሪ ሌሎች ክፍተቶችን ሊያስከትል ይችላል፣
- የአሰራር ክፍተቱ መሰብሰብ ያለበትን የመንግስት ገቢ ሊያስቀር ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

- ከላይ የተጠቀሱት የሂሳብ መዛግብት ያልተቋቋመላቸው የተሟላ መዝገብ ሊቋቋምና ቀረጥ ሳይከፈልባቸው የገቡ እቃዎች ተመልሰው መዉጣታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል መከታተያ መዘክር ሊቋቋም ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

የተጠቀሰው አስተያየት ተቀብለው በመመሪያው አግባብ መሰረት አሰራሩን የሚያስተካክሉ መሆኑን በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅትና የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ መስራት መጀመራቸውን ደግሞ ለተጠቃለለው ሂሳብ ሪፖርት በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

ተ) <u>የወጪ እቃዎች የማይታሸጉና የማይፈተሸ ስለመሆኑ</u>

<u>ግኝት</u>

የወጪ እቃ አላላክ በተመለከተ ጭነት ለያዘ ተሽከርካሪ መረጃው ተሞልቶ በ ሲል ታሽጎ በቀረበው መሰረት ቅጽ 1 በማዘጋጀት በመሀተም እና ፊርማ ተረጋግጦ ለላኪው/ወኪሉ መሰጠት እንደሚኖርበት የስራ ማኑዋሉ ይጠቅሳል ፡ ነገር ግን በ ጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት የሚስተናገድ ማንኛውም ወጪ እቃ በ ፕሎምፕ እየታሸገ አለመሆኑን ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ማንኛውም የወጪ እቃ ሲወጣ ተፈትሾ የማይወጣ መሆኑን በአካል በመገኘትም ሆነ የሰነድ ማረጋገጫዎችን በማጣራት ተረጋግጧል፡፡

<u>ስጋት</u>

በተፈጠረው የአሰራር ክፍተት ብልሹ አሰራሮች ሊሰሩ ይችላሉ፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

መታሸግ ያለበት ወጪ እቃ በፕሎምፕ እየታሸገ መላክ እና ማንኛውም የወጪ እቃ ሲወጣ ተፈትሾ መውጣት ይኖርበታል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

- ፕሎምፕ ማግኘት ስላልተቻለና በተደጋጋሚ ጠይቀን ችግሩ ሊፈታልን ስላልቻለ ጥያቄውን ማቅረባችን እንደቀጠለ ሆኖ አገልግሎቱ ግን በፕሎምፕ ሳይታሸግ ቀጥሏል፡፡
- ወጪ እቃዎች መፈተሽ እንዳለባቸው እርግጥ ነው ለማውረድ ግን የተመቻቸ ሁኔታ የለም በቀጣይ የሚሰራበት ይሆናል፡፡

ቸ) <u>በዱቤ ከተሸጡ ብር 1,017,389,090.22 ውስጥ ብር 391,213,272.36 ያልተሰበሰበ የተወረሱ ዕቃዎችን በተመለከተ</u>

<u>ግኝት</u>

በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎች አወጋገድ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 56/2003 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1፤ በዚህ መመሪያ በተለያዩ አካላት በድርድር የሚሸጡ

ዕቃዎችን የሽያጭ ገንዘብ ገዢዎች ዕቃውን በተረከቡ እስከ 45 ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ ባለስልጣኑ በሚያሳውቀው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ማድረግ ወይም በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ክፍያ መፈጸም አለባቸው ተብሎ ተደንግጓል፡፡በተጨማሪም በድርድር ለተሸጡ ዕቃዎች በተገለጸው ጊዜ ገንዘቡን ገቢ ያላደረገ ግዢ በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የተገለጸው የጊዜ ገደብ ካለፈበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ ባለው ከፍተኛ ምጣኔ ወለድ ይታሰብበታል ተብሎ በተደነገገው መሰረት ባለስልጣን መ/ቤቱ እየሰራ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች በዝርዝር በተገለጸው መሰረት ከ 2000 ዓ.ም ጀምሮ የሚከተሉት የአሰራር ክፍተቶች መኖራቸው ተረጋግጧል፡-

1ኛ. መመሪያ ቁጥር 56/2003 ተግባራዊ እንዲሆን ከተወሰነበት ጊዜ ጀምሮ በዱቤ ለተሸጡ ዕቃዎች በህግ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ የዱቤ ሽያጭ ገቢው እየተሰበሰበ አለመሆኑ፣

2ኛ. እስከ 30/10/2007 ድረስ ከ ጅንአድ ብቻ እስከ 7 ዓመት የቆየ ያልተሰበሰበ የዱቤ ሽያጭ በድምሩ ብር. 391,213,272.36 መኖሩ፣

ታውቋል፡፡

ስጋት

በዳይሬክቶሬቱ በዱቤ ለተሸጡ ዕቃዎች ክትትል እየተደረገ በወቅቱ ገቢው እንዲሰበሰብ የማይደረግ ከሆነ መንግስት ማግኘት የሚገባው ገቢ በወቅቱ እንዳያገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

መመሪያው በሚያዘው መሰረት በወቅቱ ከገዢዎች ሊሰበስብ ይገባል፡፡ በህግ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ገንዘቡን ገቢ ከማያደርጉ ገዢዎች ላይ በመመሪያው መሰረት ወለዱ እየታሰበ ገቢው ሊሰበስብ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

በዱቤ ለተሸጡ እቃዎች በህግ በተደነገገዉ ጊዜ ገደብ ያለፈውን በመፈተሽ የተከፈለውን ገንዘብ መጠን የቀሪውንም ገንዘብ ጭምር በተቀመጠው የወለድ ምጣኔ መሰረት ወለዱን የማስላት ስራ የጅ.ን.አ.ድ በቅርቡ ተጠናቅቆ በቀጣይ ሂደቱን ጠብቆ

ክፍያውን የሚፈፅሙበትን መንገድ በማመቻቸት እንዲከፍሉ የሚጠየቁ ይሆናል በማለት ለስራ አመራሩ ሪፖርት በሰጡት መልስና በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅት ገልጸዋል፡፡

2. <u>የአገር ውስጥ ገቢ ሂሳብን በተመለከተ</u>

ሀ) <u>ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብርና የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 12,089,487.91 ግብር መኖሩ</u>

<u>**ግኝት**</u>

በየቅ/ጽ/ቤቱ ግብር ከሚከፍሉ ድርጅቶች ለናሙና ከመረጥናቸው ውስጥ የንግድ ትርፍ ማስታወቂያ ላይ የተገለጸው የአመቱ (የ2006 የግብር ዘመን) ጠቅላላ ሽያጭ/ ገቢ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ከተገለጸው የአመቱ (የ2006 የግብር ዘመን) የ12 ወራት ጠቅላላ የሽያጭ ድምር ጋር ሲነጻጸር የተለያየ በመሆኑ ምክንያት፡-

• የባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት በኩል	ብር	10,916.43
• የጅማ ቅ/ጽ/ቤት በኩል	ብር	135,435.01
• በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት	ብር	7,373,393.58
• በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት	ብር	15,841.45
• የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	ብር	1,060,559.19
በድምሩ	ብር	8,596,145.66

ያልተከፈለ የንግድ ትርፍ ግብር፣

እንዲሁም

• በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት	ብር	286,320.69
• የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	ብር	3,207,021.56
በድምሩ	ብር	3,493,342.25

ያልተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ መኖሩ ታውቋል፡፡

ስጋት

ይህ ሁኔታ የመንግስትን ገቢን የሚቀንስ ከመሆኑም በተጨማሪ ክትትል የማይደረግ ከሆነ ግብር ከፋይ ድርጅቶች ሆን ብለው ገቢያቸውን በመቀነስ መክፈል የሚገባቸውን ግብር በየአመቱ ሊሰውሩ ይችላሉ ፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ያልተከፈለውን ግብር በአዋጁ መሰረት የግብር ዕዳቸውን ከነመቀጫ እና ወለድ ሊሰበስብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ግብር ከፋዮች በሚያቀርቡት ንግድ ትርፍ ማስታወቂያ ላይ የተገለጸው የሽያጭ መጠን በ12 ወራት ከሚያሳውቁት የቫት ዲክላራሲዎን ላይ ከተገለፀው የሽያጭ መጠን ጋር ልዩነት ሲኖረው የልዩነቱ መንስኤ ሊጣራ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- መረጃዎችን በማየትና በማጥራት ውሳኔ እንደሚሰጥና የግብር ዕዳውን እንደሚሰበስቡ ገልጸዋል፡፡

ለ) **በሂሳብ አያያዝ ስህተት ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ብር 98,948.89 በተመለከተ**

ግኝት

በአዋጅ ቁጥር 286/1994 ክፍል 4ንኡስ ቁጥር 17 ከንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በተገኘ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ የገቢ ግብር እየተጣለ ይሰበሰባል በሚለው መሰረት ኦዲት ሲደረግ በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት በኩል አንድ ድርጅት በንግድ ትርፍ ማሳወቂያ ላይ ተመላሽ (Refund) ሂሳብ ብር 329,829.62 በስህተት ሁለት ጊዜ ተቀናሽ በመደረጉ ምክንያት ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ግብር ብር 98,948.89 መኖሩ ታውቋል፡፡

ስጋት

ግብር ከፋዩ ሽያጩን በትክክል ባለማሳወቁ መንግስት ከንግድ ትርፍ ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ ሊያሳጣው ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

የስራ ክፍሉ ያልተሰበሰበውን የንግድ ትርፍ ግብር ቅጣትና ወለድ ታክሎበት ሊሰበስብ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

ድርጅቱ ክፍያውን እንዲፈጽም በቀን 14/06/2008 በደብዳቤ ቁጥር መሥ/3.1/5208/08 የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ወጥቷል በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

ሐ) በውል ስምምነት መሰረት ያልተሰበሰበ ብር 230 381.92

ግኝት

የግብርና ታክስ አስተዳደራዊ መቀጫዎች አነሳስ፣ የክፍያ ጊዜ ስምምነት እና የግብር ግዴታን ስለመወጣት በማረጋገጫነት የሚሠጥ የምስክር ወረቀት (ክሊራንስ) አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 55/2003 አንቀጽ 14 መሰረት የክፍያ ማራዘሚያ ጊዜ ውል ስምምነት የገቡ ግብር ከፋዮች ዕዳቸውን በገቡት የውል ስምምነት መሰረት እየከፈሉ እንደሆነ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

በኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ሁለት ግብር ከፋዮች ዕዳቸውን በውሉ መሰረት ለተጠቀሰው ዘመን ያልከፈሉት በድምሩ ብር 230,381.92 ውዝፍ እዳ መኖሩ ታውቋል፡፡

ስጋት

ቅ/ጽ/ቤቱ በመመሪያዉ መሰረት እያንዳንዱ ግብር ከፋዩ ህብረተሰብ ላይ ተገቢውን እርምጃ በመዉሰድ ግብር ከፋዮቹ ዕዳቸውን በገቡት በውሉ መሰረት ለተጠቀሰው ዘመን ውዝፍ እዳ ግብር በጊዜ ካልከፈሉ መንግስት በሚፈልገዉ ገቢ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

በዝርዝር ለተጠቀሱት ግብር ከፋይ ድርጅቶች ዕዳቸውን ከፍለው ያልጨረሱት በእዳ ክትትል ቡድን ያልተሰበሰበው ቀሪ የግብር እዳ እንዲሰበሰብ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም እዳቸውን በገቡት ውል መሰረት ባለማጠናቀቃቸው የግብርና ታክስ አስተዳደራዊ መቀጫዎች አነሳስ፣ የክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ ቁጥር 55/2003 አንቀጽ 17 መሰረት ውሉን በማቋረጥ ቀጣይ የግብር/ታክስ አሰባሰብ ስነ-ስርዓት ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

ጢጣ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ያግዝ ኢንጅነሪንግ አማካሪዎች የክፍያ ውል ስምምነት ገብተው እዳቸውን እየከፈሉ ስለሆነ ተከታትለን እዳቸውን እንዲያጠናቅቁ የሚደረግ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

መ) የጥገናና የማሻሻያ ወጪ በአዋጁ መሰረት ባለመያዙ ምክንያት ብር 66,210.92 የገቢ ግብር ያልተሰበሰበ መሆኑ

ግኝት

ድርጅቶች ወጪያቸውን በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 እና በገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 608/2001 አንቀጽ 3 መሰረት የሚይዙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በየቅ/ጽ/ቤቶቹ ገቢያቸውን እያሳወቁ ግብራቸውን የሚከፍሉ ግብር ከፋዮች በየምድቡ

ለሚኖሩ የድርጅቱ የቋሚ እቃዎች የጥገናና የማሻሻያ ወጪያቸው ለእርጅና ቅናሽ መሰረት ከሆነው ዋጋ ከ 20 በመቶ በላይ በሚሆንበት ጊዜ ወጪው ሙሉ በሙሉ በዕቃው የእርጅና ቅናሽ መሰረት በሆነው ዋጋ ላይ ተደምሮ ወጪው በእርጅና ቅናሽ ደንብ መሰረት መታሰብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን ለናሙና ኦዲት ካደረግናቸው የግብር ከፋይ ፋይሎች ውስጥ ግብር ከፋዮች ከላይ በተገለጸው አዋጅ መሰረት የቋሚ እቃዎች የጥገናና ማሻሻያ ወጪ ባለመያዙ ምክንያት፡-ምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የጥገና ወጪዎችን ያለአግባብ እንደወጪ በማሳወቃቸው ሊሰበሰብ የሚገባው የንግድ ትርፍ ገቢ ብር 66,210.92 ያልተሰበሰበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ስጋት

ተገቢው ክትትል የማይደረግ ከሆነ ግብር ከፋይ ድርጅቶች አዋጁ ላይ ከተቀመጠው በተቃራኒው ሆን ብለው የጥገናና ማሻሻያ ወጪን የዘመኑ ወጪ እንደሆነ በመውሰድ ለመንግስት መክፈል ያለባቸውን የገቢ ግብር አላግባብ እንዲቀንስ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በአዋጁ መሰረት በድጋሚ የግብር ማሳወቂያ በመስጠት ያልተሰበሰበው የንግድ ትርፍ ግብር መቀጫ እና ወለድን ጨምሮ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ሊሰበስብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጠር የሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን ጥንቃቄ ሊወስዱ ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

ሃሳቡን በመቀበል በቀጣይ ያልተሰበሰበውን የንግድ ትርፍ እንደሚሰበሰብ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

ሠ) **<u>ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ላይ መቀናነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀናነሳቸው ምክንያት ብር 2,259,617.12 የገቢ ግብር ያልተሰበሰበ መሆኑ</u>**

<u>ግኝት</u>

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 21 መሰረት ለንግድ ስራው ገቢ ለማግኘት፣ለንግድ ስራው ዋስትና ለመስጠትና እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል የተደረጉ ወጪዎች ብቻ መቀናነስ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ላይ መቀናነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀናነሳቸው ምክንያት፡-

- ምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ከሁለት ድርጅቶች ተቀናሽ መደረግ የማይገባው ወጪ ተቀናሽ በመደረጉ ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር ብር 175,509.15 መገኘቱ፣
- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ተቀናሽ መደረግ የሌለበት ወጪ ከንግድ ትርፍ ገቢ ላይ በመቀናነሱ ምክንያት ገቢ ያልሆነ ንግድ ትርፍ ግብር ብር 2,082,888.54 መኖሩ፣
- ምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ከአንድ ግብር ከፋይ ሊቀነስ የማይችል የወለድ ገቢ (Interest income) ብር 1,219.43 ንግድ ትርፍ ገቢ ላይ ተቀንሶ በመገኘቱ ንግድ ትርፍ ያልተከፈለበት መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

ስጋት

ግብር ከፋዮች የሚያቀርቡት የንግድ ትርፍ ማስታወቂያ በትክክል እየተሞላ የሚቀርብ መሆኑን በአግባቡ የማይጣራ ከሆነ በማስታወቂያው ላይ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ በመሙላት ግብር ከፋይ ድርጅቶች ግብራቸውን ሊሰውሩ ይችላሉ መንግስትም ማግኘት የሚገባውን ገቢ ሊያጣ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ያልተሰበሰበው የንግድ ትርፍ ግብር መቀጫ እና ወለድን ጨምሮ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ሊሰበስብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጠር የሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን ጥንቃቄ ሊወስዱ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- ክትትል በማድረግ የማስታወቂያ ውሳኔ በመስጠት እንደሚሰበስቡ ገልጸዋል፡፡

ረ. ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ

ግኝት

የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢዎች በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 21 ታክስ ስለማቀናነስ ንዑስ አንቀፅ 5 ላይ በአንድ ግብይት ኢንቮይስ ወይም የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ላይ የተመለከተው ታክስ በዚህ ግብይት ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ በልጦ የተገኘ እንደሆነ በብልጫ የታየው የገንዘብ መጠን በአንቀፅ 13 የተመለከተው በተፈፀመበት የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ሊቀናነስ እንደሚችል እና እንዲሁም አዋጅ 285/2002 አንቀጽ 20/1 መሰረት በትክክል መቀናነስ ያለበት ሂሳብ ተቀናንሶ ልዩነቱ ለባለስልጣኑ መ/ቤት መከፈል ያለበት ሂሳብ ስለመከፈሉ እና ተመላሽ ሂሳብ በትክክል ስለመመለሱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በጅማ ቅርንጫፍ ከ2 ግብር ከፋዮች ያልተሰበሰበ ብር 16,226.37 እና በነቀምቴ የታክስ ማዕከል ደግሞ ከ 1 ግብር ከፋይ ያልተሰበሰበ ብር 7,143.73 በድምሩ ብር 23,370.10 ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ መኖሩ ታውቋል፡፡

ስጋት

በየሂሳብ ጊዜው የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋዮች ሂሳብ የማይጣራ ከሆነ ቅ/ፅ/ቤቱ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ማግኘት የሚገባውን ገቢ በወቅቱ ወይም ሳይሰበሰብ ሊቀር ከመቻሉም በላይ ሊያስጠይቅ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ከላይ ለተመለከተው ሂሳብ ተገቢ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ ሆኖ ለወደፊቱ ተመሳሳይ የአሰራር ግድፈት እንዳይደርስ በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ ወቅታዊ የሆነ የስሌት ማጣራት ሥራ ሊከናወን ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

የተገኘው ግኝት ትክክል መሆኑንና የሚፈለግበትን ግብር እንዲከፍል የፅሁፍ ጥሪ እናደርጋለን ሲሉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

ሰ) የግብር ዕዳ ውሳኔ ማስታወቂያ ደርሷቸው ያልተከፈለ ወይም የግብር ይግባኝ አቤቱታ ያልቀረበበት ሂሳብ ብር 102,286,901.37 መኖሩ

ግኝት

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 77/1 መሰረት በታክስ ኦዲትም ሆነ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አማካኝነት ውዝፍ የግብር ዕዳ ያለባቸው ግብር ከፋዮች የግብር ዕዳቸውን በ 30 ቀናት ውስጥ እንዲከፍሉ ውሳኔ ደርሷቸው ያለባቸውን የግብር እና የታክስ ዕዳ እስካሁን ደረስ ባልከፈሉ ግብር ከፋዮች ላይ በአዋጁ መሰረት የንብረት መያዝ እርምጃ እየወሰዱ ስለመሆናቸው ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- በባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት በኩል አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔውን ያጸናው ወይም በድጋሜ እንዲታይ ታዞ በተሰጡ ውሳኔዎች መሰረት ያልተሰበሰበ ግብር ብር 3,669,332.89 የሚገኝ መሆኑ፡፡
- በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የገቢ ግብር ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ፣ እና ትርፍ ክፍፍል ግብር በጠቅላላው ብር 316,663.72 ያልተሰበሰበ የግብር ሂሳብ፣

- በከምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የግብር ዕዳ ውሳኔው የደረሳቸው ቢሆንም በገቢ ግብር አዋጁ መሰረት በ 30 ቀናት ውስጥ መጥተው ዕዳቸውን ያልከፈሉት ሂሳብ በድምሩ ብር 82,962,588.77 የሚገኝ መሆኑ፣
- የምራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በኩል በታክስ ኦዲት በኩል ውሳኔ አግኝተው በውሳኔው መሰረት ግብር ከፋዩ ስምምነት ገብቶ በስምምነቱ መሰረት ግብርን በተወሰነው ግዜ ሳይሰበሰብ የቆየ ሂሳብ በድምሩ ብር 15,338,315.92፡

መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

ስጋት

የተወሰነውን ውዝፍ የግብር ዕዳ በአዋጁ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ በማይከፍሉ ግብር ከፋዮች ላይ በአዋጁ መሰረት እርምጃ የማይወሰድ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ በወቅቱና በአግባቡ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

ያልተሰበሰበው የግብር እዳ ከሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ዕዳቸውን ለመክፈል ፈቃደኛ ባልሆኑት ግብር ከፋዮች ላይ በአዋጁ መሰረት ንብረታቸውን በመያዝ ወይም እንዲታገድ በማድረግ ያልተከፈለ ዕዳቸውን እንዲሸፍን መደረግ ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- አንዳንዶቹ ግብር ከፋዮች ውል ገብተው ከፍለው ያልጨረሱ ሌሎች ደግሞ ወደ ዋና መ/ቤት የተላለፉ በመሆኑ ተከታትለን ለማስገበት ጥረት እናደርጋለን የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ሸ) በግብር ከፋዮች ለቀረበው ቅሬታ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔው ያልተሰጠው ግብር ብር 58,036,507.02 መኖሩ

ግኝት

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 105(2) መሰረት የአቤቱታ አጣሪው ከግብር ከፋዮቹ የሚቀርበውን አቤቱታ ሊያይ የሚችለው ግብር ከፋዩ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ

በደረሰው በ10 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ማቅረብ ከቻለ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አቤቱታው ሊታይለት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ከዚህ አንፃር ለሚቀርቡ አቤቱታዎች በወቅቱ ውሳኔ በመስጠት የመንግስት ግብር እንዲሰበሰብ የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በጅማ ቅ/ፅ/ቤት የትርፍ ግብር ብር 15,600,985.29 ያለባቸው 26 ግብር ከፋዩች፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 3,338,080.95 ያለባቸው 14 ግብር ከፋዮች፣ ተርን ኦቨር ታክስ ብር 445,118.15 ያለባቸው 2 ግብር ከፋዮች፣ ቅድመ ገቢ ግብር

  ብር 1,135,070.08 ያለባቸው 11 ግብር ከፋዮች፣ትርፍ ክፍፍል (ዲቪደንድ) ብር 3,226,138.08 ያለባቸው 10 ግብር ከፋዮች በድምሩ ብር 23,745,392.55 በ2007 በጀት ዓመትና ከዚያ በፊት የአጠቃላይ ኦዲት ውሳኔ ተሰጥቷቸው ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም አሁንም ውሳኔ ያልተሰጣቸው መሆኑ፣

  - በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በኩል አንድ ግብር ከፋይ ውሳኔ ሳይሰጣቸው ለረጅም ጊዜ በኮሚቴ እጅ እንደሚገኙና በዚህም ምክንያት በድምሩ ብር 217,618.56 የግብር ዕዳ መሰብሰብ ያለበት ይሁን አይሁን ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣
  - በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት የግብር ዕዳቸውን ያልከፈሉ ከ28 ግብር ከፋዮች ያልተከፈለ የግብር ዕዳብር 34,073,495.91 መኖሩ ታውቋል፡፡

<u>ስጋት</u>

በአጠቃላይ ኦዲት ውሳኔ መሰረት የተወሰነው ያልተከፈለ የግብር ዕዳ በግብር ከፋዩ ቅሬታ ያቀረበበት ከሆነና በአስቸኳይ በቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ ተሰጥቶበት የግብር ዕዳው በአግባቡና በወቅቱ የማይሰበሰብ ከሆነ መንግስት ገቢውን ማግኘት ባለበት ወቅት እንዳያገኝ ሊያደርገው ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ከላይ በተመለከቱት የግብር ይግባኞች ላይ አፋጣኝ የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ ሆኖ ለወደፊቱ ለአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የሚቀርቡ የግብር ይግባኞች በተቀመጠላቸው ቀነ ገደብ ወይም ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ጉዳዮቹ ውሳኔ እንዲያገኙ እየተደረገ ገቢው ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

- የተቻለቸውን ሁሉ በማድረግ የቀረቡትን ቅሬታዎች ለማጣረት ጥረት የሚያደርጉ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

ቀ) <u>የተሸጠ ዕቃ ዋጋን ከፍ በማድረግ ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ግብር ብር 6,000</u>

<u>ግኝት</u>

በጅማ ቅ/ጽ/ቤጽ የተሰበሰበውን የግብር ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ወለጋ ዩኒቨርሲቲ ሆሮጉዱሩ አግሮ ኢንዱስትሪ ምርትና አገልግሎት ኢንተርፕራይዝ (0023779972) ግብር ከፋይ ያቀረበው የንግድ ትርፍ ማሳወቂያ ላይ የተገለጸው የአመቱ ጠቅላላ የተሸጠ ዕቃ ዋጋ (Cost of good sold) በብር 20,000.00 ከፍ በመደረጉ ምክንያት ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር ብር 6,000.00 ተገኝቷል።

<u>ስጋት</u>

ግብር ከፋዮች የሚያቀርቡት ማስረጃ ትክክል ለመሆኑ በተገቢው ጊዜ የማይረጋገጥ ከሆነ መሰብሰብ የሚገባው ገቢ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል።

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ከላይ ሳይሰበሰብ የቀረው የንግድ ትርፍ እንዲሰበሰብ ሆኖ ለወደፊቱ በግብር ከፋዮች የሚቀርቡ የሂሳብ እቅስቃሴ ሰነዶች ትክክል ለመሆናቸው በተገቢው ጊዜ እንዲረጋገጥና ተመሳሳይ የአሰራር ግድፈት እንዳይደርስ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ቀሪውን ግብር እንዲከፍሉ ውሳኔ እናወጣለን ብለዋል፡፡

በ) <u>ያልተሰበሰበ መቀጫ ብር 21,000.00 መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 86 ከ ሀ-ሐ በተገለጸው መሰረት ማንኛውም ግብር ከፋይ ገቢውን ካላሳወቀ እና አዘግይቶ ካሳወቀ የሚጣልበት መቀጫ እንዳለ ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሰረት ገቢያቸውን በማያሳውቁት ወይም አዘግይተው በሚያሳውቁ ግብር ከፋዮች ላይ በአዋጁ መሰረት የቅጣት እርምጃ እየወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት
    - ሜጋ ኢንዱስትሪያል ኃ/የተ/የግል ማህበር የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0004726492 ከታች በገለጽነው መሰረት ገቢውን በወቅቱ ባለማስታወቁ ያልተወሰነበት ቅጣት ብር 21,000.00 መኖሩ ታውቋል፡-

1. የ2005 ግብር ዘመን ገቢውን ያሳወቀው በ 22/07/06 በመሆኑ ለ 4 ወራት የዘገየ ሲሆን በአዋጁ መሰረት መቀጫ ብር 6,000.00 ያልተወሰነበት መሆኑ፣
2. የ2006 ግብር ዘመን ገቢውን ማሳወቅ የነበረበት ጥቅምት 2007 ዓ.ም ሲሆን እስከ ነሀሴ 2007 ዓ.ም ድረስ ያላሳወቀ በመሆኑ በአዋጁ መሰረት መቀጫ ብር 15,000.00 መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

<u>ስጋት</u>

ግብር ከፋዮች የሚያቀርቡትን የሂሳብ መግለጫ እና የገቢ ማስታወቂያ በጊዜ ገደቡ ስለመቅረቡ ካልተረጋገጠ በወቅቱ መሰብሰብ ያለበት ፍሬ ግብር፣ መቀጫ እና ወለድ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ከላይ በተገለጸው አዋጅ መሰረት መቀጫው እንዲሰበሰብ የውሳኔ ማስታወቂያ ማውጣት ይኖርበታል፡፡ ለቀጣይ ግብር ከፋይ ድርጅቶች ገቢያቸውን በወቅቱ ያላሳወቁ ከሆነ የገቢ ማስታወቂያውን ባቀረቡበት ቀን ለዘገዩበት የቅጣት ውሳኔውን በማውጣት ለግብር ከፋይ መስጠት ይኖርበታል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

ድርጅቱ ስራ ማቆሙን ስለገለጸ የይዘጋልኝ ጥያቄ ካቀረበ በኋላ መቀጫ እንደሚመለከታቸው እና እንደማይመለከታቸው ታይቶ ምላሽ/ውሳኔ በመመሪያው መሰረት እንደሚሰጡ ገልጸዋል፡፡

ተ) <u>በትርፍና ኪሳራ ማሳወቂያ (financial stetemenet) ላይ የተመለከተው የእርጅና ቅናሽ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ</u>

<u>ግኝት</u>

ከትርፍ ገቢ ግብር ማስታወቂያ ላይ ከጠቅላላ ትርፍ ላይ እንደወጪ የተቀነሰው የእርጅና ቅናሽ (depreciation) የተሰላው በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 ምዕራፍ1 ክፍል 4 አንቀጽ 23 መሰረት ለኮምፒውተሮች፣ የመረጃ ስርአቶች፣ የሶፍትዌር ውጤቶች፣የመረጃ ማከማቻ መሳሪያዎች 25% እና ለሌሎች ማናቸውም የንግድ ስራ ሃብቶች 20% የእርጅና ቅናሽ ስለመደረጉ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በትርፍ ገቢ ግብር ማስታወቂያ ላይ በተቀመጠው የቋሚ እቃዎች መረጃ መሰረት በየቋሚ እቃዎቹ አይነት የእርጅና ቅናሽ ስሌት በዝርዝር ያልተቀመጠ እና ያልተሰላ በመሆኑ በትርፍና ኪሳራ መግለጫ የተመለከተው ብር 2,189,859.76 የእርጅና ቅናሽ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>ስጋት</u>

መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ ሊያሳጣው ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

ቅጽ/ቤቱ የመንግስትን ግብር አጣርቶ እንዲሰበስብ እና ግብር ከፋዮ የሚያቀርበውን መረጃ የተሟላ እንዲያደርግ ቁጥጥር እና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

ወደፊት እያንዳንዱ ድርጅት የሚያመጣውን የሂሳብ መግለጫ የእርጅና ቅናሽ ስሌት ለመስራት የሚያስችለው ቅጥያ (Annexes) በትክክል እየሞሉ እንዲያመጡ ክትትል እና ቁጥጥር እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

ቸ) ንብረቱ ከታገደ ድርጅት ያልተሰበሰበ ግብር ብር 1,022,255.63

ግኝት

በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤቱ መሰብሰብ ያለባቸው ሂሳቦች ክትትል እየተደረገ የሚሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ሲዳማ ቡና ኃ/የተ/የግ/ማህበር የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0000952729 የሆነ ሰኔ 5 ቀን 2005 ዓ.ም በቁጥር 20.7/6073/104/3 በተወሰነው ውሳኔ መሰረት የገቢ ግብር ከ1997 አስከ 2003 ድረስ ብር 319,260.29 እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ከህዳር 1996 እስከ ሚያዚያ 2004 ዓ.ም.ድረስ ብር 702,995.34 በድምሩ ብር 1,022,255.63 ባለመክፈሉ ንብረቱ ሰኔ 2005 የታገደ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አስፈላጊው ውሳኔ ተወስኖ የሚፈለግበትን ግብር ለመንግስት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

ሊሰበሰብ የሚችል ገቢ በወቅቱ ተሰብስቦ ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደርጋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ቅ/ጽ/ቤቱ አስፈላጊውን ክትትል በማድረግ እና እርምጃ በመውሰድ ሂሳቡን እንዲሰበሰብ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

ከዚህ ቀደም የተወረሱ ንብረቶች ተሸጠው ወደ ገቢ የመቀየር ስራ በኮሚቴ የሚሰራ በመሆኑ በመደበኛ ስራ ላይ ጫና የሚፈጥር በመሆኑ ስራው በአግባቡ የማይከናወን መሆኑ

ታምኖበት የተያዙና የተወረሱ ንብረቶች አስተዳደር ቡድን በማዋቀር ወደ ተግባር ስለተገባ ችግሩን በመፍታት የመንግስት ገቢ በወቅቱ እንዲሰበሰብ እናደርጋለን በማለት ገልጸዋል፡፡

ኀ) ስለአክሲዮን ትርፍ ድርሻ በተመለከተ

ግኝት

በባህርዳር ቅ/ፅ/ቤት ያሉ ግብር ከፋዮች ሐምሌ 30/2005 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ገ/ኢ/1/2/3 የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባወጣው የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍፍል ግብር መመሪያ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 3.4 ላይ ከ2006 የበጀት ዓመት ጀምሮ ኩባንያዎች ትርፍ ለባለ አክሲዮኖች ያከፋፈሉ ወይም የኩባንያውን የካፒታል መዋጮ ለማሳደግ ያዋሉ መሆኑን የሚገልፅ ሪፖርት እና ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማቅረብ እንዳለባቸው በሚያዘው መሰረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት ቁጥራቸው 51 የሆኑ ድርጅቶች የአክሲዮን ትርፍ ለባለ አክሲዮኖች ማከፋፈላቸውን ወይም የድርጅቱን ካፒታል ለማሳደግ ያዋሉ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ቁጥራቸው 5 የሆኑ ድርጅቶች የአክሲዮን ትርፍ ለባለ አክሲዮኖች ማከፋፈላቸውን ወይም የድርጅቱን ካፒታል ለማሳደግ ያዋሉ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

ከትርፍ ክፍፍል ድርሻ (ከዲቪደንድ) ሊሰበሰብ የሚገባው ግብር በወቅቱ ወይም ሳይሰበሰብ ሊቀር ከመቻሉም በላይ መመሪያን አለመተግበር ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ጉዳዩ ተጣርቶ በሚገኘው ውጤት መሰረት ተገቢ የሆነ እርምጃ እንዲወደስ ሆኖ ለወደፊቱ የቁጥጥር ስርአቱ በወቅቱ ሊከናወን ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- የባህርዳር ቅ/ፅ/ቤት በ2007 በጀት ዓመት ትኩረት ተሰጥቶት በአጠቃላይ የ2005 እና የ2006 በጀት ዓመት በትርፍ ያሳወቁ የንግድ ትርፍ ግብር ከፋዮች እና የትርፍ

ድርሻ ግብር (Dividend Tax) መክፍል ያለባቸውን 350 ግብር ከፋዮች የመለየት ሥራ የተሰራ ሲሆን በ2008 በጀት ዓመት በዕቅድ ተይዞ የአሰስመንት ስራ የሚሠራናየሚጠበቅባቸውን ግብር እንዲከፍሉ የሚደረግ መሆኑን፣

- የጅማ ቅ/ፅ/ቤት በስድስቱም ድርጅቶች ላይ የትርፍ ክፍፍል ውሳኔ እናወጣለን፣

በማለት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

ነ) <u>በተከታታይ ለረጅም አመታት ኪሳራ የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮችን መርምሮ አስፈላጊው እርምጃ የማይወስድ መሆኑ</u>

<u>**ግኝት**</u>

በገቢ ግብር አዋጅ 286/2002 ክፍል 1 አንቀጽ 38 በተቀመጠው የግብር አስገቢው ስልጣንና ተግባር መሰረት በተከታታይ ኪሳራ የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮች ላይ ስለሚደረገው ክትትል ለማጣራት በተሞከረበት ወቅት፣

- በምራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ለኦዲት በናሙና ከታዩት ግብር ከፋዮች መካከል ሁለት(2) ግብር ከፋዮች ከአራት ዓመት እስከ ስምንት አመት በተከታታይ ኪሳራ ያሳየ መሆኑንና ምንም ዓይነት ማጣራት አለመደረጉ ታውቋል፣

<u>**ስጋት**</u>

ለተከታታይ አመታት ኪሳራ ያሳወቁትን ግብር ከፋዮች የትርፍ ግብር ማስታወቂያ ተአማኒነት ያሳጣዋል፡፡

<u>**የማሻሻያ ሃሣብ**</u>

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በተከታታይ ለረጅም አመታት ኪሳራ የሚያሳውቁትን ግብር ከፋዮች ተገቢውን ክትትልና ማጣራት በማድረግ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

<u>**የሥራ አመራሩ መላሽ**</u>

ከህግ ተገዥነት እና ስራ አመራር ቡድን ጋር በመነጋገር በቀጣይ ተከታታይ ኪሳራ የሚያሳውቁ ድርጅቶችን ኦዲት እንዲደረጉ እናደርጋለን ብለዋል፡፡

3. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

ሀ) <u>ያለ አግባብ የተከፈለ ከተከፋይ ላይ ተቀናሽ ብር 32,052.21 እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 80,441.25 መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀፅ 24 (1 እና 2) መሰረት በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸዉ ድርጅቶች, የመንግስት መሰሪያ ቤቶች ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ድርጅቶች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአንድ ጊዜ ግዥ ወይም በአንድ የእቃ አቅርቦት ዉል ከብር 10,000.00 በላይ ለሆነ የእቃ አቅርቦት ከሚፈፀም ክፍያ ላይ እንዲሁም በአንድ ጊዜ ግዥ ወይም በአንድ የአግልግሎት ውል ከብር 500.00 በላይ በሚፈፀም ክፍያ ላይ ሁለት በመቶ(2 ፐርሰንት) የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰዉ ማስቀረት እንዳለባቸው ይደነግጋል.፡፡ ከዚህ አንፃር ስራው የሚሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በሞያሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል በድምሩ ብር 3,883.96 የተከፋይ ተቀናሽና የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 2,386.98፣
- ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት በኩል የብር 28,168.25 የተከፋይ ተቀናሽ፣
- ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 2,608.70
- ኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የቅድሚያ ገቢ ግብር ብር 64,043.47
- ጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 11,402.10

መቀነስ የነበረበት ሂሳብ ያልተቀነሰ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

መሰብሰብ ያለበት ግብር ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ለወደፊቱ የሚመለከታቸው ሰራተኞች በደንቡ መሰረት መሰብሰብ ያለበት ቅድመ ግብር እንዲሰበሰብ ተገቢውን ጥንቃቄ ሊወስዱ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- ግኝቶቹን ተቀብለው ለወደፊቱ ተመሳሳይ ችግር እንዳይከሰት ጥብቅ ቁጥጥር እንደሚደረግ ለስራ አመራር ሪፖርት በለኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

ለ) በማመልከቻ ብቻ ተከፍሎ የተገኘ የውሎ አበል ብር 36,131.40፣

ግኝት

ሰኔ 2004 በወጣው የውሎ አበል መመሪያ አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 1 እስከ 4 ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ከስራ ቦታው ውጭ ወደ ሆነ ሌላ ቦታ ለስራ ሲሄድ አስፈላጊ የሆኑ ቅጾች መሞላት እንዳለባቸው ይገልጻል ፡፡ በመሆኑም በዚሁ መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት የውሎ አበል መጠየቂያ መፍቀጃ እና መክፈያ ቅጾች ሳይሞሉ አበል እየተከፈለ መሆኑን እንደዚሁም የፈቀደው ሀላፊ ስለትክክለኛነቱ የማያረጋግጥ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም የአበል ክፍያው ለማን መከፈል እንዳለበት፡ መከፈል ያለበት መጠን፡ በትክክል ስራ ላይ ለዋለበት ቀንና ሰአት መከፈሉንም ሆነ ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

ስጋት

በመመሪያው መሰረት ባለመስራቱ የመንግስት ገንዘብ አስፈላጊ ላልሆነ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በመመሪያው መሰረት ተገቢው የውሎ አበል ቅጽ እየተሞላ መሰራት ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

ክፍያው በአብዛኛው የተከናወነው ለፌዴራል ፖሊሶች በኮንትሮባንድ የተያዙ እቃዎችን አጅበው በማምጣት ለምስክርነት ሲመጡ የተከፈለ ሲሆን ለቀጣዩ እንደግብአት በመውሰድ የሚስተካከል ይሆናል በማለት በሰጡት ምላሽ ገጸዋል፡፡

ሐ) <u>አላግባብ የተከፈለ የደመወዝ፣ የውሎ አበል እና የስልክ ወጪ ብር 64,728.38 መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

በኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 648/2001 መሰረት የመስሪያ ቤቱ ገንዘብና ንብረት በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ መዋሉንና ሀምሌ 1 ቀን 2004 ተግባራዊ እንዲሆን በተደነገገው የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል መመሪያ መሰረት የውሎ አበል ክፍያ የሚፈፀም መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- የሞጆ ገ/ጉ/ቅ /ጽ/ቤት
    - ➢ ከተለያዩ የገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በጊዜያዊነት ለስራ የመጡ ሰራተኞች የከፈለው የዉሎ አበል ለሞጆ (ሌሞ) የተፈቀደዉን የዉሎ አበል መጠን ባለመጠቀሙ ምክንያት ብር 33,901.00 ያለአግባብ ለሰራተኞች መክፈሉ፣
- በቀን 28/02/2007 ዓ/ም በቁጥር 0016/ሥ/አስ/2007 በተፃፋው ደብዳቤ በቢሸፍቱ ከተማ ለ11 ቀናት ለተከናወነ ስልጠና የተሳተፉ አመራር የ2 ቀናት አበል ብር 2,864.00 (ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ አራት) የተከፈለ አበል የምን አበል እንደሆነ የሚገልፅ ሰነድ አለመኖሩ፤

  በድምሩ ብር 36,765.00 ያለ አግባብ የተከፈለ፣

- በጅግጅጋ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የቅ/ጽ/ቤቱ ሰራተኞች በስራ ቦታቸው ሆነው ለሰሩበት ብር 1,920.00 ውሎ አበል የተከፈለ፣
- በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ያለአግባብ ከስራ ገበታቸው ላልተገኙበት ቀናት ደመወዛቸው በድምሩ ብር 4,840.38 የተከፈለ፣
- አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት ለሰባት ሰራተኞች ለስራ የተላኩት ሞጆ ከተማ/ሌሜ ወረዳ ሲሆን የውሎ አበል ክፍያው የተከፈለው ግን ለአዳማ ከተማ በተመደበው የውሎ አበል መጠን በመሆኑ ያለአግባብ የተከፈለ ብር 4,137.00 እና ብር 17,066.00 በኮንትሮባንድ የተያዙ ዕቃዎችን ለሚያስወግዱ ሰራተኞች በቅርንጫፍ መ/ቤቱ የስራ አስኪያጅ ውሳኔ ሀሳብ መሰረት ያለአግባብ የተከፈለ፣ በድምሩ ብር 21,203.00 መኖሩ ታውቋል፡፡

ስጋት

ቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ከስራ ቦታቸው ሳይንቀሳቀሱ ከስራ ቦታ እንደተንቀሳቀሱ በመቁጠር አበል የሚከፍል ከሆነና ስራ ላይ ለሌሉ ሰራተኞች ደመወዝ የሚከፍል ከሆነ የመንግስት ሀብት አላግባብ የሚባክን ከመሆኑም በላይ አሰራሩም ለብልሹ አሰራር ክፍተት ያለው ይሆናል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

- አላግባብ የተከፈለው የመንግስት ገንዘብ ከሚመለከታቸው ግለሰቦች ሊሰበሰብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም በመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል እና የደመወዝ ክፍያ ከመፈጸሙ ተገቢው ቁጥጥር መደረግ አለበት፣ በተጨማሪም አለአግባብ የተከፈለው የደመወዝ ክፍያ ከሚመለከታቸው አካላት ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- በተሰጠው አስተያየት መሰረት እርምጃ ለመውሰድ ክትትል መጀመሩን ገልጸዋል፡፡

መ) ያለአግባብ የተከፈለ የያዥ አበል ብር 7,000.00

ግኝት

የሕገወጥ ዕቃዎች መረጃ አሰጣጥ አያያዝ አመዘገብ እና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመርያ ቁጥር 78/2004 መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት የያዥ ክፍያ በቀን 06/10/07 BPV 124268 ጠቅላላ ቀረጥ እና ታክስ ብር 344,381.34 ላይ 50% ሲሰላ መሆን የነበረበት ብር 172,190.67 ሲሆን የተከፈለው ግን ብር 179,190.67 በመሆኑ በልዩነት ብር.7000 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

ከመመሪያ ውጪ የሆነ ወጪ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ይዳርጋል እንዲሁም ለብልሹ አሠራር በር ይከፍታል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ክፍያዎች በተገቢው መንገድ እየተጣሩ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

በወቅቱ ሂሳቡ ሲሰራ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበት ነበረ፤ ሆኖም የሰሩት ባለሙያ በቦታው የሌሉ በመሆናቸው ጠይቀን ለመረዳት አልቻልንም፡፡ ሆኖም አሁን በኦዲት ግኝት በተገኘው መሰረት ክፍያው የተፈፀመላቸው የአውበሬ ሚሊሺያ መሆናቸውን ስላረጋገጥን ቀጣይ ክፍያዎች ስላላቸው በመንገርና ማስረጃ በመስጠት ተቀናሽ አድርገን ገቢ የምናደርግ መሆኑን እንገልፃለን ሲሉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

ሠ) <u>በመንግስት ሠራተኞች የውሎ አበል መመሪያ መሰረት ባለማስተናገዳቸው የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሳብ ብር 49,368.00</u>

<u>ግኝት</u>

ሰኔ 2004 ዓ.ም ተግባራዊ እንዲሆን በተወሰነው የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል መመሪያ አንቀጽ 5/1 መሰረት ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ከመደበኛው የስራ ቦታው ውጭ ወደ ሆነ ሌላ የስራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ሄዶ ዕለቱን መመለስ ካልቻለ በስራ ተሰማርቶ ቁርስ፣ ምሳ እና እራት በተመገበባቸው የክልል ከተማ፣ የዞን ከተማ፣ የወረዳ ከተማና የከተማ አስተዳደሮች እንዲከፈል የተመደበውን የውሎ አበል ክፍያ ለእያንዳንዱ ቀን በመመሪያው ላይ አባሪ በሆኑ ሠንጠረዦች መሰረት የውሎ አበሉ እየተከፈላቸው መሆኑን እና በተጨማሪም የውሎ አበሉ ሲወራረድም መመሪያው ላይ በተገለጸው የውሎ አበል ማወራረጃ ቅጽ 2 መሰረት እየተሞላ የሚወራረድ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- .

- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ለናሙና ከመረጥናቸው ውስጥ የተከፈሉት የቀን ውሎ አበል ክፍያዎች ከላይ በዝርዝር በተገለጸው መመሪያ እና ቅጽ 2 መሰረት ከሌላ ቦታ ወደ ድሬዳዋ የመጡ ሰራተኞች እና ከድሬዳዋ ወደ ተለያዩ ከተሞች ለስራ ጉዳይ የተሰማሩ የመ/ቤቱ ሰራተኞች የቁርስ፣ የምሳና የእራት አበላቸው በአግባቡ በቅጹ ላይ የማይሞላ እና የት እንደተመገቡና የት እንዳደሩ የማይጠቀስ በመሆኑ የተከፈላቸው የቀን ውሎ አበል ብር 49,368.00 ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>ስጋት</u>

ቅ/ጽ/ቤቱ የውሎ አበል ክፍያዎችን ከማወራረዱ በፊት በውሎ አበል ማወራረጃ ቅጽ 2 መሰረት የቀን ውሎ አበላቸው እየተሞላ የሚወራረድ መሆኑን ካላረጋገጠ አግባብ ያልሆነ ክፍያ ሊፈጽም ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

የቅ/ጽ/ቤቱ የሀብት አስተዳደር የስራ ሂደት ማንኛውንም የውሎ አበል ከማወራረዱ በፊት የውሎ አበል ማወራረጃ ቅጹ በትክክል ተሞልቶ በሚመለከታቸው የስራ መሪዎች ጸድቆ ሲቀርብለት ብቻ ክፍያውን ማወራረድ ይኖርበታል፡፡ አሁንም የተከፈሉት ውሎ አበሎች ትክክለኛው ቦታ እንዲጣራ በማድረግ የተከፈለው ሂሳብ በውስጥ ኦዲተሮች ሊጣራ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

በተገለጹት ቫውቸሮች ላይ የተከፈሉት የቀን ውሎ አበል ክፍያዎች ሰራተኞች ለስራ ሲሰማሩ ቁርስ፤ ምሳ እና እራት አበላቸው በአግባበቡ በቅፁ ላይ ያልሰፈረ ቢሆንም የተጠቀሱት ክፍያዎች አንዳንዶች እራቅ ያሉ ቦታዎች ሲሆኑ በብዛት የተከፈለው ሀረር፣ ዱሬ፣ ቢየቆቤ፣ ደወሌ እንዲሁም ምስራቅ ሀረርጌ አካባቢዎች በመሆናቸው የውሎ አበል አከፋፈል ላይ ብዙም ልዩነት የሌለው ሆኖ በፎርማቱ መሰረት አለመሞላቱ ግን ስህተት መሆኑን ያየን ሲሆን በቀጣይ እያንዳንዱ ፎርም በትክክል እየተሞላ እንዲከፈል ክትትል የምናደርግ ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

ረ) ተመላሽ ያልተደረገ የውሎ አበል ብር 723.20 መኖሩ

ግኝት

ሰኔ 2004 ዓ.ም ተግባራዊ እንዲሆን በተወሰነው የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል መመሪያ አንቀጽ 5/1 መሰረት ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ከመደበኛው የስራ ቦታው ውጭ ወደ ሆነ ሌላ የስራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ሄዶ ዕለቱን መመለስ ካልቻለ በስራ ተሰማርቶ ቁርስ፣ ምሳ እና እራት በተመገበባቸው የክልል ከተማ፣ የዞን ከተማ፣ የወረዳ ከተማና የከተማ አስተዳደሮች እንዲከፈል የተመደበውን የውሎ አበል ክፍያ ለእያንዳንዱ ቀን በመመሪያው ላይ አባሪ በሆኑ ሠንጠረዦች መሰረት የውሎ አበሉ እየተከፈላቸው መሆኑን እና በተጨማሪም የውሎ አበሉ ሲወራረድም መመሪያው ላይ በተገለጸው የውሎ አበል ማወራረጃ ቅጽ 2 መሰረት እየተሞላ የሚወራረድ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ለናሙና ከመረጥናቸው ውስጥ ሰራተኞች የተጠቀሙት የውሎ አበል ከወሰዱት የውሎ አበል በታች መሆኑ እየታወቀ ተመላሽ እንዲያደርጉ ባለመደረጉ ምክንያት በድምሩ በእላፊ የተከፈላቸው ውሎ አበል ብር 723.20 መኖሩ ታውቋል፡፡

ስጋት

ቅ/ጽ/ቱ የውሎ አበል ክፍያዎችን ከማወራረዱ በፊት ለከተሞቹ በተመደበው የውሎ አበል መጠን እና በውሎ አበል ማወራረጃ ቅጽ 2 መሰረት የቀን ውሎ አበላቸው እየተሞላ የሚወራረድ መሆኑን ካላረጋገጠ አግባብ ያልሆነ ክፍያ ሊፈጽም ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

የቅ/ጽ/ቤቱ የሀብት አስተዳደር የስራ ሂደት ማንኛውንም የውሎ አበል ከማወራረዱ በፊት የውሎ አበል ማወራረጃ ቅጹ በትክክል ተሞልቶ በሚመለከታቸው የስራ መሪዎች ጸድቆ ሲቀርብለት ብቻ ክፍያውን ማወራረድ ይኖርበታል፡፡ ገንዘቡ ተመላሽ እስኪሆን ድረስ የስራ ሂደቱ ክትትል ማድረግ እንዲችል ሂሳቡን በተሰብሳቢ መዝግቦ መያዝ ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

የመንግስት ሠራተኛ ከመደበኛው የሥራ ቦታው ውጭ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ሄዶ በዕለቱ መመለስ ካልቻለ በስራ ተሰማርቶ ቁርስ ፣ምሳ እና እራት በተመገበበት ከተማ የተመደበውን የውሎ አበል ክፍያ ለእያንዳንዱ ቀን ታስቦ እየተከፈለ ሲመለሱ ሲሄዱ ከወስዱት የውሎ አበል በታች የተጠቀሙ መሆኑ ስለተረጋገጠ 3 ሠራተኞች ገንዘቡን እንዲመልሱ ደብዳቤ የተፃፈላቸው በመሆኑ ሂሳቡን ተከታትለን በማስመለስ ሪፖርት የምናደርግ መሆኑን እንገልፃለን ሲሉ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

ሰ) **ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ብር** 507,473.42

ግኝት

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 9/7 መሰረት ለተገዛ ዕቃ አገልግሎት ሂሳብ ማወራረጃ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦርጂናል ደረሰኝ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ መመሪያ አንጻር ቅ/ጽ/ቤቱ ግዢ ሲፈጽም ግዢ ከፈጸመበት ድርጅት ኦሪጅናል የገቢ ደረሰኝ እየተቀበለ ክፍያ የሚፈጽም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፣

- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት
  - ለናሙና ከመረጥናቸው የክፍያ ቫውቸሮች ውስጥ ለተከፈለው ክፍያ ብር 446,021.42 የተቀባዩ ድርጅቱ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ሳይቀርብ ክፍያው በገቡት ውል መሰረት ወደ ድርጅቱ የባንክ አካውንት በማስተላለፍ የተፈጸመ በመሆኑ
- በዋናው መስሪያ ቤት
  - ለስልጠና ተብሎ ለአንድ ድርጅት ብር 61,452.00 የተከፈለው የተቀባዩ ድርጅት ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ወይም የባንክ አድቫይስ ባለመቅረቡ፣

ክፍያው ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስጋት

በቅ/ጽ/ቤቱ የዕቃም ሆነ የአገልግሎት ግዢ ሲፈጸም አቅራቢው የገቢ ደረሰኝ ቆርጦ እንዲሰጥ የማይደረግ ከሆነ ድርጅቱ የመንግስት ገቢን እንዲሰውር ሊያደርገው ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

ቅ/ጽ/ቤቱ ለፈጸመው ክፍያ ድርጅቱ የገቢ ደረሰኝ ቆርጦ እንዲሰጥ ማድረግ፡፡ ለወደፊቱም ማንኛውም ግዢ ሲፈጽም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች በትክክል ስለመቅረባቸው ሳያረጋግጥ ክፍያ መፈጸም አይኖርበትም፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ማስረጃዎቹን ለማቅረብ ክትትል እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

ሸ) ከመንግስት ግዢ አዋጅና መመሪያ ውጪ በብር 431,663.72 የተፈጸመ ግዥ መገኘቱ

ግኝት

በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 33 (2) እና 56/1 መሰረት የእቃም ሆነ የአገልግሎት ግዢ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም እንዳለበት እና በፕሮፎርማ የሚገዛ ከሆነ ግዢ ከመፈጸሙ በፊት ቢያንስ 3 አቅራቢዎች በውድድሩ ላይ

እንዲሳተፉ እየተጋበዙ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ከዚህ አንጻር ግዢዎች ሲፈፀም በአዋጁ በተደነገገው መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡-

- በባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት ሁለት የአገልግሎት ግዥዎች (የመስተንግዶ አገልግሎቶች) በብር 78,833.95 ያለዋጋ ማወዳደሪያ ግዥ መፈጸሙ፣
- ሞጆ ቅ/ጽ/ቤት
  - ➢ በቀን 13/05/2007 በpv ቁጥር 056482 የብር 192,436.19 ከአዳማ ጌጡ ሆቴል በዋጋ ማቅረብያ የግዥ ዘዴ ግዥ መፈጸሙ ፣ በተጨማሪ በውድድር ወቅት በቀረበው ዝቅተኛ የፕሮፎርማ ዋጋ መከፈል ሲገባው በተመሳሳይ ቀን ና ቁጥር በተዘጋጀ ሌላ ፕሮፎርማ እንዲቀርብ ተደርጎ በመከፈሉ ብር 5,000.00 ያለአግባብ መከፈሉ ፣
- ኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት የመኪና ጥገና በድምሩ ብር 33,945.08 ፕሮፎርማ በመሰብሰብ መግዛት ሲገባው ከአንድ አቅራቢ ብቻ መፈጸሙ፣
- በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት ግዢዎችን ፕሮፎርማ ተሰብስቦ በብር 10,092.50 ግዥ ቢፈፀምም 3ቱም ተወዳዳሪዎች የተጠቀሱትን መስፈርቶች ማሟላታቸውን የሚገልፅ ዶክመንት ባለመኖሩ ግዥው በመመሪያው መሰረት የተፈጸመ መሆኑን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣ እንዲሁም ሁለት የተለያዩ ግዢዎች በብር 20,510.00 ውድድር ሳይደረግ ከአንድ አቅራቢ ግዥ የተከናወነ መሆኑ፣
- የሞያሌ ቅ/ጽቤት ብር 95,846 ዋጋ ያላቸው የተለያዩ ግዥዎች ከአንድ አቅራቢ የግዥ ዘዴ የተከናወኑ መሆኑን፣

ለማወቅ ተችሏል ፡፡

<u>ስጋት</u>

የዕቃም ሆነ የአገልግሎት ግዢ ሲፈጽም በአዋጁ በተደነገገው መሰረት የማይፈጽም ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ሊባክን ይችላል፡፡ለብልሹ አሰራር በር ይከፍታል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

ማንኛውም ግዥ በኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 መሰረት ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጣው በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ/2002 ዓ.ም መሰረት ሊከናውን ይገባል፡፡ ያለአግባብ የተከፈለው ብር 5000.00 ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ግኝቶቹን ተቀብለው ደደፊት ጥንቃቄ እንደሚያድረጉ ገልጸዋል፡፡

ቀ) ለኦዲት ያልቀረበ ክፍያ ብር 27,864,370.19

ግኝት

ማንኛውም የወጪ ክፍያ በመመሪያው መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ለኦዲት እንዲቀርቡ ከተጠየቁት የክፍያ ቫውቸሮች መካከልም፣

- በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት
    - ብዛታቸው በአራት የወጪ ማስመስከሪያ በድምሩ ብር 1,047,140.70 ክፍያ የተፈጸመባቸው የያዥና ጠቋሚ አበል ክፍያ መረጃዎች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው ፣
- በዋናው መስሪያ ቤት፣ የብር 26,817,229.49 የወጪ ማስመስከሪያ ሰነዶች ለኦዲት ሥራ እንዲቀርቡ ተጠይቀው ሊቀርቡ ባለመቻላቸው፣

የክፍያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስጋት

ለኦዲት ባልቀረቡ የክፍያ ቫውቸሮች ማጭበርበር ተፈጽሞ ሊሆን ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ለኦዲት ያልቀረቡት ማስረጃዎች ተፈልገው በውስጥ ኦዲት ተጣርተው ውጤቱ ሊገለጽልን ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ መልስ</u>

- የጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት ሊቀርቡ ስላልቻሉ ከላይ የተጠቀሱት አባሪ ሰነዶች በወቅቱ የነበሩትን ጠይቀን እንደተረዳነው በአውበሬ ሚኒሻ አካውንት የገባ ሲሆን ሰነዱንም ለጊዜው ማግኘት ያልቻልን ስለሆነ ፊልገን በውስጥ ኦዲት አስመርምረን ውጤቱን የምናቀርብ መሆኑን ፣
- የዋናው መስሪያ ቤት ግን ማስረጃዎቹ ይቀርባሉ ከማለት ውጪ አጥጋቢ ምክንያት ማቅረብ አልቻሉም፡፡

በ) <u>ያልተቀነሰ የስራ ግብር ብር 110,678.45</u>

<u>ግኝት</u>

በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 12(1) በመቀጠር የሚገኝ ገቢ ማለት ከመቀጠር በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተገኘ ማናቸዉም ክፍያ ወይም ጥቅም ሲሆን በቅድመ ቅጥር የተገኘን ገቢ እና ወደፊት ለመቀጠር አስቀድሞ የሚደረግ ክፍያን እንደሚጨምር ሲደነግግ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 13 እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነፃ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸዉም ክፍያ ወይም ጥቅም ከወር ደምወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት በአዋጁና ደንብ በግልጽ ያመለክታል፡፡ነገር ግን

- የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት
  - በበጀት ዓመቱ ከተፈጸመ ትርፍ ሰዓት ክፍያ ላይ ብር 6,684.59 ያልተቀነሰ መሆኑ፣
- በባለስልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት፣
  - በመ/ቤቱ ተቀጥረው ያሉ የዐቃቢ ህግ ባለሙያዎች ከመጋቢት/2007-ሰኔ/2007 ለ47 ዐቃብያነ ህግ ሰራተኞች በድምሩ ብር የተከፈላቸው የቤት አበል መመሪያን የማውጣት ስልጣን ባልሰጠው አካል በተጻፈ ደብዳቤ መሰረት ከገቢ ግብር ነፃ እንዲሆኑ በመደረጉ ብር 103,993.85 ያልተቀነሰ ስራ ግብር መኖሩ

ታውቋል፡፡

<u>ስጋት</u>

የመንግስት ግብርና ታክስ አለመሰብሰብ የመንግስትን ገቢ ያሳጣል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ከሰራተኞች ያልተሰበሰበው ብር 110,678.45 ተሰብስቦ ለመንግስት ገቢ መደረግ አለበት ፡፡ ለወደፊት አዋጁን ደንቡን ባገናዘበ መልኩ መሰራት ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት ከትርፍ ሰዓት ክፍያ ላይ ስራ ግብር እንደሚቀረጥ ከባለስልጣኑም ሆነ ከ/ገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር መመሪያ ያልደረሰን በመሆኑ ለአሰራሩ አዲስ ነን፣ መመሪያው ሲደርሰን ተግባራዊ የምናደርግ መሆናችንን እንገልጻለን፣
- የዋናው መ/ቤት የአቃቢ ህግ ባለሙያዎች የቤት አበል ግብር እንደማይመለከተው የጠቅላይ ሚ/ር ፅ/ቤት በመጋቢት 04/2007 ዓ.ም በቁጥር መ240-899/2 የመኖሪያ ቤትና የትራንስፖርት አበል ከገቢ ግብር ነፃ መሆኑን የተፈቀደ በመሆኑ በዚሁ መሰረት ተፈፃሚ ተደርጓል፡፡

በማለት ለስራ አመራሩ ሪፖርት በላኩት መልስ ገልጸዋል፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት

በአዋጁና በደንቡ የተገለጸው አንቀጽ በዝርዝር እየተገለጸ ሌላ መመሪያ እንጠብቃለን ተብሎ የተሰጠውን መልስና ከላይ በስራ ግብር አዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን ከግብር ነጻ እንዲሆን መፍቀድ ከሚገባው ክፍል ያልተፈቀደ በመሆኑ የተሰጠው ምክንያት ትክክል ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ተ) በትክክል ያልተመዘገበ የግንባታ ሂሳብ ብር 3,681,414.89

ግኝት

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 6ለ ላይ የሂሳብ እንቅስቃሴ መነሻ ሰነድ የተዘጋጀላቸው ሂሳቦች በዕለቱ በየፋይናንስ ምንጩ በሂሳብ መዝገብ ላይ መመዝገብና በሂሳብ ሌጀር ላይ መወራረስ እንዳለባቸው በሚያዘው መሰረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ የባለስልጣን ዋና መስሪያ ቤቱ፣

- በቃሊቲ ለሚያሰራው መቅረጫ ጣቢያ በተቋራጭነት እየሰራ የሚገኘው ተገጣጣሚ የህንፃ አካላት ማምረቻ ድርጅት በክፍያ ሰርቲፍኬት ከተሰራው ስራ ላይ ተቀናሽ

የሆነው ሂሳብ (REBATE) ከተሰራው ስራ መጠን ላይ በመቀነስ በግንባታ ወጪ ተመላሽ ሂሳብ በሂሳብ መደብ 6323 (2311203) መመዝገብ ሲገባው በልዩ ልዩ ገቢ የሂሳብ መደብ 1489 (1451199) ብር 1,537,019.95 መመዝገቡ የገቢና የወጪ ሂሳብ በብልጫ እንዲታይ መደረጉ ፤(ዝርዝር በአባሪ ቁጥር 2 ተያይዟል፡፡)

- ኤ.ኤም.ቢ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ.ማ የጅግጅጋ ቅ/መ/ቤት ቢሮ ግንባታ በክፍያ ቁጥር 6 በሰነድ ቁጥር BPV 0007902 ቀን 12/5/2007 የግንባታ ሂሳብ ሲከፈል የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ መመዝገብ የነበረበት ባለመመዝገቡ ወጪ 6323 ብር 6,409,445.13 መመዝገብ ሲኖርበት ብር 4,328,774.41 በመመዝገቡ በብር 2,080,670.72 ወጪ በማነስና የቅድሚያ ክፍያ በመብለጥ ሪፖርቱ እንዲያሳይ መደረጉ ፤
- ጄሪ ማራኪ ኢንጅነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለየዋና መስሪያ ቤት ቢሮ ውስጥ የአልሚኒየም ፓርትሽን፤ የካውንተር ሥራ እና የሻተር ሥራዎች በክፍያ ቁጥር 3 በሰነድ ቁጥር BPV 0006174 ቀን 14/8/2007 የግንባታ ወጪ ሂሳብ ሲሰራ መያዣ(retention) ባለመመዝገቡ በ6323 ብር 1,274,484.40 መመዝገብ ሲኖርበት ብር 1,210,760.18 በመመዝገቡ በብር 63,724.22 የወጪና የተከፋይ ሂሳብ በማነስ እንዲጣይ መደረጉ፤

ታውቋል፡፡

ስጋት

- ሁኔታው የገቢና የወጪ ሂሳብ ሪፖርትን ሊያዛባው ከመቻሉም በላይ የሂሳብ ምዝገባ በትክክል አለመመዝገብ የሂሳብ ሪፖርትን ተዓማኒነት ያሳጣዋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ለሂሳቡ አስፈላጊው ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል፡፡ለወደፊቱም የግንባታ ሂሳቦች በተገቢው ሁኔታ ስለመመዝገባቸው አስፈላጊው ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

ቸ) ዕቃው ገቢ መሆኑ ሳይረጋገጥ ክፍያ ተፈጽሞ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ ብር 7,064,490.00

ግኝት

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀፅ 8 ንዑስ ንዑስ አንቀፅ 4ሠ ላይ መስሪያ ቤቶች በአለም አቀፍ ግዢ ስምምነት መሰረት በባንክ በኩል ለሚከፍቱት ሌተር ኦፍ ክሬዲት (Letter of credit) ለገቡት ዋስትና የሚተላለፈውን ገንዘብ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መዝግበው በመያዝ ክትትል ማድረግ፤ እንዲሁም በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2ለ ላይ የወጪ ሂሳብ ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረቡንና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት፤ በሚያዘው መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ FACE TECHNOLOGY LTD ከተባለ የውጪ ድርጅት ለጣት አሻራ የሚሆን ሪቫን ግዢ ሲፈፅም፤

- የጨረታ ሰነዱን ለኦዲት እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ ባለመቻሉ ትክክለኛነቱን ለማጣራት ያልተቻለ መሆኑ፤

ለግዢው የአሜሪካን ዶላር 337,294.08 ወይም በወቅቱ ምንዛሬ ብር 7,064,490.00 ክፍያ ሲፈፀም፤ በክፍያ ሰነዱ ላይ የሌተር ኦፍ ክሬዲት (Letter of credit) ማመልከቻ ብቻ የተያያዘና

ዕቃው ወደ መስሪያ ቤቱ ገቢ መሆኑ ሳይረጋገጥ ሂሳቡ በወጪ ሂሳብ የተመዘገበ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡ ስለሁኔታው ኦዲት አስደራጊዎች ተጠይቀው ምላሽ አልሰጡበትም፡፡

ስጋት

ንብረት ገቢ ሳይሆን ክፍያዎችን በወጪ መመዝገብ ሀብትን ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ተግባራዊ እንዲሆን የባለስልጣኑ የስራ ሃላፊዎች የተጣለባቸውን ሃላፊነት ሊወጡ ይገባል፡፡ ለሂሳቡም የማስተካከያ ምዝገባ ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

4. የሂሳብ ሪፖርትን በተመለከተ

ሀ) የተለያዩ ሂሳብ መደቦች በብር 46,860,929.52 ያልተለመደ (አብኖርማል) ባላንስ የሚያሳዩ መሆኑ

ግኝት

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 (2ለ) መሰረት የእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን/ዴቢት ወይም ክሬዲት/ጠብቆ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት ሰኔ 30/2006 በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ እያንዳንዱ ሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን የጠበቀ ለመሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የግዥ እና ፋይናንስ ሰኔ 30/2007 በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ የተጣራ ሀብት በብር 34,300.25 ዴቢት ሚዛን የሚያሳይ ሲሆን ይህም ሚዛን ከ2006 በጀት ዓመት የዞረ ሂሳብ መሆኑ፣
- በከምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት
  - በጉምሩክ ስነስርአት የስራ ሂደት (የገቢ ዋስትና ሂሳብ ቡድን) በኩል በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ በቀረበው ዝርዝር መሰረት የተጣራ ሀብት (Equity Account) ብር 2,636.18 ዴቢት የሚያሳይ መሆኑን፣
  - በአወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል የስራ ሂደት በኩል በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ዝርዝር መሰረት የተጣራ ሀብት (Equity Account) ብር 21,066,756.38 ዴቢት የሚያሳይ መሆኑን፣
- መቀሌ ቅ/ጽ/ቤት በግብር ማስታወቂያና የገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ቡድን በኩል በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ መሰረት የተጣራ ሀብት በድምሩ በብር 25,304,286.35 ዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑን፣
- የሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት በገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች ቡድን በኩል የሰኔ 30/2007 በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ የተጣራ ሀብት ሂሳብ (5601) ለባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000026238521 በብር 304,701.65 እንዲሁም በዲፖዚት ባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000026238537 በብር 18,072.15 በድምሩ በብር 322,773.80 ያልተለመደ (ዴቢት) ሚዛን የሚያሳይ መሆኑን፣

- ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ሰኔ 30/2007 በሀብት አስተዳደር ስራ ሂደት በግዢና ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ቡድን በኩል በባንክ ሂሳብ ቁጥር 2368 ላይ በተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ የደመወዝ ተከፋይ ሂሳብ ብር 107,117.29 ያልተለመደ ሚዛን/ ዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ፣
- በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት
  - በግብር እና ታክስ ማስታወቅና የገቢ ሂሳቦች አስተ/ቡድን በኩል በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ የተጣራ ሀብት ብር 23,059.27 ዴቢት ሚዛን/ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳይ መሆኑን ፣
- በዋናው መስሪያ ቤት
  - ➢ በሂሳብ መደብ 5217399 (4274) በሂሳብ መግለጫ ብር 2,653,383.42 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ክሬዲት ባላንስ (abnormal) የሚያሳይ መሆኑ

ታውቋል፡፡

ስጋት

በዓመቱ መጨረሻ በሚቀርበው የሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታዩ የሂሳብ መደቦች ትክክለኛ ሚዛናቸውን ጠብቀው በተጠቃለለው ሂሳብ ላይ ሪፖርት የማይደረግ ከሆነ የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ሁኔታ ላይገልጽ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ከላይ የተገለጸዉ ሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን ያልጠበቀበት ሁኔታ ሊጣራና ለሂሳቡም አስፈላጊው የምዝገባ ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል ፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ሂሳብ እንደገና ተጣርቶ አስፈላጊውን ማስተካከያ እንዲደረግ እየተሰራ መሆኑንእና ሂሳቡ ተጣርቶ የሚደርስበትን ማስተካከያ አንዳንዱም በስህተት በሂሳብ ምዝገባ ወቅት የተፈጠረ መሆኑ ለማስተካከል እየስራን የሚገኙ መሆኑንና፣ በዋናው መስሪያ ቤት የተሰብሳቢ ሂሳብ አመዘጋገብና አጠባበቅን የሚያስተካክሉ መሆኑን፣ በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅትና ለስራ አመራሩ በላኩት መልስ ገልጸዋል፡፡

ለ) <u>በሂሳብ ሪፖርት የተመለከተው የባንክ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ</u>

<u>ግኝት</u>

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8(8) መሰረት በባንክ ሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት ላይ የሚታየው የባንክ ሂሳብ እና የባንክ ሌጀር ሚዛን ትክከለኛነቱ የባንክ ሂሰብ ማስታረቂያ በማዘጋጀት መረጋገጥ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ከዚህ አንፃር ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶቹ ለእያንዳንዱ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በማዘጋጀት በባንክ ያለውን ገንዘብ ትክክለኛነት የሚያረጋገጥ ለመሆኑና የባንክ ሂሳቡም ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ባንክ ያለ ገንዘብ ብር 31,420,636.28 ክሬዲት ሚዛን የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ ሂሳቡን ትክክለኛነት ማወቅ ያልተቻለ መሆኑ፡-
- ሞጆ ቅ/ጽ/ቤት
  - ለባንክ ያልቀረቡ ቼኮች በሚል ከ1 ዓመት በላይ የተያዘ ሂሳብ ብር 15.74
  - በባንክ ያልተመዘገበ ገቢ በሚል ከ1 ዓመት በላይ የቆየ ሂሳብ ብር 22,951,842.34
  - በመዝገብ ያልተመዘገበ ገቢ በሚል ከ1 ዓመት በላይ የቆየ ሂሳብ ብር 3,061,405.14
  - በመዝገብ ያልተመዘገቡ ቼኮች በሚል ከ1ዓመት በላይ የቆየ ሂሳብ ብር 1,640,463.79
- ሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት
  - ባንክ ያለ የጥሬ ገንዘብ ባላንስ በተመለከተ በባንክ እስቴትመንት ላይ ብር 5,725,206.52 እና የመስሪያ ቤቱ ሌጀር ደግሞ ብር 4,436,426.91 የሚያሳይ በመሆኑ በሂሳብ ሪፖርት የተመለከተው በብር 1,288,779.61 የሚያንስ መሆኑን እና የተሟላ የባንክ ማስታረቂያ ባለመስራቱ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

ታውቋል፡፡

<u>ስጋት</u>

ትክክለኛው የተጠቃለለ የሂሳብ እንቅስቃሴ ማወቅ አይቻልም፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

መስሪያ ቤቱ የሂሳቡን ዝርዝር ሁኔታ በአስቸኳይ በማጣራት ለሂሳቡ ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

የሂሳብ ማስተካከያ (Adjestment) ችግር በመሆኑ በቀጣይ ማስተካከያ እንደሚሰሩለት፣ ከባንክ በኩል ማስረጃዎችን በማፈላለግ ለማስተካከል ጥረት መጀመራቸውን ገልጸዋል፡፡

ሐ) በሂሳብ መግለጫው ላይ እና በባንክ ስቴትመንት መካከል የብር 3,532,677.21 ልዩነት መኖሩ

ግኝት

በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ዉጥር 648/2001 እና በፌድራል መንግስት የክፍያ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ተራ ቁጥ 8 (መ) መሰረት በሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት ላይ የሚታየው የባንክ ሂሳብ እና የባንክ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነት በየወሩ ባንክ

ሂሳብ ማስታረቂያ በማዘጋጀት መረጋገጥ አለበት ይላል፡፡ በዚሁ መሰረት በየወሩ የሂሳብ ማስታረቂያ ስለመስራቱ እና የሂሳቡ ትክክለኝነት ስለማረጋገጥ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

- አዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  - ✓ በባንክ ሂሳብ ቁጥር 315C22000019 (መደበኛ ሂሳብ) ከ 2006-2007 በጀት ዓመት ድረስ የባንክ ሂሳብ እና የባንክ ሌጀር ሚዛን ትክክለኝነት በየወሩ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ያልተሰራ መሆኑ እና ብር 3,532,677.21 በሰኔ 30/2007 በጀት አመት በሂሳብ ማማዛዘኛ ሪፖርት ላይ ሲታይ የባንክ መግለጫ ላይ ግን ዜሮ ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

ስጋት

የባንክ ሂሳብ መግለጫ እና የባንክ ሌጀር ሚዛን (bank statement) ትክክለኝነት በየወሩ ካልተሰራ የመንግስት ገንዘብ ብክነት ሊያስከትል ይችላል በተጨማሪም የሂሳብ ሪፖርቱም ትክክለኛውን ሁኔታ ላያሳይ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

የባንክ ሂሳብ መግለጫ እና ሌጀር ሚዛን ትክክለኛ መሆኑ በየወሩ መስተካከል (መታረቅ) ይኖርበታል እንዲሁም ትክክለኛው ሁኔታ ተጣርቶ ለሂሳቡ ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

ኢፍሚስ ከተጀመረ በኋላ የሪኮንስሌሽን ስራ ተሰርቶ አያውቅም፡፡ ስለዚህ በኢፍሚስ ችግር የመጣ ልዩነት እንጂ በማኑዋል ገንዘብ በሚናበብበት ወቅት ልዩነት እንደሌለው ገልጸዋል ፡፡

መ) **ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በቅ/ጽ/ቤቶች ለኦዲት የቀረበውና በገቢዎችና ጉምሩክ ዋና መ/ቤት በተጠቃለለው የቅርንጫፎች ሪፖርት መካከል ልዩነት መኖሩ**

ግኝት

ለዋና መ/ቤቱ እና ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የተላከው የቅርንጫፍ መ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫዎች ተመሳሳይ መሆናቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ለዋና መ/ቤቱ የተላከው፣

- ጅግጅጋ ቅ/ፅ/ቤት በተለያዩ የወጪ ሂሳብ መደቦች ብር 13,618,758.23 በማነስ እና ብር 43 በመብለጥ፣
- ድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት መደበኛ ወጪ በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ብር 12,693,835.27 በማነስ፣
- የድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት ተከፋይ ሂሳብ በ5051 እና 5054 የሂሳብ መደብ 417,447.42 በመብለጥ፣
- የሞጆ ቅ/ፅ/ቤት ተከፋይ ሂሳብ በ5003 እና 5051 የሂሳብ መደብ ብር 51,122,937.59 በመብለጥ፣
- የአዳማ ቅ/ፅ/ቤት የመደበኛ ወጪ 6131 የሂሳብ መደብ 150,314.88 በማነስ የሚታይ
- ሞጆ ብር 38,768,393.79 የባንክ ያለ ገንዘብ 4103 በዴቢት መመዝገብ ሲገባው በክሬዲት ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ፣

በተጠቃለለው ኦዲት ወቅት ታይቷል፡፡

ስጋት

በኦዲት ያልተረጋገጠ የቅርንጫፍ መ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫ በማጠቃለያ ሂሳብ ውስጥማስገባት የባለስልጣን መ/ቤቱን ትክክለኛ የሂሳብ ሪፖርት ላያሳይ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

የቅርንጫፍ መ/ቤቱ የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛ የሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ ሊያሳይ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

መልስ አልተሰጠበትም፡፡

5. **ተሰብሳቢ ሂሳብ**

ሀ) **ትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠ ብር 16,799,692.39ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ**

ግኝት

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር በሂሳብ መግለጫ ላይ ለሰፈረው ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ የሆነ ደጋፊ ሰነድ ያለው ለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- መቀሌ ቅ/ጽ/ቤት
  - ➢ በሀብት አስተዳደር ብር 13,272.87 በተሰብሳቢ ሂሳብ ሌጀር የአበልና የረዥም ጊዜ የደመወዝ ብድር እንዲሁም ሌሎች ቅድመ ክፍያዎች ለረጅም ማስረጃ የሌላቸው መሆኑ፣
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በኩል
  - በሀብት አስተዳደር የስራ ሂደት በኩል (ለባንክ ሂሳብ ቁጥር 1996) ብር 41,621.32 ተሰብሳቢ ሂሳቦች ከማን እና መቼ እንደተፈጠሩ የማይታወቁ ተሰብሳቢ ሂሳቦች በ ሰኔ 30/2007 ዓ/ም ሂሳብ መግለጫው ላይ ሪፖርት ተደርገው መገኘታቸው፣

- አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል ብር 16,744,798.20 ባለቤትነቱ የማይታወቅ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

<u>ስጋት</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሚቀርበው የሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ትክክለኛ የመ/ቤቱ ተሰብሳቢ ሂሳብ መሆናቸው በሰነድ የተረጋገጠ ካልሆነ በቅርንጫፍ ፅ/ቤቱም ሆነ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ደረጃ የሚዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በመመሪያዉ መሰረት በተሰብሳቢ ሂሳብነት ሊያዝ የሚገባዉ ሂሳብ አግባብነት ያለው ደጋፊ ሰነድ ሊኖረዉ ስለሚገባ አስፈላጊዉን ማጣራት በማድረግ ሂሳቡ ሊስተካከል ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

- ተገቢውን ማጣረት በማድረግ በማወራረድ ላይ እንደሆኑና ቀደም ብሎ ከመዝገብ እንዲሰረዝ የተጠየቀ ሂሳብም ለዋና መ/ቤት መቅረቡን ገልጸው ምለሽ ሰጥተዋል፡፡

ለ) <u>ሳይወራረድ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ብር 67,462,255.74 ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለእያንዳንዱ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር ተሰርቶለት ክትትል በማድረግ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠርና ሂሳቡም በወቅቱ እንዲወራረድ ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡በተጨማሪም የፌደራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 16/4 መሰረት የውሎ አበልና የመጓጓዣ ቅድመ ክፍያ ሠራተኛው ስራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት (7) ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ተሰብሳቢ ሂሳቦች ተገቢው የቁጥጥር ስርአት የተዘረጋላቸውና በወቅቱም የሚወራረዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት ሰኔ 30/2007 በሀብት አስተዳደር የሥራ ሂደት የሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 4203 የሠራተኞች ቅድሚያ ክፍያ ብር 7,877.50 (ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ)
- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት
    - በአገር ውስጥ ገቢ ከ2000 ዓ/ም ጀምሮ ለባንክ አገልግሎት ክፍያ የተከፈለ ብር 105,698.40 በየጊዜው በተሰብሳቢ ቢገለፅም እስካሁን ያልተወራረደ ሂሳብ መሆኑ፣
- ምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 81,814.60 ከ 1981 ዓ/ም ጀምሮ እስካሁን ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ ፣
- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት በሂሳብ በድምሩ ብር 1,182.49 ከሶስት (3) ዓመት በላይ የቆየ ያልተወራረደ ሂሳብ መኖሩ፣
- በሐዋሳ ቅ/ጽ/ቤት
    - በገቢ ሂሳቦች ክፍል በባንክ ሂሳብ ቁጥር 2078 በሂሳብ መደብ 4201 ብር 7,798.52 እና በባንክ ሂሳብ ቁጥር 2079 ሂሳብ መደብ 4201 ብር 6,080.36 በድምሩ ብር 13,878.88፣
    - የሀብት አስተዳደር ክፍል በተሰብሳቢነት ከተያዘው ብር 13,601.69 ውስጥ በሂሳብ መደብ 4201 ብር 9,652.07 ከ5 ወራት በላይ የቆየ እንዲሁም በሂሳብ መደብ 4274 ብር 2,490.98 ከ7 አመት በላይ የቆየ በድምሩ ብር 12,143.05 በወቅቱ ሳይወራረድ በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ የሚገኝ መሆኑ ፣
- አዳማ ቅ/ጽ/ቤት ከሰራተኞች ያልተሰበሰበ ቅድመ ክፍያ(4203) ብር 11,074.13፣
- አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 67,228,586.69 በወቅቱ ሳይወራረድ ለረጅም ጊዜ የቆየ መሆኑ፡-

ታውቋል፡፡

<u>ስጋት</u>

በመመሪያው መሰረት ማንኛውም ቅድመ ክፍያዎች በህግ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማይሰበሰብ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ለብክነት ይጋለጣል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ሳይሰበሰብ የቆየው የመንግስት ገንዘብ ከሚመለከታቸው አካለት ሊሰበሰብ ይገባል ፡፡ ለወደፊቱም ሳይሰበሰቡ ረጅም ግዜ የሚያስቆጥሩ ሂሳቦች እንዳይፈጠሩ ወቅታዊ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ሂሳብ ያለባቸውን አካላት በማፈላለግ የሚወራረድበትን መንገድ እንደሚያመቻቹ ፣ ሂሳቡ እንዲስተካከል የሚቻለው ከዋና መ/ቤት ሲገለፅልን ብቻ ነው፣ ሊሰበሰብ የሚችልበት ሁኔታ ካለ እንዲሰበሰብ ካልሆነ እንዲሰረዝ (write off) የሚደረግ መሆኑን፣ ለሌሎች ደግሞ አስፈላጊውን ማስተካከያ ባለመሰራቱ ምክንያት የመጣ ችግር መሆኑንና በቀጣይም አስፈላጊውን የሂሳብ ማስተካከያ እንደሚሰሩለት፣

ገልጸዋል፡፡

6. **የተከፋይ ሂሳብ፣**

ሀ) ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ ብር 22,183,436.59 መኖሩ

ግኝት

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ማናቸውም ወደ ፊት ክፍያ የሚፈጽምባቸዉ ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸዉን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለዉ አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንጻር በቂ የሆነ ማስረጃ ያላቸውና ወደ ፊትም ክፍያ የሚፈፀምባቸዉን ሂሳቦች ብቻ በተከፋይነት መዝግቦ ሪፖርት የሚዘጋጅ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- **በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት በኩል**
  - በበጀት ዓመቱ በባንክ ዲፖዚት አካዉንት ቁጥር 3256 ብር 4,945,868.33 በተከፋይ ሂሳብ ሌጀር ዝርዝር ውስጥ የዞረ ተብሎ የተመዘገበው ሰነድ ቀርቦለት መቼና ለማን እንደሚከፈል ማስረጃ ሊቀርብ ባለመቻሉ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፡፡

- በሀብት አስተዳደር ብር 46,948.00 በተከፋይ ሂሳብ ሌጀር ዝርዝር ውስጥ የዞረ ተብሎ ቢመዘገብም ሰነድ ቀርቦለት መቼና ለማን እንደሚከፈል በኦዲቱ ወቅት ማወቅ አልተቻለም፡፡

- **<u>በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል</u>**
  - ልዩ ልዩ ተከፋዮች (ሂሳብ መደብ 5002) ብር 4,773.26
  - ዊዝሆልድ ታክስ ተከፋይ ሂሳብ (ሂሳብ መደብ 5006) ብር 19,545.10
  - ለሰራተኞች ተከፋይ ሂሳብ (5021) ብር ,3325.58
  - ተጨማሪ እሴት ታክስ (5059) ብር 3,329.61
  - ሌሎች መያጃዎች (ሂሳብ መደብ 5054) ብር 12542.07 በድምሩ ብር 43,515.62 ሂሳቡ ለማን እንደሚከፈል የሚገልጽ መረጃ ባለመኖሩ ትክክለኛነቱ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በገቢ አወ/አሰ/ክትትል የስራ ሂደት በኩል በተዘጋጀው ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ላይ የቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ዕዳና ወደፊትም ክፍያ የሚፈፅምበት ለመሆኑ መረጋገጥ ያልተቻለ ሂሳብ ብር 23,059.27፣ በሀብት አስተዳደር የስራ ሂደት በኩል የቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ እዳና ወደፊትም ክፍያ የሚፈፅምበት ለመሆኑ ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሳብ ብር 9,753.26 በድምሩ ብር 32,812.53 መኖሩ፣

- **<u>በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት</u>**

<u>በገቢ ሂሳቦች ክፍል በተዘጋጀ የተከፋይ ሪፖርት</u>

- በባንክ ሂሳብ ቁጥር 2078 በሂሳብ መደብ 5026 የሂሳቡ መነሻ ሰነድ /ሂሳቡ ለማን እንደሚከፈል እና ለስንት ጊዜ የቆየ እንደሆነ የማይታወቅ ማስረጃ ተጠይቆ ሊቀርብለት ያልቻለ ብር 1,826,510.21 መገኘቱ፤
- በባንክ ሂሳብ ቁጥር 2079 በሂሳብ መደብ 5026 ብር 407,096.34 ለማን እንደሚከፈል እና ለስንት ጊዜ የቆየ እንደሆነ የማይታወቅ ማስረጃ ተጠይቆ ሊቀርብለት ያልቻለ መገኘቱ፤

በሀብት አስተዳደር በተዘጋጀው የተከፋይ ሪፖርት

- ብር 407,096.34 ለማን እንደሚከፈል እና

- አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 14,463,971.09 ባንክ ስቴትመንት ላይ የሌለ ነገር ግን በቅ/ጽ/ቤቱ የባንክ ሚዛን ላይ የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡ ልዩነቱም በ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫ ላይ ማስተካከያ የሚል መታየቱና ለማን እንደሚከፈል ማስረጃ ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፣
- ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በሀብት አስተዳደር የስራ ሂደት በኩል በተዘጋጀው ዓመታው የሂሳብ ሪፖርት ላይ የቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ እዳና ወደፊትም ክፍያ የሚፈጸምበት ለመሆኑ ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሳብ በድምሩ ብር 9,618.13፣

ተገኝቷል፡፡

ስጋት

ሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሣይ ሊያደርገው ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በሂሳቡ ላይ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ሁኔታ እንዲያሳይ አስፈላጊው ማስተካከያ ሊደረግለት ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- አንዳንድ ሂሳቦች መረጃ /መነሻ ሰነድ ያልተገኘለትና እየተንከባለለ የመጣ ተከፋይ ሂሳብ በመሆኑ አሁንም በዋና መስሪያ ቤት የመፍትሄ አቅጣጫ መሰጠት ያለበት መሆኑን፣
    - ሌሎችም ተጣርተው እንደሚስተካከል ፣ ፈሰስ ያልተደረገ ሲሆን በግኝቱ መሰረት አጣርተን ፈሰስ የምናደርግ ይሆናል፣

በማለት ገልጸዋል፡፡

ለ. <u>የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ</u>

<u>ግኝት</u>

ማንኛውም በተከፋይ የተመዘገበ ሂሳብ ትክክለኛ መሆኑንና ቅ/ጽ/ቤቱ እዳ መሆኑን ለማረጋገጥ በተሞከረበት ወቅት በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት፣

- ከዝርዝር ተከፋይ ሂሳብ ሚዛን መሰረት የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ድምር ብር 2,597,368.50 ሲሆን በ ሂሳብ ማመዛዘኛ የተመለከተው ግን ብር 2,506,936.31 በመሆኑ በልዩነት ብር 90432.19 ምዝገባ ሳይኖረው የተቀነሰ፣
- የደሞዝ ተከፋይ ሂሳቦች (5004) ብር 292,139.00 እና (5028) ሌሎች ተከፋዮች ብር 335,843.41 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (አብኖርማል) የሚያሳዩ ሲሆን የሂሳቡ አመዘጋገብ በተመለከተ ዝርዝር ሁኔታውን የሚስረዳ ማስረጃ ሊቀርብልን ባለመቻሉ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>ስጋት</u>

የሂሳብ ማመዛዘኛው ከዝርዝር ሪፖርቱ ጋር የማይገጥም እና ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ላይ የተመዘገበ የተከፋይ ሂሳብ መገኘት የቀረበው የሂሳብ ሪፖርቱን አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ላልቻሉት ሂሳቦች ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የሂሳብ ማስተካከያ ሊደረግ ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ አስተያየት</u>

- 5004 በበጀት አመቱ የደመዎዝ ተመላሽ እና የአባይ መዋጮ ከሰራተኞች የተቆረጠ በ2006 በጀት አመት ፈሰስ ያልተደረገ ሲሆን አጣርተን ፈሰስ የምናድርግ መሆኑን ፣
- 5028 በግኝቱ ላይ የተገለፀው በ2007 በጀት ዓመት መጨረሻ የሰራተኛ የደንብ ልብስ መግዣ ፐሪፎርማ ተሰብስቦ ግዥ ሳይገዛ ወሩ ያለፈ ስለሆነ ሂሳቡ በዲፖዚት አካውንት እንዲገባ ተደርጎ ገንዘቡን በ2008 በጀት ዓመት ወጪ አድርገን ስራ ላይ የዋለ በመሆኑ ሂሳቡ በዛው እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ሰኔ 30 ወደ ዲፖዚት አካውንት የዞረ የተባለውን በተመለከተ ሂሳቡ ተሰብሳቢ እንጂ ተከፋይ አይሆንም ተከፋይ የሚሆነው ለዲፖዚት አካዉንት በመሆኑ የተሰጠው ምክንያት አጥጋቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሐ. <u>በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 43,083,022.98</u>

<u>ግኝት</u>

በፌዴራል መንግስት መስረያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 5 በተመለከተው መሰረት ተከፋይ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱን፣ የተከፋይ ሂሳቦች የጽ/ቤቱ ትክክለኛ እዳ መሆናቸውንና በማስረጃ የተደገፉ መሆናቸውን እና ሂሳቦቹም በወቅቱ የሚከፈሉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

- በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት
  - ➢ በጉምሩክ ስነስርዓት በተዘጋጀው የሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 5026 ለክልል ተከፋይ ሂሳቦች ብር 129,319.83፣ በሂሳብ መደብ 5051 የጉምሩክ መያዣዎች ብር 3,949,119.61 በሂሳብ መደብ 5054 ሌሎች መያዣዎች ብር 3,691,179.55
- በጅማ ቅ/ጽ/ቤት
  - ➢ በሀብት አስተዳደር የስራ ሂደት በልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳቦች (ሂሳብ መደብ 5005) ብር 7,200.00፣
  - ➢ በግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል የስራ ሂደት የተዘጋጀው የሂሳብ ሪፖርት ላይ በቀጥታ ገቢ የባንክ ሂሳብ (በሂሳብ መደብ 5026) ብር 1,631,310.71 እና በሂሳብ መደብ 5054 ብር 14,292.48 እና በአደራ የባንክ ሂሳብ በሂሳብ መደብ 5026 ብር 1,148,972.88 እና በሂሳብ መደብ 5054 ብር 21,800,094.54 ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል።

- ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በዴቢት ብር 16,695.48 በብልጫ ተከፍሎ በተሰብሳቢ የተያዘ 4 ዓመት ከ7ወር የቆየ እንዲሁም በክሬዲት ብር 269,021.52 ደግሞ ከ2 ዓመት ከ7 ወር እስከ 5 ዓመት ከ7 ወር የቆየ የተከፋይ ሂሳብ መሆኑና
- በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት
  - በባንክ ሂሳብ ቁጥር 2287 በሂሳብ መደብ 5051 (የጉምሩክ መያዣዎች) የተያዘ ብር 50,000 ከ1 ዓመት በላይ በተከፋይነት ተይዞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡
  - በሂሳብ ኮድ 5004 የደመወዝ ተከፋይ ሂሳቦች በድምር ብር 14,126.93 ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ፤
- በዋናው መስሪያ ቤት
  - ተከፋይ ሂሳቦች በባለስልጣን መ/ቤቱ ሂሳብ ክፍል በኩል በዕድሜ ዘመናቸው ተከፋፍለው ያልተቀመጡ መሆኑ፡
  - ከ 2006 ጀምሮ እስከ አሁን እየተንከባለሉ የመጡ፡-

የሂሳብ መደብ		የብር መጠን	መግለጫ
IFMIS	IBEX		
6173102	5022	429.82	Due to mofed for channel 1
6173108	5029	3,515.33	Due to family
6173116	5035	1,080,339.60	Due to mofed revolving fund
6173117	5028	4,042,400.57	Other payable
6174201	5051	237,405.49	Custom Deposit
6174204	5055	65,400.83	Bid bond deposit

ታውቋል፡፡

ስጋት

ተከፋይ ሂሳቦችን በወቅቱ አለመክፈል ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

በተከፋይ ሂሣቦች ላይ አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ በሚገኘው ውጤት መሰረት ተገቢ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ ሆኖ ለወደፊቱ ተመሳሳይ የአሰራር ግድፈት እንዳይደረስ በተከፋይ ሂሳብ ላይ ቁጥጥር እና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- የባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት የገቢና ዋስትና ሂሳብ ቡድን ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ያለው የዋስትና ሂሳብ በሰዓቱ መረጃው ስላልተያዘ ተለይቶ ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑንና ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ በየወሩ እየተሰራ መሆኑ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡
- **የጅማ ቅ/ጽ/ቤት ስራ አመራር**
  - አንዳንዶቹ ሂሳቦች ሌጀር የማያውቃቸው ገቢዎች ሰኔ 30/2007 ገንዘብ ሚኒስቴር ብሎክ ያደረው መሆኑን፣ መረጃ ላላቸው የተከፋይ ሂሳቦች ክፍያ እንዲፈጸም የሚደረግ መሆኑን፣ ለተከፋይ ሂሳብ ላይ ማስተካከያ የሚሰሩ መሆኑን ፣

በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

መ) በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ ተከፋይ

ግኝት

የሂሳብ ምዝገባ ክንውኖች የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የፌደራል መንግሰት መሰሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀፅ 6 ንኡሰ አንቀጽ 3 ላይ የፋይናንስ እንቅሰቃሴዎች ተለይተው እንዲመዘገቡ ለማድረግ በሚያስችሉ የሂሳብ

መለያ ቁጥሮች መሰረት ሂሳባቸውን መመዝገብ እንዳለባችው በሚያዝው መሰረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት በሂሳብ መደብ 5059 በተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ የነበረባቸው 8 ሂሳቦች ብር 218,185.26 በሂሳብ መደብ 5002-2 እና በሂሳብ መደብ 5006 በቅደመ ግብር ታክስ (Withholding tax) መመዝገብ የነበረባቸው 7 ሂሳቦች ብር 28,999.87 በ ሂሳብ መደብ በ5002-2 ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡
- በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 110,300.00 ክፍያዎች መመዝገብ በነበረባቸው የሂሳብ መደብ ሳይሆን በሌሎች የሂሳብ መደብ ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡

<u>ስጋት</u>

አሰራሩ የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የፋይናንስ አቋም እንዳያመለክት ሊያደርገው ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የመ/ቤቱ ሂሳብ ገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በተገቢው የሒሳብ መደብ መመዝገብ ያለበት በመሆኑ የማስተካከያ ምዝገባ ሊከናወን ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ስራ አመራር የተጨማሪ እሴት ታክስም ሆነ የቅድመ ግብር ገቢ አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት ክፍያ ሲፈጽም ቀንሶ በማስቀረት በወቅቱ ለሚመለከትው አካል ፈሰስ የተደረገ ሲሆን የሂሳብ ኮድን በተመለከተ ችግሩ የነበረ መሆኑን ተገንዝበን በ2008 በጀት ዓመት በትክክለኛው የሂሳብ መደብ እየተመዘገበ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡
- በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት ስራ አመራር የበጀት ችግር በመኖሩ የተጠቀምን መሆኑን እና ለቀጣዩ የምናስተካክለው ይሆናል፡፡

7. <u>በጀት</u>

ሀ) <u>በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከበጀት በላይ ብር 14,250,809.51 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ</u>

<u>ግኝት</u>

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 30 መሠረት በአንድ የበጀት አመት ውስጥ በበጀት አዋጁ ለተመለከቱት የመንግስት መሥሪያ ቤቶች እንዲከፈል በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ክፍያ መፈፀም እንደማይቻል እንዲሁም በፋይናንስ አስተዳደር ደንብቁጥር 190/2002 መሠረት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈፀም ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በዚሁም መሰረት ቅ/ጽ/ቤቶቹ ከዋናው መስሪያ ቤት በተደለደለላቸው መሰረት መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ በተሞከረበት ወቅት ፣ በተለያ የወጪ አርዕስቶች ስር፡-

ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት	2,628,891.80
በጅማ ቅ/ጽ/ቤት	4,933,756.45
ድሬ ዳዋ ቅ/ጽ/ቤት	2,721,102.05
በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት	2,888,886.80
ጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት	15,423,586.87
ሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት	2,088,080.48
ምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብረ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	1,255,267.71
በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት	86,755.66
የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	2,900,765.68
አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	862,114.84
አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት	1,259,500.26

- በጠቅላላው ብር 35,789,208.34 በፕሮግራሞቹና በርእሶቹ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ በብልጫ ወጪ መፈጸሙ፣ ተረጋግጧል፡፡

<u>ስጋት</u>

ያለእቅድ ወጪ እንዲወጣና የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊደረግ ይችላል፡፡በኃላፊነትም ሊያስጠይቅ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች የበጀት እጥረት ቢያጋጥማቸውው እንኳን በህጉ መሰረት ተጨማሪ በጀት እንዲፈቀድ ወይም የበጀት ዝውውር ማድረግ ይኖርበታል እንጂ ከተፈቀደለት በጀት በላይ ወጪ ማውጣት መፍቀድ የለበትም፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- አስተያየቱን ተቀብለው ከዋናው መ/ቤት ጋር የነበረው መጻጻፍ ሲዘገይባቸው ስራው መሰራት ስላለበት የከፈሉ መሆኑንና ለወደፊቱ በፕሮግራም በጀት እየተረዱ በመመዝገብ በበጀት በተፈቀደው ልክ ለመጠቀም ጥረት እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

ሠ) ከIFMIS እና ከሀብት አስተዳደር የቀረበ የተስተካከለ በጀት ሪፖርት በብር 10,352 394.62 ልዩነት ማሳየቱ፣

ግኝት

በ2007 በጀት ዓመት የቅ/ጽ/ቤቱ ከIFMIS እና ከሀብት አስተዳደር የቀረበው የተስተካከለ በጀት ሪፖርት አንድ ዓነት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደርግ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ከIFMIS የወጣው የተስተካከለ በጀት ብር 119,853,748.86 ሲሆን ከሀብት አስተዳደር በማንዋል የቀረበ የተስተካከለ በጀት ብር 130,206,143.48 ያሳያል፡፡

በመሆኑም በሁለቱ ሪፖርቶች መካከል የብር 10,352,394.62 ልዩነት እንዳለው ለማረጋገጥ ተችሏል ፡፡

ስጋት

ከአንድ ተቋም ሁለት ሪፖርት ሲወጣ የቀረበውን ሪፖርት ተአማኝነት ያሳጣዋል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

በመካከል ያለውን ልዩነት በማስታረቅ ተመሳሳይ ሪፖርት እንዲኖር መደረግ አለበት፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

የIFMIS Advisory (በጀት በሌለበት እንዲከፍል በመታዘዙ) ምክንያት በጀት ሳይኖር ሲስተሙ እንዲከፍል ስለተደረገ የወጪ መደቦች በብዛት ያልተለመደ ሚዛን (Negative Balance) ያሳዩ እና ልዩነት እንዲኖር አድርጓል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ረ) ከበጀት በላይ ወጪ ስለመደረጉ

ግኝት

በ2007 በጀት ዓመት የቅርንጫፍ መ/ቤቶች የበጀት ፍላጎት መሰረት ለሁሉም ቅርንጫፍ መ/ቤቶች በተላከው የበጀት ድልድል መሰረት ሥራ ላይ መዋሉን በተጠቃለለው ሀሳብ መሰረት ለማጣራት በተደረገው ኦዲት ብር 186,511,080.05 (14%) ከበጀት በላይ ወጪ ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

ስጋት

በጀት ለማጽደቅም ሆነ የማዘዋወር ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ቅ/መ/ቤቱ በዋናው መ/ቤት ተዘጋጅቶ ለቅርንጫፍ መ/ቤቶች በተላከው የበጀት ድልድል መሰረት በጀቱን ስራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቅርንጫፍ መ/ቤቱ የተጨማሪ በጀት ጥያቄ ወይም የበጀት ዝውውርም ዋና መ/ቤቱን በመጠየቅ ስራውን ሊያከናውን ይችላል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

መልስ አልተሰጠበትም፡፡

8. <u>ንብረት</u>

ሀ) <u>ለንብረት ተገቢው የቁጥጥር ስርአት ያልተዘረጋ መሆኑ</u>

<u>**ግኝት**</u>

በፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 6/1 ረ እና አንቀጽ 10/ሀ መሰረት ለመንግስት ንብረት የተሟላ የቁጥጥር ስርአት የተዘረጋ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በውርስ መጋዘን ውስጥ በሚገኙና በመደበኛ በጀት በተገዙ ንብረቶች ላይ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ክፍተቶች የሚታዩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡-

1. <u>በባህር ዳር ቅ/ጽቤት</u>

- አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ተለይተው ሪፖርት የተደረጉ ቢሆንም ሌሎች ብዛት ያላቸው ዲስክ ቶፕ ኮምፒዩተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ሼልፎች ወዘተ በቁጥር ያልተለዩ የተለያዩ ዓይነት ንብረቶች በንብረት ክፍል ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ (የንብረቶች አቀማመጥ ማለትም ንብረቶችን ለመለየት በማያስችል መልኩ የተደራረቡና ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች በአንድ ቦታ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ)

<u>**በውርስነት የተያዙ ንብረቶችን በተመለከተ**</u>

- የውርስ መጋዘን ውስጥ የተለያዩ ዓይነት ንብረቶች ምግብ ነክ የሆኑ እና የኬሚካል ይዘት ያለባችው ሳይለያዩ ተደራርበው የሚገኙ መሆኑ፣
- የውርስ መጋዘን ንብረት ቆጠራ የባህር ዳር ቅ/ፍ የተጠናቀቀ ቢሆንም የጣቢያዎች ቆጠራ ያልተደረገና ከመዝገብ ወጪ ቀሪ ጋር ያልተመዛዘነ መሆኑ፣
- በጎንደር መቅረጫ ጣቢያ የውርስ መጋዘን ውስጥ፣
- በጣቢያው የሚገኙ የተወረሱ ተሸከርካሪዎች መጠለያ ስላልተሰራላቸው በቆይታ ብዛት በዝናብና በፀሀይ ለእርጅና እየተዳረጉ መሆኑ፣

- ኮድ 3-01725 አማ ኢ.ት ፒክ አፕ እና 3-30661 ኢ.ት ገልባጭ ተሽከርካሪዎች በሀብት ንብረት ይዞ ግብር ማስከፈል የተያዙ ቢሆንም ለሽያጭ አለመቅረባቸው፡፡

2. <u>**በኮምቦልቻ ቅ/ፅ/ቤት በኩል**</u>

- ጠረጴዛ፣ወንበር፣ ሸሚዝ፡ ጫማ፣ ፕሪንተር፣ ሚስማር እና መሳቢያ ቢን ካርድ የሌላቸው መሆኑን፣
- የሚወገዱ ንብረቶች በተመለከተ አገልግሎት ከሚሰጡ ንብረቶች ጋር አብረው የተቀላቀሉ መሆኑ፣
- የእሳት ማጥፊያ አለመኖሩ፣
- አገልግሎት መስጠት የማይችሉ በቁጥር 206 የሆኑ የተለያዩ ዕቃዎች በንብረት ክፍል ተከማችተው መገኘታቸው፣

- በፍርድ ቤት ክርክር ላይ ያሉ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ
  - ተሽከርካሪዎቹ ያሉበት ቦታ ለአቧራ፡ ለፀሀይ እና ለዝናብ የተጋለጠ በመሆኑ ተሽከርካሪዎቹ እየተበላሹና ከጥቅም ውጪ እየሆኑ መሆኑ
  - በሞዴል 265 ገቢ ከሆኑት ዉስጥ አንድ ተሽከርካሪ ታርጋ የሌለው መሆኑ፣
  - በሞዴል 265 ገቢ ከሆኑት ዉስጥ አንድ ተሽከርካሪ እንዲሁም በሞዴል 270 ገቢ ከሆኑት ዉስጥ ሦስት ተሽከርካሪዎች የሞተር ቁጥራቸው ተፈልጎ ያልተገኙና ያልተመዘገበ መሆኑን፣ በኦዲቱ ለማወቅ የተቻለ በመሆኑ የቅ/ጽ/

3. <u>**ጅግጅጋ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ፡-**</u>

<u>**በኮንትሮባንድ የተያዙ ንብረቶች በተመለከተ**</u>

- በቁጥር 110 በላይ የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች ተለይተው ውርስ በሞዴል(265) ጊዜያዊ ሞዴል (270) ገቢ ያልተደረጉ መሆኑን እንዲሁም ያሉት ተሽከርካሪዎች ያሉበት ቦታ ለአቧራ፣ ለፀሀይ እና ለዝናብ የተጋለጠ መሆኑ፡

- እንደዚሁም ተሸከርካሪዎች ተመላሽ በሚደረጉበት ጊዜ ገቢ ሳይሆኑ በሞዴል 266 ወጪ የሚሆኑ መሆኑን፣
- 10 ሙሉ መኪና የሚሆኑ ከተለያዩ ጣቢያዎች እና ከባለድርሻ አካላት የመጡ እቃዎች ረዘም ላለ ጊዜ የቆሙ መሆኑን እንዲሁም ርክክብ ሳይፈጸም ሶስት ወር ያለፈው ጭነት መኖሩን፡፡
- ከባለድርሻ አካላትም ሆነ ከጣቢያ መጥተው በሞዴል ያልተመዘገቡ ነገር ግን ከተመዘገቡ ወይም ገቢ ከሆኑ እቃዎች ጋር ተደባልቀው መጋዘን ውስጥ የተቀመጡ እቃዎች መኖራቸው፣
- 350 ኪስ የሚሆን ስኳር ውጭ ላይ ከአንድ አመት በላይ ቆይቶ የተበላሸ መሆኑ፣
- ህገ ወጥ እቃዎች በቅ/ጽ/ቤቱ ወይም በተቋማት ሲያዙ ለባለቤቱ ደረሰኝ የማይሰጥ መሆኑ፣
- ማንኛውም የተያዘ ኮንትሮባንድ ቢን ካርድ የሌለው ስለሆነ ባላንሱ የማይታወቅ መሆኑ እንደ ሳምፕል በተወሰደው መሰረት የቁም እንስሳት ባላንስ እንዲሁም ለማስወገድ ለጨረታ ኮሚቴ የተላኩ እንስሳት መቼ መቼ የገቡ እንደሆኑ ተጠቅሶ ባላንሳቸው ስለማይቀመጥ ለማጣራት ያለመቻሉ፣
- የተወረሱ ንብረቶች በሞዴል 265 መመዝገብ ሲኖርባቸው ሞዴል 270 እየተመዘገቡ መሆኑን፡፡

<u>ወጫሌ መቆጣጠሪያ ጣቢያ</u>

- ኬላ የተያዙ ንብረቶች በሞዴል 270 እንደ ተያዙ እዛው ገቢ የማይደረጉ መሆኑን፣
- በኮንትሮባንድ የተያዙ ንብረቶች ቢን ካርድ የሌላቸው ስለሆነ ባላንሱ የማይታወቅ መሆኑ፣

<u>ስለ ቋሚ ንብረት አስተዳደር እና ስቶክ አስተዳደር አመዘጋገብ እና አያያዝ</u>

- ንብረት በሚገባበትና በሚወጣበት ጊዜ ተከታትሎ ቢን ካርድ ላይ እንደማይቀናነስ እና፣

- ለንብረት ተጠቃሚ ሰራተኞ የንብረት ምዝገባ ካርድ (UC) በተጠቃሚዎች እጅ እንደማይገኝ እና በንብረት ክፍል የሚገኘው የምዝገባ ካርድ በየጊዜው ማስተካከያ እንደማይደረግለት፣
- ሰራተኞች ስራ በሚለቁበት ሰዓት ንብረት ገቢ ሳይደረግ የተገኘ መሆኑ፡
- የመስሪያ ቤቱ ንብረቶች ኮንትሮባንድ መጋዘን ውስጥ ከኮንትሮባንድ ጋር ተደባልቆ የተቀመጠ መሆኑ፡፡
- የተበላሹ ተሽከርካሪዎች ሳይጠገኑ ወይም ሳይወገዱ ለረዥም ጊዜ የቆዩ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

4. <u>**በድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት በኩል፡-.**</u>

- በሞዴል 19 ገቢ የተደረጉ እና በሞዴል 22 ወጪ የተደረጉ ቋሚ እቃዎች በመዝገብ ላይ ምንም አይነት የምዝገባ ስርዓት ያልተካሄደላቸው መሆኑን፣
- የተወረሱት ንብረቶች በስቶክ ካርድ እና ቢን ካርድ እየተመዘገቡ ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፣
- የተወረሱ ንብረቶች በመዝገብ የማይመዘገቡ በመሆናቸው ወደ መጋዘን የገባውና የወጣው እንዲሁም ቀሪው በትክክል ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ የሚያስቸግር መሆኑ፣
- የተወረሱ ንብረቶችን የሚመዘግብ ባለሙያ የሌለው መሆኑ፡፡

5. <u>**በሞያሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል፡-**</u>

- እቃ በሚገባበትና በሚወጣበት ጊዜ ተከታትሎ ቢን ካርድ ላይ እንደማይቀናነስ እና የአብዛኛው እቃ ቢን ካርድ 2006 ዓ/ም በኃላ እንዳልተቀናነሰ ወይም ወቅታዊ እንዳልሆነ፣
- ለንብረት ተጠቃሚ ሰራተኞን የንብረት ምዝገባ ካርድ (UC) በተጠቃሚዎች እጅ እንደማይገኝ እና በንብረት ክፍል የሚገኘው የምዝገባ ካርድ በየጊዜው ማስተካከያ እንደማይደረግለት፣
- ንብረት ክፍል ሰራተኞች በሚቀየሩበት ሰአት ለንብረቶቹ ህጋዊ ርክክብ ያልተደረገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

<u>የውርስ መጋዘን አያያዝ በተመለከተ</u>

- ጉዳያቸው ያላለቀ (በክርክር ላይ) ላሉ ተሽከርካሪዎች ሞዴል ያልተቀረጠ እና ምንም አይነት መዝገብ የማያውቃቸው መሆኑን እንዲሁም በሁሉም ጣቢያ ያሉት ተሽከርካሪዎች ያሉበት ቦታ ለአቧራና ለፀሀይ የተጋለጡ መሆናቸው፣
- በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ኬሚካሎች ሳይወገዱ መጋዘን ውስጥ ለረጅም ጊዜ መቆየታቸውን ፣
- በቅ/ጽ/ቤቱ ለረጅም አመታት በግምት ከ60 በላይ ሙሉ ማዳበሪያ የመለዋወጫ እቃዎች እንዲሁም በሁለቱም መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች በዛ ያሉ መለዋወጫ እቃዎች ምንም አይነት ምዝገባ እና ቆጠራ ሳይደረግላቸው በመጋዘን ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
- በቅ/ጽ/ቤቱ እና በሁለቱም መቆጣጣሪያ ጣቢያዎች ከአመት በላይ ያስቆጠሩ እና በህግ ውሳኔ ያላገኙ ደረቅ ጫት መገኘቱ፣
- በያቤሎ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ከአመት በላይ የቆየ 14 ጀሪካን ቤንዚን ሳይወገድ ተገኝቶአል ፡፡

6. ምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብረ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በሲዝ ኮሚቴ የተያዙ ንብረቶች እስካሁን እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ

7. **<u>ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በኩል</u>**

   - ቋሚ ዕቃ ቆጠራ ዝርዝር ውስጥ ንብረቶቹ የሚገኙበት ክፍል አለመገለጹ፣
   - አንዳንድ ንብረቶች የንብረት መለያ ቁጥር አለመሰጠት መለያ ቁጥር የተሰጣቸውም ቢሆን በአካል የማይታይ እና የጠፋ መሆኑ፣
   - እንደ ላፕቶፕ ያሉ ንብረቶች የንብረት መለያ ቁጥር በንብረቶቹ ሲሪያል ቁጥር መሰረት ተለይተው አለመያዝ፣
   - ቋሚ ንብረቶች ለተጠቃሚው የመ/ቤቱ ሰራተኛ በውሰት በሚሰጥበት ሰዓት የንብረት ምዝገባ ካርድ ለሰራተኞች አለመሰጠት፣
   - ዋጋቸው ከብር 1000.00 (አንድ ሺ) በታች እና የአገልግሎት ዘመናቸው ከአንድ ዓመት በላይ የሆኑ ንብረቶች ለብክነት ሊዳረጉ ስለሚችሉ ለብቻ ተመዝግበው ያልተያዙ መሆኑ ታይቷል፣

- በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በሚገኝ የአላቂ ንብረቶች ማስቀመጫ መጋዘን ውስጥ ለተጠቃሚዎች ሳይሰጡ ረዥም ጊዜ ያስቆጠሩ ቶነሮች፣ ቁርጥራጭ የደንብ ልብስ ጨርቆች፣ መዝገቦች (መዚ 21,22,24,26,27) የገቢ ግብር ቀንሶ ገቢ ማድረጊያ መዚ 12 16 ሞዴል 127 የሰራተኛ ማህደር ቅጽ የመሳሰሉት ለረዥም ጊዜ በንብረት ክፍል ተቀምጠው የሚገኙ ሲሆን፣ በቅጥር ግቢው ውስጥ በሚገኙ ሶስት መጋዘኖች እና በአማኑኤል አካባቢ በሚገኝ አንድ መጋዘን አገልግሎት የማይሰጡ ከ100 በላይ ኮምፒዩተሮች፣ ፕሪንተር፣ ዩፒኤስ፣ የስልክ ቀፎ፣ የሂሳብ መደመሪያ መሳሪያ፣ ፋክስ፣ የፎቶ ኮፒ ማሽን፣ ጎማ፣ መኪና ተጠግኖ ተመላሽ የተደረገ መለዋወጫ፣ ፋይል ካቢኔት፣ ወንበር እና ጠረጴዛ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፡-
- የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2006 በጀት ዓመት ሊወገዱ በሂደት ላይ የነበሩ 4 ማሩቲዎች እና በመ/ቤቱ ቅጥር ግቢ የሚገኙ 2 ሞተር ሳይክሎች መኖራቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጦ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርት መቅረቡ ይታወቃል፡፡ሆኖም ተሽከርካሪዎቹ እስካሁን ምንም አይነት እርምጃ እንዳልተወሰደ፣

በኦዲት ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

8. አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ለተወረሱ ንብረቶች የንብረት መረከቢያ ሰነዶችን የመያዝ ወይም የመመዝገብ ስራ እና ንብረትን የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ስራ የሚከናወነው በአንድ ሰራተኛ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

9. አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት

<u>ቋሚ ንብረት፡-</u>

- የቅ/ጽ/ቤቱ ቋሚ ንብረቶች የቋሚ ንብረት ቢን ካርድ ላይ የማይመዘገቡ እና የማይቀናነሱ መሆናቸው፣
- የስቶክ ቁጥጥር ስርዓት አለመኖሩ፣
- በዓአመቱ የሚካሄደው የቋሚ ንብረቶች ቆጠራ የተሟላ አለመሆን ታውቋል፡፡

<u>የውርስ ዕቃዎች አያያዝና አጠባበቅ</u>

- የተለያዩ ኬሚካሎች ከ10 አመት በላይ ሳይወገዱ የቆዩ መሆናቸው፣

- መድሀኒቶች እና የህክምና እቃዎች እረጅም ግዜ በመጋዘን ተከማችተው የሚገኙ መሆናቸው፣
- በመጋዘን ቁጥር 9 የተለያዩ ኬሚካሎች ከሌሎች እቃዎች ጋር ተደባልቀው መገኘታቸው፣
- በቂ የሆነ መጋዘን አለመኖሩና እንዲሁም እስካሁን እርምጃ አለመወሰዱ፣

በኦዲቱ ወቅት ታይቷል፡፡

<u>ስጋት</u>

ለንብረቶች ተገቢው የቁጥጥር ስርአት የማይዘረጋላቸው ከሆነ ለብክነትና ለብልሽት ይዳረጋሉ፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- የስቶክ መዛግብት መያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች ለአንድ ሰራተኛ መሰጠት የለባቸውም፣

- በየዓመቱ በውርስ መጋዘን ውስጥ ያሉ ንብረቶች በመ/ቤቱ በተቋቋመው የቋሚ ንብረት ቆጠራ ኮሚቴ ሊቆጠር ይገባል፣
- የውርስ መጋዘን ንብረትን የሚያስተዳድር ክፍል የተጠናከረ መረጃ የያዘ የተወረሱ ንብረቶችን መመዝገቢያ ካርድና መዝገብ መያዙን የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- የንብረት አያዝና አመዘጋገብ ችግሮቹን ለመቅረፍ ጥረቶች እንዳሉና የሚወገዱትን ለማስወገድ እንቅስቃሴ የጀመሩም መኖራቸው ተገልጾል፡፡

9. ልዩ ልዩ

ሀ) የባለፈው የኦዲት ሪፖርት አስተያየት መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ በተመለከተ

ግኝት

በፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 17(3) መሰረት ኦዲት ተደራጊ መስሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገኙ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን ከዚህ በታች በቀረበው ዝርዝር መሰረት ከዚህ በፊት ለተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች የእርምት ወይም የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- **በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት በኩል**
  - ያልተሰበሰበ ውዝፍ ግብር ብር 37,740,849.55 መኖሩ፡
  - የህብረት ሥራ ማህበራት ብር 80,691,304.76 እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣
  - አምባሰል ንግድ ስራዎች ድርጅት ላይ መሰብሰብ የነበረበት ብር 8,400,831.68 ቀረጥና ታክስ አለመሰብሰቡ፡፡

- **በጅማ ቅ/ጽ/ቤት በኩል**
  - በ2005 በጀት ዓመት ኦዲት ከቤስት ኢስት አፈሪካ ኃ/የተ/የግ/ማ የሚፈለግ ግብር ብር 22,261.17 እንዲሰብ የኦዲት ማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም አለመተግበሩ፡፡

- **በኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት በኩል**
  - የግብር ዕዳ ማስታውቂያ ደርሷቸው ያልተከፈለ ወይም የግብር ይግባኝ አቤቱታ ያልቀረበበት ብር 2,348,844.23 በተመለከተ፣
  - የተጣራ ሀብት ብር 299,806.45 አብኖርማል ባላንስ የሚያሳይ መሆኑ በተመለከተ፣
  - ያልተሰበሰበ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ሂሳብ ብር7,672,325.68 መኖሩን በተመለከተ፣

- የረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ልዩ ልዩ የቅድመ ክፍያ ሂሳቦች ብር 6,050.07 ሳይወራረዱ መገኘታቸውን በተመለከተ፣

<u>ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል</u>

- በ2006 በጀት ሂሳብ ኦዲት በቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ከማን እንደሚሰበሰብ መረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ሂሳብ በድምሩ ብር 3,238,328.26 ሰኔ 30/2006 በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ በተሰብሳቢነት ሪፖርት የተደረገ፣ እንዲሁም በግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል የሥራ ሂደት በኩል (ለባንክ ሂሳብ ቁጥር 6226) ቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ከማን እንደሚሰበስበው መረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ሂሳብ በሂሳብ መደብ ቁጥር 4201 ብር 44,337.98 ሰኔ 30/2006 በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ በተሰብሳቢነት ሪፖርት የተደረገ፣
- በጉምሩክ ስነስርአት የስራ ሂደት በኩል (ገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች ቡድን) ለባንክ አካውንት ቁጥር 3756 በሂሳብ መደብ 5051 ብር 72,561.97 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 5054 ብር 344,885.45 የቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ እዳና ወደፊትም ክፍያ የሚፈፅምበት ለመሆኑ መረጋገጥ ያልቻለ ሂሳብ በድምሩ ብር 417,447.42 ተከፋይ ሂሳቦች ሰ ኔ 30/2006 በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ
- በተከፋይ ሂሳብነት ሪፖርት የተደረገ መሆኑን በፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የእርምት እርምጃ ሳይወሰድበት በ 2007 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርት ላይም በድጋሚ የተገለጸ መሆኑ፣
- ገቢ ያልተደረገ ውዝፍ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ብር 42,779,886.45 ለቅ/ጽ/ቤቱ የንብረት ያገር ኮሚቴ የተላለፈ ቢሆንም ኮሚቴው በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 77 መሰረት የግብር ከፋዮችን ሀብት በመያዝ የሚፈለግባቸውን የግብር እና ታክስ እዳ እንዲሸፈን ያደረገ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

- <u>በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት</u>

- የ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ በመስሪያ ቤታችን ኦዲት ተደርጎ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች በሙሉ እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ፣

- **<u>ምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት</u>**

  - በዜድ ሪፖርት እና በተጨማሪ እሴት ታክስ ሽያጭ መካከል በታየ ልዩነት ምክንያ ያልተሰበሰበ ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 55,135.41 መኖሩ፣
  - በትርፍና ኪሳራ መግለጫ ላይ የተመለከተው ሽያጭ በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ ተመለከተው ጠቅላላ ሽያጭ ጋር ሲታይ ንግድ ትርፍ ብር1,082,124.95 እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 401,875.07 በድምር ብር 1,484,000.02 ያልሰበሰበ ግብር መኖሩ፣
  - ኢስትረን ኢያስ መሀንዲሶችና ሥራ ተቋራጮች ኃ/የተ/የግ/ማህበር የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር /0000010150/ በጥቅምት ወር 2005 ዓ.ም በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ ሽያጭ ብር 236,283.00 የሚታይ ሲሆን በዓመቱ ንግድ ትርፍ ላይ ምንም ሽያጭ እንደልተከናወነ በማሳወቁ እና ንግድ ትርፍ ላይ ብር 236,283.00 ባለማሳወቁ ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ግብር ብር 70,884.90 መኖሩ፣
  - የ14 ድርጅቶች ግብር ማሳወቂያ በግብር ከፋዮች ፋይል ውስጥ አለመኖሩ፣

- **<u>በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በኩል</u>**

  - በ2005 እና በ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝት መሰረት ገቢ ያልተደረገ ውዝፍ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ብር 16,645,098.36 መኖሩ፤

<u>በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት በኩል</u>

- ሀገስና አለምፀሀይ ኃ/የተ/የግ.ማህበር (0002386614) በንግድ ትርፍ ግብር እና ተ.እ.ታ ጠቅላላ ሽያጭ ልዩነት መኖር ሲሆን ድርጅቱ ቋሚ ንብረት ከሆኑት ውስጥ አንዱ ተሽከርካሪ የተሸጠ እና ሽያጩ በተ.እ.ታክስ ድክለር ተደርጎ በንግድ ትርፍ ግብር ያልተካተተ መሆኑ፤
- ሆንዶዋ ሽቆ ኃ/የተ/የግል ማህበር (0000047893) የመጋቢት ወር 2006 የተ.እ.ታ ማስታወቂያ ያልተያያዘ መሆኑ፤2006 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

- **<u>በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት በኩል</u>**
  - ሳይሰበሰብ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረና እርምጃ ያልተወሰደበት ቀሪ ሂሳብ ብር 104,603,256.54፣
  - እቃዎች በጊዜያዊነት የሚቆዩበት የጊዜ ገደብ የተጠናቀቀ ቢሆንም ብር 88,547,639.35 ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ፤

- **<u>በዋናው መስሪያ ቤት</u>**
  - ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች የተከፈለ ብር 3,465.77 የደመወዝ ክፍያ ተመላሽ አለመደረጉና በዚህ በጀት ዓመትም ተመሳሳይ ስህተት ተፈጽሞ መገኘቱ፣
  - ማስረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ብር 10,372,719.65 የተሰብሳቢ ሂሳብ እስካሁን ተጣርቶ እርምጃ አለመወሰዱ፣
  - ትክክለኛ ተከፋይ ሂሳብ መሆኑ ያልተረጋገጠ ሂሳብ ብር 2,350,867.88 ተጣርቶ እርምጃ አለመወሰዱ፣
  - ሳይወገዱ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ የተወረሱ 9 ተሽከርካሪዎች አሁንም ድረስ መኖራቸው፣

  በኦዲቱ አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደና ያልተወሰደበት አጥጋቢ ምክንያት አለመኖሩ ታውቋል፡፡

<u>ስጋት</u>

በኦዲት አስታየት ላይ እርምጃ ካል ተወሰደ የኦዲቱን ዓላማ ካለማሳካቱም በላይ ችግሮች ከዓመት ዓመት እንዲቀጥሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡ተገቢውን የእርምት እርምጃ አለመውሰድ በኃላፊነት ሊያስጠይቅ ይችልል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

አሁንም ቢሆን በባለፉት አመታትም ሆነ በዚህ ዓመት በተገለጹት የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን ኦዲት ዳይሬክቶሬት

የ2007/2008 ዓመት የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርት

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት			መግለጫ
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር	
1	የማዕከላዊ ስታቲስ ቲክስ ኤጀንሲ	20/3/2008	79,082,192.15	184,415,413.34	263,497,605.49	
2	የኢትዮጵያ ብሮድ ካስቲንግ ኮርፖሬሽን	27/1/2008	366,794,420.00	300,558,800.00	667,353,220.00	
3	የወለጋ ዩኒቨርስቲ	30/2/2008	330,846,492.00	391,776,035.70	722,622,527.70	
4	የመንግሥት ኮሙ/ ጉዳዮች ጽ/ቤት	05/1/2008	62,337,072.14	17,862,612.00	80,199,684.14	
5	የባህልና ቱሪዝም ሚ/ር	17/3/2008	60,073,734.01	0.00	60,073,734.01	
6	የቤተ መንግስት አስተዳደር	07/12/2007	134,827,832.88	181,027,358.39	315,855,191.27	
7	የኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል	29/1/2008	16,559,260.00	0.00	16,559,260.00	
8	የብሔራዊ ቤተ-መዛግ ብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ	11/4/2008	24,130,433.67	51,600,000.00	75,730,433.67	
9	የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን	ነሐሴ 19/2007	29,130,500.35	8,698,100.00	37,828,600.35	
10	የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን	ነሀሴ 26/2007	10,834,260.00	2,624,433.41	13,458,693.41	
11	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር	መስከረም 18/2007	24,376,879.00	24,600,000.00	48,976,879.00	
12	የመንግስት የፋይና ንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ	ህዳር 17/2008	8,893,980.00	00.00	8,893,980.00	
13	የፕሬዚደንት ጽ/ቤት	15/2/2007	67,027,854.05	00.00	67,027,854.05	
14	የፌዴሬሽን ምክር ቤት	02/2/2008	35,425,857.04	5,000,000.00	40,425,857.04	
15	የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር	ጥር 26/2008	36,219,799.15		36,219,799.15	
16	የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን	ጥቅምት 11/2008	19,721,742.19	00.00	19,721,742.19	
17	የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ	27/1/2007	12,785,170.00			

ተ.ቁ		የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት ያቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት			
			መደበኛ በጀት	ካፒታል በጀት	የውስጥ ገቢ	ድምር
18	የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ	መስከረም 28/2008	283,714,563.00	261,025,000.00	5,698,100.00	550,437,663.00
19	የድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ	26/4/2008	223,144,399.00	235,000,000.00	6,032,900.00	464,177,299.00
20	የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት	29/2/2008	555,634,966.60			555,634,966.60
21	የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ	1/1/2008	6,876,428.62			6,876,428.62
22	የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ	26/12/2008	43,843,126.00		1,980,900.00	45,824,026.00
23	የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት	8/3/2008	120,911,968.00	6,630,000.00		127,541,968.00
24	የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት	28/1/2008	180,960,421.91	3,500,000.00		184,460,421.91
25	የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በጀት	20/5/2008	412,295,107.8	136,472,401.42		548,767,509.22
26	የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ	2/13/07	7,021,620.00			7,021,620.00
27	የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት	19/1/2008			109,672,340.00	109,672,340.00
28	የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት	19/12/2007	23,333,538.00			23,333,538.00
29	የደብረ ብርሀን ዩኒቨርስቲ	25/4/2008	729,432,278.00	250,105,700.00	9,669,277.60	539,207,255.60

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች

1. ጥሬ ገንዘብ ሂሳብ

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችል የቁጥጥር ስርአት መዘርጋቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ፕሬዚደንት ጽ/ቤት የሂሳብ መግለጫ ላይ በተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታየው ብር 12,697.87 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት (በ4202) በ2005 እና በ2006 በጀት ዓመት ካጎደሉት ገንዘብ ያዥ እንዲሰበሰብ ወይም ሊ ሰበሰብ ካልቻለ ቀጣይ እርምጃ

- እንዲወሰድበት የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እስከ አሁን እርምጃ አለመወሰዱ፣
- የደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፤ሰኔ 30/2007 በተደረገው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ብር 30,901.31 በጥሬ ገንዘብ እና በሰነድ የተገኘ ሲሆን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ብር 19,683.78 በመሆኑ የሂሳብ ሪፖርቱ በብር 11,217.53 በማነስ የሚታይ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

በመሆኑም ከላይ በተመለከቱት ግኝቶች ላይ ተገቢው እርምጃ እና ማስተካከያ እንዲወሰድ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2. ተሰብሳቢ

2.1 በወቅቱ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) የተሰብሳቢ ሂሳብ

በፋይናንስ አስተዳር ደንብ መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱንና ሂሳቡም በወቅቱ መወራረዱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ19 መ/ቤቶችና 7 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 607,789,107.1 ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝተል/ዝርዝሩ በአባሪ-6 ተመልክተል/

በመሆኑም ውዝፍ ሰነዱን በወቅቱ አለማወራረድ ለመንግስት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት# ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው የስራ አመራር ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2.2 በማነስ ሪፖርት የተደረገ ተሰብሳቢ ሂሳብ

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት የተመለከተው ሂሳብ ትክክለኛነት ሲጣራ በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በሂሳብ መደብ 4201 ብር 108,424.60፤ በሂሳብ መደብ 4251 ብር 8,704,920.66 በድምሩ ብር 8,813,345.26 በሂሳብ ሪፖርቱ በማነስ የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡

በሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተሰብሳቢ ሂሳብ ከተያዘው ሂሳብ ውስጥ ብር 582,551.80 ደጋፊ ሰነድ የሌለው ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፣

የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የሒሳብ እንቅስቃሴ ሊያሳይ ስለማይችል አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደረግ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.3 ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ከ2002-2007 ዓ.ም በዱቤ ካስተላለፈው ማስታወቂያ መሰብሰብ የነበረበት ውዝፍ ሂሳብ ብር 35,364,503.56 እስካሁን አለመሰብሰቡ ታውቋል፡፡ ለረጅም ዓመታት ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ሳይሰበሰብ መቆየቱ በጥሬ ገንዘብ ፍሰት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድርና ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል አስፈላጊው ክትትል ተደርጎ ውዝፉ ተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲሰበሰብ ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ፡ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. የወጪ ሂሳብ

3.1 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች

ግዥዎች በመንግስት የግዥ ደንብና መመሪያ መሰረት መፈፀማቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ9 መ/ቤቶችና በ5 የገ/ጉ/ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 53,079,171.88 የመንግስት ግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዥ ፈጽመው ተገኝቷል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ- 21 ተመልክቷል/

በመሆኑም ከመመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቶቹን ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል ለወደፊቱ መመሪያው ተፈፃሚ እንዲሆን በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

3.2. ያለ ሂሳብ መደባቸው የተመዘገቡ ወጭዎች

ወጪዎች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሂሳብ አወቃቀር ሥርዓት /chart of account/ መሰረት በትክክለኛው የሂሳብ መደባቸው መመዝገባቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ9 መ/ቤቶች በተለያዩ የወጪ ሂሳብ መደቦች በድምሩ ብር 6,483,691.37 ያለ ሂሳብ መደባቸው የተመዘገቡ ወጭዎች ተገኝቷል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ-25 ተመልክቷል/

የሂሳብ መደብን ጠብቆ ያለመመዘገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅእኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም ከበጀት በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱንም ያዛባል፡፡ በመሆኑም የበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ትክክለኛ የሂሣብ መደቡን ጠብቆ መመዝገብ ያለበት ሲሆን ሂሣቡም በትክክል ስለመመዝገቡ የሚረጋገጥበት ሥርዓትም መዘርጋት አለበት፡፡ ለወደፊቱም የታየው የምዝገባ ስህተት የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ የተስተካከለ የሂሳብ ሪፖርት እንዲዘጋጅ ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.3 <u>ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች</u>

ለውሎ አበል ወጪ ሆነው የተከፈሉት ክፍያዎች በውሎ አበል ክፍያ መመሪያ መሰረት መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭ በምሽት እና በእረፍት ቀናት ለሚሰሩ ሰራተኞች ከሥራ ሰዓት ውጪ ለሰሩበት የምሳና የእራት ክፍያ በውሎ አበል ሂሳብ መደብ (6231) ብር 24,984.97 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱና ተመሳሳይ የአሰራር ግድፈት በ2006 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት ተገኝቶ የማሻሻያ ሃሳብ የተሰጠ ቢሆንም አለማረሙ፣
- በኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል ለውሎ አበል የውሎ አበል መጠየቂያ፣ መፍቀጃና መክፈያ, የደመወዝ መጠን, እንዲሁም ሲመለሱ የቀን ውሎ አበል ክፍያ መቆጣጠሪያና የሥራ ክንውን መመዝገቢያ ቅጽ ሳይሞላ፣ ብር 9,000.00 (ለ20 ሰው×150×3) ከቀን ውሎ አበል በተጨማሪ ለመክፈል የሚያስችል መመሪያ ሳይኖር ለቁርስ መከፈሉ፣ ለአንድ ተሳታፊ ከውሎ አበል በተጨማሪ ለአልጋ ብር 150.00 መከፈሉ፣ ለተሳታፊዎቹ አበሉ በሐረር ከተማ ሂሣብ በመከፈሉ ለተሳታፊዎቹ በትክክል በመንገድ ላይ (ሲሄዱና ሲመለሱ) በተጨማሪም በፌስቲባሉ ላይ ለቆዩበት ቀን ሊከፈላቸው የሚገባቸውን የአበል መጠን ለማወቅ አለመቻሉ፣
- በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ ስልጠና ለተካፈሉ ሰልጣኞች (ለኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች) የምሳ አበል በቀን ብር 100 ሂሳብ (ብር 100×259) ብር 305,650.00 ተከፍሎ መገኘቱና ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭ በትርፍ ሰዓታቸው ለሰሩ ተብሎ

ለኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች ብር 562,764.15 የውሎ አበል ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣

- በፕሬዚደንት ጽ/ቤት ከስራ ሰዓት ውጪ ገብተው ለሰሩ ሂሳብ ሠራተኞች ብር 2,721.00 በጥሬ ገንዘብ የመስተንግዶ ሂሳብ ተከፍሎ መገኘቱ፣
- በብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻህፍት ኤጀንሲ ቤተመጻሕፍት እያመሹ ለሚሰሩ ሰራተኞች የትራንስፖርት አበል እንዲከፈል የሚመለከተው አካል ሳይጠየቅና ሳይፈቀድ በተለያዩ 32 ክፍዎች በሂሳብ መደብ 6232 ብር 294,975.90 ክፍያ መፈጸሙና ባለፉት በጀት ዓመታቶች ግድፈቱ እንዲታረም የኦዲት ማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም አለመታረሙና ሠራተኞች ለስራ ጉዳይ ከመሄዳቸው በፊት መሞላት የሚገባው የውሎ አበል መጠየቂያ፣ መፍቀጃ፣ መክፈያና ሲመለሱ የቀን ውሎ አበል ክፍያ መቆጣጠሪያና የሥራ ክንውን መመዝገቢያ ቅጽ ሳይሞላ ብር 34,450 ከክልል ለስልጠና ለመጡ ተሳታፊዎች (ለእያንዳንዳቸው ብር 200) መከፈሉና መቀሌ ለተደረገው የመጻህፍ አውደርእይ ላይ ለተሳተፉ ለመስተንግዶ ብር 95,908.37 (በጥሬ ገንዘብ) በሂሳብ መደብ 6231 ክፍያ መፈጸሙ እና ለ71 ተሳታፊዎች ብር 14,200.00 ከሙሉ ቀን ውሎ አበል በተጨማሪ ለአልጋ መከፈሉ፣

- በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በድምሩ ብር 199,174.75 የተለያዩ 6 ያለአግባብ የተከፈለ የውሎ አበል ክፍያ በትርፍ ሰዓት ሂሳብ መደብ (6116) ተመዝግቦ መገኘቱ እና የተለያዩ 15 ክፍያዎች በቢሮ ውስጥ ለተሰሩ ስራዎች በድምሩ ብር 152,000.15 የውሎ አበል ክፍያ መፈጸሙ፣ የደመወዝ መጠን, መነሻና መድረሻ ቦታና ሰአት ሳይገለጽ ለ 5 ቀናት በቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ታላቁን የሕዳሴ ግድብ ለጎበኙ 225 ሠራተኞች የ 5 ቀን የወሎ አበል ክፍያ ብር 562,500.00 (ለ 225 ሰው × 500 × 5) መክፈሉ፣

  ለትራንስፖርት አገልግሎት (ለሁሉም ሠራተኞች) በብር 215,640.00 ተሰጥቶ ሳለ በተጨማሪ ለትራንስፖርት አበል ብር 48,400.00 (ለአንድ ሠራተኛ ብር 200.ሂሳብ ለ242 ሠራተኞች) የተከፈለ መሆኑ፣ በነገሌ ቦረና ከተማ ላይ

ለተካሄደው የመቻቻል ቀን በዓል ለተሳታፊዎች የምግብ አገልግሎት በብር 105,407.62 እና ለአልጋ ብር 146,697.41 ተከፍሎ ሳለ የደመወዝ መጠን, መነሻና መድረሻ ቦታና ሰአት ሳይገለጽ በተጨማሪ በሂሣብ መደብ 6233 የ9 ቀን ውሎ አበል ብር 156,475.00 ለታሳታፊዎች የተከፈለ መሆኑ፣በአፋር ክልል የዓለም ቱሪዝም ሲከበር (መስከረም 17/2007 ዓ.ም ለ9 ቀናት) ለተሳታፊዎች የምግብ አገልግሎት በብር 797,425.17 እና ለአልጋ ብር 637,115.58 ተከፍሎ ሳለ የደመወዝ መጠን, መነሻና መድረሻ ቦታና ሰአት ሳይገለጽ በተጨማሪ በሂሣብ መደብ 6233 የ9 ቀን ውሎ አበል ብር 352,668.00 ለታሳታፊዎች የተከፈለ መሆኑና ከውሎ አበል በተጨማሪ ለ10 የሚዲያ ባለሙያዎች(ጋዜጠኞች) ብር 10,000.00 የቆዩበት ቀን ሳይገለጽ ውሎ አበል መከፈሉ፣

- በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን በድምሩ ብር 574,860.00 የተከፈለው የውሎ አበል ሂሳብ፣ የውሎ አበል መክፈያው ሰነድ የመነሻና መድረሻ ቦታና ሰአት፣ የደመወዝ መጠን፣ በየቦታው ለቁርስ ምሳና እራት(ለአዳር) የተደረሰበትን ቦታ የማያመለክት በመሆኑ እና የቀን ውሎ አበል ብር 168.50 ሲከፈል ተመኑ ባለመታወቁ በአጠቃላይ ለእያንዳንዱ ሠራተኛ ሊከፈል የሚገበውን የውሎ አበል መጠን ለማወቅ አለመቻሉ፣ ለእያንዳንዱ ሠራተኛ ብር 200.00 ለአልጋ ሲከፈል ተመኑ(ታሪፉ) ምን እንደሆነ አለመታወቁ፣ ለእያንዳንዱ ሠራተኛ 30% የበረሀ አበል ሲከፈል በጉዞው ላይ የበረሀ አበል የሚያስከፍለው ቦታና ጊዜ ሳይለይ ለሁሉም ቀናት የበረሀ አበል በመከፈሉ ሊከፈል የሚችለውን የበረሀ አበል ለማስላት አለመቻሉ መታወቁ፣
- የመንግስት የፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ ለ 12 የጥናትና ምርምር ጽሑፍ ለሰሩ ተመራማሪዎች የ 21 ቀን የወሎ አበል ክፍያ ብር 48,384.00 (ለ 12 ሰው × 192 × 21) የቀን ውሎ አበል ከፍሎ ሳለ በተጨማሪ የምግብ እና አልጋ በሂሣብ መደብ 6231 ብር 29,787.18 መክፈሉ እና እና ተሳታፊዎቹ 21 ቀን ያህል የጥናትና ምርምር ጽሑፍ ሲሰሩ ለመቆየታቸው የሰዓት መቆጣጠሪያ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

- በቤተመንግስት አስተዳደር የውሎ አበል መጠየቂያ፣ መፍቀጃና መክፈያ እንዲሁም ሲመለሱ የቀን ውሎ አበል ክፍያ መቆጣጠሪያና የሥራ ክንውን መመዝገቢያ ቅጽ ሳይሞላ ወደ ዋናው ቤተመንግስት ለስልጠና ለመጡ ሠራተኞች ብር 198,146.00 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- በመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 24305 የአውደ ጥናቱ ወይም የግንዛቤ ማስጨበጫዉ ተሳታፊዎች ቁጥር የተገለጸ ቢሆንም የተሳታፊዎች ስም ዝርዝር፣ የሰአት መቆጣጠሪያና የስብሰባውን ቀን ብዛት የሚያሳይ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 38,510.84 በመከፈሉ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣

አሰራሩ ስራዎች በመደበኛ የስራ ሰዓት እንዳይሰሩ የሚገፋፋና ያልተፈቀዱ ክፍያዎችን በመፈፀም መንግሥትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል በመመሪያው መሰረት መስራት ወይም የሚመለከተውን ክፍል ማስፈቀድ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4 <u>የክፍያ ሂሳብ</u>

ለባለመብቶች (ለዕቃና ለአገልግሎት አቅራቢዎች) ወጪ ሆነው የተከፈሉት ክፍያዎች በደንብና በመመሪያ መሰረት መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ8 መ/ቤቶች ለባለመብቱ በባንክ በኩል መተላለፍ ሲገባ በተለያዩ ጊዜና የክፍያ ሰነዶች በድምሩ ብር 4,770,457.32 በክፍያ መመሪያ ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ በጥሬ ገንዘብ ወይም በቼክ ወጪ የተደረገ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ-5/ሐ ተመልክቷል/

እነዚህ የተመለከቱት የአከፋፈል ግድፈቶች በድጋሚ እንዳይደርሱ ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል።

3.5 <u>የሥራ ግብርና ቅድመ ግብር ያልተቀነሰለት ወጪ</u>

የቤት አበል ከተከፈሉ ክፍያዎች ላይ የሥራ ግብር መቀነሳቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል በበጀት ዓመቱ ከተከፈለ የቤት አበል (ለዋና ዳይሬክተር) ላይ ብር 6,300.00 የሥራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ፣
- በኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን ለዋና ዳይሬክተሮች ከተፈቀደው ብር 1,500.00 ወርሀዊ የቤት አበል በበጀት ዓመቱ ከተፈጸመው የቤት አበል ክፍያ ላይ ብር 3,675.00 (ብር 1,500X35% X 7ወር) የሥራ ግብር ተቀናሽ አለመደረጉ፣
- በኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን ለሎደር ኪራይ ከከፈለው ተከፋይ ሂሳብ ብር 18,000.00 ላይ ቅድመ ግብር (Withholding tax 2%) ብር 360.00 አለመቀነሱ፣
- በሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር የዓመት ፈቃድ ክፍያ ሲከፈል መቀነስ የነበረበት ብር 2,963.91 የስራ ግብር አለአግባብ ተከፍሎ መገኘቱ፣

ታውቋል።

መ/ቤቶች መንግስት እንዲሰበስቡ ኃላፊነት የጣለባቸውን የሥራ ግብር ተቀናሽ አለመሰብሰባቸው ተጠያቂነትን ሊያስከትል ስለሚችል እና በመንግስት ገቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ስለሚችል ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ቀንሰው ማስቀረት ያለባቸውን ሂሳቦች በወቅቱ ቀንሰው እንዲያስቀሩ ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል።

3.6 <u>የሂሳብ ማስተካከያን በተመለከተ</u>

የሂሳብ ማስተካከያ ሲሰራ የሚጠቃቀስ መሆኑን (መጀመሪያ የተሳሳተውን ምዝገባ የሚያሳይና በትክክል ሊስተካከል እንደሚገባው ገላጭ መሆኑን) ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የቤተ መንግስት አስተዳደር ለብር 57,103.16 የሂሳብ ማስተካከያ ሲሰራ መነሻ ሰነዱ ያልተጠቃቀሰ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ መጀመሪያ በወጪ ያልተመዘገበ ሂሳብ ማስተካከያ ሊሰራለት ስለሚችል ትክክለኛው ወጪ ሊቀነስ ወይም የማስተካከያ ድግግሞሽ ሊኖር ስለሚችል ለወደፊቱ የሚሰሩ የማስተካከያ ሂሳቦች ከመጀመሪያው ምዝገባ ሰነድ ጋር ሊጠቃቀሱ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል።

3.7 በበጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ የተፈፀሙ ክፍያዎች

- በኢትየጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን በተለያዩ 4 ክፍያዎች ብር 143,836.34 ወጪ ሆኖ ሲከፈል በበጀት ክፍሉ በጀት ስለመኖሩ በፊርማ ሳይረጋገጥ መሆኑ፣
- በኢትዮጰያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል በተለያዩ 9 ክፍያዎች ብር 185,079.90 ወጪ ሆኖ ሲከፈል በበጀት ክፍሉ በጀት ስለመኖሩ በፊርማ ያልተረጋገጠ መሆኑ፣
- የብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ በጀት ስለመኖሩ በፊርማ ሳይረጋገጥ በተለያዩ 20 ክፍያዎች ብር 484,288.00 ክፍያዎች የተፈጸሙ መሆኑ፣
- የመንግስት የፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ በተለያዩ 9 ክፍያዎች በድምሩ ብር 1,435,467.17 በጀት ለወጪው ስለመያዙና በርዕሱ ተራፊ በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ክፍያዎች የተፈጸሙ መሆኑ፣
- በመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ በተወሰኑ የወጪ ማስመስከሪያዎች ላይ በድምሩ ብር 148,348.84 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በጀት ስለመኖሩ እና ስለመፈቀዱ በሚመለከተው ክፍል ሳይረጋገጥ ክፍያዎች የሚፈጸሙ መሆኑ፣
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ፣ብር 51,375.95 የያዙ አራት የወጪ ቫውቸሮች በጀት ስለመኖሩ በሚመለከተው ኃላፊ ሳይፈረምባቸው ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፤
- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፤ በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ እና ሳይረጋገጥ ብር 25,020.36 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፤

ታውቋል።

የተፈቀደ በጀት ሳይኖር ወይም ተፈቅዶ በጀቱ ባለቀ ርዕስ ክፍያ ሊፈጸምና ሊያስጠይቅ ስለሚችልመ ለወደፊቱ ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት በሚመለከተው አካል ሊፈቀድ እንዲሁም በበጀት ክፍሉ በጀት ስለመኖሩ በፊርማ ሊረጋገጥ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.8 <u>በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ</u>

በተመዘገቡ ሂሳቦች ላይ የተመለከተው የገንዘብ መጠን ለምዝገባ መነሻ ከሆኑት ሰነዶች ጋር እኩል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የወሊጋ ዩኒቨርስቲ በተለያዩ 3 የክፍያ ምስክር ወረቀቶች (Payment Certificates) ከተሰራው ሥራ በላይ ብር 1,527,392.56 በብልጫ ክፍሎ መገኘቱ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ ሂሳቦችን ሳያጣሩ ክፍያ መፈፀም የመንግስትን ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍትና ተጠያቂነትን ሊያስከትል ስለሚችል ጉዳዩ ተጣርቶ በሚገኘው ውጤት መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ ሆኖ ለወደፊቱ ተመሳሳይ የአሰራር ግድፈት እንዳይደርስ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.9 <u>በስራ አመራሩ የተወሰነ ወርሃዊ የስልክ ጣሪያ አለመኖሩ፣</u>

በኢትዮጲያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል እና በመንግስት የፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ የመስሪያቤቱ የተለያዩ ኃላፊዎች ለሚጠቀሙባቸው መደበኛ ስልኮች በስራ አመራሩ የተወሰነ ወርሃዊ የስልክ ጣሪያ አለመኖሩ በመታወቁ የስልክ ፍጆታ ሂሳብ ለመስርያቤቱ ሥራ ስለመዋሉና ስለአለመዋሉ ለመከታተል አስቸጋሪ በመሆኑ ለየሥራ ኃላፊዎች የስልክ ፍጆታ ጣሪያ አለመወሰኑ በመንግስት ውስን ሀብት ላይ ብክነት ሊደርስ ስለሚችል ከላይ በተመለከተው የበጀት ዝግጅትና ግምገማ ደረጃ /ስታንዳርድ/ መሰረት ለእያንዳንዱ የስራ ኃላፊ የስልክ ፍጆታ ጣሪያ ተወስኖ ሊተገበር እንደሚገባ በላክነው በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.10 <u>ተጨማሪ ጉዞና ክፍያ ስለማስፈለጉ ለበላይ ኃላፊ ሳይቀርብና ሳይፈቀድ ከዉል በላይ የተከፈለ</u>

በኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል ተጨማሪ ጉዞና ክፍያ ስለማስፈለጉ ለበላይ ኃላፊ ሳይቀርብና ሳይፈቀድ ከዉል በላይ ለትራንስፖርት አገልግሎት ብር 12,000.00 ክፍያ በመፈጸሙ፣ በውል የሚፈጸሙ ክፍያዎች በውላቸው መሰረት መፈጸማቸው የማይረጋገጥ ከሆነ የመንግሥት ገንዘብ (ሀብት) ያለአግባብ ወጪ ሊሆን ከመቻሉም በላይ ሊያስጠይቅ ስለሚችል ጉዳዩ ተጣርቶ በሚገኘው ውጤት

መሰረት ተገቢ የሆነ እርምጃ ሊወሰድ የሚገባ መሆኑንና ለወደፊቱ ተመሳሳይ አሰራር ግድፈት እንዳይደርስ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ተገቢው ማጣራት ሊደረግ እንደሚገባበላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.11 <u>በስራ አመራሩ ከተወሰነው ወርሃዊ የስልክ ጣሪያ በላይ የተፈጸመ ክፍያ</u>

በብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ በስራ አመራሩ ከተወሰነው ወርሃዊ የስልክ ጣሪ.ያ በላይ በበጀት ዓመቱ ብር 49,306.29 ክፍ.ያ ተፈፅሞ በመገኘቱ ከስልክ ሂሳብ አጠቃቀም አስቸጋሪነት ባህሪ አንጻር ከተወሰነው ጣሪያ በላይ ሲከፈል ቁጥጥር የማይደረግ ከሆነ የመንግሥት ገንዘብ ያለ አግባብ ወጪ ሊሆን ስለሚችል ለእያንዳንዱ ስልክ ተጠቃሚ ኃላፊ ከተደለደለው ጣሪያ በላይ የተከፈለው የስልክ ሂሳብ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ ሆኖ ለወደፊቱ ተመሳሳይ የአሰራር ግድፈት እንዳይደርስ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ተገቢው ማጣራት ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.12 <u>የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ክፍያ</u>

- በብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ ለሞባይል ካርድ በተለያዩ 35 ክፍያዎች በጥሬ ገንዘብ ብር 15,600.00 ያለ ወጪ ማስረጃ ክፍያ መፈጸሙ፣
- በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ለሞባይል ካርድ በተለያዩ ሁለት ክፍያዎች በጥሬ ገንዘብ ብር 7,100.00 ያለ ወጪ ማስረጃ ክፍያ መፈጸሙ፣
- በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በደሴ ቅ/ጽ/ቤት ለመስተንግዶ ወጪ ሆኖ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 612496 ለተከፈለው ብር 73,109.64 ሂሳቡ ወጪ የተደረገበት የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ዋናው (ኦሪጅናሉ) እና ደጋፊ የወጪ ማስረጃዎች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የክፍያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ መታወቁ፣

በመታወቁ ውስን የሆነው የመንግስት የፋይናንስ ሀብት ለብክነት ሊዳረግ ስለሚችልና ለመ/ቤቱ አገልግሎት ያልዋሉ ወጪዎች ሊመዘገቡ ወይም ወጪው

ሁለት ጊዜ ሊመዘገብ እንደሚችል፣ ስለሚችል በጥሬ ገንዘብ ለሞባይል ካርድ ወጪ ሆኖ የተከፈለውን ሂሳብ በተመለከተ ለሂሳቡ (ለስልክ ፍጆታ) አገልግሎት የወጪ ማስረጃ ሊቀርብ ስለሚገባው በጥሬ ገንዘብ ለመክፈል ስለማይቻል ገንዘቡ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ ሆኖ ለወደፊቱ ተመሳሳይ የአሰራር ግድፈት እንዳይደርስ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባና ለወደፊቱ ማንኛውም ወጪ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት አስፈላጊ የሆኑ የወጪ ማስረጃዎች ሁሉ ተሟልተው መቅረባቸው ሊረጋገጥ የሚገባ ሲሆን ከላይ የተመለከተውን የመስተንግዶ ሂሳብ በተመለከተ በውስጥ ኦዲት ተጣርቶ በውጤቱ መሰረት እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በላክነው በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.13 የተሰረዙ (Void) የተደረጉ ቼኮች ከመዝገብ ሳይሰረዙና ሌሎች ቼኮች ተዘጋጅተው በመዝገብ ላይ አለመመዝገባቸው፣

በብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ ብር 443,976.77 የያዙ የተለያዩ 5 ቼኮች ተሰርዘው (Void) ተደርገው ሳለ ከመዝገብ ሳይሰረዙ ሌሎች ቼኮች መዘጋጀታቸውና በመዝገብ ላይ አለመመዝገባቸው በመታወቁ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ የተደረገውን ምዝገባ ተዓማኒነት ሊያሳጣው እና የተሰረዙ (Void) ቼኮች ከሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ካልተሰረዙ ሊያሳስቱ ስለሚችሉ በልዩ ልዩ ምክንያት ተመላሽ ተደርገው የተሰረዙ (Void) ለተደረጉ ቼኮች በቅድሚያ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራላቸው ከተደረገ በኋላ ሌላ ቼክና የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ተዘጋጅቶ በሚመለከተው ኃላፊ ተፈርሞ የሂሳብ ምዝገባ እንዲከናወንለት ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.14 አላግባብ ለቅጣት የተከፈለ የወጪ ሂሳብ

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከኢትዮጵያ አየር መንገድ የትራንስፖርት አገልግሎት ሲያገኝ የትኬት መቁረጫ በትክክለኛው ሰአት ጉዞው ባለመከናወኑ ምክንያት የጉዞ መሰረዣ ለኢትዮያ አየር መንገድ ብር 8,029.00 በመከፈሉ ውስን በሆነው የመንግስት የፋይናንስ ሀብት ላይ ብክነት ሊደርስ ስለሚችል ክፍያው ተገቢነት የሌለው ክፍያ መሆኑን በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.15 በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ገቢ ያልተደረገ

- የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ለጽህፈት መሳሪያ ወጪ ሆኖ ከተከፈለው ብር 62,790.00 ውስጥ በብር 36,400.00 የተገዛው/የታተመ የማስታወሻ ደብተር እና አስክሪብቶ (ቁጥራቸው 700) በሞዴል 19 ገቢ አለመደረጉ፣
- በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ከቶታል ኢትዮጵያ አክሲዮን ማህበር በብር 367,568.80 የተገዛ 21,040 ሊትር ናፍጣ የእቃ ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት ክፍያ ተፈጽሞ በመገኘቱ፣

የተገዙት ንብረቶች ለመንግስት ሥራ አገልግሎት ላይውሉ ስለሚችሉ መ/ቤቶቹ ክፍያ የተገዙት ንብረቶች ለመንግስት ሥራ መዋልና አለመዋላቸው ተረጋግጦ በሚገኘው ውጤት መሰረት ተገቢ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ ሆኖ ለወደፊቱ ተመሳሳይ የአሰራር ግድፈት እንዳይደርስ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.16 ተሽከርካሪ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር እየተመዘገበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ የማይቀርብ መሆኑ፣

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር መጠን ጋር እየተመዘገበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ የማይቀርብ መሆኑ፣ (በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሚገኙ 29 ተሽከርካሪዎች የሁለት ወር ብቻ ማለትም የሚያዚያና የግንቦት ወር/2007) ብቻ በመቅረቡ በመመሪያው መሰረት እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር መጠን ጋር እየተመዘገበ ሪፖርት የማይቀርብ ከሆነ በነዳጅ ላይ ብክነት ሊደርስ ከመቻሉም በተጨማሪ መመሪን አክብሮ አለመስራት ሊያስጠይቅ ስለሚችል በመመሪያው መሰረት እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር መጠን ጋር እየተመዘገበ ሪፖርት እየቀረበ በሪፖርቱ መሰረት ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.17 ያለአግባብ የተከፈለ ሂሳብ

- የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጽ/ቤት፣ ከመ/ቤቱ በዝውውር ወደ ሌላ መ/ቤት ለሄዱ ሰራተኛ የአንድ ወር ደመወዝ ብር 2,366.00 ተከፍሏቸው መገኘቱ፣

- ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ፤ ከዩኒቨርስው እውቅና ውጪ ለተከናወነ ግንባታ አላግባብ ብር 113,594.10 መከፈሉ፣
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ፤ ከመ/ቤቱ ለተሰናበቱ ሁለት ሠራተኞች አለአግባብ የተከፈለ የዓመት ፈቃድ ብር 1,602.92 መገኘቱ፡፡
- የደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፤ ከውስጥ ገቢ በጀት ሳይኖር እና በቦርድ ሳይፈቀድ ገቢ አመንጪ ላልሆነ ተግባር ለመንቆረር ኢንተርፕራይዝ በጀት ድጋፍ ብር 8,100,000፣ ለደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ እግር ኳስ ክለብ ሥራ ማስኬጃ ብር 1,132,938.48 በድምሩ ብር 9,232,938.48 ተከፍሎ መገኘቱ፤
- የደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፤ያለአግባብ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 747,574.31 መገኘቱ፤
- በሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር በብር 26,1525.00 በአውሮፕላን ለተደረጉ ጉዞዎች የቀረበው የትራንስፖርት ደረሰኝ የተጓዡን ስም የተጓዘበት ቀን የት አገር እንደሚሄድ የማይገልጽ በመሆኑ በተጓዡ የስልጣን ደረጃ ላይ የተመሰረተና በትክክል ለተገኘ አገልግሎት የተከፈለ መሆኑን ለማረጋገጥ አለመቻሉ፡፡

በመታወቁ አላግባብ ክፍያዎችን መፈጸም ውስን በሆነው የመንግስት የፋይናንስ ሀብት ላይ ብክነት ሊደርስ ስለሚችል የሚከፈሉ ክፍያዎች አግባብነት ያላቸው መሆኑ ተጣርቶ ሊሆን እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4. <u>ተከፋይ ሂሳብ</u>

4.1 <u>በወቅቱ ያልተከፈሉ ተከፋዮች</u>

በሂሳብ መግለጫው ላይ የተመለከተው የተከፋይ ሂሳብ የመ/ቤቱ ትክክለኛ እዳ መሆኑንና ሂሳቡም ትክክለኛ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ; በ11 መ/ቤቶችና በ5 የገ/ጉ/ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 617,270,855.60 በወቅቱ ያልተወራረደ/ ያልተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-31 ተመልክቷል/

ተከፋይ ሂሳቦችን በወቅቱ አለማወራረድ ለብልሹ አሰራር ወይም ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ስለሚችል ለየመ/ቤቶቹ በተከፋይ ሂሳብ ላይ ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግና

በመክፈያ ጊዜያቸው ክፍያ በመፈፀም ተገቢው ምዝገባ እና ማስተካከያ ሊሠራ እንደሚገባ በላክናቸው የስራ አመራር ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

4.2 ያልተመዘገበ የተከፋይ ሂሳብ

መመዝገብ ያለባቸው ተከፋይ ሂሳቦች በትክክል የተመዘገቡ መሆኑ ሲጣራ በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፤ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ከሚገነቡ ግንባታዎች ክፍያ ላይ ከተለያዩ ኮንትራክተሮች የተቀነሰ በድምሩ ብር 2,995,104.05 የመያዣ ሂሳብ በተከፋይ ሂሳብ (5061) መመዝገብ ሲገባው ያልተመዘገበ መሆኑ በመታወቁ የተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ የመ/ቤቱን ትክክለኛ የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊያሳይ ስማይችል ለሂሳቡ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድለት በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5. በጀት

5.1 የገቢ በጀት

የገቢ ሂሳብ በበጀት ዓመቱ ለመሰብሰብ በታቀደው ልክ መሰብሰቡን ለማረጋገት ኦዲት ሲደረግ፣

- የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በበበጀት ዓመቱ ከተለያዩ ገቢ ማስገኛ የስራ ዘርፎች ለመሰብሰብ ካቀደው ብር 399,925,000.00 ውስጥ የሰበሰበው ብር 283,301,451.18 (70%) መሆኑ፣

- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሁለት የገቢ ሂሳብ መደቦች በእቅዱ መሰረት ያልተሰበሰበ ብር 61,169,090.32 መኖሩ፣

በመታወቁ የመ/ቤቶች የገቢ እቅድ ከልማት እቅድ ጋር ባለው ትስስር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ስለሚችል መ/ቤቶቹ ለመሰብሰብ ያቀዱትን ገቢ ለመሰብሰብ ጥረት እንዲያደርጉ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበዋል፡፡

5.2 የወጪ በጀት

5.2.1 በጀት ሳይያዝ የተፈጸሙ ክፍያዎች

የመንግስት የፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ ለማስተርስ ዲግሪ ትምህርት ለሚማሩ ኃላፊዎች በጀት ሳይያዝ በድምሩ ብር 454,342.50 ክፍያ መፈጸሙ በመታወቁ በጀት ሳይያዝ ክፍያ መፈጸም ለሌች ለኤጀንሲው ተልዕኮ ማስፈጸሚያ ሥራ በተያዙ በጀቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ከመቻሉም በላይ መመሪያን አክብሮ አለመስራት ሊያስጠይቅና ስለሚችል የኤጀንሲው ዓመታዊ ዕቅድ በጥናት ላይ የተመሰረተ ሊሆን፣ በበጀት ዓመቱ ያልታቀደ ሥራ ለመስራት እድሉ ከተገኘ በበጀት አስተዳደር አዋጅ መሰረት የተጨማሪ በጀት ጥያቄ ለሚመለከተው አካል አቅርቦና አስፈቅዶ ሊያከናውን እንደሚገባ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.2.2 ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ኦዲት ሲደረግ፣ በ7 መ/ቤቶች በመደበኛ በጀት ብር 243,496,308.86 እና ካፒታል 16,122,942.00 በድምሩ ብር 259,619,250.88 ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ መሆኑ ታውቋል፡፡

የበጀት አዋጅችና ደንቦችን አክብሮ ለመስራት ካለማስቻሉም በላይ በሕግ ሊያስጠይቅ ስለሚችል የተጨማሪ በጀት ወይም የበጀት ዝውውር ጥያቄ አቅርቦና አስፈቅዶ ያጋጠመን የበጀት እጥረት መቅረፍ እንደሚገባ ለየመ/ቤቶቹ በላክነው ሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል።

5.2.3 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ሥራ ላይ ማዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ16 መ/ቤቶች መደበኛ ብር 188,493,576.88 እና ካፒታል 171,575,457.15 በድምሩ ብር 360,069,034.03 በበጀት ዓመቱ ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም መንግስት ለሌሎች መሠረታዊ ለሆኑ ሥራዎች ሊያውል የሚችለውን ገንዘብ በበጀት ዓመቱ ስራ ላይ እንዳይውል ሊያደርግ ስለሚችል የበጀት ዝግጅት ጥያቄ መ/ቤቶች ሲያቀርቡ በተጨባጭ ሊሰራ ከታቀደው ተግባር ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ያለፉትን ዓመታት የዕቅድ አፈፃፀም በመገምገም ሊከናወን የሚገባ ሲሆን ለወደፊቱም የበጀት ጥያቄ ሲቀርብ ከእቅድ ጋር እየተገናዘበ የሚቀርብበት ሁኔታ እንዲመቻች በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6. <u>የንብረት ሂሳብ</u>

6.1 <u>የንብረት አስተዳደርና አጠባበቅ ሁኔታ</u>

- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር የ2007 በጀት ዓመት ዓመታዊ የቋሚና የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ቆጠራው ከንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ ጋር ያልተመሳከረ መሆኑ፣
- በፕሬዚደንት ጽ/ቤት የንብረት ሂሳብን በተመለከተ፣

- የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና ስቶክ የመረከብ ሀላፊነቶች በአንድ ሠራተኛ ተደርበው እየተሠሩ መሆኑ፣
- በጽ/ቤቱ ስቶር ውስጥ የመቆጣጠሪያ ቢን ካርድ የሌለ መሆኑ፣
- በጽ/ቤቱ ውስጥ ያሉ ቋሚ ንብረቶች አልፎ አልፎ መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ እና የ2007 በጀት ዓመት የቋሚና የአላቂ ዕቃዎች
- ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም የቆጠራው ውጤት ከንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ ጋር ያልተመሳከረ መሆኑ፣

- በኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል ዓይነታቸው 98 የሚደርሱ ንብረቶች (ለምሳሌ የፅህፈት ጠረጴዛ፣ ኮምፒውተር ማስቀመጫ፣ የሻይ፣ የወተትና የቡና ሲኒ ማስቀመጫ፣ የጠረጴዛ ቢላዋ፣ ፔርሙዝ፣ የሻይ ሲኒ, የቡና ሲኒ, የፕላስቲክ ወንበር, የለስላሳ ሳጥን ባዶ እና ኒኬል ኩባያ ወዘተ...) የሆኑና ቁጥራቸው የተለያዩ ንብረቶች በንብረት ክፍል ዉስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
- በወለጋ ዩኒቨርስቲ በ2007 በጀት ዓመት ባደረገው የንብረት ቆጠራ 3 LCD ፕሮጀክተር, 1 DELL ኮምፒዩተር, 2 ላፕቶፕ ኮምፒዩተር, 1 የቴቪ ዲኮደር በሠራተኞች ወጪ ተደርገዉ በቆጠራ ወቅት አለመገኘታቸው፣

- በቤተ መንግስት አስተዳደር ለሚገኙ ቅርሳቅርሶችና፣ ጌጣጌጦች እንዲመዘገቡና በየጊዜው ቆጠራ እየተደረገ በውጤቱ መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ የተሰጠውዬኦዲት አስተያየት ፣

- በቅርስና ጥናት ጥበቃ ባለስልጣን የ2007 በጀት ዓመት የቋሚና የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም የቆጠራው ውጤት ከንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተመሳከረ መሆኑ፣

- በብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፣ ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ ሲናበብ በሁለቱም ላይ ዜሮ ሚዛን (ባላንስ) ቢያሳዩም የሞዴል 19 ገቢ እና የሞዴል 22 ወጪ የሆኑት ንብረቶች በስቶክ ካርድ ላይ እንደማይመዘገቡ እና መኪናዎች ከተጠገኑ በኋላ አሮጌ እቃዎች ተመላሽ የማይደረጉ መሆኑ፣

- በመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የ2007 በጀት ዓመት የቋሚ እና የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑንና ባለፈው በጀት ዓመት የ2006 የቋሚ እና የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ አለመደረጉ ተገልጾ የኦዲት ማሻሻያ ሀሳብ የተሰጠ ቢሆንም ግድፈቱ አለመታረሙ፣

- በኢትጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ቆጠራው መዝገብ ከሚያሳየው ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተመዛዘነ መሆኑና ለቋሚ ንብረቶች ለሁሉም መለያ ቁጥር (ኮድ) ያልተሰጠ መሆኑ፣

- በመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰራተኛ ተደርበው የሚሰሩ መሆኑ፣ በመጋዘን (በስቶር) ውስጥ የመቆጣጠሪያ ቢን ካርድ በከፊል የሌለ ሲሆን ሰቶክ ካርድ ግን ሙሉ በሙሉ የሌለ መሆኑና የ2007 በጀት ዓመት የቋሚና የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ቆጠራው የንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ ከሚያሳየው ከወጭ ቀሪ ጋር ያልተመሳከረ መሆኑ፣

- በሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር ቢን ካርድ ያልተዘጋጀና የ2007 በጀት አመት የንብረት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፣

- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የፅህፈት ጠረጴዛዎች፣ ኮምፒውተር ከነተጓዳኝ ዕቃዎች ፣ተሽከርከሪ ወንበሮች፣ ፕሪንተር፣ የእንጨት ሸልፍ፣ የመሳሰሉት ንብረቶች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤

- በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፤ለአብዛኞቹ ቋሚ ንብረቶች ምዝገባ ያልተከናወነ መሆኑ፤ቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤
- በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ፤በሰኔ /2007 ዓ.ም. መጨረሻ በዩኒቨርስቲዉ የንብረት ቆጠራ ኮሚቴ በተደረገው ቆጠራ ብር 264,588.20 ዋጋ ያላቸው የተለያዩ ቋሚ እቃዎች ተገኝተው ያልተቆጠሩ መሆኑ፤
- በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፤ በተለያየ ወቅት ከአማራ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት የገዛቸው 11 የመኖሪያ ህንፃዎች ኮንደምኒየም ቤቶች በንብረት ክፍል በኩል የገቢ ሰነድ የሌላቸውና እና በማን ስም ወጪ እንደተደረጉ እንዲሁም ያሉበትን ሁኔታ የሚገልፅ መረጃ የሌለ መሆኑ፤ህንፃዎችና ግንባታዎች በንብረት ቆጠራው ውስጥ ያልተካተቱ መሆኑ፤ከአማራ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት የተገዙት የመኖሪያ ቤቶችና ግንባታቸው ተጠናቅቆ ርክክብ የተፈፀመባቸው ህንፃዎች በንብረት መዝገብ ላይ ያልተመዘገቡ መሆኑ፣
- በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፤ሶስት የዩኒቨርሲቲውን ሰራተኞች ኮምፒዩተሮችና የቢሮ መገልገያዎችን ሳያስረክቡ የለቀቁ መሆኑ፣

በንብረት ሂሳብ ላይ ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ በንብረቶች ላይ የሚፈጸምን ጥፋት በወቅቱ ለማግኘት ስማያስችልና ለብልሹ አሰራር በር ለከፈት ስለሚችል ከላይ በተመለከቱት የንብረት አስተዳደር ድክመቶች ላይ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል።

6.2 <u>የንብረት አወጋገድን በተመለከተ</u>

- በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣንና አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ብዛት ያላቸው በቁጥር ያልተለዩ ካሜራዎች, ላፕቶፖች, ፎቶ ኮፒ ማሽን, ኮምፒዩተሮች, ጂፒኢስ፣ ጎማዎች, ቆርቆሮዎች, የመኪና መለዋወጫዎች እና የተለያዩ ልዩ ልዩ እቃዎች በንብረት ክፍል ተከማችተው መገኘታቸው፣
- በብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተ መጻህፍት ኤጀንሲ የተለያዩ ዓይነትና ብዛት ያላቸው (ለምሳሌ 9 የማባዣ ቀለሞች ፣ 3 የፎቶ ኮፒ ቀለም፣ 1 ዶት ማትሪክ ፕሪንተር፣ 1 ዲጂታል ሳተላይት ሪሲቨር፣ 1 CHANGH +NG ቴሌቭዥን፣ 1 የማባዣ ማሽን፣ 2 ሳምሶናዊት፣ 1 ቬንትሌተር፣ ወንበሮች፣ ጠረንጴዛዎች፣ 1 የፎቶ ኮፒ ማሽን፣ የተለያዩ ኮምፒውተሮች፣ 1

ታይፕራይተር፣ 1 የግድግዳ ሰአት፣ 1 ማንበቢያና ማሳያ፣ 3 መሰላሎች፣2 የአትክልት ማዞሪያ ጋሪ፣ ዩፒኤሶች፣ 2 ምንጣፍ፣ በርከት ያሉ መጋረጃዎች፣ በርከት ያሉ ጋዜጦች፣ 1 ሉል፣ እስቴፕለሮች፣ ፓንቸር፣ የስፒልና የወረቀት ትሪ፣ ማከፋፈያዎች ፣ ካታሎግ ካርድ ማስቀመጫ ብረቶች ፣የውሃ መሳቢያ ጎማዎች፣ 1 የኤሌትሪክ ቦርድ፣ የመኪና ባትሪውችና ጎማዎች እና የመሳሰሉት) ንብረቶች በንብረት መጋዘን ዉስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

- በባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር 4 አገልግሎት የማይሰጡ ፕሪንተሮች, 2 አገልግሎት የማይሰጡ ፒሲ ኮምፒዉተሮች, አንድ ሙሉ አሮጌ ሶፋ, 2 የማይሰሩ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች, 10 አገልግሎት የማይሰጡ ወንበሮች, 1
- ተገጣጣሚ አገልግሎት የማይሰጥ ጠረጴዛ, አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ንብረቶች ከአዲሶቹ ጋር የተቀላቀሉ መሆኑ፣
- በፌዴሬሽን ምክር ቤት አገልግሎት የማይሰጡ ብዛት ያላቸው 160 የተለያዩ ጎማዎች፣ዴስክ ቶፕና ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች፣ የፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ጠረጴዛዎች፣ ወንበሮች፣ የመኪና መለዋወጫዎች፣ 1 ጄኔሬተር፣ ምንጣፎች፣ መጋረጃዎች፣ አንሶላዎች፣ የስልክ ቀፎዎች፣ ብዛት ያላቸው ፕሪንተርና የፎቶ ኮፒ ቀለሞች የተለያዩ የህትመት ውጤቶችና እና ብዘት ያላቸው የኤሌትሮኒክስ ዕቃዎች እንዲሁም ብዛት ያላቸው ልዩ ልዩ ዕቃዎች መገኘታቸው፣
- በኢትጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን ዓይነታቸው 69 የሚደርሱ ንበረቶች የሚወገዱትና የማይወገዱት ሳይለዩ (ለምሳሌ አዲስ የመኪና ጎማ፣ የእንግዳ ወንበር እና ትልቅ ቦርሳ (የእንጨት መስንጠቂያ) ወዘተ...) ቁጥራቸው የተለያዩ ንብረቶች በንብረት ክፍል ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
- በመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት አገልግሎት መስጠት የማይችሉ በቁጥር ያልተለዩ፣ ዴል ኩምፒተሮች፣ ሞኒተሮች፣ ሞተር ሳይክል፣ ፕሪንተሮች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ ካኖን ፋክስ ማሽን፣ ሶኒ ቴሌቪዥን፣ ሲዲ ቴፕ እና የተለያዩ ንብረቶች በንብረት ክፍል ውስጥ ተከማችተው የተገኙ መሆኑ፣
- በማእከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በደሴ ቅ/ጽ/ቤት ንብረት ክፍል ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ 92 ጎማዎች፣ 2 ኮምፒውተሮች እና 122 ፓኮ እስክሪፕቶዎች መገኘታቸው፣

- በሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር የሚወገዱ ንብረቶች ከአዲስ እና አገልግሎት መስጠት ከሚችሉ ንብረቶች ጋር ተደባልቀው የተቀመጡ መሆናቸው እና በሚወገድ ንብረት ዝርዝር ውስጥ ዝርዝራቸው ያልተካተቱ 45 ጎማዎች እና ሌሎች ንብረቶች መኖራቸው፣

- በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ፤አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ ንብረቶች በወቅቱ እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፣

- በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ፤በትምህርት ሚ/ር በኩል ተገዝተወ ወደ ዩኒቨርስቲው የገቡ የተለያዩ ለማስተማሪያነት የሚያገለግሉ ንብረቶች ርክክብ ያልተፈጸመላቸው መሆኑ፤

- በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት፤ በተለያዩ መጋዘኖች በርካታ ቋሚ እቃዎች ለብዙ ጊዜያት ያለአገልግሎት በመጋዘን ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፤ብዛት ያላቸው የተለያዩ ኮምፒውተሮች፣ ቶነሮች፤ ፎቶኮፒ ማሽን፤ ኤሌክተሪክ ታፕራይተር፣ ፕሪንተር፤ ኬብል፤ ረሲቨር ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፤ ቁምሳጥን፤ ሼልፍ፤ ፎቶኮፒ ማሽን፤ እና ሎሎች እቃዎች ለረጅም ጊዜ ተከማችተው ሳይወገዱ የተገኙ መሆኑ፤
- በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፤አገልግሎት የማይሰጡ 25 ፕሪንተሮች፣12 የተለያየ ኢንች ያላቸው ቴሌቪዥኖች፣65 ዴል እና አሰር ኮምፒዩተሮች ፣2 ፎቶ ኮፒ ማሽኖች እንዲሁም 6407 የመመገቢያ ሳህኖች ያለ አገልግሎት በመጋዘን ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

ንብረቶች ሳይጠገኑ በቆዩ ቁጥር በለጠ እርጅናና ብልሽት ሊዳረጉ ስለሚችሉ ለግድፈቶች ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.3 የተሽከርካሪዎች ሁኔታ

6.3.1 ያለአገልግሎት የቆሙ ተሽከርካሪዎች

- በባህልና ቱሪዝም ሚ/ር 3 መኪናዎች ከ 2 ወር - 6 ወር በላይ የቆሙ መሆኑ፣

6.3.2 <u>የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ/ በተመለከተ</u>

- በባህልና ቱሪዝም ሚ/ር 1 መኪና (ሰሌዳ ቁጥር 4-10052 ኢ.ት፣ ሊብሬ ያልቀረበለት መሆኑ፣
- በቤተመንግስት አስተዳደር የሚገኙት ተሸከርካሪዎች የሚወገዱት፣ በቅርስነት ሊጠበቁ የሚገባቸው፣ ሊብሬ የሌላቸውና ሊጠገኑ የሚችሉት ተለይተው ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ የተሰጠው የኦዲት አስተያት አለመተግበሩ፣
- የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ፤ ስድስት (6) ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት ማረጋገጫ መታወቂያ የሌላቸው መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

በመሆኑም ከላይ በተመለከቱት ተሽከርካሪዎች ላይ ተገቢው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ለየመቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

7. <u>ልዩ ልዩ</u>

7.1 በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተለያዩ ገንዘብ ሰብሳቢዎች የሰበሰቡት ገንዘብ ተጠቃሎ ወደ ባንክ ገቢ ሲደርግ በገቢ ማጠቃለያ መ/ሂ 64 መሆን ሲገባው ገቢው የሚጠቃለለው በራሱ መ/ሂ 1 የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ በመሆኑና በዚያው ደረሰኝ ገቢ የሚሰበሰብ በመሆኑ ሊስተካከል እንደሚገባው በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

7.2 <u>የገቢ ሂሳብ</u>

በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሚሰበሰበው ገቢ በትክክል የገቢ ደረሰኝ እየተቆረጠለት የሚመዘገብ መሆኑ ሲጣራ የተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 111,476.47 በገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ በታወቁ የሚሰበሰብ ገቢ ሁሉ በህጋዊ የገቢ ደረሰኝ ገቢ መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2007/08 እቅድ ክንውን

1.1 የኦዲት ዕቅድና ክንውን በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና በበጀት አንፃር

ተ ቁ.	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት ያቀረበበት ቀን	የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ከፒታል	ድምር
1	ትምህርት ሚኒስቴር		193,825,790.00	467,328,070.47	661,153,860.47
2	አዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ				
3	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ	29/02/08	779,914,935.03	977,888,352.33	1,757,803,287.36
4	ሐዋሳ ዩኒቨርስቲ	24/05/08	1,042,963,180.27	675,666,817.79	1,718,629,998.06
5	ጅማ ዩኒቨርስቲ	21/01/08	795,527,501.00	866,000,000.00	1,661,527,501.00
6	ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ	22/03/08	694,783,971.23	930,344,044.79	1,625,128,016.02
7	ጎንደር ዩኒቨርስቲ	26/01/08	830,582,191.00	628,219,341.00	1,458,801,532.00
8	ሐረማያ ዩኒቨርስቲ	20/01/08	447,731,143.00	787,762,140.00	1,235,493,283.00
9	አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	25/04/08	461,951,136.00	578,768,800.00	1,040,719,936.00
10	አምቦ ዩኒቨርስቲ	25/01/08	361940746	554298648	916,239,394.00
11	አዳማ ዩኒቨርሲቲ	18/05/08	468,592,248.75	428,578,611.97	897,170,860.72
12	ዲላ ዩኒቨርስቲ	7/3/2008	366,924,263.60	340,338,061.52	707,262,325.12
13	አክሱም ዩኒቨርሲቲ	10/5/08	295,637,514.03	385,127,660.97	680,765,175.00
14	ወሎ ዩኒቨርስቲ	29/02/08	278,881,999.00	327,900,710.00	606,782,709.00
15	አ.አ.ሳይንስና ቴ. ዩ.	25/12/07	296,447,321.02	297,787,199.02	594,234,520.04
16	አድግራት ዩኒቨርሲቲ	3/2/2008	230,736,160.00	334,155,920.00	564,892,080.00
17	ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ	25/12/07	292,251,020.00	250,500,000.00	542,751,020.00
18	መደወላቡ ዩኒቨርስቲ	4/2/2007	267,353,578.00	272,308,300.00	539,661,878.00
19	ወልድያ ዩኒቨርሲቲ	12/2/28	182,824,893.14	345,011,492.00	527,836,385.14
20	ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ	3/4/2008	202,180,677.72	295,435,100.00	497,615,777.72
21	ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ	25/01/08	265308824	232064700	497,373,524.00
22	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ	ነሐሴ/07	234,636,248.00	250,520,000.00	485,156,248.00
23	ሰመራ ዩኒቨርስቲ	24/1/2008	250,500,000.00	234,636,248.00	485,136,248.00
24	ደብረታቦር ዩኒቨርስቲ	4/12/07	170,606,302.47	300,800,140.00	471,406,442.47
25	ቡሌ-ሆራ ዩኒቨርስቲ	17/02/08	149,847,788.50	305,069,394.45	454,917,182.95
26	ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ	6/5/2008	169,618,818.00	259,185,390.00	428,804,208.00

ተ ቁ.	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት ያቀረበበት	የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
27	አሶሳ ዩኒቨርስቲ	13/01/08	91466240	245718300	337,184,540.00
28	መቱ ዩኒቨርስቲ	19/01/08	133,934,911.00	193,642,300.00	327,577,211.00
29	የመ.ና ኢ.ን.ቴክ.ሚ/ር	27/01/08	56,098,757.29	261,060,000.00	317,158,757.29
30	ሲቪል ሰ. ዩኒቨርስቲ	28/01/08	145,835,800.00	124,000,000.00	269,835,800.00
31	አገ.አቀ.የትም.ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ	16/05/08	263,444,682.00	------	263,444,682.00
32	የቴ/ሙ/ትም/ሥ/ ኢንስትቲዩት	15/0108	63150430	122653400	185,803,830.00
33	ቴ/ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ	28/03/08	75,111,277.64	106,824,467.14	181,935,744.78
34	ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚ/ር	ታህሳስ/08	80536000	56452100	139,988,100.00
35	ሳይንስና ቴክ. ሚ/ር	10/1/08	60,500,028.00	20,781,600.68	81,281,628.68
36	የትም/ስትራቴጂ ማ.	21/12/07	15,829,550.00	16,904,590.00	32,734,140.00
37	የሣይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል	24/11/07	10,801,925.00	----	10,801,925.00
38	ከፍ.ትም.ጥ/ና አ. ኤ.	5/12/07	10,576,110.00	---	10,576,110.00
39	የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት	6/1/08	5,252,649.19	----	5,252,649.19
40	ፖሊሲ ጥናት	6/2/08	29,805,409.03		

2.2. <u>የተሰጠው የኦዲት አስተያየት፣</u>

የተሰጠው ኦዲት አስተያየት ከጥቂት ስህተቶች በስተቀር አጥጋቢ በመሆኑ ነቀፌታ ያለበት (Except for opinion) 20 መ/ቤቶች፣ የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ (Adverse opinion) 16 መ/ቤቶች እና አቋም ለመውሰድ ያልተቻለባቸው (Disclaimer opinion) 3 መ/ቤቶች ናቸው፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ-2/ ሀ እስከ መ ተመልክቷል/

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣

1. የጥሬ ገንዘብ፣ ባንክና ሰነድ ሂሣብ፣

1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፦

ተ.ቁ.	የመ/ቤቱ ስም	ቆጠራ በመብለጥ	ቆጠራው በማነስ	የጥሬ ገንዘብ ጉድለት
1	በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ		19,513.21	
2	የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ			38,380.94
3	ጅማ ዩኒቨርስቲ			50,707.00
4	ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	327,433.34		
5	በሚዛን ቴፒ	74,922.55		
6	በወሎ ዩኒቨርሲቲ	449,774.37		
7	አሶሳ ዩኒቨርስቲ		23,357.44	
8	በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ግብርና ኮሌጅ		104,483.65	
9	ሀሮማያ ዩኒቨርስቲ	1,158,770.02	261,367.43	
	ድምር	2,010,900.28	408,721.73	89,087.94

ከላይ ከተመለከተው ሂሳብ ውስጥ በሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ፡ የአንድ የዕቃ ግዥ ሠራተኞች ተቀፅላ ሌጀር የተመለከተ ከወጪ ቀሪ በውስጥ ኦዲት ቆጠራ በዕቃ ግገር ሠራተኞች እጅ የተገኘ ጥሬ ገንዘብና የሰነድ ማስረጃ ድምር ጋር ሲመሳከር በ 3 የግዥ ሠራተኞች በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብና ሰነድ ብር 1,158,770.02 ብልጫ የታየ ሲሆን በ4 የግዥ ሠራተኞች ደግሞ ብር 261,367.43 በቆጠራ የተገኘው በማነስ የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡

1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች፣

- መቱ ዩኒቨርስቲ፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ፣ ሀረማያ ዩኒቨርስቲ፤የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ፣ የዲላ ዩኒቨርስቲ እና ትምህርት ሚኒስቴር በጥሬ ገንዘብ

መጠበቂያ ካዝና ውስጥ የሚገኘው ጥሬ ገንዘብ በመቁጠር የቆጠራ ውጤቱ በእያንዳንዱ ገንዘብ ያዥ ስም ከተከፈተው የጥሬ ገንዘብ ተቀጽላ ሌጀር ጋር እየተመሳከረ ከወጪ ቀሪው ትክክል ለመሆኑ ወቅታዊ ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፤

- **በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡-**
  - የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የመዝናኛ ክበብ (የገቢ ማመንጫ) ገቢ ሂሳብ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚንቀሳቀስበትን የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000062109487 ለመክፈት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በጽሁፍ ለመፍቀዱ ማስረጃ አለመቅረቡ፣
  - በእጅ ያለ ጥሬ ገንዘብ (4101) ተብሎ በሳጥን ሌጀር ላይ የሚታይ ብር በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በቆጠራ ያልተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ገንዘቡን የሚይዘው ሠራተኛ ማን እንደሆነ የማይታወቅ መሆኑ፣
  - በባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ መሠረት ባንክ ተቀናሽ ተደርጎ በባንክ ሌጀር ላይ ያልተቀነሰ ከ2005 በጀት ዓመት በፊት ጀምሮ የመጣ የብር 626,477.41 ልዩነት መኖሩ፣

1.3 በባለመብቱ የባንክ ሒሳብ በማስተላለፍ መከፈል ሲገባው በቼክና ጥሬ ገንዘብ የተከፈለ

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ሥም	በቼክ የተከፈለ	በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ
1	በመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ	76,569.76	**223,155.59**
2	በፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ	3,150,896.51	14,309.63
3	በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ	2,204,000.11	
4	በወልዲያ ዩኒቨርሲቲ		252,657.65
ድምር		5,431,466.38	490,122.87

በቀጥታ በባለመብቱ የባንክ ሂሳብ ገቢ መደረግ ሲገባው በቼክና በጥሬ ገንዘብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

1.4 በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ ሳይደረግ የሚዘገይ ሂሳብ፤

ከብር 100,000.00 በላይ፣ ከተለያዩ አገልግሎቶች የተሰበሰበው ገንዘብ ወደ ባንክ ገቢ የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፣ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ- ብር 2,585,503.68፣የሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ- ብር 218,430.00 በድምሩ ብር 2,803,933.68 በወቅቱ ባንክ ገቢ ሳይደረግ የሚዘገይ መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

ስለሆነም፡-

- በጥሬ ገንዘብ መጠበቂያ ካዝና ውስጥ የሚገኘው ጥሬ ገንዘብ በመቁጠር የቆጠራ ውጤቱ በእያንዳንዱ ገንዘብ ያዥ ስም ከተከፈተው የጥሬ ገንዘብ ተቀጽላ ሌጀር ጋር በማመሳከር ከወጪ ቀሪው ትክክል ለመሆኑ ወቅታዊ ቁጥጥር እንዲደረግ፤
- በብልጫ የሚታየው ጥሬ ገንዘብ ብልጫው ሊደርስበት የቻለበት ምክንያት ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራለት፣
- በጉድለት የሚታየው ጥሬ ገንዘብ እንዲተካ፣
- በበጀት አመቱ መጨረሻና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብና ሰነድ ድምር በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተቀጽላ ሌጀር ከሚታየው ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘን የሥራ አመራሩን አሳስበናል፡፡

2. ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

2.1 ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ፤

የተሰብሳቢ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በወቅቱ ያልተወራረደ በ30 መ/ቤቶች ብር 886,900,744.18 ተገኝቷል፡፡

ከዚህ ሂሳብ ውስጥ ወላይታ ዩኒቨርሲቲ- በ4251 የተያዘ ብር 1,161,265.61 ጉዳዩ በህግ የተያዘ መሆኑ፣ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ- ብር 19,674,851.40 ከ2001-2005 ተከፍሎ ያልተወራረደ እና እስከ 2007 በጀት ዓመት መጨረሻ እንቅስቃሴ ያልታየበት፣ አድግራት ዩኒቨርሲቲ- ሂሳቡ ከ2006 በጀት ዓመት የዞረና በ2007 በጀት ዓመት እንቅስቃሴ ሳይታይበት ለ2008 በጀት ዓመት የተላለፈ ፣ ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ- ብር 10,418,599.01 ከ2004 - 2006 በጀት ዓመት ተከፍሎ

ያልተወራረደ፣ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የብር 1,789,736.30 ጉዳይ በህግ የተያዘ የቼክና የገንዘብ ማጭበርበር መሆኑ፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ - በ4201 የተያዘ ብር 1,369,724.57 ማስረጃው ለኦዲት አለመቅረቡ፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ- ብር 4,950,996.16 ከ2006 በጀት ዓመት የዞረና እንቅስቃሴ ሳይታይበት ለ2008 በጀት ዓመት የተላለፈ፣ አክሱም ዩኒቨርሲቲ- ብር 404,687.25 ከ2006 በጀት ዓመት የዞረና እንቅስቃሴ ሳይታይበት ለ2008 በጀት ዓመት የተላለፈ ፣እና ትምህርት ሚኒስቴር-ብር 43,984,025.43 ከ1997 ጀምሮ ብር 284,914,502.73 ከ2004 ዓ.ም ብር 2,233,294.64 ከ2006 ዓ.ም ያልተወራረደ ሂሳብ ይገኝበታል፡፡

2.2 <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ ልዩ ልዩ የአሠራር ችግሮች</u>

<u>ተቀጽላ ሌጀር የሌላቸው ተሰብሳቢ ሂሳቦች</u>

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ሥም	የገንዘቡ ልክ
1	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ፡-	123,290,433.00
2	በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ	638,019.07
3	ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ	1,118,789.67
4	በአዲግራት ዩኒቨርሲቲ	48,976,649.20
	ድምር	**174,023,890.94**

- <u>ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

  በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሰኔ 30/2007 ሐረማያ ዩኒቨርስቲ ብር 52,935,818.12፣ ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ፡- ብር 2,425,138.00 ፤አዲግራት ዩኒቨርሲቲ የቅድሚያ ተመላሽ እንዲሁም የመያዣ ሂሳብ ብር 12,026,892.28 ተሰብሳቢ ሂሳብ የነበረ ቢሆንም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት አልተደረገም፡፡

- <u>ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (በክሬዲት) የሚታይ ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

  በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ በድምሩ ብር 638,019.07 ፣ **በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ** ብር 24,752,657.74 እና **ወሎ ዩኒቨርስቲ** ብር 632,485.87 በመደበኛ የሂሳብ ሚዛን (ዴቢት) መያዝ ሲገባ መደበኛ ባልሆነ/ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን

(ክሬዲት) መያዙ ፣ **በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፤**_በመገንባት ላይ ያሉ እና የተጠናቀቁ ግንባታዎች ሂሳብ ከቤቶች ልማት ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እና ከትምህርት ሚኒስቴር ተገቢው ርክክብ ተደርጎ ምዝገባ ባለመከናወኑ እና የመነሻ ሂሳብ እንዲያዝ ባለመደረጉ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በዩኒቨርሲቲው በቀረበው የሂሳብ መግለጫ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ብር 3,569,624.35 በሂሳብ መደብ 4274 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን በክሬዲት ተይዞ መገኘቱ፤

ተረጋግጧል፡፡

ከላይ ለተመለከቱት ግኝቶች፡-

- ባልተለመደ የሂሣብ ሚዛን የሚታየው የሂሣብ ማስተካከያ እንዲሠራለት፤
- በውዝፍ የሚገኘው ተሰብሳቢ ሂሳብ በአስቸኳይ እንዲወራረድ፣
- የዕቃ ግዢ ሠራተኞች ለተለያዩ አገልግሎቶች ማስፈጸሚያ በቅድሚያ የወሰዱት ገንዘብ በደንብና መመሪያ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያወራርዱ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

3. <u>የገቢ ሂሳብ፤</u>

3.1 <u>ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልቀረበ የውስጥ ገቢ ሂሳብ</u>

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ሥም	የገንዘቡ መጠን	ወጪ
1	አዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	5,718,905.99	
2	ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	17,530,181.13	7,557,547.17
3	የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል	784,289.36	
4	በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የመዝናኛ ክበብ	33,596,256.44	
5	በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የማዕከላዊ የዉስጥ ገቢ እና የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	18,971,907.43	

ከላይ በሰንጠረዥ የተገለጸው በበጀት ዓመቱ ከተሰበሰበ የውስጥ ገቢ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ያልቀረበ በመሆኑ፣ እንዲሁም ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ፣ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የውስጥ ገቢ ሂሳብ እንዲሁም የአዲስ አበባ ሣይንስና

ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ለተለያዩ ድርጅቶች የተከራዩ ሱቆች ገቢ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርትየማይቀርብ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

- የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የማዕከላዊ የዉስጥ ገቢ እና የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ተራፊ ገንዘብ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈሰስ አለመደረጉ፣- ታውቋል፡፡

ሐረማያ ዩኒቨርስቲ፡-

- በበጀት አመቱ ውስጥ ከተለያዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮች የተሰበሰበ የውስጥ ገቢ ሂሳብ ከፕሮጀክት ሂሳቦች ጋር ብር 296,326,341.20 በጥቅል የተያዘ ሲሆን የውስጥ ገቢ የሂሳብ እንቅስቃሴ ለይቶ በዝርዝር ኦዲት ለማድረግ አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም ከዩኒቨርስቲው የገቢ ማስገኛ ምንጮች የተሰበሰበው ገቢ ተለይቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት አልተደረገም፡፡
- ከዩኒቨርሲቲው ፕሮጀክቶች ውስጥ በድምሩ ብር 19,987,619.92 ከወጪ ቀሪ የነበራቸው በቁጥር 159 ፕሮጀክቶች ከ2006 በጀት ዓመት የተላለፉ ቢሆንም በ2007 በጀት ዓመት ምንም ዓይነት የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሌላቸው በመሆኑ የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች፣ የተቋረጡ ወይም የታጠፉ ፕሮጀክቶች እና ቀጣይነት ያላቸውና በክንውን ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች ዝርዝር መረጃ ለኦዲት እንዲቀርብ በተደጋጋሚ ተጠይቆ መረጃው ባለመቅረቡ የፕሮጀክቶቹን ሂሳብ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት አለመቻሉ፡፡

3.2 <u>በሚመለከተው አካል የጸደቀ የማስከፈያ ዋጋ ተመን/ታሪፍ የሌለው</u>

ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ፣ በወልድያ ዩኒቨርሲቲ፣ በአዲግራት ዩኒቨርሲቲ፣ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ፣ በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ እና በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ማመንጫ የሥራ ክፍል ባለመኖሩ የውስጥ ገቢ ምንጮች በዝርዝር የማይታወቁ መሆኑ የውስጥ የገቢ ማስገኛ ምንጮች ዓይነት እንዲሁም የእያንዳንዱ የገቢ ማስገኛ ምንጭ የማስከፈያ ዋጋ ተመን/ታሪፍ በዝርዝር የሚገልጽና በሚመለከተው አካል የጸደቀ ሠነድ የሌላቸው መሆኑ፡፡

3.3 ያልተሰበሰበ ገቢ

ዕቃ አቅራቢዎችና ሕንጻ ተቋራጮች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ሊሰበሰብ የሚገበው ሂሳብ ያልሰበሰቡ መ/ቤቶችና የገንዘብ መጠን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተራ ቁ.	የመ/ቤቱ ስም	የቅጣት መጠን	
		ከዕቃ አቅራቢዎች	ከሕንጻ ተቋራጮች
1	የአዲስ አበባ ሣይንስና ቴክኖሎጂዩኒቨርሲቲ	1,081,913.24	
2	የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ		27,088,193.43
3	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	311,878.79	
4	ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	332,889.20	
5	ጅማ ዩኒቨርሲቲ		147,652,432.00
6	አሶሳ ዩኒቨርሲቲ		53,573,621.00
7	አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ	372,673.29	19,146,257.08
8	የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ	1,004,718.90	32,565,718.50
9	የዲላ ዩኒቨርስቲ		109,782.50
10	የሐዋሳ ዩነቨርስቲ		817,764.40
11	አዴግራት ዩኒቨርሲቲ	163,757.57	1,480,454.64
12	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ		7,828,958.22
13	አክሱም ዩኒቨርሲቲ		21,163,962.31
14	ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ		15,329,482.39
15	ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ		35,451,234.64
16	ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ		135,762,545.48
	ድምር	3,267,830.99	497,970,406.59
	ጠ/ድምር	501,238,237.58	

አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው፣ ህንፃዎች በውላቸው ላይ በተገለፀው የግዜ ገደብ ባለመጠናቀቃቸው በገቡት ውል መሰረት ላደረሱት የጉዳት ካሳ የሚፈለግባቸው ተሰብስቦ ገቢ አለመደረጉ፡

- በአዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ከሚከራዩ ሱቆች ያልተሰበሰበ፣
- ከኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት ለትምህርት ወደ ተለያዩ ሀገራት የሄዱ ሠራተኞች ከኢንስቲትዩቱ ጋር በገቡት ውል መሠረት ወደ ስራ

ገበታቸው ተመልሰው ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው የሚፈለግባቸው ብር 89,800.00 እና USD 211,930.00 ተሰብስቦ ገቢ አለመደረጉ፡ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

3.4 <u>የገቢ ሂሳብ አያያዝ እና አመዘጋገብን በተመለከተ</u>

<u>የገቢ ሂሳብ አያያዝ እና አመዘጋገብን በተመለከተ</u>

- **ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር** 185,146.32 ፣ **ሰመራ ዩኒቨርሲቲ** ብር መቀነስ ከነበረበት በማነስ ያልተቀነሰ ብር 94,615.28 የቅድሚያ የገቢ ግብር ተቀናሽ (withhold እና **ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ** የግንባታ ስራ ከሚያከናውኑ ተቋራጮች ላይ በትምህርት ሚኒስቴር ስም በታተመ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደረሰኝ የተሰበሰበ ብር 1,361,755.40 እንዲሁም በGIZ-IS ስም በታተመ የቅድሚያ ግብር ደረሰኝ ብር 166,296.85 በድምሩ ብር 1,528,052.25 በጠቅላላው ብር 1,807,813.85 የተጨማሪ እሴት ታክስና የቅድሚያ ገቢ ግብር ታክስ (2%) እንዲሁም

በአክሱም ዩኒቨርሲቲ ብር 269,901.21 እና **በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ** ብር 552,229.94 ለውጭ ሀገር መምህራን ከተከፈለው ደመወዝ ላይ መቀነስ የነረበት የሥራ ግብር በድምሩ ብር 822,131.15 ተቀንሶ ለሚመለከተው መ/ቤት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፣

- በ2007 ዓ.ም ከተከፈሉት ጥቅማ ጥቅም ውስጥ በድምሩ ብር 296,800.00 ከቤት አበል ክፍያ ላይ የስራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በሀሮማያ ዩኒቨርስቲው ማኔጅመንት በተወሰነ የክፍያ ተመን መሰረት ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች ፈተና ለፈተኑበት/ለገመገሙበት እና የማማከር አገልግሎት ለሰጡበት ከውጪ ለመጡ ፈታኞች በድምሩ ብር 2,209,766.00 ከተፈጸመው ክፍያ ላይ የመንግስት የስራ ግብር ያልተቆረጠ መሆኑ፤

3.5 <u>በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ ሌሎች የአሠራር ድክመቶች፤</u>

- **በአዲግራት ዩኒቨርሲቲ** ሁለት የመዝናኛ ክበብ፤ የፎቶ ኮፒ፤ 3 ሱቆች፤ እና 2 የሴቶች ጸጉር ቤት ወዘተ በአክሱም ዩኒቨርሲቲ፡-ዩኒቨርሲቲው በዋና ግብ ከ17 ድርጅቶች እና በሽሬ ካምፓስ ከ1 ድርጅት ጋር አገልግሎት

የሚሰጥባቸውን ቤቶች ኪራይ የተማሪዎች ህብረት ገቢውን ሰብስቦ እንዲጠቀም የፈቀደ መሆኑ እና ሂሳቡ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማይደረግ መሆኑን፤

መቀሌ ዩኒቨርስቲ እስከ መጋቢት/2007 ገቢ የመሰብሰብ ስልጣን የሌለው የተማሪዎች ህብረት ከተለያዩ የውስጥ ገቢዎች ሰብስቦ ሲጠቀምበት የነበረ ሲሆን ከመጋቢት/2007 በፊት በህብረቱ የተሰበሰበው የገቢ መጠን ኦዲት ሳይደረግና ከወጪ ቀሪው ሳይታወቅ በባንክ እና በእጅ የነበረ በድምሩ ብር 529,361.20 ወደ ዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢ ሂሳብ ገቢ መደረጉ፣

አክሱም ዩኒቨርስቲ ዩኒቨርሲቲው በዋና ግብ ከ17 ድርጅቶች እና በሽሬ ካምፓስ ከ1 ድርጅት ጋር የቤት ኪራይ ውል የገባ ቢሆንም በውሉ መሰረት በየወሩ ብር 34,474.00 ሰብስቦ ገቢ መድረግ ሲገባው ገቢውን ለመሰብሰብ ህጉ የማይፈቅድለት የተማሪዎች ህብረት ገቢውን ሰብስቦ እንድጠቀምበት የፈቀደ መሆኑ እና ገቢው በተማሪዎች ህብረት ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 100010191058 ገቢ የሚደረግ እንዲሁም ከውስጥ ኦዲት በተገኘው ሪፖርት መሠረት ገቢው መሰበሰብ ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ ወደ ባንክ አካውንቱ የገባው ብር 521,820.00 ለመሆኑ ከመገለጹ በስተቀር የተሰበሰበ ገቢ መጠን የማይታወቅ ከመሆኑ በተጨማሪ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፣

4. <u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

4.1 <u>በተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት ያልተደረገ የወጪ ሂሳብ</u>

በአዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ በበጀት ዓመቱ ከተሰበሰበው የውስጥ ገቢ ወጪ የተደረገ ብር 3,928,212.04 ፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የማዕከላዊ የዉስጥ ገቢ እና የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት-ብር 18,971,907.43፣ **አሶሳ ዩኒቨርስቲ፡-** ብር 2,509,874.00 እና ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,557,547.17 በወጪ ሂሳብ ሪፖርት እንዲካተት ባለመደረጉ ፣እንዲሁም ሀሮማያ ዩኒቨርስቲ ብር 182,665,559.14 በጥቅል በመያዙ ለፕሮጀክት የወጣው ወጪ እና ከውስጥ ሂሳብ ለተለያዩ አገልግሎቶች የወጣው ወጪ ተለይቶ ሪፖርት ያለመደረጉ፤

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በቀረበው የሂሳብ መግለጫ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፣

4.2 <u>ምንም ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ፣</u>

በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ ለመመዝገቡ ኦዲት ሲደረግ፣

ተ. ቁ	የመ/ቤቱ ሥም	የገንዘብ መጠን
1	የሃዋሳ ዩኒቨርስቲ	40,150,000.00
2	ጅማ ዩኒቨርስቲ	5,929.00
3	መቱ ዩኒቨርስቲ	3423863
4	የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ	62,629.00
5		
	ድምር	43,642,421.00

በድምሩ ብር 43,642,421.00 በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ ለመመዝገቡ ኦዲት ሲደረግ፣ የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ በውስጥ ገቢ ሂሳብ ለእንጦጦ ኦብዘርባቶሪ የበጀት ድጋፍ ለማድረግ በዩኒቨርሲቲዎች ምክር ቤት በተወሰነው መሰረት ብር 150,000.00 ለተከፈለበት እና ዩኒቨርሰቲው ለሚያቋቁመው የገቢ ማመንጫ የበጀት ድጋፍ ለማድረግ በሚል የተፈቀደ

በጀት ሳይኖር ብር 40,000,000.00 የተሰጠ ሲሆን ቀሪዎቹም ለምግብ ጥሬ ዕቃ ግዥ የወጡ ቢሆንም አገልግሎት ሰጪው ገንዘቡን ለመቀበሉ የክፍያ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ናቸው፡፡

የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ወደ ውጪ ሀገር ለተደረገ ጉዞ ብር 516,920.22 እንዲሁም የሀገር ውስጥ የአየር ጉዞ ብር 39,722.00 በጠቅላላ ብር 556,642.22 የተከፈለ ሲሆን ጉዞውን የሚያረጋግጥ የአየር ትኬት ወይም በቂ ማስረጃ ሳይያያዝ በወጪ የተመዘገበ በመሆኑ ትክክለኛነቱ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

4.3 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፣

ተ ቁ.	የመ/ቤቱ ሥም	የገንዘብ መጠን ብር	በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተወራረደ(ብር)
1	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ	5,100,434.00	4,928,868.00
2	የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ	698,895.07	
3	ወሎ ዩኒቨርሲቲ	4,646,850.00	
4	አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ	8,601,445.18	
5	ወላይታ ዩኒቨርሲቲ	137,098.13	
6	ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ	2,904,606.91	
7	ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ	26,417,436.86	152,855.05
8	ቡሌሆራ የኒቨርሲቲ	1,248,503.96	
9	የቴ/ሙ/ት/ሥ/ኢንስትቲዩት	15,604.00	
10	ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	147,531.00	
11	በትምህርት ሚ/ር	95,526,864.83	
	ድምር	145,445,269.94	

በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ የተሟላ የወጪ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ ለብር 26,417,436.86 የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ ብር 1,248,503.96 ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ፤ብር 5,100,434.00 ፣ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 8,316,886.08 በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 698,895.07 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ፣ የሽያጭ ደረሰኝ እና ህጋዊ ደረሰኝ ሳይቀርብ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፣

ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ

- ዋናው ግቢ ከወንዶ ገነት ደንና ተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ ገቢ ማመንጫ የፈርኒቸር ዕቃዎች የተገዛበት ብር 2,472,216.62፣ የባዮሲስተሚክና ኢንቫይሮመንታል ኮሌጅ ብር 1,497,782.90፣ ከዩኒቨርሲቲው እርሻ ማዕከል ብር 7,828,925.90 እና የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከእርሻ ማዕከል ብር 1,175,785.00 ከተለያዩ ድርጅቶች ብር 1,290,629.50 በአጠቃላይ ብር 14,265,339.29 የተከፈለ ሲሆን ከተቋሞቹ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ፣

- ከተለያዩ ድርጅቶች የዕቃ ግዥ ለዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ ፒዮር ቴክ ድርጅት ሌዊ ጀኔራል ትሬዲንግ ከቢኒያም ሀይለግዚ አስመጪ ሰመርሱበል ፓምፕ ያሳርት ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግል/ማህበር ፣እሙ ጀኔራል ትሬዲንግ ፣አርቲስቲክ ማተሚያ እንዲሁም የተለያዩ ድርጅቶች በአጠቃላይ ብር 7,156,307.94 ክፍያ ሲከናወን የሽያጭ ደረሰኝ /(Cash sale attachmen)/ መቅረብ ሲገባው የዱቤ ደረሰኝ (Credit sale attachement) የቀረበ መሆኑ፣ ለህክምና ዕቃዎች ግዥ ብር 4,928,868.00 ለመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የተከፈለ ሲሆን በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተወራርዶና ተመዝግቦ መገኘቱ፤ ብር 66,921.00 ስለተከናወነው ስራ የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ለውሎ አበል የተከፈለ መሆኑ፣

የቴ/ሙ/ት/ሥ/ኢንስትቲዩት ፤

- ብር 15,604.00 **ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ፡-**ብር 147,531 ለውሎ አበል የተከፈለ ቢሆንም ሠራተኛው የተጓዘበት ቦታና ስላከናወነው ሥራ የውሎ አበል ማወራረጃ ቅጽ ሳይሞላ በወጪ መመዝገቡ፤

በወሎዩኒቨርስቲ፣

- የተሽከርካሪዎች ነዳጅ በትክክል እና በአግባቡ መሞላቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተይዞ መገኘቱን፤
- በትምህርት ሚ/ር በወጪ ሀገር በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ለሚማሩ ተማሪዎች በውጪ ጉዳይ ሚ/ር ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች 95,526,864.83 የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገበት የባንክ ማስረጃ ቢኖርም በትምህርት ላይ መሆናቸውና የተላከው የኪስ ገንዘብ ለተማሪዎቹ መድረሱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የተሟላ ደጋፊ የክፍያ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ማስረጃ እንዲቀርብ ሆኖ ማስረጃው ከወጪው ጋር እንዲያዝ፤በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተመዘገበው ሂሳብ ትክክለኛው የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ እንዲቀርብለት ስራ አመራሩን አሳስበናል፡፡

4.4 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች፣

ወጪ ሆነው የተመዘገቡት ሂሳቦች ደንብና መመሪያን የተከተሉ ለመሆናቸው ኦዲት ሲደረግ በ21 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 40,217,705.15 ለትርፍ ስዓት ሥራ፣ የትምህርት ድጋፍ እና ለቤት አበልና ለትራንስፖርት የክሊኒካል አበል ለአስተዳደር ሠራተኞች የትርፍ ሰዓት ከመደበኛ በጀት ለኢንተርፕራይዞች ተማሪዎች እና ለሠራተኞች አበል፣ ደመወዝና ማበረታቻ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ክፍያዎች ተገኝተዋል፡፡/ዝርዝራቸው አባሪ-19 ተመልቷል/

በወልድያ ዩኒቨርሲቲ መደበኛ አበል ክፍያ እንዳለ ሆኖ ለአልጋ የሚሆን ክፍያ ከዉስጥ ገቢ በቀን ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) በመስክ ቆይታ መሠረት እየተደጎመ እንዲሚከፈል በሥራ አመራር ካውንስል ውሳኔ ፈተኞችና የአማካሪዎች፣ የማበረታቻና የአስተባባሪነት፣ ለአስተዳደር ሠራተኞች የቤት አበል፣ ለስፔሻልስት ሀኪሞች እና ለጠቅላላ ሀኪሞች፣ ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች ድጋፍ በሚል ከደንብና መመሪያ ውጭና ደንብና መመሪያ ሳይኖር ተከፍሎ መገኘቱ፣

- **በአዲግራት ዩኒቨርሲቲ** የኮንትራት ሠራተኞች በቋሚ የሥራ መደብ ላይ በቋሚነት ሳይመደቡ ወይም ዘላቂነት ከሌለው የሥራ መደብ ላይ ሳይሰናበቱ እና ዩኒቨርስቲው በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ሳያስፈቅድ ለደመወዝ እና በመመሪያ ላልተደገፈ የቤት አበል የተከፈለ መሆኑ፣
- **በአክሱም ዩኒቨርሲቲ** የመንግስት የጋራ መኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው መምህራን በየደረጃው ከሚገባቸው የቤት አበል ላይ ለመኖሪያነት የተሰጣቸው ቤት ዋጋ ግምት ተቀንሶ ልዩነቱ በዓይነት ከተገኘው የቤት አገልግሎት በተጨማሪ ያለአግባብ በጥሬ ገንዘብ መከፈሉ፣
- **በአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ** በመመሪያ ከተፈቀደው የተመን ስሌት በተጨማሪ ለመኝታና ለመስተንግዶ በመመሪያ በተፈቀደው የተመን ስሌት ውል በመግባት ከተከፈላቸው ክፍያ በተጨማሪ ብር የቤት ኪራይ ከመደበኛው በጀት አላግባብ የተከፈለ መሆኑ፣ አበሉ ለማይገባቸው

መክፈሉ፣ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጽ/ቤትበወቅቱ ግብር ባለመክፈሉመቀጫ ያለአግባብ መክፈሉ፣

- **በደብረታቦር ዩኒቨርስቲ** የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የቅድሚያ ታክስ (withholding) ተቀናሽ ባለማድረጉ ቅጣት እንዲከፈል መደረጉ፤
- **በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ፡-**ለማበረታቻ (ቶፕ አፕ) መቀጫ ያለአግባብ ተከፍሎ መገኘቱ፤

  የጋራ መኖርያ ቤት ለተሰጣቸው መምህራን በየደረጃው ከሚገባቸው የቤት አበል ላይ ለመኖሪያነት የተሰጣቸው ቤት ዋጋ ግምት ተቀንሶ ልዩነቱ በጥሬ ገንዘብ አላግባብ የተከፈላቸው መሆኑ፣
- **በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡-**የወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ከወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ብር 2,500.00 የቤት አበል በየወሩ የሚያገኙ ቢሆንም ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተሰጣቸውን የመኖሪያ ቤት ሳያስረክቡ እየተጠቀሙበት መሆኑ፣ ክፍያው እና የክፍያዉ መጠን (Rate) በሚመለከተው የመንግሥት አካል ሳይወሰን የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ካውንስል በወሰነው መሠረት በህክምና ሳይንስ ኮሌጅ ለጠቅላላ ሀኪሞች ለማትጊያ እና በክሊንክ ለሚሰሩ ሀላፊዎች እና መምህራን ለሹፌሮችና ለቦርድ አባላት፣ለግዥ አጽዳቂ ኮሚቴዎች ለቴክኒካል አሲስታንስ ለአበል፣ ለማበረታቻ እና ቶፕ አፕ በሚል ከህግ፣ ደንብና መመሪያ ውጭ መከፈሉ፣ የዩኒቨርሲቲዉን ቦርድ ፈቃድና ዕዉቅና ሳያገኝ የዩኒቨርሲቲው የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ከርቀትና ተከታታይ ትምህርት ጋር የተገናኙ ልዩ ልዩ ሥራዎችን ላስተባበሩት በሚል በየደረጃቸዉ ከውስጥ ገቢ ውል ገብተው ለትምህርት ሀገር ውስጥ ሌላ ቦታ ሄደው ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ላልተመለሱ መምህራን አለአግባብ ደመወዝ እና የትምህርት ድጋፍ መከፈሉ፣ የሚሉት ዋና ዋና ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ክፍያዎች ናቸው፡፡

4.5 <u>ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈፀሙ ግዢዎች፤</u>

መ/ቤቶች የመንግስት የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ተከትለው ግዥ የሚፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ 26 መ/ቤቶች በድምሩ ብር

338,034,098.03 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈፀሙ ግዢዎች፣ በበጀት ዓመቱ እንደተከናወኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-21 ተመልክቷል/

የአንዳንዶቹ በዝርዝር ሲታይ፡-

- **በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ**፡-የቫት ተመዝጋቢ ለመሆናቸው ማስረጃ አለመቅረቡ፣ ግዢ ያለውድድር በቀጥታ የተፈፀመ መሆኑ፣የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ቀጥታ ከድርጅቶቹ የተፈጸመ መሆኑ፤
- ቡሌ ሆራ ብር 111,670.00 በተራ ፋክቱር ክፍያ ተፈፅሞ መገኘቱ፣
- **በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ**፣ግዥ ተቆራርጦ በዋጋ ማወዳደሪያ መፈጸሙ፣
- **በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ**፡-ያለምንም ውድድር በቀጥታ ግዢ መፈጸሙ፣በግልጽ ጨረታ መገዛት የነበረበት በዋጋ ማወዳደሪያ ተገዝቶ በአንድ ቀን በሁለት የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣዎች ተከፋፍሎ መወራረዱ፣
- **በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ** በድምሩ ብር 5,925,044.69 የግንባታ ሥራ በግልጽ ጨረታ በዘርፉ ከተሰማሩ ድርጅቶች በውድድር መፈጸም ሲገባ በውስን ጨረታ መፈጸሙ፣
- አዲግራት ዩኒቨርስቲ ያለምንም ውድድር ከአቅራቢዎቹ በቀጥታ መገዛቱ፣
- የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ፡ብር 15,242,632.70 ከዩኒቨርስቲው ኮሌጆች ለጨረታ የሚያበቃቸው ሰነድም ሆነ ህጋዊ ሰውነት ሳይኖራቸው በቀጥታ ግዥ ብር 5,035,941.87 ከመመሪያ ውጭ የዋጋ ማስተካከያ ተደርጎ ያለአግባብ ተከፍሎ መገኘቱ፣

ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ግዥ መፈጸሙ ታውቋል፡፡

4.6 <u>አለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ</u>

በወሎ ዩኒቨርስቲ በበጀት ዓመቱ ዩኒቨርስቲውን ለለቀቁ ሠራተኞች በድምሩ ብር 36,283.59 ደመወዝ አለአግባብ ተከፍሎ መገኘቱን፤

4.7 <u>በወጪ መያዝ ሲገባው በተሰብሳቢ የተመዘገበ ሂሳብ፣</u>

በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 11,839,361.33 ወጭ በሂሳብ መደብ 6111 መመዝገብ ሲገባው በበጀት እጥረት የተከሰተ በማለት በተሰብሳቢ የሂሳብ መደብ 4210 መመዝገቡ፣

በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ፡ብር 11,839,361.33 ወጭ በሂሳብ መደብ 6111 መመዝገብ ሲገባው በበጀት እጥረት የተከሰተ በማለት በተሰብሳቢ የሂሳብ መደብ 4210 መመዝገቡ፣

4.8 <u>በወጪ የተያዘ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሂሳብ</u>

በአዲስ አበባ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ለሥራ ተቋራጮች ከሚከፈለው የቅድሚያ ክፍያ ላይ ተቀናሽ የተደረገ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 5,916,376.19 በሂሳብ መደብ 6323 በወጪ የሂሳብ አርዕሰት በመመዝገቡ የበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ከፍ እንዲል መደረጉን፤

4.9 <u>ከወጪ መፍቀድ ስልጣን ገደብ በላይ የተፈፀመ ክፍያ</u>

በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ በተለያዩ ወጪ ማስመስከሪያዎች ለአገልግሎት እና ለዕቃዎች ግዥ የተከፈለ በድምሩ ብር 10,757,285.00 ወጪ በተደረገባቸው የክፍያ ማስረጃዎች ላይ ኃላፊዎች ከተፈቀደላቸው የክፍያ መፍቀድ ስልጣን ገደብ በላይ በመፈረማቸውና ክፍያ በመፈፀሙ የወጣው የፌዴራል መንግስት የክፍያ መመሪያ ተግባራዊ አለመደረጉን

4.10 <u>በሚመለከተው ኃላፊ ሳይፈቀድ የተፈፀመ ክፍያ</u>

- በወሎ ዩኒቨርስቲ የአዳራሽ ወንበሮች ለተሰሩበት ብር 342,902.40 በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 38,500.00 በድህረ ምረቃ ትምህርት ላይ ላሉ መምህራን ለኪስ ገንዘብ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 9,703,152.07 በተለያዩ ቀናት ለተለያዩ ድርጅቶች ክፍያዎች ሲከፈል በሚመለከተው ኃላፊ ሳይፈቀድ የተከፈለ መሆኑን፣
- በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የተለያዩ ኮሌጆች በድምሩ ብር 11,394,422.15 ለተለያዩ ክፍያዎች ገንዘብ ወጪ ሲደረግ ወጪዉን የማረጋገጥና የመፍቀድ /የማጽደቅ/ ተግባር በአንድ ሰዉ እንዲፈፀም በማድረግ ክፍያ መከናወኑን፡፡

4.11 በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ቅድሚያ ክፍያ

ጅማ ዩኒቨርስቲ፡-ለተለያዩ ጉዳዮች ማስፈጸሚያና ለስራ ማስኬጃ የወጣው ብር 133,800.00 ገንዘቡን በወሰደው ሰው ስም በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ መመዝገቡ፤ **በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ፡-**ለኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ዩቲሊቲ ለተከፈለ ብር 7,495,648.14 ዩኒቨርሲቲው አገልግሎቱን ለማግኘቱ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ የተያዘ መሆኑ፣

4.12 በብልጫ የተከፈለ

ተ. ቁ.	የመ/ቤት ስም	የክፍያው ምክንያት	የገንዘብ መጠን
1	በአክሱም ዩኒቨርሲቲ	የትርፍ ሰአት ላስተማሩ120.00 መከፈል ሲገባ ብር 400.00 በመከፈሉ	77,840.00
2	በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ	የውጪ ሀገር መምህር ደመወዝና የቤት አበል ከተፈቀደው በላይ	86,755.52
		በትርፍ ሰአት ላስተማሩ መምህራን ከተፈቀደው በላይ	610,372.00
	በጤና ሳይንስ ኮሌጅ	የውሎ አበል ከተፈቀደው በላይ	58,823.00
3	ባህርዳር ዩኒቨርስቲ	ውል ገብተው ላልተመለሱ መምህራን ደመወዝ	75,576.00
		ለውስጥና ለውጭ ሀገር የውሎ አበል ከተፈቀደው በላይ	28,695.82
		ሌክቸረር መምህራን የቤት አበል ከተፈቀደው በላይ	153,842.00
4	የዲላ ዩኒቨርስቲ	ዝቅተኛ ዋጋ ከአቀረበ ድርጅት ባለመገዛቱ	756,859.84
5	የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ	የሥራ ግብር ከሠራተኞቹ መቆረጥ ሲገባው በዩኒቨርስቲው የተሸፈነ መሆኑ፣	237,596.85
	የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ	ከተመን በላይ፣	288,792.00
6	የመገናኛና ኢንፎር ሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር	ለሠራተኞች መከፈል ከሚገባው በላይ	13,973.38
		ድምር	**2,389,126.41**

4.13 <u>በድጋሚ በወጪ የተመዘገበ</u>

- በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ የመኪና መለዋወጫዎች የተገዛበት ብር 58,170.45 በ07/12/2006 በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት ከተደረገ በኋላ በድጋሚ በ27/06/2007 ተመዝግቦ ሪፖርት መደረጉ፤
- በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ የመማሪያ እና የመረጃ ማዕከል ማደራጃ ዕቃዎች በመገዛታቸው በድምሩ ብር 1,488,657.95 ለጉምሩክ የቀረጥ የተከፈለ እና በተለያዩ የባንክ ወጪ ማመሳከሪያዎች በወጪ የተያዘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 594,804.95 በድጋሚ በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱን፤

4.14 <u>በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ ወጪዎች</u>

ተ.ቁ	የመቤቱ ስም	የገንዘቡ ልክ
1	የዲላ ዩኒቨርስቲ	3,429,450.78
2	የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል	154,772.20
3	በወልድያ ዩኒቨርሲቲ	2,056,347.16
4	በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	4,618,133.48
5	የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ	470,880.00
	ድምር	10,729,583.62

የተመዘገበው የወጪ ሂሳብ መደቡን ጠብቆ መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ያለሂሳብ መደቡ የተመዘገበ እና ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣

4.15 <u>ለከፈለው ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም ማግኘቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣</u>

- **በአክሱም ዩኒቨርሲቲ** በዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች ተረጋግጦ በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ገቢ የተደረገ በቁጥር አንድ ሳውንድ ፕሩፍ ጀኔሬተር ብር 4,499,700.00 የተከፈለበት ቢሆንም ሌሎች የዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች እንደገና በረጋገጡት መሰረት ዕቃው በውሉ ላይ በተገለጸው ዝርዝር (specification) መሰረት አለመሆኑ ስለተረጋገጠ ዩኒቨርስቲው ለከፈለው ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም ማግኘቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፡፡

4.16 በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ

ተ ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	ምክንያት	የገንዘብ መጠን
1	በፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ		408,152.51
2	በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	ለዱቄትግዢ፣ለማገዶ ለአየር መንገድ እና ለመሳሰሉት	2,305,425.63
3	በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ		86,400.00
4	በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ		10,826,857.38
5	በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ		1,216,366.25
6	በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ	በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ እና የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ	4,125,302.40
7	በጎንደር ዩኒቨርሲቲ		1,103,339.37
8	የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ	ለስልጠናና ለደንብ ልብስ	**307,110.00**
		ድምር	**20,378,953.54**

በድምሩ ብር 20,378,953.54 የ2006 በጀት ዓመት ወጪ ሆኖ እያለ በ2007 በጀት ዓመት በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

4.17 የተለያዩ የመሰረተ ልማት ግንባታ ወጪዎችን በተመለከተ፣

4.17.1 በብድር የተሰጡ የግንባታ ዕቃዎች ከክፍያቸው ተቀናሽ ያልተደረገ፤

የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ ብር 2,597,743.62 መቀነስ ያለበት የስሚንቶና የብረት ዕዳ ሳይቀነስ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

4.17.2 ከውሉ ዋጋ በላይ በብልጫ የተከፈለ

- የቡሌ ሆራ ዩኒኒርስቲ፡- ብር 7,864,832.62 በውል ውስጥ በተቀመጠው መጠን መጠቀም ሲገባ፣ በዩኒቨርስቲው አማካሪ ድርጅት በተሠራው ስሌት መሰረት ከተፈቀደው የመስተዋት፣ የስሚንቶና የብረት ዋጋ በላይ ወጪ ተደርጎ መገኘቱ፣ ብር 4,023,112.08 በውሉ ስምምነት ውስጥ ሳይካተተ ለተለያዩ ኮንትራክተሮች የውሃ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣

- የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ በተለያዩ ምዕራፎች ለሚያስገነባቸው ህንፃዎች በድምሩ ብር 4,585,404.47 ከውል ዋጋቸው በላይ ከፍሎ መገኘቱን፤ በአዲግራት ዩኒቨርሲቲ በአንድ ግንባታ ብር 1,123,050.00 የዋጋ ማስተካከያ ብቻ መጨመር ሲገባ በድምሩ ብር 3,358,303.85 በመጨመር ከተፈቀደው በላይ ብር 2,235,253.85 የዋጋ ማሻሻያ የተደረገ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 596,903.84 መከፈሉ፣

4.17.3 <u>ማስረጃው ባለመቅረቡ ሂሳብ በዝርዝር ኦዲት ማድረግ ስላለመቻሉ</u>

- **የቡሌ ሆራ ዩኒኒርስቲ፡-**
  - ✓ ብር **2,162,827.73** የተከፈለው የለውጥ ሥራ ትእዛዙ የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ያጸደቀበት ቃለ ጉባኤ ያልቀረበ መሆኑ፣
  - ✓ ብር 67,585,702.92 የሚያወጣ ስሚንቶና ብረት ወጪ የሆነበት ሞ/22 ከክፍያ ሰነድ ጋር ባለመቅረቡ ለእያንዳንዱ ተቋራጭ የተሰጠውን ለማረጋገጥ አለመቻሉን፡፡
- **የዲላ ዩኒቨርስቲ** ብር 16,735,379.14 የዋጋ ማስተካከያ፣ የለውጥ ሥራ እና የተጨማሪ ሥራ በሚል በነባር ፕሮጀክት በትምህርት ሚ/ር እና በኤም.ኤች.ኢንጂነሪነግ አማካኝነት በዩኒቨርሰቲው ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፡፡
- **የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ፡-** ብር 9,034,619.17 ለለውጥ ሥራ(varation order)፣ ብር 14,730,789.26 ለተጨማሪ ሥራ ትእዛዝ (supplimentry Agrrement፣ ብር 564,802.07 ባለው ህንፃ ላይ ተጨማሪ ስራ (Additional work) የሥራውን አስፈላጊነት በአማካሪ ድርጅቱ የቀረበ ሠነድ፣ የፕሮጅክት ጽ/ቤት ኃላፊ ያረጋገጠበትና ለዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ያሳወቀበት ደብዳቤ እና የሥራ አመራሩ የወሰነበት ቃለ ጉባዔ ማስረጃዎች ያልቀረበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

- **በወሎዩኒቨርሲቲ** ዩኒቨርስቲው ከGIZ-IS የግንባታ ሥራዎች አስፈፃሚ ድርጅት የተረከባቸው ያልተጠናቀቁ ግንባታዎች የሰነድ ርክክብ ሲደረግ፣ተገቢው ምዝገባ ባለመከናወኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉን፡፡

- **የዲላ ዩኒቨርስቲ፡-**
  - ✓ ብር 16,142,260.00 የሚያወጣ ዩኒቨርስቲው ለማሕበራት በብድር ለሰጠው ጤፍ ከሚከፈላቸው የእንጀራ ዋጋ ተቀንሶ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ባለመቅረቡ ስለትክክለኝነቱ ማረጋገጥ አለመቻሉን፣
  - ✓ ብር 3,709,426.53 የተከፈለ እና የወጪ ሰነዶች ለክልሉ ትምህርት ቢሮ እንደተላከና ሰነዱን ማቅረብ እንደማይቻል በመገለጹ የወጪውን ትክክለኝነት ማረጋገጥ አለመቻሉን፣

4.17.4 <u>ያለአማካሪ ድርጅት የክፍያው ትክክለኛነት የማረጋገጥ እና የመሳሰሉት ሥራዎች</u>

<u>**በግንባታ ጽ/ቤት አማካኝነት የተከናወነ መሆኑ፣**</u>

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	የገንዘብ መጠን
1	የዲላ ዩኒቨርስቲ	74,495,345.59
2	የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ	35,419,596.22
3	የሐረማያ ዩኒቨርስቲ	717,312,735.03
4	በአክሱም ዩኒቨርሲቲ	7,428,032.90
	ድምር	834,655,709.74

- የግንባታ ቡድን ኃላፊውን ጨምሮ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ አማካሪ መሃንዲስ ለመሆን የሚያስችል የስራ ፍቃድም ሆነ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ሳይኖረው በዩኒቨርስቲው የሚገነቡ የኮንስትራክሽንና የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ውስጥ እንደ አማካሪ መሃንዲስ በመሆን የቁጥጥርና የሱፐርቪዥን ሥራ በማከናወን የግንባታ ሰርተፊኬት በማጽደቅ ክፍያ እንዲፈጸም ከማድረጉም

በተጨማሪ፤ የዋጋ ዝርዝር (Bill of qauintity) የማዘጋጀት፤ ጨረታን የመገምገም፤ የክፍያው ትክክለኛነት የማረጋገጥ እና የመሳሰሉት ሥራዎች በሥራ ክፍሉ የሚከናወኑ መሆኑ፤

4.17.5 ሌሎች ከግንባታዎች ጋር የተያያዙ ችግሮች፤

አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ

ከአንድ ኮንትራክተር ጋር የተቀጽላ ውል ተዋውሎ በአንድ ካምፓስ ለሚያሰራው ህንጻ ግንባታ ብር 26,092,748.93 ሲከፍል ያልተሠሩ ሥራዎች (Staff Apartment, Dormitory Supplementary, Cafeteria Supplementary &ና Hard care connect for ground floor slab) ክፍያ ውስጥ ተካተው የመጡ መሆኑ ተገልጾ እያለ ወቅታዊ የሆነ ማስተካከያ ሳይደረግ ገንዘቡ ለድርጅቱ መከፈሉ፣

ሐረማያ ዩኒቨርስቲ፡-

ከምዕራብ ሐረርጌ ዞን መስተዳድር የሐረማያ ከተማ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤት ጋር በቀን 5/07/2005 በፈጸመው ውል መሰረት ለመምህራን መኖሪያነት የሚያገለግሉ 413 የመኖሪያ ቤቶች የያዙ በቁጥር 22 ህንጻዎች ግዥ ብር 38,783,544.70 የተከፈለ ቢሆንም ሕንጻዎቹ ባለመጠናቀቃቸው ለታቀዱበት ዓላማ ያልዋሉ መሆኑ፣ ተቋሙ ከሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት የቤቶች ልማት ጋር 158 የመኖሪያ ቤቶች የያዙ በቁጥር 8 ህንጻዎች ግዢ ውል የፈጸመ ሲሆን በውሉ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 3.1 ውል ሰጪ በውል ስምምነቱ መሰረት ቅድሚያ ክፍያውን እንደተቀበለ በ12 ወራት ውስጥ የግንባታ ሥራውን አጠናቆ ለማስረከብ የግዴታ ውል የፈጸመ ቢሆንም ብር 16,824,455.55 ክፍያ የተፈጸመባቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዩኒቨርስቲው ያልተረከበ መሆኑ፤

ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ፡-

ዩኒቨርሲቲው ግንባታ ለማካሄድ ጨረታ ሳይወጣ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለ12 ኮንትራክተሮች ማኔጅመንቱ ባላቸው የስራ አፈፃፀም በሚል

ያለምንም የጨረታ ውድድር የብር 159,578,647.14 ስራ የተሰጣቸው መሆኑ፣

የዲላ ዩኒቨርስቲ

ብር 5,788,233.27 ዩኒቨርስቲው የመመገቢያ አዳራሽ ወደ መሰብሳቢያ አዳራሽ ለመቀየር ለአጥናፉ ኦክሬ ኮንስትራክሽን ውል የተገባበት ሥራ በበጀት ዓመቱ በጀት ያልተያዘለት መሆኑ፣ በግዥ ኤጄንሲ ያልፀደቀ መሆኑ፡፡

4.18 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት የወጪ ሂሳብ፣</u>

- በአዲስአበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ በድምሩ ብር 1,488,657.95 ለጉምሩክ የቀረጥ የተከፈለ ሲሆን፤ ንብረቶቹ ገቢ ለመደረጋቸው የገቢ ደረሰኝ /ሞ19/ ባለመቅረቡ ዕቃዎቹ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ አለመቻሉን፤ **ሠመራ ዩኒቨርሲቲ፤** ለምግብ ጥሬ ዕቃዎች ግዥ ብር 12,238.00 **ጅማ ዩኒቨርስቲ** ፡- ለህክምና መሳሪያዎች ግዥ ቀረጥና ታክስ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ለሞጆ ደረቅ ወደብ ኪሊራንስ ጽ/ቤት ብር 3,169,680.00 በወጪ የተመዘገበ ቢሆንም የተገዛው ዕቃ ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ አልቀረበም፡፡

- **ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ፡**-ኮንትራክተሮች ለግንባታ ግብአት አገልግሎት የሚውል ሲሚንቶና የአርማታ ብረቶችን ከዩኒቨርሲቲው ወጪ አድርገው የወሰዱበት ከክፍያ ላይ በድምሩ ብር 60,928,486.36 ተቀናሽ የተደረገ ቢሆንም ንብረቱ ወጪ የሆነበት ሞዴል 22 ከክፍያ ሰነድ ጋር ባለመቅረቡ የተወሰደው ብዛትና የዋጋውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- **ትምህርት ሚ/ር** ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በተጻፈ ደብዳቤ በሰነድ ቁጥር 141፤ ብር 7,986,766.78 በሰነድ ቁጥር 249፤ ብር 271,564.37 በሰነድ ቁጥር 251 ብር 1,953,639.78 እና በሰነድ ቁጥር 250 ብር 6,847,160.57 በድምሩ የብር 17,059,131.50 የቀረጥ ሂሳብ

ምዝገባ የተከናወነ ሲሆን ለተከፈለባቸው እቃዎች ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) አልቀረበም፡፡

5. የተከፋይ ሂሳብ፤

5.1 ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ፤

በተከፋይ ሒሳብ መግለጫዎቹ ላይ የተመለከቱት ሒሳቦች በተገቢው ማስረጃ የተደገፉ መሆኑንና ለሚመለከተው አካል የሚከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ26 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 164,204,770.92 በወቅቱ ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-31 ተመልክቷል/

ከዚህ ሂሳብ ውስጥ፣

- አድግራት ዩኒቨርሲቲ- ብር 168,982.30 ከ2006 በጀት ዓመት ለ2007 በጀት ዓመት የዞረ ተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር የሌለው እና በ2007 በጀት ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ያልታየበት መሆኑ፣ ከመደበኛ በጀት በሂሳብ መደብ 5061 የተያዘ ብር 18,789,721.99 ተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር የሌለው መሆኑ፣
- አክሱም ዩኒቨርሲቲ- ብር 10,754,888.58 ከ2006 በጀት ዓመት ዞሮ በ2007 በጀት ዓመት ምንም እንቅስቃሴ ሳይታይበት ባለበት ሁኔታ ለ2008 በጀት ዓመት መተላለፉ፣
- መቀሌ ዩኒቨርሲቲ- ከ2006 በጀት ዓመት የዞረና በ2007 በጀት ዓመት እንቅስቃሴ ሳይታይበት ለ2008 በጀት ዓመት የዞረ ነው፣
- ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ-ከ2004 እስከ 2007 በጀት ዓመት የቆየ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

በመሆኑም ሂሳቡ እንዲወራረድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

5.2 <u>ከተከፋይ ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ ግብርና ታክስ፣</u>

ተ. ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	ተቀናሽ ያልተደረገ ግብርና ታክስ
1	የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ	1,602,169.04
2	የዲላ ዩኒቨርስቲ	1,947,778.29
3	የሐዋሳ የኒቨርስቲ	160,048.27
4	በአዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ	209,499.06
	ድምር	**3,919,494.66**

ከተለያዩ ኮንትራክተሮች የመያዣ ሂሳብ (Retention payment) ሲከፈል መቀነስ ያለበት የተከፋይ ተቀናሽ (ዊዝሆልዲንግ) ታክስ ሳይቆረጥ ተገኝቷል፡፡

5.3 <u>በተከፋይ ሂሳብ ዙሪያ የታዩ የአሠራር ድክመቶች፣</u>

- በአዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ለሕንጻ ሥራ ተቋራጮች ክፍያ ሲፈፀም በመያዣነት ተቀናሽ የሚደረገው የመያዣ (Retention) ሂሳብ፤ በተከፋይ ሂሳብ በሂሳብ መደብ 5061 የማይያዝ እና በሂሳብ መግለጫም ሪፖርት የማይደረግ መሆኑን፤
- **አምቦ ዩኒቨርስቲ** ብር 3,516,925.00 ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 3,179,272.00 ተቀጽላ ሌጀር የሌላቸው መሆኑ፣
- ሰመራ ብር 2,433,062.00 ፣ **ጅማ** ብር 43,943,000.00 እና **በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ** ብር 285,759.85 ተከፋይ ሂሳብ ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ዴቢት) የተያዘ መሆኑ፣

6. <u>የበጀት አጠቃቀም፣</u>

6.1 <u>መደበኛና ካፒታል በጀት</u>

ኦዲት የተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በ2007 በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሳብ ሲመዛዘን፡ ከበጀት በላይ የወጣ በ15 መ/ቤቶች ብር 230,139,089.04 እና ካፒታል ብር 101,576,843.72 በድምሩ ብር 331,715,932.76 ሲሆን፣ በ34 መ/ቤቶች

ያልተሰራበት መደበኛ ብር 424,420,648.17 እና ካፒታል ብር 425,636,999.48 በድምሩ ብር 850,057,647.65 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 33 ተመልክቷል/

በተጨማሪም፣

- በጎንደር ዩኒቨርስቲ የውስጥ ገቢ ብር 2,466,655.01 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡
- የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የሰራተኞች መዝናኛ ክበብ ቁጥር 2 ብር 4,392,679.67፤ የሰራተኞች መዝናኛ ክበብ ቁጥር 1 ብር 853,524.37፤ የልጆች ትምህርት ቤት ብር 1,136,548.22 በድምሩ ብር 6,382,752.26 ከሰበሰቡት ገቢ ወጪ በመብለጥ (Deficit) የሚያሳይመሆኑ፣

7. የዕቃና ንብረት አስተዳደር፣

7.1 ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት

7.1.1 የንብረት አያያዝ ድክመቶች

የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል የንብረት አስተዳደር ሲታይ፣-

- የንብረት መዛግብቶችን የመያዝ፣ ንብረት የመቀበል እና ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶችን በአንድ ሠራተኛ የሚከናወን መሆኑ፣
- የቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርድ ያልተዘጋጀና ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፣
- የቋሚ ንብረት መለያ ቁጥር በአግባቡ ያልተሰጠ መሆኑ፣

ትምህርት ሚኒስቴር

- የቋሚና አላቂ ዕቃ ቆጠራ ቢደረግም ከመዝገብ ባላንስ ጋር ያልተመዛዘነ መሆኑ፣
- ንብረት ተረካቢና ንብረት ወጪየሚደረገው በአንድ ሰራተኛ መሆኑ፡፡
- በአላቂ እቃ መጋዘን ውስጥ ብዛት ያላቸው እቃዎች ያለአገልግሎት የተቀመጠ መሆኑ፣

በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ

ያገለገሉ የሂሳብ ማሽኖች የተለያየ መጠን ያላቸው የመኪና ጎማዎች፤ ፕሪንተር ማሽኖች እንዲሁም 48 ዓይነት የተለያዩ ዕቃዎች ሳይወገዱ በግምጃ ቤት ተከማችተው የሚገኙ መሆኑን፤ እንዲሁም አስቀድሞ የተገዙት የቤተ መፅሀፍት ጠረጴዛዎች ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ በጥቅም ላይ ሳይውሉ በተጨማሪ በ2007 በጀት ዓመት ግዥ በመፈፀሙ አለአግባብ እንዲቀመጡ መደረጉን፤ እንዲሁም 32 አይነት ዕቃዎች አገልግሎት ሳይሰጡ ለብልሽት ላይ የሚገኙ መሆኑ፤

በጎንደር ዩኒቨርስቲ

በተመላሽ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ ብዛት ያላቸው ኮምፒዩተሮች እና ፕሮጀክተሮች፤ የኮምፒዩተር ዕቃዎች፣ ማቀዝቀዎች የፎቶ ኮፒ ማሽኖች የተለያዩ የዕህፈት ማሽኖች የመኪና ጎማዎች እንዲሁም ወንበሮች አገልግሎት የማይሰጡ መሆናቸው በባለሙያ ሳይረጋገጥና የማያገለግሉት ተለይተው ሳይወገዱ ለበርካታ ጊዜያት በንብረት ክፍል ውስጥ እንዲቀመጡ መደረጉን፤

<u>በወሎ ዩኒቨርስቲ</u>

- አገልግሎት የማይሰጡ ብዛት ያላቸው የመኪና ጎማዎች፤ ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተሮች ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች፤ ፕሮጀክተሮች ፣ ቴሌ ቪዢኖች፣ የሻይ ማሽን፣ እስታብላይዘር፣ እስካነር፣ ፕሪንተር፣ የተለያዩ ወንበሮች እና የተለያዩ የሕክምና መሳሪያዎች፣ በግምጃ ቤቶች ተከማችተው መገኘታቸውን፤

<u>በሣይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር</u>

- በዋናው መ/ቤት ዕቃ ግምጃ ቤት ኮምፒዩተሮችና ተያያዥነት ያላቸው የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች፣ የመኪና መለዋወጫዎች፣ የመኪና ጎማዎች፣ የመካኒክ መሳሪያዎች፣ የጥበቃ የጦር መሳሪያዎችና ጥይቶች እንዲሁም ኦዲዮ ቪዥዋል ዕቃዎች ሳይወገዱ መገኘታቸውን፤

- በስነ-ልክ ኢንስቲትዩት መጋዘን ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ሳይወገዱ የቆዩ የቢሮ እና የክበብ ዕቃዎች፣ የጽህፈት ጠረጴዛ፣ የፎቶኮፒ ማሽን፣ ተሽከርካሪ ወንበርና ሊሎች ልዩ ልዩ ዕቃዎች መገኘታቸውን፤
- በጨረራ መከላከያ ባለስልጣን 3 ተሽከርካሪዎችና 1 ሱዚኪ ሞተር ሳይክል፤ የመኪናና የሞተር ሳይክል መለዋወጫዎች፣ የመኪና ማንሻና ሌሎች ልዩ ልዩ ዕቃዎች ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ተከማችተው መገኘታቸውን፡፡

የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ

- በቋሚ ንብረት ክፍል ውስጥ መቀመጥ ያለባቸው የተለያዩ የቧንቧ መለዋወጫዎችና የመኪና ባትሪዎች በአላቂ ንበረት ክፍል እንደሚገኙ፣
- ሞ/22 ወጪ ተቀርጦላቸው የአውቶቡስ ጎማዎች በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ እንደሚገኝ፣

- የፕሪንተር ቀለም የተገዙ ብዛታቸው 151 የሆኑ ንብረቶች 2 ዓመት በላይ ያለአገልግሎት አላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ እንደሚገኙ፣
- የወንድ 57 የሴት 51 ጫማዎች በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ ተገዝተው ሳይከፋፈሉ ተጨማሪ እንዲገዛ መደረጉ፣
- በመድኃኒት አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ ላይ ደንቡ በሚያዘው መሠረት ተፈጻሚ አለመደረጉ፣
- የተማሪዎች ምግብ አያያዝና አጠባበቅ ደንብና መመሪያ በሚያዘው መሠረት የማይከናወን መሆኑ፡፡

የዲላ ዩኒቨርሲቲ

- በቋሚ ንብረት ክፍል ውስጥ መቀመጥ የነበረባቸው የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች በአላቂ ንብረት ክፍል መገኘታቸው ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም የተሽከርካሪ መለዋወጫዎቹ በአላቂ ንብረት ክፍል ለረጅም ዓመት እንደተቀመጡ እና ብዛታቸው እንደማይታወቅ፣
- በቋሚ ንብረት ክፍል ዩፒኤስ ባለ 700 ዋት ብዛታቸው 236 እና ባለ 1000 ዋት ብዛት 14 የሆኑ ንብረቶች ከ2 ዓመት በላይ ያለአገልግሎት መቀመጡ፣

- ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ መሳሪያዎች ወጪ ሆነው ለአገልገሎት መዋል ሲገባቸው ያለአገልገሎት በቋሚ ንብረት ክፍል እንደሚገኙ፣
- እስከ ሰኔ 30 2007 ዓ.ም ድረስ ቆጠራው መጠናቀቅ ሲገባው ለኦዲት እስከ ቆየንበት ድረስ ቆጠራው አለመጠናቀቁ፡፡

<u>የሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የንብረት አስተዳደር ሲታይ፣-</u>

- አዲስ EPSON ፕሪንተር በ2001 ዓ.ም የተገዛ ብዛት 3 ያለአገልግሎት በቋሚ ዕቃ ንብረት ክፍል ውስጥ ተቀምጦ የተገኘ መሆኑ፣
- አዲስ የተለያዩ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች ከአራት ዓመት በላይ ያለአገልግሎት በአላቂ ዕቃ ንብረት ክፍል የተገኙ መሆኑ፣
- የሚወገዱ ቁጥራቸው በዛ ያሉ የቶነር ዕቃዎች፣ 85 የመኪና ከመነዳሪያዎችና ጎማዎች እና ከአራት ዓመት በላይ የቆዩ የመኪና መለዋወጫዎች መኖራቸው፡፡

የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ሲታይ፡-

- በኤጀንሲው በሚገኙ መጋዘኖች ብዛት ያላቸው አሮጌ እና የሚወገዱ ቋሚ ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፣
- በመጋዘኖች ዋጋ ያልተሰጣቸው ብዛት ያላቸው የተለያዩ ቋሚ ዕቃዎች መኖራቸው፡፡

የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር የንብረት አስተዳደር ሲታይ፣--

- በአልሳም ዋናው ንብረት ክፍል የተለያዩ የመኪና ጎማዎች፤ ከመነዳሪዎች፤ የመኪና ባትሪ፤ ወንበሮች፤ የፎቶ ኮፒ ማሽኖች፤ እስካነሮች፤ ዩፒኤስ፤ የህትመት ማሽኖች፤ የተለያዩ ኮምፒዩተሮች፤ የኮምፒዩተር ማስቀመጫዎች፤ የኔትዎርክ ማገናኛ (ራውተሮች)፤ የተለያዩ ማብሪያና ማጥፊያዎች፡ ጠረጴዛዎች፡ የዕቃ መደርደሪያዎች፡ የፋይል ማስቀመጫዎች፤ አሮጌ ምንጣፎች፡ ልዩ ልዩ ፋይሎች፡ የተለያዩ የመኪና ተመላሽ ዕቃዎች እና ሌሎች አሮጌ ዕቃዎች በንብረት ክፍሉ ተከማችተው መገኘታቸው፣

ጅማ ዩኒቨርስቲ፥

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የአላቂና የቋሚ ንብረቶች ቆጠራ (Inventory) የተደረገ ቢሆንም የቆጠራ ውጤቱ በመዝገብ ከተመለከተው ጋር ያልተመሳከረ በመሆኑ ከወጪ ቀሪ ትክክል ለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡
- በከፍተኛ ገንዘብ የተገዙና በርካታ ቁጥር ያላቸው የተለያዩ ኮንፒዩተሮች፤ የኮንፒዩተር ቀለሞች፤ ስተብላይዘሮች፤ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፤ ፕሪንተሮች፤ ቆርቆሮዎች፤ የግንባታ እቃዎች፤ ወንበሮች፤ ፊሪጆች፤ የብረት ቱቦዎች፤ የቧንባ እቃዎች በንብረት መጋዘን ውስጥ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤

<u>የተበላሹና ያልተወገዱ ንብረቶች፤</u>

- ለብዙ ጊዜ መጋዘን ተቀምጠው የቆዩ የተለያዩ ኬሚካሎች የኬሚካልና ላብራቶሪ ሪኤጀንት መጋዘን ዉስጥ መገኘቱ፤
- የተለያዩ የተማሪዎች መቀመጫዎች፤ ወንበሮች፤ አልጋዎች፣ የመኪና ጎማዎችና ቁጥራቸዉ በርካታ የሆኑ ብረታ ብረቶች ያልተወገዱ መሆኑ፤

➢ **መቱ ዩኒቨርስቲ፡-**

የህክምና መድሃኒቶች አያያዝና አጠባበቅ

- ከማዕከላዊ ዕቃ ግምጃ ቤት ወጪ ሆነው ወደ ተማሪዎች ክሊኒክ ስቶር ገቢና ወጪ የሚደረጉ መድሃኒቶች መከታተያና መቆጣጠሪያ መዝገብ (ስቶክ ካርድ እና ቢን ካርድ) ያልተቋቋመ መሆኑ፤በበጀት አመቱ መጨረሻ በተማሪዎች ክሊኒክ ስቶርና እንዲሁም በህክምና መስጫ የሚገኙ መድሃኒቶች ቆጠራ እና ከወጪ ቀሪ የሚያሳይ (reconciled report)ያልተረጋገጠ መሆነ፤ በህክምና መስጫ (Dispensary Room) የመድሃኒቶች ዓይነትና ዋጋ እንዲሁም የታካሚው ተማሪ ስምና ዲፓርትመንት የተሰጠውን መድሃኒት ዓይነት ሚገልፅ መረጃ ተመዝግቦ የማይያዝ መሆኑ፤

ቋሚና አላቂ ዕቃዎች

- ዩንቨርሲቲው የተደራጀ የንብረት መጋዘን ስለሌው ንብረቶች በየማዕከላቱ የተበታተኑና የተቀናጀ አስራር የሌለ መሆኑ፡
- በንብረት መጠበቂያ መጋዘኖች ውስጥ የሚገኙት እቃዎች በዓይነት፣በባህሪይና በሚሰጡት አገልግሎት ተለይተው በሥርዓት ያልተቀመጡ መሆኑ፣
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የአላቂና የቋሚ ንብረቶች ከወጪ ቀሪ ቆጠራ (Inventory) ያልተደረገ መሆኑ፤
- በንብረት ስቶር ዉስጥ የንብረት መከታተያና መቆጣጠሪያ መዝገብ (ስቶክ ካርድ)ና ቢን ካርድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- የዩኒቨርሲቲው ቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር የሌላቸውና ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፤

በአገልግሎት ላይ ያልዋሉ ቋሚ ንብረቶች

- 2 አዳዲስ የጤፍ መፍጫ ወፍጮዎች፤50 የንብ ቀፎዎች፤ብዙ ግዜ የቆዩ የቤት ክዳን ቆርቆሮዎች፤ የተለያዩ የላብራቶሪእና የህክምና መገልገያዎች በአገልግሎት ላይ ያልዋሉ መሆኑ፤
- በከፍተኛ ገንዘብ በግዥ የተገኙ በጣም ብዙ የግንባታ ፌሮዎች በዩኒቨርሲቲው ግቢ ዉስጥ በተለያየ ቦታ ላይ ተከማችተው የሚገኙ ከመሆኑ በተጨማሪ ለዝናብና ጸሐይ በመጋለጣቸው ከጥቅም ውጭ እየሆኑ መሆኑ፡፡

ያልተወገዱ ንብረቶች

- ብዙ ግዜ የቆዩ የተለያዩ ኬሚካሎች ከንብረት ጋር ስቶር ዉስጥ ተቀምጠው መገኘታቸው፤ ያገለገሉ ወንበሮች፤አልጋዎች፣የመኪና ጎማዎችና ቁጥራቸዉ በርካታ የሆኑ ሌሎች ንብረቶች እንዲወገዱ አለመደረጉ፡፡

- **አሶሳ ዩኒቨርስቲ**
  - በበጀት ዓመቱ ውስጥ በንብረት ክፍል ውስጥ ያሉ ንብረቶች ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፡

- ቋሚ ንብረቶች ለተጠቃሚው ሲሰጥ የትውስት ፎርም በከፊል የማይሞላ መሆኑ፤
- በተጠቃሚዎች እጅ ያሉት ላፕቶፖች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤
- የአላቂ እቃ መከታተያ ቢን ካርድ የማይሰራበት መሆኑን፡፡

- **ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር**
- የቋሚ ዕቃ ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም የቆጠራ ውጤቱ ከመዝገብ ጋር ያልተገናዘበ መሆኑ እና ንብረቶች በትክክል በተመዘገበው ሰው ስለመኖሩ፤ያገለገሉና የሚሰሩ መሆናቸው ያልተለየ መሆኑ፤
- በርካታ ያገለገሉ ንብረቶች እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ለኃላፊዎች ከሚመደቡ ተሽከርካሪዎች በስተቀር እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር መጠን ጋር እየተመዘገበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ የማይቀርብ መሆኑ፡፡

ሐረማያ ዩኒቨርስቲ

- በመጻህፍት አያያዝና አጠባበቅ ላይ፤
- ለተማሪዎች ህክምና አገልግሎት የሚውሉ መድሃኒቶች ስርጭት ላይ፤
- የእንስሳት መድሃኒቶች አያያዝና አጠባበቅ ላይ፤
- የግብርና ምርት ውጤቶች፤
- ለተማሪዎች አገልግሎት የሚውሉ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች፤
- በነዳጅ አጠቃቀምና ስርጭት ላይ፤
- በህትመትና ጥረዛ አገልግሎት የሥራ ክፍል የሚገኙ ንብረቶች፤

አስተማማኝ የውስጥ ቁጥጥር ስርአት ባለመዘርጋቱ በርካታ የአሰራር ክፍተቶችና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች መኖራቸው በኦዲት መረጋገጡ፡

ለስራ ማከናወኛ ወጪ የተደረጉ የተለያዩ ቋሚ ንብረቶች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤ንብረት በመጠበቅ ስራ ላይ የተመደቡ ሠራተኞች በተለያየ ምክንያት የሥራ ክፍል ሲቀይሩ ወይም ተቋሙን ሲለቁ ማስረከብ በሚገባቸው ልክ ለማስረከባቸው የማይረጋገጥ መሆኑ፤

ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ፡-

- ከማዕከላዊ ዕቃ ግምጃ ቤት ወጪ ሆነው ወደ ተማሪዎች ክሊኒክ ስቶር ገቢና ወጪ የሚደረጉ መድሃኒቶች መከታተያና መቆጣጠሪያ መዝገብ (ስቶክ ካርድ እና ቢን ካርድ) ያልተቋቋመ መሆኑ፤
- በተማሪዎች ክሊኒክ ስቶር ክፍል ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው የተላለፈ መድሃኒቶች ሳይወገዱ መገኘታቸው፤
- በህክምና መስጫ (Dispensary Room) መድሃኒቶች ዓይነትና ዋጋ እንዲሁም የታካሚው ተማሪ ስምና ዲፓርትመንት የተሰጠው መድሃኒት ዓይነት የሚገልፅ ዝርዝር መረጃ ተመዝግቦ የማይያዝ በመሆኑ የተገዙት መድኃኒቶች ለተፈለገው ዓለማ መዋላቸውን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች ከወጪ ቀሪ ቆጠራ (Inventory) ያልተደረገ መሆኑ፤
- የንብረት መከታተያና መቆጣጠሪያ መዝገብ (ስቶክ ካርድና ቢን ካርድ) ያልተቋቋመ መሆኑ፤
- ከፍተኛ ዋጋና ብዛት ያላቸው የተለያዩ የብረት ምድጃዎች፤የዉሃ ቧንቧዎች፤ የብረት ድስቶች፤ማቀዝቀዣዎች፤ የድንች መላጫ ማሽኖችና የመሳሰሉት አዳዲስ ማሽኖች በዕቃ መጋዘን ውስጥ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤

ሠመራ ዩኒቨርስቲ

- እያንዳንዱ የቋሚ ዕቃ ዓይነት ዋጋና የተጠራቀመ የአገልግሎት ቅናሽ ከመቆጣጠሪያ ቋት ጋር የማይታረቅ መሆኑ፤
- በመዝገብ የተመዘገበው ዕቃና በቆጠራ ከተገኘው ዝርዝር ጋር በማገናዘብ ሳይመዘገቡ የቀሩ ዕቃዎች አለመኖራቸው የማይረጋገጥ መሆኑ እንዲሁም በቆጠራና በመዝገብ ባለው መካከል ጉልህ የሆኑ ልዩነቶች ሲያጋጥሙ ለስራ አመራር በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተማሪዎች ክሊኒክ ሚኒ ስቶርና እንዲሁም በህክምና መስጫ የሚገኙ መድሃኒቶች ቆጠራ የማይደረግ መሆኑ፤

- በተማሪዎች ክሊኒክ በበጀት አመቱ ውስጥ በግዥ (በእርዳታ) የተገኘው መድሀኒቶች እንዲሁም ለታከመው ተማሪ የታደሉ መድሀኒቶች ዓይነትና ዋጋ የማይገለፅ መሆኑና በሪፖርት እንዲቀርብ የማይደረግ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

በአዲግራት ዩኒቨርሲቲ

- የመኖሪያ የሆኑና ያልሆኑ የዩኒቨርስቲው ህንፃዎች እንደቋሚ ንብረት በተለየ መዝገብ ላይ መመዝገብ ሲገባ አለመመዝገባቸው፣
- በ2006 በጀት ዓመትና ከዚያ በፊት በከፍተኛ ገንዘብ ተገዝተው ገቢ ከተደረጉ ንብረቶች ውስጥ የዳቦ መጋገሪያ እና የማቡኪያ ማሽኖች፣ የተለያዩ ወፍጮዎች እንዲሁም ዓይነታቸው የተለያየ የላቦራቶሪ ማስተማሪያ መሣሪዎች ላይ እርምጃ አለመውሰዱ፣
- የተለያየ መጠን ያላቸው የአርማታ ብረቶች ያለ አገልግሎት በሜዳ ላይ ተበታትነው መቀመጣቸው፣
- ስቶር ክፍል ተመድበው የሚሰሩ ሰራተኞች ንብረት የመያዝ፣ ገቢና ወጪ የማድረግ ሃላፊነቶችን በተደራቢነት የሚሰሩ መሆኑ፣
- በተማሪዎች ምግብ ግምጃ ቤት አላቂና ቋሚ ዕቃዎች የገቢና ወጪ መከታተያ (ስቶክ ካርድ) እና ቢን ካርድ የማይዘጋጅ መሆኑ፣
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የንብረት ቆጠራ መካሄዱ ሲጣራ የቋሚ እና አላቂ ንብረቶች፣ የመድኃኒት እና ኬሚካሎች፣ የቤተ-መጻሕፍት፣ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች እና የግንባታ ዕቃዎች ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ አለማካሄዱ፣

- **በአክሱም ዩኒቨርሲቲ፡-**
    - የመኖሪያ የሆኑና ያልሆኑ የዩኒቨርስቲው ህንፃዎች እንደ ቋሚ ንብረት በተለየ መዝገብ ላይ መመዝገብ ሲገባ አለመመዝገባቸው፣
    - በዋናው ግቢ ቤተ-መጽሐፍት ያለ አገልግሎት የተቀመጡ እንዲሁም የተገነጣጠሉና ተገቢውን ጥገና ያላገኙ የተለያዩ መጻህፍት መኖራቸው፣ በተጨማሪም በስጦታ የተገኙ ነገር ግን ዋጋቸው ያልተገለጸ የተለያዩ መጽሐፍት መኖራቸው፣

- በከፍተኛ ገንዘብ ተገዝተው ገቢ የተደረጉ የማህን ማጠቢያ ማሽን፣ የስጋ መፍጫ ማሽን የድንች መፍጫ ማሽን እና ጀኔሬተር ያለአገልግሎት መቀመጣቸው፣
- ትምህርት ሚኒስቴር ከLucky Export Plc ጋር ውል ከገባ በኋላ ወደ ዩኒቨርሲቲው የተላኩ ለሜካኒካል ምህንድስና ትምህርት ክፍል የሚያገለግሉ የላብራቶሪ ዕቃዎች ጥራታቸውን ያልጠበቁ /አዲስ ያልሆኑ/ መሆናቸው የዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች በሰጡት የጽሁፍ አስተያየት የተረጋገጠ መሆኑ፣

- **በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ፡-**
  - የመኖሪያ የሆኑና ያልሆኑ የዩኒቨርስቲው ህንፃዎች እንደቋሚ ንብረት በተለየ መዝገብ ላይ መመዝገብ ሲገባ ያልተመዘገቡ መሆኑ፣
  - በኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ በተፈጥሮ ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ እና በቢዝነስ ኮሌጅ በከፍተኛ ገንዘብ ተገዝተው ያለ አገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች መኖራቸው፣
  - በህግ እና ሥነ-መንግሥት ኮሌጅ ከኢሲዲዲ (ECDD) በእርዳታ የተገኙና በሞዴል 19 ቁጥር 02671 ገቢ የተደረጉ ብሪል ቦርድ፣ ብሪል ሪቮልቨር፣ ታሚኖዝ፣ ፎቶ ኮፒ ቶነር ወዘተ ዋጋቸው የማይታወቅ መሆኑ፣
  - በዓዲ ሐቂ ግቢ ውስጥ የተለያዩ ብረቶች፣ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ በርሜሎች እና ከብረት የተሰሩ አልጋዎች በሜዳ ላይ ተበታትነው መገኘታቸው እና ፀሐይ ዝናብ እየተፈራረቀባቸው ለበለጠ ብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ እንዲሁም ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉትና መወገድ የሚገባችው ንብረቶች ተለይተው አለመወገዳቸው፡፡

- **በወልድያ ዩኒቨርሲቲ፡-**
  - የቋሚ ዕቃ ንብረት ክፍል የህንጻው መስኮቶቹ በመስታወት ብቻ የተሰሩና ፍርግርግ ያልተሰራላቸው በመሆኑ ንብረቶች በቀላሉ ለዝርፊያ የተጋለጡ መሆኑ፣

- በቋሚ እና በአላቂ ዕቃ ንብረት ክፍል ውስጥ ሞዴል 19 እና ሞዴል 22 የመሥራት እንዲሁም ንብረት የመያዝ ሥራ በአንድ ሰው የሚከናወን መሆኑ፣
- በቋሚ ዕቃዎች ንብረት ክፍል ውስጥ ከ2007 በፊት የገቡ 70 ኤች ፒ ኮምፒተሮች፣1 የላውንደሪ ማሽን፣ 20 የላይብረሪ የመፀሕፍት መደርደሪያዎች፣ 8 ቡክ ትራክ እና 5 ቴሌቪዥን ከ2 ዓመት በላይ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣
- በንብረት ክፍል ውስጥ ተበላሽተው የተከማቹ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ ጋሪዎች፣ ካዝናዎች፣ ፋይል ካብኔቶች፣ አንድ አዳብተር፣ አንድ ስታቢላይዘር እና ባትሪዎች ተከማችተው የተገኙ መሆኑ፣
- **በተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃ ግምጃ ቤት**
  - በተማሪዎች የምግብ ቤት ውስጥ 9 ፍሪጆች፣10 ባለ አንድ ምድጃ የወጥ ቤት ስቶቮች እና 8 ባለ አራት ምድጃ የወጥ ቤት ስቶቮች ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣
  - የምግብ ጥሬ ዕቃ መጋዘን ዉስጥ ምስር ክክ በአይጥ ከመበላቱ የተነሳ ማዳበሪያው ተቀዶ ምስሩ መሬት ላይ ተዘርግፎ መገኘቱ፣ 1 ኩንታል የተበላሸ ምስር ክክ አገልግሎት ላይ ሊውል ከሚችል ምስር ክክ ጋር በአንደ ላይ ስለተቀመጠ ያልተበላሸውም ለበለጠ ብልሽት እየተጋለጠ መሆኑ፣
  - የተማሪዎች የምግብ አስተዳደር ንብረት ክፍል ሞዴል 19 እና ሞዴል 22 የመሥራት እንደሁም ንብረት የመያዝ ሥራ በአንድ የሰው የሚከናወን መሆኑ፤
  - በተማሪዎች የምግብ አስተዳደር ንብረት ክፍል ውስጥ 6 ኩንታል ስኳር እና ብዛት ያላቸው መርቲዎች ተበላሽተው መገኘታቸው፣
  - ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ አገልግሎት ላይ ያልዋለ አንድ የዳቦ መጋገሪያ ማሽን አገልግሎት ሳይሰጥ የተቀመጠ መሆኑ፣
  - በተማሪዎች የምግብ አስተዳደር ንብረት ክፍል መጋዘን ውስጥ ያሉት ስኳር እና ሽሮ መሬት ላይ በመቀመጣቸው ለብልስት የተጋለጡ መሆኑ፣

– በተማሪዎች የምግብ አስተዳደር ንብረት ክፍል ሥጋና ሽንኩርት መፍጫ ክፍል ውስጥ የተበላሹ 3 የስጋ መፍጫ፣ 5 የሽንኩርት መፍጫ እና 3 የድንች መፍጫ ሳይጠገኑ የተቀመጡ መሆኑ፡፡

➢ **በተማሪዎች ክሊኒክ** መድሀኒት መጠበቂያ (እስቶር) ክፍል የሞዴል 19 እና የሞዴል 22 ሥራ የሚከናወነው በአንድ ሰራተኛ መሆኑ፣

- **በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ፡-**

➢ ተቋሙ ወደ ዩኒቨርስቲ ከመቀየሩ በፊት የተገዙ ብዛት ያላቸው የተለያዩ የመኪና መለዋወጫ እቃዎች በስቶር ውስጥ አግባብ በሌለው አቀማመጥ /በአቧራማ ስቶር ውስጥ/ ተከማችተው መቀመጣቸው፣

➢ አገልግሎት የሰጡና መወገድ ያለባቸው የመኪና ባትሪዎች በስቶር ውስጥ ተከማችተው በመቀመጣቸው ለስቶሩ ባለሙያዎች የጤና ችግር እየሆኑ መሆኑ፣

➢ ከተገዙ ብዙ ጊዜ የሆናቸው የሻወር /የመታጠቢያ/ ቤት ሳህኖች ዩኒቨርስቲው ከሚያስገነባቸው ህንጻዎች ጋር የማይገጥሙ በመሆናቸው በሚል ያለመፍትሄ ተከማችተው ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣

➢ ተገዝተው አገልግሎት ሳይሰጡ የተፈላጊነታቸው ጊዜ ያለፈባቸው ብዛት ያላቸው የሽንት ቤት እቃዎች በስቶሩ ውስጥ መገኘታቸው፣

➢ የተለያዩ መጠን ያላቸው በጣም ብዙ የውሀ መስመሮች /ቱቦዎች/ ለዝርፊያና ለብልሽት ሊያጋልጥ በሚችል መልኩ ያላግባብ ከስቶር ውጭ ተበታትነው በየሜዳው የሚገኙ መሆኑ፣

➢ በዋናው ግቢ የግንባታ ዕቃዎች ስቶር ውስጥ የተለያዩ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ወጪ ሳይደረጉ በንብረት ስቶር ውስጥ ተከማችተው መገኘታቸው፣

➢ ባለፈው መንግስት /በደርግ/ ጊዜ ለኮንስትራክሽን ግንባታ ለዩንቨርስቲው ከተገዙ ባለ 32 እና ባለ 20 የፌሮ ብረቶች የተረፉ በአሁኑ ሰአት

ምንም አገልግሎት ሳይሰጡ ከስቶር ውጭ ሳር በቅሎባቸው የሸፈናቸው እና ለስርቆት በሚያጋልጥ መልኩ መቀመጣቸው፣

- በ1980 ዓ.ም ገቢ የተደረጉ 13 የውሃ ማሞቂያ ቦይለር አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ መሆኑ፣
- ብዛታቸው 320 የሆነ LCD Pointer በ2004 ዓ.ም ተገዝተው ያለ አገልግሎት በስቶር ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- የተበላሹና አገልግሎት የማይሰጡ የተለያየ ብራንድ ያላቸው ቴሌቪዥኖች፣ የፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ፕሪንተሮች፣ ኮምፒዩተሮች እና UPS ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወሰድባቸው በተለያየ ክፍል ዉስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
- እጅግ በጣም ብዙ ትልልቅ ብረቶች ያለአገልግሎት በየሜዳው ሳር በቅሎባቸው ለስርቆት በሚያጋልጥ መልኩ የሚገኙ መሆኑ፣
- ብዛት ያላቸው የሙቀት መከላከያ ቬንቲሌተሮች ገቢና ወጪ ሳይደረጉ ለረጅም ጊዜ በታሸገ የእንጨት ኮንቴነር ውስጥ በተማሪዎች ክሊኒክ በር አካባቢ ያለ አገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣
- አገልግሎት መስጠት የሚችል ዘመናዊ ትልቅ ስቶቭ፣ የተበላሹ /አገልግሎት የማይሰጡ/ ሲስተም ዩኒቶች፣ ዩፒኤስ ባትሪዎች፣ ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተሮች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ስቶቭ፣ ጀኔሬተር፣ ኦሎምፒያ ካልኩሌተርእና ታይፕራይተር ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ በቆርቆሮ ስቶር ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የተበላሸ 176 ኩንታል አተር እና ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ የተበላሸ 17 ኩንታል ምስር ክክ ምንም አይነት የመፍትሄ እርምጃ ሳይወሰድባቸው በስቶር ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በ2004 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ 75 ስቶቮች ያለ አገልግሎት በስቶር ውስጥ ያሉ መሆኑ፣
- በአባያ ተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ የሚወገዱ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች ምስር ክክ በኩንታል 65.95 እና በብር 161,725.50፤ ሩዝ በኩንታል 23.4 እና በብር 35,053.20፣ አተር ክክ በኩንታል 6.06 እና በብር

9,077.88፣ በአጠቃላይ ብር 205,856.58 ዋጋ ያላቸው ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ምንም አይነት እርምጃ ሳይወሰድባቸው /ሳይወገዱ/ በንብረት ክፍል ስቶር ውስጥ ከንፁህ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች ጋር መቀመጣቸው እና ሌሎቹን ለብልሽትና ለብክነት እያጋለጡ መሆኑ፣

- እጅግ በጣም ብዛት ያላቸው ስፕሪንግ ፍራሾችና ትልልቅ ብረት ድስቶች ከ2004 ዓ/ም ጀምሮ አገልግሎት ሳይሰጡ በአላቂና ቋሚ ንብረት ስቶር ውስጥ የሚገኙ መሆናቸው፣
- በ2006 ዓ/ም ለወላጅ አልባ ተማሪዎች አገልግሎት መስጫ በእርዳታ የገቡ 2 የወንዶች ፀጉር ማስተካከያ ወንበሮች ከነሙሉ እቃቸው እና አንድ ጂ-ፓስ አገልግሎት ሳይሠጡ በስቶር ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣
- ለናሙና ከተመረጠው ዉስጥ የጠረጴዛ ቁልፍ በቢን ካርድ ተመዝግቦ የሚገኘው 90 ሲሆን ንብረቱ መኖሩን ለማረጋገጥ ሲቆጠር 56 ብቻ የተገኘ በመሆኑ በልዩነት 34 በማነስ መገኘቱ፣
- በ2006 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ የኮምፒዩተር ጠረጴዛዎች እና የብረት ሼልፎች እንዲሁም በ2004 ዓ.ም በእርዳታ የገቡዴል ኮምፒዩተሮች አገልግሎት ሳይሰጡ በስቶሩ ውስጥየተቀመጡ መሆኑ፣
- ቋሚና አላቂ እቃ እና ኬሚካሎች በአንድ ላይ የሚጠበቁ ሲሆን በየካቲት 22/2007 በተነሳው የእሳት ቃጠሎ ምክንያት እጅግ በጣም ብዛት ያለው ንብረት የወደመ መሆኑና በቃጠሎው ምክንያት የወደመው ንብረት ምን ያህል እንደሆነና ምን ያህል እንደ ተረፈ በገንዘብ እና በዓይነት የሚገልጽ ማስረጃ የሌለውና የቃጠሎው መንስኤም ያልታወቀ መሆኑ፣
- ከ2006 ዓ.ም በፊት የገቡ አዳዲስ 4 ፍሪጆች አገልግሎት ሳይሰጡ በስቶሩ ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣ በ2003 ዓ.ም ተገዝተው አገልግሎት ላይ ያልዋሉ 29 ማይክሮስኮፖች በስቶር ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በተላያዩ ካምፓሶችና በዋናው ብዛት ያላቸው የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈ (expired) የተለያየ ዓይነት መድኃኒቶች መወገድ ሲገባቸው ያልተወገዱና አገልግሎት ከሚሰጡት ጋር አብረው የሚገኙ መሆኑ፤
- በዋናው ግቢ የተማሪዎች የመድሃኒት ስቶር የሼልፍ እጥረት በመኖሩ መድሃኒቶች በሜዳ ላይ የተቀመጡ መሆኑ፣

- በነጭ ሣር ካምፓስ አስቀድሞ በነበሩ ባለሙያ ወቅት የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈ መድኃቶች ያለምንም ርክክብ አንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑ

- **በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ፡-**
  - ዩንቨርስቲው ሲቋቋም ጀምሮ የመጣ ለተማሪዎች ዳቦ መጋገሪያ የሚሆን 1 የዳቦ ማሽን እና 9 ጋሪዎች ያለ አገልግሎት በተማሪዎች ምግብ ቤት እና አካባቢ ባለ ሜዳላይ የተቀመጡ መሆናቸው፣
  - ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ያገልግሎት ጊዜው ያለፈበት 37 ኩንታል ሲሚንቶ ያለ መሆኑ፣
  - በአላቂና በጥገና ስቶር እና በኬሚካል የኢንጅነሪንግ ማስተማሪያ ላብራቶሪ ክፍል ውስጥ ያሉ ንብረቶች ወጪ በሚሆኑበት ጊዜ ቢንካርዱ የማይቀናነስ (update) የማይደረግ መሆኑ፣
  - በ2007 ዓ.ም የተገዙ 49 ሻርፕ የፎቶ ኮፒ ማሽኖች እና 30 ዲሲፒ ፕሪንተሮች ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆናቸው ፣
  - በ2006 ዓ.ም የተገዙ 11 ሃይሰንስ ፍሪጆች አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ መሆናቸው ፣
  - በ2005 ዓ.ም እና በ2006 ዓ.ም ከትምህርት ሚኒስቴር የመጡ ብዛት ያላቸው የኢንጅነሪንግ የማስተማሪያ እቃዎችና ማሽኖች በቆርቆሮ ስቶር ውስጥ ያለአገልግሎት ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ ፣
  - በ2006 ዓ.ም ተገዝተው የገቡ ሳምሰንግ ዲቪዲ ቴፕ ብዛት 3 ፣ ዴል ኮምፒዩተር ብዛት 10 ፣ ፓናሶኒክ የልብስ ማጠቢያ ማሽን ብዛት 2 ፣ ኩከር በርነር የምግብ ማብሰያ ማሽን ብዛት 1 ፣ ኤልጂ ቴሌቪዢን ባለ 64 ኢንች ብዛት 2 ፣ የድንች መላጫ ማሽኖች በ2005 ዓ.ም ተገዝተው የገቡ ብዛት 3 ዲጂታል ኮኦርዲኔተር ብዛት 12 ዲጂታል ፕላናተር ብዛት 12 ቲዶ ላይት በቁጥር 6 ሲሊንደር ብዛት 2 ያለ አገልግሎት የተቀመጡ መሆናቸው፣

- ከ2006 ዓ.ም በፊት የተገዛ 17 ጥቅል የፕላስቲክ ሸራ ያለ አገልግሎት በስቶሩ ውስጥ ያለ መሆኑ ፣
- የዩንቨርስቲው ግብርና ምርምር ክፍል ያመረተው ስንዴና አተር በአላቂ በስቶሩ ውስጥ በመገኘቱ ለአይጦች መራባት ምቹ ሁኔታን በመፍጠር አላቂ እቃዎችን ለብልሽት የሚዳርግበት ሁኔታ መኖሩ፣

- **በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ፡-**
  - የዋናው ግቢን ጨምሮ ለአገልግሎት ወጪ የተደረጉ ቋሚ ንብቶች ቆጠራ ካለመደረጉም በተጨማሪ የተሟላ መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
  - በዋናው ግቢ በእርዳታ የገቡ በርካታ ዘመናዊ የምግብ ማብሰያ እቃዎች አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ መሆኑ እና መወገድ የነበረባቸው አገልግሎት የማይሰጡ እጅግ በጣም ብዙ የተማሪዎች የመመገቢያ ሳህኖች፣ የውሃ መጠጫ ኩባያዎች፣ የሻይ ኩባያዎች፣ እጅግ በጣም ብዙ የማርማላታ ጣሳዎች፣ የተበላሸ 62 ኩንታል የጤፍ ዱቄት ሳይወገዱ መቀመጣቸው፣
  - በቁጥር 12 የሚሆኑ ስቶቮች አገልግሎት ሳይሰጡ በምግብ ግምጃ ቤት አዳራሽ ዉስጥ የሚገኙ መሆኑ፣
  - በዋናው ግቢ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል የማተሚያ ማሽኖች ከነሙሉ አክሰሰሪዎቹ ጋር ቢኖሩም ተገቢዉን አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑና በብልሽት ምክንያት አገልግሎት ሳይሰጥ ከ3 ዓመት በላይ የተቀመጠ የፎቶ ኮፒ ማሽን፣ ከ2 ዓመት በላይ የተቀመጡ 3 የማባዣ ማሽኖች በማባዣ ክፍሉ ውስጥ መኖራቸው፣
  - በጤና ሣይንስ ኮሌጅ ተገዝተው 8 ወር ያስቆጠሩ እንደ X-ray፣ ሲቲ ስካን ያሉ እና የተለያዩ የታሸጉ የህክምና መገልገያ ዕቃዎች ተገቢ ቦታ ሳያገኙ በድንገተኛ ህክምና ክፍል ኮሪደር በተለያዩ ቦታዎች ላይ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣

- በጤናና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ የቋሚ ንብረት ቆጠራ ያልተደረገ እና በስቶር ውስጥ በ2 በርሜሎች ነዳጅ መገኘቱ፣ ይህም በስቶሮች አካባቢ የእሳት አደጋን ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ መሆኑ፣
- ለህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተገዝተው ከዋናው ግቢ የተወሰዱ አዲስ 200 የዳቦ ማስቀመጫ ቅርጫቶች አገልግሎት ከማይሰጡ / ከሚወገዱ / በጣም እጅግ በርካታ የህሙማን አልጋዎች፣ አሮጌ የመኪና ጎማዎች እና ሌሎች እጅግ በርካታ የሚወገዱ እቃዎች ባሉበት ስቶር ውስጥ በመደራረብ የተቀመጡ መሆናቸው፣
- አገልግሎት የማይሰጡ በጣም እጅግ በርካታ የህሙማን አልጋዎች፣ እስትሬቸር ጋሪዎች እና የልብስ ማጠቢያ ላውንደሪዎች በስቶሮች እና ከስቶር ውጭ ሜዳ ላይ ለበርካታ አመታት ሳይወገዱ የተከማቹ መሆኑ፡፡
- በዋናው ግቢ ዩንቨርስቲው ሲቋቋም ትምህርት ሚኒስቴር ለግንባታ ካመጣው የተረፉ በጣም ብዙ ብረቶች እና 6 አዳዲስ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ጎማዎች በአንድ ስቶር ውስጥ የተከማቹ መሆኑ፣
- በዋናው ግቢ በ2006 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የሆኑ 65 የመማሪያ ሰሌዳዎች፣ 4310 መወልወያዎች፣ 480 የጣሪያ መጥረጊያዎች፣ 1384 ሜትር የወለል ንጣፍ፣ 300 የዳቦ ማስቀመጫ ቅርጫት፣ 4954 ፀረ-ተባይ መድሀኒት (ሮች ኪለር)፣ 5627 የእቃ ማጠቢያ እስፖንጅ፣ 1000 ቶነሮች እና 1493 ሜትር አቡጀዲ ጨርቅ አገልግሎት ሳይሰጡ በስቶር ውሰጥ መቀመጣቸው፣
- በዋናው ግቢ እና በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው ብዛት ያላቸው መድሀኒቶች ሳይወገዱ በተማሪዎች ክሊኒክ ስቶር ውስጥ መቀመጣቸው እንዲሁም የስቶር ጥበትና የሼልፍ እጥረት በመኖሩ የተወሰኑ መድሃኒቶች በካርቶን ለብልሽት ሊዳርግ በሚችል ሁኔታ ወለል ላይ መቀመጣቸው፣

- **በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡-**

በይባብ ግቢ፣

- በንብረት ክፍል ውስጥ የተበላሹ ሳሙናዎች፣ የማይሰሩ ወንበሮች እና አንድ የማይሰራ ፕሪንተር ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በተለያዩ ቢሮዎች ውስጥ ያሉ ብዛት 23 ዴክስ ቶፕ ኮምፒውተሮች፣ 6 ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች፣2 ስማርት ዩፒኤስ፣ 4 የቢሮ ተሽከርካሪ ወንበሮች፣ 2 ፕሪንተሮች፣ 1570 የተማሪ ወንበሮች እና ሌሎች ቁሳቁሶች ሳይወገዱ የሚገኙ መሆኑ፣

መሪታይም ግቢ

- በየክፍሉ ያሉ ቋሚ ንብረቶች ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣

በቴክስታይልና ፋሽን ኢንስቲትዩት

- አገልግሎት የማይሰጡ ኤሌክትሮኒክስና ተያያዥ ንብረቶች እንዲሁም ሌሎች መወገድ የሚገባቸው ሳይወገዱ የሚገኙ መሆኑ፣

በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

- በንብረት መጋዘን ውስጥ ካለአገልግሎት ከአምስት ዓመት በላይ የተቀመጡና በብዛት ተጠቃሚ የሌላቸው የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች እና ሌሎች ብዛት ያላቸው የተለያዩ ንብረቶች የሚገኙ መሆኑ፣

ዋናው ግቢ

- በአላቂና ቋሚ ዕቃዎች ንብረት ክፍል አጠገብ ብዛት ያላቸው የማያገለግሉ ጎማዎች፣ ሁለት የብረት በሮች እና ሁለት መስኮቶች መስክ ላይ ወድቀው የተቀመጡ መሆኑ፣
- በንብረት ክፍል ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ የሽንት ቤት መርዝ፣ የጥበቃ ቆብ፣ የተለያዩ የሴት ጫማዎች፣ የጽ/መሳሪያዎች፣ ህትመቶች፣ ቅጻቅጾችና የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ እና ብዛት ያላቸው የተለያዩ ንብረቶች ሳይወገዱ ተከማችተው የተቀመጡ መሆኑ፣

- ከ2000 ዓ.ም በፊት የተገዙ ኦቨር ሄድ ፕሮጀክተር፣ ታይፕ ራይተሮች እና ቶነሮች ያለ አገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣

ግብርና ግቢ

- በቋሚ ንብረት ክፍል ውስጥ የማያገለግሉ ንብረቶች ኮምፒተሮች፣ የመኪና ቸርኬ፣ የመኪና ጎማ፣ ፓንቸሮች፣ ሳሙናዎች፣ ስቴፕሌሮች እና ብዛት ያላቸው የተቀራረጡ የደንብ ልብስ ጨርቆች፣ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች እንዲሁም ሌሎች ንብረቶች ሳይወገዱና ሳይጠገኑ የተቀመጡ መሆኑ፣
- 805 ደስጣ ክላሰሮች በትርፍነት (ኦቨር ስቶክ በመሆናቸው) ከሁለት አመት በላይ የተቀመጡ መሆኑ፣

<u>የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃ ግምጃ ቤት</u>

በይባብ ግቢ

- በተማሪዎች ምግብ ቤት ውስጥ ያሉ ፍሪጅ፣ የሽንኩርት መፍጫ ማሽን፣ የትሪ ማጠቢያ፣ የሻይ ማፍያ፣ የፓስታ መቀቀያ እና የወጥ መስሪያ እስቲም ቦይለሮች እና የሥጋ መፍጫ ማሽን ሳይጠገኑ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣
- የዳቦ መጋገሪያ ክፍል ወለሉ ያልተመቻቸ በመሆኑ የዳቦ ጋሪዎች እየተበላሹ እና የአዋራ ብናኝ ዳቦዎች ላይ የሚያርፍ መሆኑ፣ ይህም ለተማሪዎች ጤና መታወክ መንስኤ ሊሆን እንደሚችል፣

በቢዝነስ እና ኢኮኖሚክስ

- የተማሪዎች የምግብ ግብአት መጋዘን ውስጥ ከተበላሹ ከሁለት አመት በላይ የሆናቸው ሁለት የድንች መላጫ ማሽኖች እና ሁለት የወጥ ቦይለሮች መቀመጣቸው፣

በዋናው ግቢ

- በተማሪዎች የምግብ ቤት ውስጥ 4 የሻይና የወጥ መስሪያ የኤሌክትሪክ መሽኖች በቅርብ ጊዜ የገቡ ቢሆንም የማይሰሩ ሆነው በመገኘታቸው ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣ 8 የኤሌክትሪክ ስቲም ቦይለር፣ 4 የሰህን ማጠቢያ ማሽን እና አንድ የስጋ መፍጫ በብልሽት ምክንያት ሳይጠገኑ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በተማሪዎች የምግብ አስተዳደር ንብረት ክፍል አካባቢ የወዳደቁ ብዛት ያላቸው ወንበሮችና ጠረጴዛዎች ለበለጠ ብልሽት እየተጋለጡ መሆኑ፤
- በተማሪዎች የምግብ አስተዳደር ንብረት ክፍል ውስጥ 1 ኩንታል የሚሆን የተለያዩ የምግብ ግብዓቶች ተበላሽተው መገኘታቸው፣

በግብርና ግቢ

- በተማሪዎች የምግብ ግብዓት መጋዘን ውስጥ ከቴክኖሎጂ ግቢ የመጡ የማይሰሩ አራት ቦይለሮች ከአራት አመት በላይ ያለአገልገሎት የቆሙ እና ከሁለት አመት በላይ ያለአገልግሎት የቆመ የዳቦ መጋገሪያ ማሽን የሚገኝ መሆኑ፣

<u>**የተማሪዎች ክሊንክ**</u>

በቢዝነስ እና ኢኮኖሚክስ እና በዋናው ግቢዎች

- በመድኃኒት መጠበቂያ (እስቶር) ክፍል ጊዜ ያለፈባቸው መድሀኒቶች የሚገኙ መሆኑ፣

በግብርና ግቢ

- በመድሀኒት ዋና ስቶር እና በህክምና መስጫ ክፍል ጊዜ ያለፈባቸው መድሀኒቶች የሚገኙ መሆኑ፣
- በመድሀኒት ዋና ስቶር በመደርደሪያ እጥረት የተወሰኑ መድሀኒቶች ጠረጴዛ ላይ የተቀመጡ መሆኑ፣

7.1.2 <u>በነዳጅ አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮች</u>

- **በአክሱም ዩኒቨርሲቲ** ስለተሽከርካሪዎች እና ጄኔሬተሮች ነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት ፍጆታ አጠቃቀም በመመሪያው በተቀመጠው መሠረት ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት የማይቀርብ መሆኑ፣

- **በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ** የተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታ አጠቃቀም ሪፖርት በተወሰነ ጊዜ ለሚመለከተው አካል የማይቀርብ እንዲሁም ጀኔሬተሮች የሚጠቀሙበት ነዳጅ መቆጣጠሪያ እና መከታተያ ሥርዓት ያልተሟላ መሆኑ፣

- **በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ** ቢዝነስ እና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ በተማሪዎች የምግብ ግብአት መጋዘን ውስጥ የቦይለር መሽኖች እና የዳቦ መጋገሪያ መሽን የሚጠቀሙት ነዳጅ መጠን በግምት የሚሰጥ መሆኑ፣

7.2 <u>የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም</u>

<u>**በወሎ ዩኒቨርስቲ**</u>

እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜ መጠን ጋር እየተገናዘበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ ለሚመለከተው አካል የማይቀርብ ከመሆኑም በላይ የነዳጅ ወጪ በእያንዳንዳቸው መኪኖች የሚጠየቅበት ሥርዓት አለመዘርጋቱን፤ያገለገሉ የመኪና መለዋወጫዎች በአዲስ ሲተኩ ለዩንቨርሲቲዉ ንብረት ክፍል ገቢ የማይደረጉ መሆኑን፤

<u>**የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ**</u>

- በዩኒቨርስቲው የሚገኙ መኪናዎች ሹፌሮች ተመድበው እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በማን ኃላፊነት ሥር እንደሆነ በስምሪት ክፍል ያልተመደቡ መሆኑንና አንድ መኪና በተለያዩ ሹፌሮች የሚነዳ ስለሆነ ለተሽከርካሪዎች ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን እንዳይኖር መደረጉን፣

- **መቱ ዩኒቨርስቲ፤**- 15 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ወይም ሊብሬ የሌላቸው ሲሆን 2 ተሽከርካሪዎች ደግሞ በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፤-
- **ጅማ ዩኒቨርስቲ፡-** 5 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ወይም ሊብሬ የሌላቸው መሆኑ፤በጅማ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ በቁጥር 9 ተሽከርካሪዎች እንዲሁም ለግብርና ኮሌጅ የተመደቡ በቁጥር 8 ተሽከርካሪዎች የኪሎ ሜትር መመዝገቢያ ጌጅ የማይሰራ መሆኑ፤
- **አሶሳ ዩኒቨርስቲ፡-** 7 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ወይም ሊብሬ የሌላቸው መሆኑ፤ ኮድ 4 ታርጋ ቁጥር 17012 ቀንዶ ባስ (sun long bus) ምንም መረጃ የሌለው መሆኑ፤
- **አምቦ ዩኒቨርስቲ፡-** በቁጥር 20 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ወይም ሊብሬ የሌላቸው መሆኑ፤ መለስተኛ አውቶብስ ኮድ 4-03973ኢ.ት እና አውቶብስ ኮድ 4-12554ኢ.ት በጥገና ምክንያት 1 ዓመት የቆሙ ሲሆን ኒሻ ደብል ፒካፕ 4-05255ኢ.ት ከ10 ዓመት በላይ በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የቆመ መሆኑ፤
- **ሐረማያ ዩኒቨርስቲ፡-** 15 ተሽከርካሪዎች የቻንሲና የሞተር ቁጥር የሌላቸው መሆኑ፤ ዩኒቨርሲቲው ካሉት 211 ተሽከርካሪዎች ውስጥ በቁጥር 81 (39%) ተሽከርካሪዎች በጥገና ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ ሲሆን 5 ተሽከርካሪዎች ደግሞ የመንግስት ሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው መሆኑ፤
- **ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ፡-** 11 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው መሆኑ፤ በቁጥር 21 (ባለ 4 እግር) ተሽከርካሪዎች 1 ባጃጅ (ባለ 3 እግር) እና 4 ሞተር ሳይክሎች (ባለ 2 እግር) በጠቅላላ 26 ተሽከርካሪዎች የተገዙበት ዋጋ ወይም በዩኒቨርሲቲው ባለቤትነት ሥር የዋለቡት ገዜ የሚገልጽ መረጃ የሌላቸው መሆኑ፤ 3 ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፤
- **ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ፡-** በቁጥር 7 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው መሆኑን፤

የሀገርአቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ፡-

- 15 ተሽከርካሪ መኪናዎች የተገዙበት ዋጋ አለመታወቁ፣
- 14 ተሽከርካሪ መኪናዎች በግዢ ወይም በስጦታ ለመምጣታቸው ማረጋገጫ አለመቅረቡ፣
- 4 ተሽከርካሪ መኪናዎች ለሰርቪስ፤ ለሞተር ጥገና እና በግጭት ምክንያት የቆሙ መሆናቸው፣

- የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ የተሽከርካሪ መኪናዎች አያያዝ እና አጠባበቅ ሁኔታ ሲታይ፣-
  - 4 ተሽከርካሪዎች ከትምህርት ሚ/ር መጠተው ስማቸው በኤጀንሲው ስም ሳይዘዋወሩ መገኘታቸው፣
  - 1 ተሽከርካሪ በግዥ ኤጀንሲ በኩል መጥቶ የባለቤትነት መታወቂያውና የሰሌዳው ቁጥር ያልቀረበለት መሆኑ፣
  - 5 ተሽከርካሪዎች የተገዙበት ዋጋ አለመታወቁ፣
  - 1 ተሽከርካሪ የሞተር ቁጥሩ የታሸገ በመሆኑ ቁጥሩን ማየት አለመቻሉን፣
  - 1 ተሽከርካሪ የሞተር ቁጥሩን ለማወቅ አለመቻሉ፣
  - 1 ተሽከርካሪ በሞተሩ ላይ የተጻፈው የሞተር ቁጥር እና በባለቤትነት መታወቂያው ላይ የተጻፈው የተለያየ መሆኑ፣

በአዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ

- የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸው 13 ተሽከርካሪዎች መገኘታቸውን፤ እና ሌሎች 13 ተሽከርካሪዎች በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑንና ለአገልግሎት እንዲበቁ ወይንም እንዲወገዱ አለመደረጉን፤
- በጎንደር ዩኒቨርስቲ ተሽከርካሪዎች በስማቸው ወጪ ባደረጉ እና ንብረቱን ለመያዝ ኃላፊነት ሊሰጣቸው በሚገባ ሠራተኞች እጅ እንዲያዙ የማይደረግ መሆኑንና የርክክብ ቅጽ በንብረት ክፍል የማይቀመጥ መሆኑን፤

- የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በሊትር ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደሚሄድ በባለሙያ ያላስጠና መሆኑ፣

- **በአዲግራት ዩኒቨርሲቲ** 5 ተሽከርካሪ መኪኖችና 1 ትራክተር፣ **በአክሱም ዩኒቨርሲቲ** 14 ተሽከርካሪዎች እና አንድ ትራክተር፣ **በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ** 30 ተሽከርካሪ መኪኖች እና አንድ ትራክተር፣ **በወልድያ ዩኒቨርሲቲ** 11 መኪኖች፣ **በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ** 13 ተሽከርካሪዎች እና **በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ** 18 ተሽከርካሪ መኪናዎች ሊብሬ የሌላቸው መሆኑ፣

7.2.2 <u>በብልሽት ምክንያት የቆሙና በወቅቱ ያልተጠገኑ ተሽከርካሪዎች</u>

- **በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ** 3 ተሽከርካሪዎች ከአራት ዓመት በላይ በብልሽት ምክንያት በመቆማቸው በፀሐይና በዝናብ ለተጨማሪ ብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣

8. <u>ልዩ ልዩ፤</u>

- **የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ** የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል በተሟላ የሰው ሃይል አለመደራጀቱ እና የሥራ ክፍሉ የአራተኛው ሩብ ዓመት ሪፖርት እስከ ነሃሴ 15/2007 መቅረብ የነበረበት ቢሆንም የመስክ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት እስከ ታህሳስ/2008 አጋማሽ አከባቢ ድረስ ያልቀረበ መሆኑ፣
- **በአክሱም ዩኒቨርሲቲ** በፐሣ 9 የሥራ ደረጃዎች ላይ ያለውድድር እና የሥራ ልምዳቸው አግባብነት ሳይኖረው በመማር ማስተማር ሥራ ላይ የተሠማሩ ባለሙያዎች በአይ ቲ ዳይሬክተርነት እና በተቋማዊ ዕቅድና አፈፃፀም ግምገማ ማዕከል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተርነት መመደባቸው፣
- **በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ** በመቐሌ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ስም በታተሙ የክፍያ ቫውቸሮች ተሠርቶባችው መገኘቱ፣
- **በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ፡-**
    - ለአንድ የዕቃ ግ/ቤት ሠራተኛ እና አንድ የሬጂስትራር ሰራተኛ ከህዳር/07 አስከ ሰኔ/07 ዓ.ም በተመሳሳይ የመደብ መታወቂያ ቁጥር ደመወዝ የተከፈላቸው መሆኑ፣
    - ከተቋሙ ጋር ውል በመግባት ለትምህርት ተልከው በገቡት ውለታ መሠረት ግዴታቸውን ካልተወጡ ሁለት መምህራን በድምሩ ብር 314,304.00 እና አንድ ግለሰብ ያልከፈለው የቤት ኪራይ ብር 48,000.00 ጉዳያቸው በህግ

ተይዞ ገንዘቡን እንዲከፍሉ በፍርድ ቤት ብይን የተሰጠ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው እስከ አሁን ድረስ ገንዘቡን ያላስመለሰ መሆኑ፣

- **በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ፡-**
    - በዩኒቨርሲቲው ድርጅታዊ መዋቅር መሠረት የዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት 9 የሰው ኃይል የሚያስፈልገው ቢሆንም በክፍሉ አንድ ኦዲት ኃላፊ በቅርብ እንደተመደበ፣
    - በፌደራል መንግስት የውስጥ ኦዲት መመሪያ መሰረት የውስጥ ኦዲት ሪፖርት የጊዜ ሰሌዳውን ጠብቆ ሪፖርት ማቅረብ ሲገባው እስከ መጋቢት 30/2007 ዓ/ም ድረስ ምንም ዓይነት የኦዲት ሪፖርት ያላቀረበ መሆኑ፣
    - በመዋቅሩ መሰረት ለሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አንድ ሠራተኛ ብቻ መሆን ሲገባው በአዋጅና ተፈላጊ ችሎታዎች መመሪያ መሠረት በሜሪት አፈጻጸም በሠራተኛ ተይዞ በሚገኘው መደብ ላይ ከደንብ ውጭ በተደራቢነት አካደሚሺያን /መምህር/ በቁጥር ዋዩ/ፕ/ጽ/04/169/08 በቀን 02/02/2008 ከፕሬዚደንት ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ መመደቡ፣
    - የሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የስራ ደረጃው የባችለር ዲግሪ እና 9 ዓመት ወይም የማስተርስ ዲግሪ እና 7 ዓመት የስራ ልምድ የሚጠይቅ ሲሆን በወቅቱ የተመደቡ ግለሰብ ያላቸው የስራ ልምድ 5 ዓመት ብቻ መሆኑ፣
    - የሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬትን ጨምሮ ሌሎች መምህራን ከማስተማሩ ሥራ በተደራቢነት በመምህራን እንዲያዙ ባልተፈቀዱ የአስተዳደራዊ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ተመድበው የሚሰሩ መሆኑ፣

- **በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ፡-**
    - አንድ ሠራተኛ ከግንቦት 01/2005 ዓ/ም ጀምሮ የፕሮጄክት መሀንዲስ ሆነው የተቀጠሩ ሲሆን የስራ ደረጃው የምህንድስና ዲግሪ እና 3 ዓመት የስራ ልምድ የሚጠይቅ ሆኖ ሳለ በወቅቱ ግለሰቡ ያላቸው የስራ ልምድ 6 ወር ብቻ መሆኑ፣

- የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ኃላፊ ቦታን በጊዜያዊነት ኃላፊ ሆነው እንዲሰሩ ባለሙያ የተመደበ ሲሆን በቦታው ላይ ሃላፊ በቋሚነት መመደብ ሲገባ ያልተመደበ እና እስከአሁን በቦታው ላይ ከአንድ ዓመት በላይ በጊዜያዊነት እየሰሩ መሆኑን፣

- **በባህር ዳር ዩኒቨርቲ** እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ከዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ግቢዎች በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ አገር በትምህርት ላይ ያሉ 43 መመህራን ውል ሳይገቡ ለትምህርት የሄዱ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 10 መምህራን መቼ ለትምህርት እንደሄዱ እና የሚማሩበት ተቋም የማይታወቅ መሆኑ፣ 15 መምህራን ደግሞ መቼ ለትምህርት እንደሄዱ የማይታወቅ መሆኑ፣

8. <u>የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት፣</u>

- **የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ፡-**
    - በዩኒቨርስቲው የተማሪዎች ማደሪያ አካባቢ የውሃ እጥረት፣ መፀዳጃ ቤቶች ባለመሰራታቸው በግቢው ውስጥ ባሉት ባህር ዛፎች አካባቢ የሚጠቀሙ በመሆኑ በአካባቢው መጥፎ ጠረን እያመጣ መሆኑን፣
    - የዩኒቨርሰቲው ሀብት ከዘረፋና ከጥፋት ለማዳን ግቢው ምንም ዓይነት አጥር የሌለው መሆኑን፣

9. <u>ልዩ ልዩ፣</u>

9.2 <u>ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ፣</u>

- <u>በአዲግራት ዩኒቨርስቲ፡-</u>

<u>በ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት</u>

- ዩኒቨርሲቲዉን ለለቀቁ 12 ሠራተኞች በድምሩ ብር 13,038.60 ላልሰሩባቸው ወራት እና ቀናት አለአግባብ ደመወዝ መከፈሉ፣
- ከህንድ ለመጡ የዩኒቨርሲቲው የኮንትራት መምህር ከውል ውጭ ላልሰሩባቸው 5 ቀናት አለአግባብ የተከፈለ ብር 5,705.55 መኖሩ፣

<u>በ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ</u>

- ከመመሪያ ውጪ አለአግባብ የተከፈለ የቤት አበል እና ተቀናሽ ያልተደረገ የገቢ ግብር በድምሩ ብር 53,000.00 ከሚመለከታቸው አካላት ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ገንዘቡ ገቢ አለመደረጉ፣
- በብር 244,000.00 የተገዛ የዕቃ ማጠቢያ ማሽን የማብሰያ እና የመመገቢያ ክፍሎች የኤሌክትሪክ ዝርጋታው የማይሰራ በመሆኑ አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ እና የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢውን እርምጃ ባለመውሰዱ ችግሩ እንደቀጠለ መሆኑ፣

- **በአክሱም ዩኒቨርሲቲ** ከ01/11/2005 ዓ.ም ጀምሮ ዩኒቨርሲቲውን በለቀቁ አንድ ሠራተኛ ስም የተከፈለ የሐምሌ እና የነሐሴ 2005 ደመወዝ ብር 3,971.60 እና የቤት አበል ብር 600.00፤ በድምሩ ብር 4,571.60 ተመላሽ እንዲደረግ በ2006 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ተመላሽ አለመደረጉ፣

- **በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ** ግንባታዎች ለዘገዩበት ከተለያዩ የህንፃ ሥራ ተቋራጮች ብር 43,846,260.41 የጉዳት ካሳ ገቢ አለመደረጉ በዩኒቨርሲቲው የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት ሪፖርት የተደረገ ቢሆንም እስከ 2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ማብቂያ ጊዜ ድረስ የተሟላ እርምጃ አለመወሰዱ፣

- **በወልድያ ዩኒቨርሲቲ** ከ2006 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ውስጥ፣
  - በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ ዩኒቨርስቲው የመምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች መዝናኛ ክበብ፣ የተማሪዎች መዝናኛ ክበብ እና የተለያዩ አገልግሎት መስጫዎች የገቢ ማመንጫዎች በንግድ ስራ እንቅስቃሴ ላይ የሚገኙ ቢሆንም ምንም ዓይነት የአገልግሎት ክፍያ እንደማይከፍሉ፣
  - ተቋሙ ለአካዳሚክ ኃላፊዎች የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ቢሆንም ብር 68,520.00 ለትራንስፖርት አገልግሎት ከወሩ ደመወዝ ጋር አላግባብ ተከፍሎ መገኘቱ፣

- ዩኒቨርስቲው የሚገለገሉባቸው ህንጻዎች እንዲሁም የጋራ መኖሪያ ቤቶች በቋሚ የንብረት መዝገብ ያልተመዘገቡ መሆኑ፣

- **በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ** በ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት፡-
  - በድምሩ ብር 150,000.00 አላግባብ ከውስጥ ሂሳብ ለቤት አበል የተከፈለ የወጪ ሂሳብ ተመላሽ እንዲሆን፣
  - ቤት ተሰጥቷቸው እያለ የቤት አበል ከተከፈላቸው የውጭ አገር መምህራን በድምሩ ብር 633,291.86 ተመላሽ እንዲደረግ፣
  - በድምሩ ብር 24,765.00 ከመመሪያ ውጪ አላግባብ የተከፈለ የኃላፊነት አበል ከሠራተኞቹ /ከመምህራኑ/ ተመላሽ እንዲደረግ፣

- **በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ** በ2006 በጀት ዓመት ግኝት ወቅት
  - በበጀት ዓመቱ ለአስተዳደር እና ለአካዳሚክ ሰራተኞች ማነቃቂያ ክፍያ ከውስጥ ሂሳብ በየወሩ ከብር 350.00 - 1,500.00 በድምሩ ብር 122,396.67 አላግባብ የተከፈለ ተመላሽ እንዲሆን፣
  - የአስተዳደር ዘርፍ ለፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ያልተፈቀደ ኃላፊነት አበል እና አኑዋላይዜሽን ከጥር/06 እስከ ሰኔ/06 በየወሩ ብር 1,500.00 እና 450.00 በጠቅላላ ድምር ብር 11,700.00 አላግባብ የተፈፀመ ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፣
  - ከሆሳዕና ከተማ ቤቶች ል/ፕሮ/ጽ/ቤት ለቤቶቹ ግዢ ውለታ ከተገባበት ብር 30,755,115.21 በላይ ብር 31,904,310.40 በመከፈሉ የዋጋ ለውጥ በሚል ከውለታ በላይ አላግባብ ብር 1,149,195.19 (30755115.21+ 3190431.40) ክፍያ የተፈጸመ መሆኑና ከውለታ በላይ የተከፈለው የመንግሥት ገንዘብ ከሻጭ ተመላሽ እንዲደረግ፤

አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም ምንም ዓይነት እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣

- **በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ፡-**

<u>የ2006 በጀት ዓመት ኦዲት</u>

- የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዲፈፀም ከተፈቀደላቸው ሠራተኞች ውጪ ለተለያዩ የሥራ ክፍሎች ለፋይናንስ፤ ግዢ፤ ሰው ሃብት እና ጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች አላግባብ በማኔጅመንት ውሳኔ ከሃምሌ/05 እስከ ጥር/06 (ለ7 ወራት) ብር 558,586.45 የተከፈለ መሆኑና ከላይ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተፈቀደው የጊዜ ገደብ አስቀድሞም ለ2 ወር (ሃምሌ እና ነሃሴ/05) እና ለተፈቀደላቸውም ለ1 ወር (የጥር/06) የተፈቀደው የጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀ በኋላ ብር 60,840.02፣ በድምሩ ብር 619,426.47 አላግባብ ለትርፍ ስዓት ሥራ ተከፍሎ መገኘቱና አላግባብ በማናጅመንት ውሳኔ መሰረት የተከፈለው የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተመላሽ እንዲሆን፣
- ብር 72,905,956.91 ለአቅራቢዎች በቅድሚያ ክፍያ ለGIZ-IS International Service የተከፈለው የተሟላ ማስረጃ ባለመቅረቡ ሳይወራረድ የቆየ መሆኑና ሊወራረድ የሚችለውን ተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲወራረድ፤ ሊወራረድ የማይችለውን ደግሞ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ገንዘቡን ተመላሽ እንዲደረግ፣
- ለተቋሙ የህግ አገልግሎት የተመሩ የፍታብሄር ጉዳዮች ወደሚመለከተው የህግ አካል የቀረቡና ውሳኔ ያገኙ መሆኑ ሲጣራ፣ ከዩኒቨርስቲው እውቅና ውጪ የለቀቁ 16 መምህራን ለትምህርት ተልከው በገቡት ውለታ መሠረት ግዴታቸውን ባለመፈጸማቸው በጉዳዩ ላይ ክስ ለመመሥረት እንዲቻል በትምህርት ላይ በቆዩበት ወቅት የተከፈላቸው ደመወዝና ጥቅማጥቅም የሚያመለክት ማስረጃ ከሂሳብ ክፍሉ ባለመቅረቡ በመምህራኑ ላይ ክስ ያልተመሰረተ መሆኑ፤
- በፍርድ ቤት ውሳኔ ከመምህር አብርሃ አስራትና አቶ ዓለሙ አሳሌ በዕዳ የሚፈለገው ብር 103,152.72 ከመስከረም/06 ጀምሮ በየወሩ ብር 1,300.00፤ ከመምህር አሳምነው ደባይና ረታ አላምቦ የሚፈለገው ብር 86,251.64 ከጥቅምት/06 ጀምሮ ብር 1,500.00 ከደመወዛቸው እየተቀነሰ ገቢ እየተደረገ

መሆኑ ከህግ አገልግሎት ጽ/ቤት ለኦዲቱ ሥራ የቀረበው መረጃ ቢያመለክትም ከመምህራኑ ደመወዝ ዕዳው እየተቀነሰ አለመሆኑ፣

- በፍርድ ቤት ውሳኔ ያገኘው ከመምህር ደረጀ ወርቁ በዕዳ የሚፈለገው ብር 39,324.00 ከመስከረም/2006 ጀምሮ በየወሩ ከደመወዛቸው አንድ ሶስተኛ መምህሩ ከሚገኙበት ወለጋ ዩኒቨርስቲ እየተቀነሰ ለወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ ገቢ እንዲደረግ የተወሰነ ቢሆንም እስካሁን ከባለጉዳዩ ገንዘቡ ገቢ እየተደረገ አለመሆኑ፣

የ2005 በጀት ዓመት ኦዲት

- በዩኒቨርሲቲው ተቀጣሪ ለሆኑት መምህራን እና አስተዳደር ሰራተኞች በክረምት ትምህርት ዲፕሎማ ፕሮግራም ከሃምሌ 2004 ዓ.ም እስከ መስከረም 2005 ዓ.ም በማስተባበር እና በመስራት ላገኙት ገቢ ከደመወዛቸው ጋር ተደምሮ ግብር መክፈል ሲገባቸው ብር 9,093.76 (454,688.00*2%) ብቻ የተከፈለ መሆኑ፣
- የቤት አበል አከፋፈል ኦዲት ሲደረግ የዩኒቨርስቲው ከፍተኛ ኃላፊዎች የመንግስት መኖሪያ ቤት ውስጥ እየኖሩ በጠቅላላው ብር 46,900.00 በጥሬ ገንዘብ የቤት አበል አላግባብ የተከፈላቸው መሆኑ፣
- የጥቅማጥቅሞች /አበል/ ክፍያዎች ኦዲት ስናከናውን የቀድሞ የምህንድስናና ቴክኒክ አገልግሎት ቡድን መሪ ለሆኑት የዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ኮሚቴ የቦታ አበል በድምሩ ብር 8,077.00 የተከፈለ መሆኑ፣
- ለአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 60,000.00 እና ለሴንተር ፎር ዴቨሎፕመንት ብር 11,000.00፣ በድምሩ ብር 71,000.00 ለተከፈለው ደረሰኝ ያልተያያዘ መሆኑና እንዲያያዝ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰዱ አስመልክተን በኦዲታችን የእርምት እርምጃ እንዲወሠድበት ያሳሰብን ቢሆንም ምንም ዐይነት እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣

- **በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የ2006 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት፡-**

  - የተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች በመንግስት የተወሰነላቸውን የአመራርና የኃላፊነት አበል ከመደበኛ በጀት ላይ ከደመወዛቸው ጋር እየተከፈላቸው በተጨማሪ ከውስጥ ገቢ ላይ ለከፍተኛ አመራሮችና ለህክምና መምህራን በድምሩ ብር 7,063,367.47 ያለአግባብ ተከፍሏቸው መገኘቱ፣
  - በሀገር ውስጥ የድህረ ምረቃ ትምህርት ላይ እና በውጪ ሀገር ስልጠና ላይ ያሉ መምህራን/ሠራተኞች/ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በሀገር ውስጥ በድህረ-ምረቃ ለሚሰለጥኑ በዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ የሚገኙ 18 መምህራን የሀላፊነት አበልና ጥቅማጥቅሞች ሊከፈልባቸው በሚገባ የሥራ መደቦች ላይ ለመመደባቸው ማስረጃ ሳይቀርብ ለአበል ብር 23,150.00፣ (Annualize) ብር 26,177.60፣ ለትራንስፖርት ብር ብር 4000.00፣ በድምሩ ብር 53,377.60 የተከፈላቸው መሆኑ፣ከተቋሙ ውጪ በሀገር ውስጥ በድህረ- ምረቃ ለሚሰለጥኑ መምህራን ድጋፍ ተብሎ ለቤት አበል ብር 9,000.00፣ ለትራንስፖርት ብር 2,550.00፣ ለጽሕፈት መሳሪያ ብር 5,500.00፣ በድምሩ ብር 17,050.00 አለአግባብ መከፈሉ፣

በደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ

- በዩኒቨርሰቲው የሚከናወኑ የሕንጻ ግንባታዎችን ሲያስተዳድር በነበረው የቤቶች ልማት ድርጅት ለህንጻ ተቋራጮች በድምሩ ብር 4,784,196.59 በብድር የተሰጠ ሲሆን፤ ገንዘቡ ተመላሽ ሳይደረግ ከ3 ዓመታት በላይ መቆየቱን
- የተለያዩ አቅራቢዎች ዕቃዎችን በውሉ መሠረት በወቅቱ ባለማቅረባቸው ላዘገዩበት መከፈል የሚገባው የጉዳት ካሳ በድምሩ ብር 346,315.60 ከሚመለከታቸው አካላት ገቢ እንዲደረግ የኦዲት አስተያየት ቢሰጥም ገንዘቡ ገቢ አለመደረጉን፤
- በሂሳብ መደብ 4274 በተሰብሳቢ የተያዘ ብር 419,486.34 ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በስህተት በድጋሚ ክፍያ የተፈጸመ ተብሎ ቢገለጽም

በኦዲት ሪፖርት የክፍያ ማስረጃው እንዲቀርብ አስተያየት ቢሰጥም ሊቀርብ አለመቻሉን፣

➢ **አሰሳ ዩኒቨርስቲ**

- ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በስህተት በብልጫ የተከፈለው ብር 17,072.14 እንዲመለስ፣
- አዳማ በትምህርት ላይ ለነበሩ አንድ ሠራተኛ ለትምህርት ድጋፍ በብልጫ የተከፈለ ብር 4,800.00 ሰራተኛው ገንዘቡን እንዲተኩ፤
- በድምሩ ብር 1,687.47 ከተከፋይ ላይ የሚቀነስ ታክስ ከተለያዩ ክፍያዎች ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ በመሆኑ ገንዘቡ ከሚመለከታቸው ላይ እንዲመለስ፣

➢ **ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ**

- በ1 መደበኛና የውስጥ ሂሳብ ገንዘብ ያዡ የመደበኛ በጀት ብር 70,170.00 ጥሬ ገንዘብ ያስቀጠሩ ቢሆንም በስማቸው በተያዘው ተቀጽላ ሌጀር ደግሞ ብር 282,277.66 የሚያሳይ በመሆኑ ልዩነቱ ተጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድ፣
- በእጅ በእጅ ሽያጭ ፋክቱር የተወራረደው ብር 1,788,526.00 የቫት ደረሰኝ እንዲቀርብለት፤
- ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት የሚውል የሥጋ አቅራቢ አላግባብ የተደረገው የዋጋ ማስተካከያ ብር 157,893 (68901+88992) ተመላሽ እንዲደረግ፤
- በገቡት ውለታ መሠረት ግዴታቸውን ካልተወጡ አቅራቢ ድርጅቶች ብር 327,420.86 እንዲሰበሰብ (13)
- ከመመሪያ ውጪ የተከፈለው የትርፍ ሰዓት ብር 1,107.77 ተመላሽ እንዲደረግ፤ ተቋሙን ለለቀቁ ሠራተኞች አላግባብ የተከፈለው ብር 17,563.86 ተመላሽ እንዲደረግ፤

- ለአስተዳደር ሠራተኞች አላግባብ ለትርፍ ሰዓት የተከፈለው ብር 13,343.29፤ የኃላፊነት አበል (ማትጊያ) ብር 14,450 በድምሩ ብር 27,793.29 ተመላሽ እንዲሆን፤

ጅማ ዩኒቨርስቲ

- ዩኒቨርሲቲው ብር 225,281.77 የኮሚቴ አባላት የጨረታ ዶክመንት ያዘጋጁበት በሚል እና ብር 34,879.16 የሪፈራል ሆስፒታል ሠራተኞች የቁሳቁስ ግዥ በርካታ ውስብስብ ስራዎች በእረፍት ጊዜያቸውና የበአላት ቀንን ጨምሮ ለሰሩበት በሚል በድምሩ ብር **260,160.93** አለአግባብ ክፍያ የፈጸመ መሆኑ እና የተለያዩ ኮሚቴዎችን በማዋቀር እና እንደ ትርፍ ሰዓት ስራ ተደርጎ የተከፈሉ ክፍያዎች በሙሉ አግባብነት የሌላቸው በመሆኑ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ፣
- ዩኒቨርሲቲው መምህራን ለክረምት ትምህርት ፕሮግራም ላስተማሩበት የስራ ጫና (over load) ክፍያ ሲፈጸም ከትርፍ ሰዓት አከፋፈል ተመን በላይ በድምሩ ብር 846,336.48 አለአግባብ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ እና አለአግባብ በብልጫ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከታቸው ሁሉ ተመላሽ እንዲደረግ፣
- ዩኒቨርሲቲው ከመደበኛ በጀት የራሱ የገቢ ምንጭ ላለውና በራሱ ገቢ ሊንቀሳቀስ ለሚገባው ለተከታታይና ርቀት ትምህርት ፕሮግራም በድምሩ ብር 3,485,983.75 ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣ በተጨማሪም የትርፍ ሰዓት ክፍያው ከክፍያ ተመን በላይ ማለትም ብር 120.00 መክፈል ሲገባ ብር 150.00፣ብር 100.00 መከፈል ሲገባ ብር 1,10.00፣ብር 65.00 መከፈል ሲገባ ብር 75.00 በመክፈል በኦዲት ናሙና ከታዩት የወጪ ሰነዶች ውስጥ ብር 502,714.50 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ ፤
- የሥራ ተቋራጮች በፀደቀ የውል ማራዘሚያ መሠረት ስራቸውን አጠናቀው ማስረከብ ሲኖርባቸው ባለማስረከባቸው እስከ 2004 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ በድምር ብር 81,110,000.00 ዩኒቨርሲቲው ከሥራ ተቋራጮች በቅጣት መልክ Liquidation Damage ካሳ ማስከፈል ሲገባው ያላስከፈለ

መሆኑ፣ በተጨማሪም አቅራቢዎች በገቡት ውል መሠረት በወቅቱ ንብረቱን ገቢ ባለማድረጋቸው በድምሩ ብር 2,625,402.93 የቅጣት ክፍያ እንዲከፍሉ መደረግ ሲገባው እንዲከፍሉ ያልተደረገ መሆኑ በአጠቃላይ ድምር ብር 83,735,402.93 የቅጣት ክፍያ ያልተሰበሰበ መሆኑ እና ያልተሰበሰበው ቅጣት ብር 83,735,402.93 ከሚመለከታቸው ላይ ተሰብስቦ ገቢ እንዲደረግ፣

- በድምሩ ብር 18,870,460.03 ዩኒቨርሲቲው ለአካዳሚክ ምርምር፣ ለላብራቶሪ ዕቃዎችና የህክምና እቃዎች እና ለመኪና፣ ላውንደሪ እና Retinal Camera ላስገባበት ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቀረጥ እንደከፈለ ቢገለጽም ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ወይም ደረሰኙን ሊተካ የሚችል ማረጋገጫ ደብዳቤ ባለመቅረቡ ንብረቱ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ መሆኑን ማረጋገጥ አለመቻሉና ቀረጥ ተከፍሎባቸው ገቡ የተባሉት ንብረቶች
- ለመግባታቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ወይም ከንብረት ክፍል ማረጋገጫ ሊቀርብ የሚገባ መሆኑ፣
- የ2005 በጀት አመት ኦዲት ሲደረግ እንደተመለከትነው በተቋሙ ውስጥ ለሚሰሩ አንዳንድ ሰራተኞች እና መምህራን የቤት ኪራይ እንደሚሸፍን የሚታወቅ ሲሆን ከሚከፈላቸው ክፍያ ላይ ታክስ ቆርጦ መክፈል ሲገባው በድምሩ ብር 1,494,517.99 ዩኒቨርሲቲው ታክሱን ከውስጥ ገቢው በመሸፈን ክፍያ የፈጸመ መሆኑና የዩኒቨርሲቲው የክፍያ ስርአት የመንግስት ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ መሆን ስላለበት ከውስጥ ገቢ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከታቸው አካል ተመላሽ እንዲደረግ ። በተጨማሪም የድጎማ ክፍያ ላይ ታክስ ሳይቀነስ የተከፈለው ከሚመለከተው አካል ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ እንደሚገባ፤
- በጅማ ዩኒቨርሲቲ በኮንትራት ቅጥር ተመድበው የሚስሩ በምህንድስና እና ጠቅላላ አገልግሎት ክፍል የሚገኙ ባለሙያዎች ከመንግስት ደንብ እና መመሪያ ውጭ በማኔጅመንት ውሳኔ ደመወዝ፤ የሙያ አበልና፤ የቤት አበል በጠቅላላ ድምር ብር 409,900.00 ከሲቪል ሰርቪስ ሚ/ር መስሪያ ቤት ፍቃድ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል።

- በጅማ ዩኒቨርሲቲ የክረምት ትምህርት ለሚከታተሉ ተማሪዎች መማሪያ የሚሆን ሞጁል ለመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች በገፅ ብር 104.00፣ ለሁለተኛ ዲግሪ በገፅ ብር 150.00፤ ሞጁሉን ለማረም በገፅ ብር 17.00፤ ሞጁሉን ለመከለስ በገፅ ብር 150.00 በመንግስት የተቀመጠ መመሪያና ደንብ ሳይኖር በድምሩ ብር 377,200.00 ከመመሪያ ውጪ ክፍሎ ተገኝቷል።በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው በስሩ ለሚገኙ መምህራንና የህክምና ባለሙያዎች ለሞጁላራይዜሽን ዝግጅት፤ ለኤክስትራ ወርክ ሎድ፤ ቲቶሪያል ለሰጡበት፤ የተሰሩ ስራዎችን ዶክመንት ላደረጉበት፤ እና በተለያዩ ጉዳዮች ለተሳተፉበት በሚል በድምሩ ብር 2,370,524.34 የከፈለ ሲሆን በጠቅላላ ድምር የብር 2,747,724.34 ከደንብና ከመመሪያ ውጪ ክፍያ ፈጽሞ መገኘቱ፡፡
- በ2005 በጀት ዓመት በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚሰሩት የአስተዳደር ሠራተኞች፣ የፋይናንስ ክፍል ስራተኞች ፣ በማኔጅመንት ውሳኔ ቶፕአፕ (TOP UP)የሠራተኛ ማትጊያ አበል ከውስጥ ገቢ በድምሩ ብር 1,582,668.37 ከደንብና መመሪያ ውጭ አላግባብ ተከፍሎ መገኘቱና ዩኒቨርሲቲው በስሩ የሚገኙትን የአስተዳደር ሠራተኞች መንግስት ከፈቀደላቸው ውጪ የቤት ኪራይ አበል በሚያገኘው የውስጥ ገቢ በማኔጅመንት ውሳኔ በድምሩ ብር 223,957.80 ከደንብና መመሪያ ውጭ አላግባብ ክፍሎ ተገኝቷል።
- ብር 1,657,148.55 ለተፈጸመ ክፍያ ከድርጅቶቹ ህጋዊ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ፣
    - ብር 1,423,440.00 ለተማሪዎች አበል እና ብር 137,591.83 ለሠራተኞች በድምሩ ብር 1,561,031.83 ከደንብ ውጪ አበል ተከፍሎ መገኘቱ፣
    - የብር 731,179.48 ግዥ ሲፈጸም የዱቤ የሽያጭ ደረሰኝ እንደ ሽያጭ ደረሰኝ ቀርቦ መገኘቱ፣
    - ብር 505,550.18 መነሻ ካፒታል ተመድቦለት ለሚንቀሳቀስና የራሱ የገቢ ምንጭ ላላቸው መዝናኛ ክበቦች የዕቃና አገልግሎት ግዥ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣

መቱ ዩኒቨርስቲ

- ብር 6,001,683.21 ኮንትራክተሮች የገንዘብ እጥረት ስላጋጠማቸው በሚል ብድር ተሰጥቶ መገኘቱ እና ለመውሰዳቸው ከድርጅቶቹ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ብር 12,225,995.14 በነጭ ወረቀት የተዘጋጀና የደረሰኝ ተከታታይ ቁጥር በሌለው ተራ ወረቀት ለኮንትራክተሮች ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- ብር 3,568,559,99 መቀነስ ከሚገባው የሲሚንቶ ዋጋ በታች በመቀነሱ ከኮንትራክተሮች በዕዳ የሚፈለግ ሲሆን፣ ብር 962,557.36 ደግሞ ከኮንትራክተሮች ላይ መቀነስ የሚገባው የሲሚንቶ ዕዳ ሳይቀነስ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- ብር 151,137.00 የግንባታ ሥራ የሚያከናውኑ ኮንትራክተሮች አፈር በመድፋታቸው እና አፈሩን ለማስነሳት በሚል ተከፍሎ መገኘቱ፣
- ብር 15,842,757.83 ንብረቱ ወጪ የሆነበት ሞዴል 22 ማስረጃው ከሰነድ ጋር ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- ብር 299,101.70 ከደንብና መመሪያ ውጪ ቤት ለተሰጣቸው ሠራተኞች የቤት አበል ተከፍሎ መገኘቱ፣

ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የዩኒቨርሲቲውን የ2005/2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በማድረግ የኦዲት ውጤትና የማሻሻያ ሀሳቦች የያዘ ሪፖርት ለተቋሙ ያቀረበ ቢሆንም በተሰጠው አስተያየት መሠረት የእርምትና የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም፤

ሠመራ ዩኒቨርስቲ፡-

- በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4202 ብር 123,599.27 በጉድለት የተያዘው አለመተካቱ፣

- በተሰብሳቢ ሂሳብ 4211 ብር 113,860.31 በጥቅል የተያዘው ሂሳብ ባለዕዳው የማይታወቅ በመሆኑ ጉዳዩ ተጣርቶ ገንዘቡ እንዲሰበሰብ፤
- በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4274 ብር 131,533.82 ብር ተቀጽላ ሌጀር ባለመኖሩ ገንዘቡ ከማን እንደሚሰበሰብ የሚገልጽ ማስረጃ ባለመኖሩ ጉዳዩ ተጣርቶ ገንዘቡ እንዲተካ፤

በልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት
የ2007 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ
መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት

1. የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ ዕቅድና ክንውን

1.1. ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ የያዛቸውን ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ የሰላሳ ዘጠኝ መሥሪያ ቤቶችን የኦዲት ሥራ አጠናቋል፡፡ ይህም የዕቅዱን 100% የሸፈነ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

1.2. በኦዲት ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶችን ዝርዝር፣ በ2007 በጀት ዓመት የተፈቀደላቸውን የመደበኛና የካፒታል በጀት እና የበጀት ዓመቱን ሂሳብ የዘጉበትን ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተራ ቁ.	የመሥሪያ ቤቱ ስም	ሒሳብ የዘጉበትቀን	የተፈቀደ በጀት ለመደበኛ በጀት	ለካፒታል በጀት	ድምር
1	የቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር	05/04/08	834,069,917.30	476,584,470.86	1,310,654,388.16
1.1	የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት				
1.2	የብሄራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል				
1.3	የቀድሞው የቅድመ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት				
1.4	የሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ				
1.5	የገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ				
1.6	የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ				
2	የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	22/12/07	32,660,809.94	629,054,825.57	661,715,635.51
2.1	የገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል				
3	የቀድሞው የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር	02/02/08	69,032,047.14	3,096,221,049.00	3,165,253,096.14
4	የቀድሞው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	17/03/08	102,790,188.59	604,453,420.00	707,243,608.59
4.1	የተቀናጀ የከተማ መሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት				
4.2	የመንግሥት ቤቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት				
	የሚዞር ድምር		**1,038,552,962.97**	**4,806,313,765.43**	**5,844,866,728.40**

ተራ ቁ.	የመሥሪያ ቤቱ ስም	የተፈቀደ በጀት			
		ሒሳብ የዘጉበት ቀን	ለመደበኛ በጀት	ለካፒታል በጀት	ድምር
	የዞረ ድምር		1,038,552,962.97	4,806,313,765.43	5,844,866,728.40
5	የኢትዮጵያ ምግብ ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን	10/01/08	60,854,746.39	4,486,220.44	65,340,966.83
6	የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ	08/02/08	50,428,068.00	55,247,160.00	105,675,228.00
7	የቀድሞው የማዕድን ሚኒስቴር	24/01/08	31,132,541.26	49,511,360.00	80,643,901.26
8	የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት	04/11/07	5,825,591.62	50,000,000.00	55,825,591.62
9	የኢትዮጵያሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	23/12/07	21,304,610.00		21,304,610.00
10	የትራንስፖርት ሚኒስቴር	15/01/08	42,157,609.44		42,157,609.44
11	የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዥድ ሆስፒታል	20/01/08	45,219,847.49	71,600,000.00	116,819,847.49
12	የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት	20/12/07	52,043,568.91	16,520,880.00	68,564,448.91
13	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	5/01/08	65,146,979.35		65,146,979.35
14	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	06/11/07	45,773,014.03	94,000,000.00	139,773,014.03
15	የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ	13/01/08	19,731,164.30		19,731,164.30
16	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	22/04/08	69,317,522.00	21,021,525.31	90,339,047.31
17	የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን	14/01/08	32,185,370.00		32,185,370.00
18	የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ	06/01/08	32,169,364.20		32,169,364.20
19	የቀድሞው የኢፌዲሪ ስፖርት ኮሚሽን	25/12/07	69,918,606.76	375,520,000.00	445,438,606.76
20	የብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት	25/01/08	26,241,745.90	8,000,000.00	34,241,745.90
21	የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን	24/01/08	10,815,463.43		10,815,463.43
22	የብሔራዊ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ አስተዳደር ጽህፈት ቤት	18/11/07	1,323,980.00		1,323,980.00
23	የህብረት ሥራ ኤጀንሲ	10/01/08	18,585,970.00		18,585,970.00
24	የቀድሞው የአካባቢና ደን ሚኒስቴር	18/01/08	76,733,438.89	27,045,290.00	103,778,728.89
	የሚዞር ድምር		1,815,462,164.94	5,579,266,201.18	7,394,728,366.12

ተራ ቁ.	የመሥሪያ ቤቱ ስም	የተፈቀደ በጀት			
		ሒሳብ የዘጉበትቀን	ለመደበኛ በጀት	ለካፒታል በጀት	ድምር
	የዞረ ድምር		1,815,462,164.94	5,579,266,201.18	7,394,728,366.12
25	የመንገድ ፈንድ ጽሕፈት ቤት	29/12/07	6,625,250.00		6,625,250.00
26	የሰራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር	05/04/08	26,594,108.72		26,594,108.72
27	የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን	13/01/08	9,281,083.44	4,278,142.04	13,559,225.48
28	የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን	26/12/07	19,882,644.00	15,000,000.00	34,882,644.00
29	የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን	25/01/08	67,408,229.00	63,046,080.00	130,454,309.00
30	የኢትዮጵያ ጤና መድኅን ኤጀንሲ	25/12/07	57,902,440.00		57,902,440.00
31	የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል	22/01/08	31,380,813.41	120,085,882.91	151,466,696.32
32	የአለርት ማዕከል	19/01/08	68,612,900.00	18,060,000.00	86,672,900.00
33	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	28/01/08	181,360,410.55	263,029,554.09	444,389,964.64
34	የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን	25/01/08	41,167,426.27		41,167,426.27
35	የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ	03/02/08	34,238,710.25		34,238,710.25
36	የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን	22/12/07	10,000,000.00		10,000,000.00
37	የውሃ ቴክኖሎጂ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት	11/02/08	15,000,000.00		15,000,000.00
38	የኢትዮጵያ ግብርና ኢንቨስትመንት መሬት አስተዳደር ኤጀንሲ	19/12/07	16,525,870.00		16,525,870.00
39	የምግብ መጠጥና ፋርማስቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	23/02/08	18,194,782.80		18,194,782.80
	ጠቅላላ ድምር		2,419,636,833.38	6,062,765,860.22	8,482,402,693.60

1.3 የተሰጠው የኦዲት አስተያየት

በዳይሬክቶሬቱ ኦዲት ለተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው አጥጋቢ ያልሆነ የኦዲት አስተያየት ለ11 መሥሪያ ቤቶች፤ የኦዲት አስተያየት መስጠት ያልተቻለ ለ1 መሥሪያ ቤት፤ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ነቀፌታ ያለበት የኦዲት አስተያየት ለ14 መሥሪያ ቤቶች፣ ነቀፌታ የሌለበት የኦዲት አስተያየት ደግሞ ለ13 መሥሪያ ቤቶች ተሰጥቷቸዋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-2 ተመልክቷል።/

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች

በዳይሬክቶሬቱ በ2007 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

2 የገቢ ሂሳብ

2.1 በውስጥ ገቢ አሰባሰብ ላይ የታዩ የአሰራር ክፍተቶች

2.1.1 ግኝት

1. **በብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ**

- ኤጀንሲው በበጀት ዓመቱ ለሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የአየር ትንቢያ መረጃ አገልግሎት ለሰጠበት ብር 507,000.00 ገቢ የሰበሰበ ቢሆንም ለገቢው በሚመለከተው አካል የጸደቀ ታሪፍ ባለመኖሩ ምክንያት ገቢው በታሪፉ መሰረት ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ ያልተቻለ ሲሆን፣ ስለሁኔታው በ2006 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

2. **በኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን**

- ✓ ባለሥልጣኑ በገቢ ደረሰኝ ከአደን የሰበሰበው ገቢ የገንዘብ መጠን ብቻ የሚገለጽ በመሆኑ በአደን ወቅት የሚታደኑ እንስሳት ብዛት፤ ስምና በየራሳቸው የሚከፈለው ታሪፍ፤ አዳኞች ይዘውት የሚገቡት የአደን

መሳሪያ ብዛትና የተከፈለው ታሪፍ በዝርዝር የማይጠቀስ በመሆኑ የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

- ✓ የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚያስተዳድራቸው ፓርኮች የሰበሰቡት ገቢ ብር 1,994,448.02 በታሪፉ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፓርኮች ገቢ የሰበሰቡበት የገቢ ደረሰኞች ቁጥሮች በዋናው መሥሪያ ቤት በሚዘጋጁት የገቢ ደረሰኞች ላይ የማይጠቃቀሱ በመሆኑ የገቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻል ሲሆን፣ ቀደም ሲል በተደረገው ኦዲት ወቅትም ተመሳሳይ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እንዲስተካከል ያልተደረገ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

1.1.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

- ✓ ያለታሪፍ ለሚሰበሰበው ገቢ ታሪፍ እንዲወጣለትና በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ መደረግ እንዳለበት እንዲሁም ለተሰበሰበው ገቢም የደንበኞች የአገልግሎት መጠየቂያና መፍቀጃ መረጃ ሊቀርብ እንደሚገባ፤
- ✓ የገቢ ሂሳቦቹ የገቢ ምንጭ በዝርዝር እንዲገለጽ እየተደረገ ትክክለኛነታቸው መረጋገጥ እንዳለበት፤
- ✓ በየፓርኮቹ ገቢ የተሰበሰበባቸው የገቢ ደረሰኝ ቁጥሮች በዋናው መሥሪያ ቤት በሚዘጋጁት የገቢ ደረሰኞች ላይ እንዲጠቃቀሱ መደረግ ያለበት መሆኑን፤

አሳስበናል፡፡

2.2 <u>ገቢ ያልተደረገ ሂሳብ</u>

1.2.1 <u>ግኝት</u>

ታህሳስ 23 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር በጠ2/6/64 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በስተላለፈው መመሪያ መሰረት የከፍተኛ ትምህርት

ተቋማት የሚሰበሰቡትን የውስጥ ገቢ የመንግሥት ፋይናንስ ደንብና መመሪያ ተከትለው በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መልኩ መጠቀም እንዲችሉ በተላለፈው የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 መሰረት የፌዴራል ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎችም ከጥር 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲያውሉ ተፈቅዷል፡፡ በመሆኑም ከውሳኔው በፊት ከግል ህክምና አገልግሎቱ የተሰበሰበው 15% የትርፍ ድርሻ ፈሰስ መደረጉ ሲጣራ፡

1. **<u>በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ</u>**

- ✓ ከግል የህክምና አገልግሎቱ ከሐምሌ 1 ቀን 2005 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2006 ድረስ ያለው የኮሌጁ የትርፍ ድርሻ ብር 1,611,851.48 ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ በ2004 እና በ2005 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት ከግል የህክምና አገልግሎቱ ገቢ የኮሌጁ የትርፍ ድርሻ ፈሰስ ያልተደረገ በመሆኑ ገንዘቡ ፈሰስ እንዲደረግ በየበጀት ዓመቱ ኦዲት ወቅት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የማሰተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

2. **<u>የአለርት ማዕከል</u>**

- ✓ ከግል የህክምና አግልግሎቱ ከግል የህክምና አገልግሎት ከሀምሌ 2006 አስከ ሰኔ 2007 ዓ.ም ድረስ ከተገኘው የትርፍ ሂሳብ ብር 2,395,357.15 ውስጥ መመሪያው ከመውጣቱ በፊት እስከ ታኅሳስ 30 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ ያለው የማዕከሉ ድርሻ ፈስስ ያልተደረገ መሆኑ ፤
- ✓ በ2005 እና በ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት ከግል የህክምና አገልግሎቱ ገቢ የማዕከሉ የትርፍ ድርሻ ፈሰስ ያልተደረገ በመሆኑ ገንዘቡ ፈሰስ እንዲደረግ በየበጀት ዓመቱ ኦዲት ወቅት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የማሰተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

1.2.2 የማሻሻያ ሀሳብ

መመሪያው ተግባራዊ እንዲሆን ከተወሰነው ከጥር 1 ቀን 2007 በፊት ያለው ከግል የህክምና አገልግሎቱ 15% የኮሌጁና የማዕከሉ ድርሻ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ፈሰስ መደረግ እንዳለበት ወይም እንዲፈቀድ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

1.3 የውስጥ ገቢ ዕቅድ ክንውን

1.3.1 ግኝት

የሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ የ2007 በጀት ዓመት የውስጥ ገቢ ዕቅድ ከክንውኑ ጋር ሲመዛዘን ኮሌጁ በ2007 በጀት ዓመት ብር 2,154,690.00 ለመሰብሰብ አቅዶ ብር 303,411.00 የሰበሰበ ሲሆን፤ ብር 1,851,279.00 (86%) በዕቅዱ መሰረት ያልሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡

1.3.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ኮሌጁ በተጨባጭ ማስረጃ ላይ የተደገፈ እቅድ ማቀድ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

2. ተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1 በደንቡ መሰረት ያልተሰበሰበ ወይም ያልተወራረደ ሂሳብ

2.1.1 ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በመመሪያው ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡

ይሁንና በሃያ ሰባት ሂሳብ አቅራቢ መሥሪያ ቤቶች እና በአራት ለግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ በሆኑ መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር 205,888,263.11 ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

ለዝርኑ አባሪ 1 ተያይዟል፡፡

2.1.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ከዓመት ወደ ዓመት ሳይወራረዱ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ የሚታዩ ከሆነ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡት ከመቻላቸውም በላይ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነትና ለጥፋት ሊዳረግ የሚችል ስለሆነ መሥሪያ ቤቶቹ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች እንዲወራረዱ፤ መሰብሰብ የማይችሉትን ደግሞ አጣርተው አስፈላጊውን እርምጃ መወሰድ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

2.2 <u>መደበኛ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ተሰብሳቢ ሂሳቦች</u>

2.2.1 <u>ግኝት</u>

በተሰብሳቢ ተቀጽላ ሌጀሮች (Subsidery ledger) ላይ የተመለከቱት ዝርዝር ሂሳቦች ውጤት ከአጠቃላይ ሌጀሩና (General Ledger) በሂሳብ መግለጫው ጋር ከተመለከተው ሂሳብ ሚዛን ጋር ተመሳሳይ መሆኑን እና ተሰብሳቢ ሂሳቦቹም መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

1. <u>በቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር</u>

በተሰብሳቢ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች ላይ በተለያየ ሂሳብ መደቦች የዞሩት ከወጪ ቀሪ ሂሳቦች መነሻ ሚዛን (Beginning Balance) ብር 5,162,124.97 በክሬዲት ሚዛን የታየ መሆኑ፤

2. **<u>በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጄክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት</u>**

በተሰብሳቢ ተቀጽላ ለጀሮች ላይ በተለያየ ሂሳብ መደቦች የዞሩት ከወጪ ቀሪ ሂሳቦች መነሻ ሚዛን (Beginning Balance) ብር 20,369,072.84 በክሬዲት ሚዛን የታየ መሆኑ፣

3. **<u>በኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን</u>**

በተቀጽላ ለጀሮች ላይ የተመለከቱት ብር 729,935.36 ተሰብሳቢ ሂሳቦች መደበኛ ሚዛናቸው ሳይጠብቁ ክሬዲት ሚዛን የሚያሳዩ መሆኑ፤

4. **<u>በስትራተጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ</u>**

በተቀጽላ ሌጀሮች ላይ የተመለከቱት ብር 588.51 ተሰብሳቢ ሂሳቦች መደበኛ ሚዛናቸው ሳይጠብቁ ክሬዲት ሚዛን የሚያሳዩ መሆኑ፤

5. **<u>በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል</u>**

በተቀጽላ ሌጀሮች ብር 13,969.15 የመደበኛ ሚዛናቸው ሳይጠብቁ ክሬዲት ሚዛን የሚያሳዩ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

2.2.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ወይም የክሬዲት ሚዛናቸውን የጠበቁ ለመሆኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡ የሂሳቡም ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4. ተከፋይ ሒሳብ

4.1 ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ተይዞ የሚገኝ ሂሳብ

4.1.1 ግኝት

በተከፋይ ሒሳብ መግለጫዎቹ ላይ የተመለከቱት ሒሳቦች በተገቢው ማስረጃ የተደገፉ መሆኑንና ለሚመለከተው አካል የሚከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሂሳብ አቅራቢ ከሆኑ አስራ ሶስት መሥሪያ ቤቶች እና ለግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ ከሆኑ ሶስት መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር 32,940,785.39 ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡ ለዝርሩ አባሪ 2 ተያይዟል፡፡

4.1.2 የማሻሻያ ሃሳብ

የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡ ስለሚችሉ መሥሪያ ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳቦቹን ሁኔታ በማጣራት አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ እናሳስበናል፡፡

4.2 መደበኛ የሂሳብ ሚዛኑን ያልጠበቀ ተከፋይ ሂሳብ

4.2.1 ግኝት

በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት የእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን (ዴቢት ወይም ክሬዲት) መጠበቅ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ሆኖም፡

1. **በቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር**

   በተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች ላይ በተለያየ ሂሳብ መደቦች የዞሩት ከወጪ ቀሪ ሂሳቦች መነሻ ሚዛን (Beginning Balance) ብር 2,017,580.24 በዴቢት ሚዛን የታየ መሆኑ፤

2. **<u>በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጄክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት</u>**

በተከፋይ ተቀጽላ ለጀሮች ላይ በተለያየ ሂሳብ መደቦች የዞሩት ከወጪ ቀሪ ሂሳቦች መነሻ ሚዛን (Beginning Balance) ብር 352,509.15 በዴቢት ሚዛን የታየ መሆኑ፤

3. **<u>በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር</u>**

በተከፋይ ሂሳብ መደብ 5054 በሌሎች (Others) ተቀጽላ ሌጀር ላይ ለ2007 በጀት ዓመት የዞረው የተከፋይ ሒሳብ መነሻ (Opening Balance) ብር 163,942,074.98 ክሬዲት ሚዛን ማሳየት ሲገባው ዴቢት ሚዛን ያሳየ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

4.2.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የሒሳቦቹ ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራላቸው፤ ለወደፊቱም በአመዘጋገብ ላይ አስፈላጊው ጥንቃቄ ሁሉ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.3 <u>በማዕድን ሚኒስቴር የሮያሊቲ ክፍያው ለተላከላቸው ለመድረሱ የገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት ስለመሆኑ</u>

4.3.1 <u>ግኝት</u>

በፋይናንስ ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል አምስት አንቀጽ 25(2) መሰረት ለማናቸውም ተመላሽ ገንዘብ፣ በጥሬ ገንዘብ፣ በቼክ ወይም በባንክ ለሚዘዋወር ገንዘብ ተቀባዮ ሕጋዊ ደረሰኝ መስጠት እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ በዚሁ መሰረት የማዕድን ፍቃድ አውጥተው ማዕድን በማምረት ላይ ከሚገኙ ግብር ከፋዮች ውስጥ የሮያሊቲ ክፍያ 40 ከመቶ የክልሎች ድርሻ ለአፋርና ለኦሮሚያ ክልሎች እንዲሁም ለድሬዳዋ መስተዳደር የሮያሊቲ ድርሻ ክፍያ ሲፈጸም ገንዘቡ ለመድረሱ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ብር 61,438,938.44 ለክልሎቹ

በባንክ በኩል የተላከው ሂሳብ ለመድረሱ የሚያሳይ ማረጋገጫ (ደረሰኝ) ያልቀረበ ሲሆን፣ ቀደም ሲል በተደረገው ኦዲት ወቅትም የገቢ ደረሰኝ መቅረብ እንዳለበት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ሁኔታው ያልተስተካከለ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.3.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ገንዘቡ ለመድረሱ የደብዳቤ ማረጋገጫ (ደረሰኝ) መቅረብ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5. የወጪ ሂሳብ

5.1 ጨረታ ሳይወጣ የተፈጸመ ግዥ

5.1.1 ግኝት

የፌዴራል መንግሥት ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት ከብር 100,000.00 በላይ የሚፈጸሙ የዕቃ ግዥዎች እንዲሁም ከብር 75,000.00 በላይ የሚፈጸሙ የአገልግሎት ግዥዎች በግልፅ ጨረታ መከናወን እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ ሆኖም ሂሳብ አቅራቢ በሆኑ አሥራ ሁለት መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው በብር 6,235,309.80 ለተፈጸሙ የእቃና የአገልግሎት ግዥዎች ጨረታ ያልወጣ መሆኑ ታውቋል፡፡

ለዝርዝሩ አባሪ 3 ተያይዟል፡፡

5.1.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ግዥዎች የግዥ መመሪያውን ተከትለው የማይፈጸሙ ከሆነ፡

- በግዢ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያስገኝ፤ ቁጠባን የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል የሚያደርግ በመሆኑ፤

- የመንግሥት ግዢ አፈጻጸምን ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት መደገፍ እንዳይቻልና በጀትን በቁጠባ መጠቀም እንዳይቻል የሚያደርግ መሆኑ፤
- ግልጽ አሰራር እንዳይኖር እና የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን የሚችልና ተጠያቂነትን የሚስከትል በመሆኑ፤

መሥሪያ ቤቶች ግዥ የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትለው ግዥዎችን መፈጸም ያለባቸው መሆኑን አሳስበናል፡፡

5.2 ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ለመውጣቱ ማስረጃ ያልቀረበለት የህግ የማማከር አገልግሎት ግዥ

5.2.1 ግኝት

የፌዴራል መንግሥት ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት ከብር 2,500,000.00 በላይ የሚፈጸሙ የምክር አገልግሎት ግዥዎች በአለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ መከናወናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ለአለም አቀፍ የህግ አማካሪ ኢንተርናሽናል አርቢትሬሽን ግሩፕ በ2007 በጀት ዓመት ብቻ ብር 15,187,734.36 ክፍያ የፈፀመ ቢሆንም በግዥ መመሪያው መሰረት ለአገልግሎት ግዥው አለምአቀፍ ጨረታ ለመውጣቱ የጨረታ ሰነድ፣ ተጨራቾች ለውድድር ያቀረቡት ሰነድ፣ በግዥ ኮሚቴ የጨረታ ግምገማ የተደረገበት ሰነድ ለኦዲት ሥራው እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

5.2.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ክፍያዎችን የሚፈፅም አካል ለክፍያው መሰረት የሆኑትን ህጋዊ ዶክመንቶችን፤ የጨረታ ሰነዶች፣ ተጫራቾች ለውድድር ያቀረቡት ሰነዶች፣ በግዥ ኮሚቴ የጨረታ ግምገማ የተደረገበት ሰነዶችን ከሚገኝበት ቦታ

ተሰብስቦ በተገቢው ሁኔታ በመያዝ ለኦዲቱ ሥራ መቅረብ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.3 የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ

5.3.1 ግኝት

የፌዴራል መንግሥት ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣዉ የእቃና የአገልግሎት ግዢ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 24/3 መሰረት የዋጋ ማወዳደሪያ ተሰብስቦ ሊገዙ ለሚገባቸው ግዢዎች መሥሪያ ቤቶች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሂሳብ አቅራቢ በሆኑ አስር መሥሪያ ቤቶችና ለግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ በሆነ አንድ መሥሪያ ቤት በጠቅላላው በብር 1,047,100.39 ለተፈጸሙ የእቃና የአገልግሎት ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡

ለዝርዝሩ አባሪ 3 ተያይዟል፡፡

5.3.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ግዥዎች የግዥ መመሪያውን ተከትለው የማይፈጸሙ ከሆነ፡

- በግዢ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያስገኝ፤ ቁጠባን የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል የሚያደርግ በመሆኑ፤
- የመንግሥት ግዢ አፈጻጸምን ቀልጣፈና ውጤታማ በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት መደገፍ እንዳይቻልና በጀትን በቁጠባ መጠቀም እንዳይቻል የሚያደርግ በመሆኑ፤
- ግልጽ አሰራር እንዳይኖር እና የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን የሚችል በመሆኑ፤
- ተጠያቂነትን የሚስከትል በመሆኑ፤

መሥሪያ ቤቶች ግዥ የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትለው ግዥዎችን መፈጸም ያለባቸው መሆኑን አሳስበናል፡፡

5.4 <u>የሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ የመምህራን ቤቶች ግንባታ የጨረታ ሂደትን በተመለከተ</u>

5.4.1 <u>ግኝት</u>

ኮሌጁ የመምሕራን መኖሪያ ቤት ግንባታ እስክንድር ታዬ የተባለ የህንጻ ሥራ ተቋራጭ እንዲገነባ በብር 2,177,208.30 ውል የገባ መሆኑ ታውቋል ፡፡ ሆኖም የጨረታው ሂደት አፈጻጸም ሲታይ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡

- በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 29 መሰረት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ መዘጋጀት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም ሰኔ 2002 ዓም በወጣው የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል አራት አንቀጽ 16.5(ሸ) መሰረት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው በጨረታው መጫረት ለሚፈልጉ ተጫራቾች የተሟላና ትክክለኛ የመጫረቻ ሰነድ እንዲያዘጋጁ በሚያስችል ዓይነት ተሟልቶ እና በዝርዝር ተዘጋጅቶ የጨረታው ሰነድ አንድ ክፍል መሆን እንዳለበት ተቀምጧል፡፡ ሆኖም የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ያልቀረበ መሆኑ፤

- ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16(5) መሰረት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ያልተዘጋጀ ከመሆኑም በተጨማሪ በግዥ አጽዳቂ ኮሚቴም የተወሰነው ውሳኔ በፋይናንሻል ግምገማ ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑ፤

- የኮንትራት ውሉ በግዥ መመሪያው ክፍል አራት አንቀጽ 16(27) መሰረት በዝርዝር መዘጋጀት ሲገባው ውል ተብሎ የተዘጋጀው በአጭሩ (በተጠቃለለ መልኩ) መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

4.4.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

- ✓ ግዥው አዋጁንና መመሪያውን ተከትሎ የማይፈጸም ከሆነ ጨረታውን ተዓማኒነት ሊያሳጣውና ለብልሹ አሰራር መንገድ ሊከፍት የሚችል በመሆኑ፤

✓ በውሉ ውስጥ መካተት የሚገባቸው ጉዳዮች የማይካተቱ ከሆነ በሂደት ሊከሰቱ (ሊነሱ) የሚችሉ አከራካሪ ሁኔታዎችን በቀላሉ ለመፍታት እንዳይቻል ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ በመሆኑ፤

ኮሌጁ የግዥ አዋጅንና መመሪያውን ተከትሎ ግዥዎችን መፈጸም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.5 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ

4.5.1 ግኝት

የወጪ ሂሳቦች የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት በተገቢው የሒሳብ መደብ የሚመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአስራ ዘጠኝ ሂሳብ አቅራቢ መሥሪያ ቤቶችና ለቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ በሆኑ ስስት መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር 8,599,994.74 መመዝገብ ባለባቸው የሂሳብ መደቦች ሳይመዘገቡ ተገኝቷል፡፡ ለዝርዝሩ አባሪ 4 ተያይዟል፡፡

4.5.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ክፍያ ከመፈጸሙና ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ለወጪዎቹ በጀት መያዙንና በትክክለኛ የሂሳብ መደብ ለመመዝገባቸው መረጋገጥ እንዳለበትና ለሂሳቡም ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.6 በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ

4.6.1 ግኝት

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት በ2006 በጀት ዓመት በተፈቀደው የበጀት ድልድል መሰረት መሆኑን እና የበጀት ዓመቱ ሂሳብ በበጀት ዓመቱ የሚመዘገብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሰባት ሂሳብ አቅራቢ መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር 566,189.00 የ2006 በጀት ዓመት የወጪ ሂሳቦች በ2007 በጀት ዓመት በወጪ ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡ ለዝርዝሩ አባሪ 4 ተያይዟል፡፡

4.6.2 የማሻሻያ ሀሳብ

የበጀት ዓመቱ ወጪ በበጀት ዓመቱ እንዲመዘገብ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት እናሳስበናል፡፡

4.7 አለአግባብ የተፈጸመ የውሎ አበል ክፍያ

4.7.1 ግኝት

የውሎ አበል ክፍያ የፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ሰኔ 2004 ዓ.ም ባወጣው የመንግሥት ሰራተኞች የአገር ውስጥ የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈፃፀም መመሪያ እና በፌዴራል የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት እንደሚፈጸም ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ፡-

1. የኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በተለያየ ጊዜ በአዋሳና አዳማ ሥልጠና ባካሄደበት ወቅት ሥልጠናውን ለተካፈሉ ሠራተኞች በመመሪያው መሠረት የቀን የውሎ አበል መክፈል ሲገባው ለመኝታ ብር 645,835.12 ለምሳና ለእራት አገልግሎት ብር 467,293.15 እንዲሁም በኮንትራት ለተቀጠሩ ሾፌሮች የአልጋ ሒሣብ ብር 3,628.24 በድምሩ ብር 1,113,128.27 ክፍያ የፈጸመ መሆኑ ፤

2. የማዕድን ነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር ለሠራተኞች በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ለካሄደው ስልጠና ለምሳ አበል ብር 176,645.00 ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

3. የትራንስፖርት ሚኒስቴር የመሥሪያ ቤቱ ባልደረባ ያልሆኑ ግለሰብ አይ.ቲ.ኤስ. (I.T.S) ከአሜሪካ አውሮፓና ጃፓን ጋር በመተባበር የሚችጋን ስቴት ዲትሮይት ባዘጋጀው የአለም አይ.ቲ.ኤስ (Intelligent Transport System) ኮንግርስ ላይ ለተሳተፉ ግለሰብ አለአግባብ የውጭ ጉዞ አበል ክፍያ ብር 84,553.37 የፈጸመ መሆኑ፤

4. የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን በተለያየ ጊዜ ሥልጠና ባከናወነበት ወቅት በሥልጠናው ላይ ለተካፈሉ ሠራተኞች በመመሪያው መሠረት የቀን የውሎ አበል መክፈል ሲገባው ለምሳና ለመኝታ በድምሩ ብር 118,781.49 ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

5. የቀድሞው የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር በአዳማ ድሬ ኢንተርናሽናል ሆቴል ባካሄደው ወርክ ሾፕ ተሳታፊዎች በወርክሾፑ ቆይታ ወቅት ከ 7 እስከ 10 ቀን ድረስ እንደመጡበት አካባቢ በጠቅላለው ብር 176,009.00 አበል እንዲከፈል የተደረገ ቢሆንም ለሁሉም የስልጠና ተሳታፊዎች ለስድስት ቀን የምሳ አበል የሸፈነ ሆኖ ሳለ በተጨማሪ ብር 35,037.00 የውሎ ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

6. <u>በቀድሞው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር</u>

- ከመደበኛ የሥራ ጊዜአቸው ውጪ በዘላቂነት አገልግሎት መስጠት በሚያስገድዱ የሾፌር መደቦች ላይ ተመድበው ለሚሰሩ ሾፌሮችና ረዳቶቻቸው ከየካቲት 1 ቀን 2007 ጀምሮ ልዩ አበል ስለመፈቀዱ ከሲቪል ሰርቪስ (ከፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር) ጥር 9 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ 30/M/13/49/1056 እንዲሁም ሚያዝያ 16 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ 30/M/13/49/1062 በተጻፈ ደብዳቤ መመሪያ ተላልፏል፡፡ ሆኖም መመሪያው ከተላለፈ በኋላ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሾፌሮች ቅዳሜ እና እሁድ እና አምሽተው ለሰሩበት ተብሎ የውሎ አበል ክፍያ እንዲፈጸም በመደረጉ ብር **53,350.90** ከመመሪያ ወጪ አለአግባብ ክፍያ ፈጽሞ መገኘቱ፤

- የቀድሞው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለሰራተኞች ሥልጠና በሰጠበት ወቅት የተፈጸመው ክፍያ ሁኔታ ሲጣራ ህዳር 24 ቀን 2007 ዓ.ም በደረሰኝ ቁጥር 00086526 የተወራረደው ሂሳብ ሲታይ በአንድ ቀን ለ2220 የታሸገ ውሃ ብር 23,794.65 ክፍያ የፈጸመ ሲሆን፣ ይሄ ለተሳታፊዎቹ ቁጥር ሲካፈል አንድ

ሰው በቀን ከ20 በላይ ውኃ የተጠቀመ መሆኑ እና እጅግ የተጋነነ ክፍያ መፈጸሙን ለመገንዘብ የተቻለ መሆኑ፤

7. የምግብ መጠጥና ፋርማስቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ኢንስቲትዩቱ ከሰኔ 26 እስከ ሰኔ 28 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ አመታዊ ትምህርታዊ ጉብኝት በአዳማ ከተማ ሲያደርግ ለአልጋና ለምግብ ክፍያ እንዲፈጸም የሚፈቅድ ህግ በሌለበት ሁኔታ ኢንስቲትዩት ለአልጋ ለአንድ ሰው በቀን ብር 631.00 በጠቅላላው ብር 119,732.20 ለምግብ ብር 93,495.00 በድምሩ ብር 213,227.20 ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 1,815,414.23 አለአግባብ የውሎ አበልና የመስተንግዶ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.7.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ደንብና መመሪያን ሳይከተል የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፣ ለወደፊቱም የውሎ አበል ክፍያዎች የወጣውን መመሪያ ተከትለው መፈጸም እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.8 የወጪ ሂሳብ ማስረጃ ያልቀረበላቸው ሂሳቦች

4.8.1 ግኝት

በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 መሰረት ለወጪ ሂሳቦች ተገቢው ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

1. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለበላይ ኃላፊዎች ሕክምና ወጪ ለተፈጸመው ክፍያ ብር 272,956.87 በመመሪያው መሰረት ማስረጃው ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ ፤

2. **በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፤**

ኢንስቲትዩቱ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮ የኢቦላ በሽታን ለመከላከል ብሎም ከተከሰተ ለመቆጣጠርና የተለያዩ ቅድመ

ዝግጅቶችን ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ለላከው ሂሳብ ብር 800,000.00 የጤና ቢሮው የወጪ ሂሳቡን የሚያሣይ ዝርዝር መግለጫ (Statement of Expenditure) በላከው መሰረት ኢንስቲትዩቱ ግንቦት 5 ቀን 2007 ዓ.ም በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ (Journal Voucher) ቁጥር 592533 መዝግቦ በሒሳብ መግለጫ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ነገር ግን የጤና ቢሮው ያቀረበው ሂሳብ ትክክለኛነትንና አግባብነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

- የጤና ቢሮው የወጪ ሂሳቡን የሚያሣይ ዝርዝር መግለጫ (Statement of Expenditure) የለካው ለብር 758,964.75 ሆኖ ሳለ ለብር 41,035.25 ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ እንዲመዘገብ የተደረገ መሆኑ፤
- የጤና ቢሮው ለወጪ ሂሳቡ በለካው ዝርዝር መግለጫ (Statement of Expenditure) ውስጥ በወጪ ቫውቸር ቁጥር 047692 ለቀረበው ሂሳብ ብር 45,750.00 ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፤
- የጤና ቢሮው ለወጪ ሂሳቡ በለካው ዝርዝር መግለጫ (Statement of Expenditure) ውስጥ በወጪ ቫውቸር ቁጥር 033759 የቀረበው ሂሳብ ብር 600,000.00 ተብሎ ይቅረብ እንጂ የቀረበው የክፍያ ሰርተፊኬት (Payment Certificate) የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ለብር 481,233.69 ከመሆኑም በተጨማሪ ለዚህም ቢሆን የግንባታ ሥራውን ካከናወኑትና ክፍያው ከተፈጸመላቸው ድርጅቶች ገንዘቡን ለመቀበላቸው የክፍያ ደረሰኝ ያልቀረበለት መሆኑ፤

3. በፋይናንስ ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል አምስት አንቀጽ 25(2) መሰረት ለማናቸውም ተመላሽ ገንዘብ፣ በጥሬ ገንዘብ፣ በቼክ ወይም በባንክ ለሚዘዋወር ገንዘብ ተቀባዮ ሕጋዊ ደረሰኝ መስጠት እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ሆኖም የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን በባንክ በኩል ለተለያዩ ተቋማት የስፖንሰር ድጋፍ በሚል ብር 80,000.00 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ሲልክ፡-

- ✓ ገንዘቡ ለተቋማቱ ለመድረሱ የገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፣
- ✓ ለስፖንሰር ሺፕ ለሚሰጥ ተብሎ የተፈቀደ በጀት ሳይኖር ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ፣

4. የተቀናጀ የመሬት ልማት መረጃ ጽህፈት ቤት ሰራተኞች በቢሾፍቱ የሥራ አመራር ኢኒስቲትዩት የመሬት መረጃ ሥርዓት ስታንደርድ ለማዘጋጀት በሄዱበት ወቅት የወጣው ሂሳብ ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ.ም btzUjW የባንክ ክፍያ ማስመስከሪያ ቁጥር 0111081 ሲወራረድ በድምሩ ለብር 6,292.00 የወጪ ማስረጃ ያልቀረበበት መሆኑ ፤
5. በብዝሀ ህይወት ኢንስቲቱት ግንቦት 20 ቀን 2007 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 874797 ለፈጸመው ክፍያ ብር 141,105.00 ፤
6. በሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ለብር **1,622,919.33** የወጪ ሂሳብ ማስረጃዎች ለኦዲቱ ሥራ ሊቀርቡ ያልቻሉ መሆኑ ፤
7. <u>**በገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ**</u>

- ♦ በተለያዩ ጊዜ ሰራተኞች ስም ለወጣው ብር 12,003.00 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብላቸው በወጪ የተመዘገቡ መሆኑ ፤
- ♦ በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 መሰረት ሰራተኛው የሚጠቀመው የህዝብ ትራንስፖርት ከሆነ ለጉዞ ያወጣውን በሚያቀርበው ደረሰኝ መሰረት ወይም የትራንስፖርት መረጃ ማቅረብ የማይቻል ከሆነ ግን የመንገድ ትራንስፖርት በሚያወጣው ተመን መሰረት ሒሳቡ መወራረድ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ሆኖም ለትራንስፖርት ለተፈጸመው ክፍያ ደረሰኝ ሳይቀርብ ወይም ክፍያው በመንገድ ትራስፖርት ተመን መሰረት ለመሆኑ ሳይረጋገጥ ብር 17,500.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

- ለብር 24,818.51 የነዳጅ ክፍያዎች የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብላቸው በወጪ ተመዝግበው የተገኙ መሆኑ፤

8. የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ በወጪ ከተመዘገበው ሂሳብ ውስጥ በቀድሞው የግብርና ሚኒስቴር ትዕዛዝ የጎዴ እና የአማራ ክልል ግብርና ቴ/ሙ/ት/ሥ ኮሌጅ ሂሳብ ከ1996 ዓ.ም በፊት ጀምሮ ለስራ ማስኬጃ ተልኮ በተሰብሳቢ ሂሳብ የተያዘው ሂሳብ በአጣሪ ኮሚቴ ተጣርቶ ብር 22,805.00 በ2007 በጀት ዓመት እንዲወራረድ የተደረገው እና ቀሪው ብር 670,582.80 ደግሞ የ2007 በጀት አመት ወጪ ሂሳብ ሲሆን፣ በድምሩ ለብር 693,387.80 በወጪ እንዲመዘገቡ ለተደረጉት የወጪ ሂሳቦች ማስረጃ ያልቀረበላቸው መሆኑ፤

9. በወጣቶች ስፖርት አካዳሚ ሥር ለሚገኘው የጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ (አሰላ ካምፓስ) ለደመወዝና ለሥራ ማስኬጃ እስከ ሰኔ 30/2007 ድረስ በአካዳሚው የተላከው ሂሳብ በቀጥታ በወጪ ተመዝግቦ በሂሳብ ሪፖርቱ ውስጥ የተካተተ ቢሆንም ለብር 1,344,200.31 የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፤

10. ጽህፈት ቤቱ የ15 ከተሞች የመጠጥ ውሃ ሳኒቴሽን ፕሮጀክት ግንባታ ስትራክቸሮችንናቁሳቁሶች ለጠበቁ ጊዚያዊ የጥበቃ ሰራተኞች አገልግሎት ለሰጡባቸው ቀናቶች ክፍያ ሲፈጽም ተቀናሽ የተደረገው ብር 6,762.50 የደመወዝ ገቢ ግብር ለገቢዎችና ግምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፤

11. የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ በተለያየ ጊዜ ለጎዴና ለአማራ ክልል ቴ/ሙ/ት/ሥ/ ኮሌጆች ለሥራ ማስኬጃ የላከውና በተሰብሳቢ ሂሳብ የተያዘው ሂሳብን ለማወራረድ እንዲቻል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አጣሪ ኮሚቴ አቋቁሞ ሂሳቡ ተጣርቶ በ2007 በጀት ዓመት እንዲወራረድ የተደረገ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ሂሳቡ ሲወራረድ በበቂ ማስረጃ የተደገፈ መሆኑ በናሙና ሲጣራ ኮሌጆቹ የተለያየ ግዥዎችን ሲፈጽሙ የቀነሱት

የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 112,957.79 እና የቅድሚያ ግብር ብር 19,971.00 በድምሩ ብር 132,928.79 ለገቢዎችና ግምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ስለመደረጉ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፤

12. በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ብር 81,545.00 ለጥናትና ምርምር ለሥራ ማስኬጃ ቅድሚያ ክፍያ የፈጸመ ቢሆንም ለወጪው ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ እንዲመዘገብ የተደረገ መሆኑ፤

13. የሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ከሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 308,154.23 እንዲሁም የቅድሚያ ግብር (ዊዝሆልዲንግ) ብር86,309.74 በድምሩ ብር 394,463.97 ለሚመለከተው የገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ገቢ ከመደረጉ በፊት ወዲያው ተቀናሽ እንደተደረገ ምዝገባ እንዲከናወን ያልተደረገና ክፍያው ለመፈጸሙም ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

የታወቀ ሲሆን፣ በድምሩ ለብር 5,517,668.33 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብላቸው በወጪ ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡

4.8.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

- በወጪ ለተመዘገቡት ሂሳቦች ማስረጃዎቹ መቅረብ እንዳለባቸው፤ ማስረጃዎቹ ሊቀርቡ ካልቻሉ ግን ገንዘቡ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት፤
- ለመሥሪያ ቤቶቹ ለተከፈለው ገንዘብ ማስረጃው እስኪቀርብ ድረስ በተሰብሳቢ መዝግቦ በመያዝ ገንዘቡ ለመድረሱ የክፍያ ደረሰኝ ሲቀርብ በወጪ መመዝገብ እንዳለባቸው እንዲሁም ገንዘቡ ለመድረሱ ከድርጅቶቹ የገቢ ደረሰኝ ሊቀርብ እንደሚገባ ፤
- ለጊዜያዊ የጥበቃ ሰራተኞች ደመወዝ ሲከፈል ተቀናሽ የሆነው የደመወዝ ገቢ ግብር ለሚመለከተው አካል ገቢ ለመደረጉ በማስረጃ መደገፍ አለበት፡፡ ለወደፊቱም ደመወዙ እንደተከፈለ ወዲያውኑ ተቀናሽ የሆነው የደመወዝ ገቢ ግብር ለሚመለከተው አካል ገቢ ተደርጎ ማስረጃው ሊቀርብ እንደሚገባ፤

አሳስበናል፡፡

4.9 ከልዩ ልዩ የጥቅማጥቅም ክፍያዎች ላይ ሥራ ግብር ያልተቀነሰ ስለመሆኑ

4.9.1 ግኝት

በገቢ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 13 እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነጻ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም (ለምሳሌ የቤት አበል፣ ቦነስ፣ የዓመት ፍቃድ ክፍያ፣ የአገልግሎት ካሳ ….ወዘተ ከወር ደመወዝ ጋር እተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት በአዋጁና በደንቡ በግልጽ የተመለከተ መሆኑን በመግለጽ ነሐሴ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በቁጥር 1አውግ-54 በተጻፈ ደብዳቤ የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባሳወቀው መሠረት መፈጸሙን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የህብረትሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከመጋቢት 2007 እስከ ሰኔ 2007 ከፈጸመው የቤት አበል ክፍያ ላይ ብር **430,325.00**፤
2. የአካባቢና ደን ሚኒስቴር ከፈጸመው የቤት አበል ክፍያ ብር 2,156,000.00 እና ለልጆች ትምህርት ቤት ክፍያ ብር 84,000.00 በድምሩ ከብር 2,240,000.00 ፤
3. የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታሉ በበጀት ዓመቱ ከፈጸመው የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 2,040,600.03፤

በድምሩ ከብር 4,710,925.03 ለቤት አበልና ለትርፍ ሰዓት ከተፈጸመው ክፍያ ላይ የሥራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.9.2 የማሻሻያ ሀሳብ

በገቢ ግብር አዋጁ፣ ደንብና በተላለፈው መመሪያ መሰረት ያልተቀነሰው የገቢ ግብር ተቀንሶ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.10 <u>ከልዩ ልዩ የጥቅማጥቅም ክፍያዎች ሊቀነስ የሚገባው ሥራ ግብር ያልተቀነሰ ስለመሆኑ</u>

4.10.1 <u>ግኝት</u>

በገቢ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 13 እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነጻ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም (ለምሳሌ የቤት አበል፣ ቦነስ፣ የዓመት ፍቃድ ክፍያ፣ የአገልግሎት ካሳ ....ወዘተ ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት በአዋጁና በደንቡ በግልጽ የተመለከተ መሆኑን በመግለጽ ነሐሴ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በቁጥር 1 አውግ-54 በተጻፈ ደብዳቤ የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባሳወቀው መሠረት መፈጸሙን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

የወጣቶች ስፖርት አካዳሚ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ሲፈጽም መቀነስ ያለበትን የገቢ ግብር ከደመወዛቸው ጋር እየተደመረ መሰላት ሲገባው በተከፈለው የትርፍ ሰዓት ክፍያው ላይ ብቻ ተስልቶ በመቀነሱ ምክንያት ብር 5,538.23

1. የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንስቲትዩት ከየካቲት 2007 እስከ ሰኔ 2007 ከፈጸመው የኃላፊነት አበል እና የቤት አበል ክፍያ ላይ ብር 6,300.00፤
2. የእንሰሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን ከሐምሌ 2006 እስከ ሚያዝያ 2007 ዓ.ም ከፈጸመው የቤት አበል ክፍያ ላይ ብር 5,250.00፤
3. ለቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታሉ የጤና ባለሙያዎች ከተፈጸመው የልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች ክፍያ ላይ ብር 524,976.60 ፤

4. በቀድሞው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የፌዴራል የተቀናጀ የከተማ መሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት

   ✓ የኃላፊነት አበል ከሚከፈላቸው አንድ ሰራተኛ ላይ ብር 6,300.00፤

5. ለምግብ መጠጥና ፋርማስቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ም/ዋና ዳይሬክተሮች ከተፈቀደው የቤት አበል ላይ ብር 9,450.00 ፤

6. ለኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ከተፈቀደው የቤት አበል ብር 15,225.00 ፤

7. በቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር ፡

   - ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሚኒስቴር ዴኤታ ከተፈጸመው የቤት አበል ክፍያ ላይ ብር 24,150.00፤
   - ለብሄራዊ አፈር ምርምር ላብራቶሪ ማዕከል ለመኖሪያ ቤት እና ለኃላፊነት ከተፈቀደው አበል ላይ በግንቦትና በሰኔ ወር 2007 ዓ.ም ዓመት ብር 21,405.70 በድምሩ ብር 618,595.53 ግብር ተቀናሽ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.10.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በገቢ ግብር አዋጁ፣ ደንብና በተላለፈው መመሪያ መሰረት ያልተቀነሰው የገቢ ግብር ተቀንሶ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.11 <u>ሳይፈቀድ ከመመሪያ ውጪ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ</u>

4.11.1 <u>ግኝት</u>

በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 34/2 መሰረት ከሐምሌ 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረግ የትርፍ ሰዓት ሥራ አከፋፈል መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ30/ጠ13/36/8/3 በተጻፈ ደብዳቤ ያሳወቀ ቢሆንም፤

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እንደገና ጳጉሜ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ30/13/37/820 በተጻፈ ደብዳቤ የትርፍ ሰዓት ክፍያው ተግባራዊ ሳይደረግ እንዲቆይ ማሳወቁ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ፡-

- በኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ብር 221,035.10፣
- በኢትዮጵያ የምግብ መድሃኒትና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን ብር 879,123.62፣
- በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ብር 15,597.75፣
- በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ከሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም እስከ መጋቢት 2007 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ብር **336,240.00**፣

በድምሩ ብር 1,451,996.47 የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

4.11.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ለትርፍ ሠዓት የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፣ ለወደፊቱም በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዳይፈጸም ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበት እናሳስበናል፡፡

4.12 <u>በመመሪያው መሰረት ያልተቀነሰ የህክምና ክፍያ</u>

4.12.1 <u>ግኝት</u>

ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚያዝያ 16 ቀን 2004 ዓ.ም በቁጥር መ30-899/4 የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን የሚመሩ ዋና እና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚያገኙትን ጥቅማ ጥቅሞች አሰጣጥ በተመለከተ በተላለፈው መመሪያ መሰረት ቤተሰቦቻቸው በጦር ሀይሎች ሆስፒታል የነጻ ህክምና አገልግሎት ማግኘት እንደሚችሉ ከወር ደሞዛቸው ላይ 1% የህክምና መቀነስ እንዳለበት እንዲሁም ለሚኒስትሮችና ለሚኒስትር ድኤታዎች በምክር ቤት የተፈቀደበትን መመሪያ ጠቅሶ የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ታኅሳስ 4 /1998 ባስተላለፈው ደብዳቤ ቁጥር በጠ1/6/76 ከደመወዛቸው ከደመወዛቸው ላይ በየወሩ 2% የህክምና

መቀነስ እንዳለበት መመሪያ ተላልፏል፡፡ ሆኖም ከሐምሌ 2006 እስከ ሰኔ 2007 ዓ.ም ድረስ በመመሪያው መሰረት መቀነሱ ሲጣራ፡-

ተ.ቁ	የመ/ቤት ስም	የገንዘብ መጠን
1	ከቀድሞው ማዕድን ሚኒስቴር	5,138.52
2	ከኢትዮጲያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ	2,883.31
3	ከኢትዮጵያ ግብርና ኢንቨስትመንት መሬት አስተዳደር ኤጀንሲ	1,309.68
4	ከእንሰሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን	595.92
5	ከስምጥ ሸለቆ ተፋሰስ ባለስልጣን	1,288.20
6	ከቀድሞው የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር	2,337.60
7	ከቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር	13,901.16
8	በቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር ከብሄራዊ አፈር ምርምር ላብራቶሪ ማዕከል	140.40
	ድምር	27,594.79

በድምሩ ብር 27,594.79 ያልተቀነሰ የህክምና ክፍያ መኖሩ ታውቋል፡፡

4.12.2 የማሻሻያ ሀሳብ

በተላለፈው መመሪያ መሰረት ያልተቀነሰው የህክምና ክፍያ እንዲቀነስ፤ ለወደፊቱም በተላለፈው መመሪያ መሰረት እንዲፈጸም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.13 በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ

4.13.1 ግኝት

መሥሪያ ቤቶች የሚፈጽሟቸው ክፍያዎች አግባብነት ያለውን ደንብና መመሪያ ተከትለው የሚፈጸሙና በሚለከተው አካል የተፈቀዱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. **<u>በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ</u>**

- የአካዳሚው አስተዳደር ቦርድ ለሰልጣኞች የኪስ ገንዘብ እንዲከፈል ያቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሳይጸድቅ ብር 552,500.00 የኪስ ገንዘብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- የምርምር ጥናት ጽሁፍ እና የቢ.ፒ.አር. ጥናት ላቀረቡ የአካዳሚው ሠራተኞች ማበረታቻ ተብሎ በድምሩ ብር 177,914.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

2. **<u>የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል</u>**

ከጥናትና ምርምር ሥራ ጋር በተያያዘ ለተለያዩ የሆስፒታሉ ሰራተኞች ለኪስ አበል የሚፈጸመው ክፍያ በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድና ለክፍያው መሰረቱ ምን እንደሆነ ሳይታወቅ ብር 67,300.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

3. **<u>የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል</u>**

ሆስፒታሉ የትምህርትና ምርምር ዕዉቅና ሳይኖረው እና ሳይፈቀድ የራሱን የውስጥ የክፍያ መመሪያ በማውጣት ለምርምርና ለሥልጠና ብር 1,266,904.00 ክፍያ የፈጸመ ቢሆንም ክፍያው ለሚመለከተው አካል የመንግሥት አካል ቀርቦ እንዲጸድቅ ያልተደረገ ሲሆን፣ በ2005 እና በ2006 በጀት ዓመታት ኦዲት ወቅትም ሁኔታው እንዲስተካከል አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

4.13.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በሚመለከተው የመንግሥት አካል ያልተፈቀደ አበል ክፍያ መፈጸም አግባብ ባለመሆኑ ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱ ክፍያው በሚመለከተው አካል እንዲፈቀድ መደረግ እንዳለበትና ሳይፈቀድ ክፍያ መፈጸም እንደሌለበት አሳስበናል፡፡

4.14 በበጀት ሂሳብ ላይ በወጪ እንዲመዘገብ ተደርጎ ወደ ፕሮጀክት የተዛወረ ሂሳብ

4.14.1 ግኝት

የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት በ6412 በሂሳብ መደብ ለብድር መስጠትና ማስመለስ እንዲውል ብር 50 ሚሊዮን በጀት የተፈቀደለት ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከተያዘለት በጀት ውስጥ ሳይጠቀሙበት የቀረውን ብር 50 ሚሊዮን በወጪ ሒሳብ መደብ 6412 በወጪ መዝግቦ ወደ ጽህፈት ቤቱ ፕሮጀክት ሂሳብ እንዲዞር ያደረገ ሲሆን፣ በ2004፣ በ2005 እና በ2006 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም ወደ ፕሮጀክት (ፈንድ) ሂሳብ እንዲዞር የተደረገው ሂሳብ በተሰብሳቢ ሒሳብ መያዝ እንዳለበት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በዚህ ኦዲት ወቅትም አሰራሩ የቀጠለ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.14.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ለብድር መስጠትና ማስመለስ አገልግሎት እንዲውል ከመንግሥት በጀቱ የተፈቀደው ለከተሞች መጠጥ ዉሀ አገልግሎት እንዲውል ብድሩ ተሰጥቶ በሥራ ላይ እንዲውልና ከተሞቹ ብድሩን ከፈንዱ ጽህፈት ቤት ጋር ባደረጉት ውል (ሥምምነት) መሰረት ለማስመለስ እንዲቻል ነው፡፡ በጀቱም ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ማረጋገጥ የሚቻለው በበጀት ዓመቱ ለየከተሞቹ በብድር ተሰጥቶ ገንዘብ በተሰብሳቢ ሒሳብ ተይዞ ብድሩ በውሉ መሰረት እየተሰበሰበ መሆኑን ማረጋገጥ ሲቻል ብቻ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ለብድር መስጠትና ማስመለስ አገልግሎት እንዲውል የተፈቀደው በጀት በወጪ ሲመዘገብ አንድ የወጪ ሂሳብ ማሟላት የሚገባዉን ነገር ሁሉ ሊያሟላ ይገባል፡፡ ስለሆነም በበጀት አዋጁ ላይ በጀቱ የተፈቀደው ለብድር መስጠትና ማሰመለሰ በመሆኑና ጽህፈት ቤቱ ለክልሎች በስጦታ ሳይሆን በረጅም ጊዜ ለሚመልሱት የብድር አገልግሎት እየሰጠ የሚሰበስበው ገንዘብ በመሆኑ እና ያልወጣን ወጪ ወደ ፕሮጀክት ሂሳብ ለማዞር ሲባል ብቻ በወጪ መመዝገብ የሂሳብ መግለጫውን

ተዓማኒነት የሚያሳጣው በመሆኑ አሰራሩ ሊስተካከል እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.15 በመረጃ ያልተደገፉ የሂሳብ ማስተካከያዎች

4.15.1 ግኝት

የምዝገባ ለውጦች ሲደረጉ የፋይናንስ ሥርዓትና መመሪያን መሰረት በማድረግ ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያዎች የተሰራላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለብር 23,138,963.90 ለተሠሩት የሂሳብ ማስተካከያዎች ስህተቱ በየትኛው የገቢና የወጪ ደረሰኞች ላይ እንደተፈፀመ እንዲሁም የሂሳብ ማስተካከያው እንዲሠራ ያስፈለገበት ምክንያት፣ ማስተካከያ በተሰራበት የሂሣብ ምዝገባ ማዘዣ ላይ በአግባቡና ጭራሹኑ ባለመገለጹ ማስተካከያው ትክክለኛ መሆን ወይም አለመሆኑን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ ፤
2. የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ለብር 145,703.55 የተሰሩት የሂሳብ ማስተካከያዎች በተጨባጭ መረጃ ያልተደገፉ እና ግልጽነት የጎደላቸው መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

4.15.2 የማሻሻያ ሀሳብ

በፋይናንስ ሥርዓትና መመሪያው መሰረት ለአመዘጋገብ ስህተቶች የተሰሩት የሂሳብ ማስተካከያዎች በተገቢው መረጃ መደገፋቸው እንዲረጋገጥ መደረግ እንዳለበት፤ ሂሳብ እንዲገጥም ወይም የተወሰኑ የሒሳብ መደቦች ላይ የሚታዩ ሒሳቦችን ለማጥፋት ተብለው የሚሠሩ ማስተካከያዎች ለጥፋትና ለጉድለት መንገድ የሚከፍቱና የሂሳብ መግለጫውን ተዓማኒነት የሚያሳጡት በመሆኑ ማስተካከያው የተሰራበት አግባብ በተገቢው ማስረጃ መደገፍ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.16 ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን የማያሳይ የወጪ ሂሳብ

4.16.1 ግኝት

በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የሚፈፀሙ ወጪዎች በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ተመዝግበዉ ወደ ሌጀር ተላልፈውና በሪፖርት ዉስጥ መካተታቸዉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፡

- ✓ ከመደበኛ ሂሳብ በሂሳብ መደብ 6251 ለብር 42,000.00 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 751396 የወጪ ሰነድ ተሰርቶለት የተመዘገበ ቢሆንም የሌጀር ሚዛኑ ብር 42,000.00 ማሳየት ሲገባዉ ዜሮ የሚያሳይና በወጪ ሪፖርቱ ውስጥ ያልተካተተ መሆኑ፤
- ✓ ከካፒታል ሂሳብ በሂሳብ መደብ 6251 የሰኔ 30 ቀን 2007 የሌጀር ሚዛንና በሂሳብ መግለጫ ውስጥ መካተት ያለበት ሂሳብ ብር 14,845,560.75 መሆን ሲገባው ብር 11,962,826.39 ሚዛን የሚያሳይና በወጪ ሪፖርቱ ውስጥ ብር 2,882,734.36 ያልተካተተ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

4.16.2 የማሻሻያ ሀሳብ

የአመዘጋገብ ስህተቱ ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራለት፤ ለወደፊቱም በአመዘጋገብ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.17 ንብረቶቹ ገቢ ሳይሆኑ በወጪ የተመዘገበ የሌተር ኦፍ ክሬዲት (Letter of Credit) ሂሳብ

4.17.1 ግኝት

መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት መሥሪያ ቤቶች በአለም አቀፍ ግዥ ስምምነት መሠረት በባንክ በኩል ለሚከፍቱት ሌተር ኦፍ ክሬዲት ለገቡት ዋስትና የሚተላለፈውን ገንዘብ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መዝግበው በመያዝ ክትትል ማድረግ እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የላቦራቶሪ ዕቃዎችና ኬሚካሎች እንዲሁም ለድሪሊንግ ሥራ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ዕቃዎችን ከውጭ ሀገር ለመግዛት በብር 6,629,165.34 ለከፈተው ሌተር ኦፍ ክሬዲት (Letter of Credit) ሂሳብ በተሰብሳቢ የተያዘ ሲሆን፣ ንብረቶቹ ገቢ ሳይሆኑ በወጪ የመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.17.2 የማሻሻያ ሀሳብ

የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለትና ዕቃው በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ገቢ ሳይደረግ ሂሳቡ በወጪ መያዙ አግባብ ስላልሆነ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.18 የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ያልቀረበለት የአገልግሎት ግዥ

4.18.1 ግኝት

መሥሪያ ቤቱ የኢንዱስትሪ ዘርፍን የ15 ዓመታት የእድገት አቅጣጫ ለማመልከት በተዘጋጀው ፍኖተ ካርታ (Road Map) ላይ ዝርዝር ጥናቶችን
(ስትራቴጂክ ጥናት 2015-2025) ከሚያካሂዱ አራት የከፍተኛ ተቋማት እና ከአንድ ድርጅት ጋር በገባው የውል ስምምነት መሰረት ብር 14,519,235.75 የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ለዩኒቨርስቲዎቹ ክፍያ የፈጸመ ቢሆንም፡

- ዩኒቨርስቲዎች የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተመዝጋቢ ለመሆናቸው የምዝገባ ሰርተፊኬት ያልቀረበ መሆኑ፣
- ለክፍያው የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በ2005 በጀት ተመሳሳይ ክፍያ ፈጽሞ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም፡፡

4.18.2 የማሻሻያ ሀሳብ

በተጨማሪ ዕሴት ታክስ አዋጁ ደንቡና መመሪያ መሰረት አንድ ሰው ወይም ድርጅት የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ለመሰብሰብ በቅድሚያ የታክስ ተመዝጋቢ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ የታክስ ተመዝጋቢ የሆነ ሰው ወይም ድርጅት ደግሞ ለሰበሰበው ታክስ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደረሰኝ መስጠት ግዴታው ነው፡፡ የታክስ ተመዝጋቢ ያልሆነ ሰው ወይም ድርጅት የታክስ ተመዝጋቢ ሳይሆን የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ሊሰበስብ አይችልም፡፡ ስለሆነም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለፈጸመው ክፍያ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ማቅረብ እንዳለበት እናሳስበናል፡፡

5.8 ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎች ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው መሆኑ

4.19.1 ግኝት

መሥሪያ ቤቶች ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በተጻፈላቸው ደብዳቤ መሠረት የቀረጥ ሂሣብ ምዝገባ የሚያከናውኑ ሲሆን፣ በ2007 በጀት ዓመት ቀረጥ የተከፈለባቸው አቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ገቢ ለመደረጋቸው ሲጣራ፡-

- ✓ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 11,989,874.47 ፤
- ✓ በኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ብር 120,302.46፤
- ✓ በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ለብር 2,734,486.29፤
- ✓ በቀድሞው የቅድመ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ብር 321,500,900.33፤

በጠቅላላው ብር 336,345,563.55 የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ የተከናወነ ቢሆንም፣ ቀረጥ ለተከፈለባቸው ንብረቶች የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) እንዲያያዝ ባለመደረጉ ዕቃዎቹ ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

4.19.2 የማሻሻያ ሀሳብ

መሥሪያ ቤቶች የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጥ የተከፈለባቸው ንብረቶች ከቀረጥ ሂሳብ ምዝገባው ጋር እንዲያያዙ መደረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.20 ተቀናሽ የተደረገው ግብርና ታክስ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ገቢ ባለመደረጉ ለቅጣት የተከፈለ

4.20.1 ግኝት

የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ የተለያዩ ግዥዎችና አገልግሎቶች ግዥ ሲፈጽም የቀነሰውን የቅድሚያ ግብርና የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተከፋይ ሂሳብ በአዋጅ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን ገቢ ባለማድረጉ ብር 20,057.09 ቅጣት የከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.20.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ሥራቸውን በአግባቡ በማይፈጽሙ ሰራተኞች ላይ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ፤ ለወደፊቱም ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ገቢ ለመደረጋቸው ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.21 ሕጉ ከሚፈቅድው በላይ የተጨማሪ ሥራ ውል ሥምምነት ስለመፈጸሙ እና በግንባታ አፈጻጸሞች ላይ የታዩ ክፍተቶች

4.21.1 ግኝት

በግዥ መመሪያው አንቀጽ 25(3ለ) መሰረት በተጨማሪነት የሚታዘዘው የግንባታ ሥራ የገንዘብ መጠን ከመጀመሪያው ውል ጠቅላላ ዋጋ ከ30% (ሰላሳ በመቶ) የበለጠ መሆን እንደሌለበት ተመልክቷል፡፡ በዚሁ መሰረት መሥሪያ ቤቶች ለሚያሰሩት ግንባታዎች የተጨማሪ ሥራዎች የውል ሥምምነት የሚፈጸሙት በህጉ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. <u>በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ</u>

- ✓ ለተስፋዬ በርሔ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ለብር **1,180,397.03** የለውጥ ሥራዎች ተብሎ የተፈጸመው ውል የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ከተፈጸመው የመጀመሪያው ውል ብር 1,988,796.25 ጋር ሲነጻጸር 59% መሆኑ፤
- ✓ ለአሰፋ ሐጎስ ቢያድግልኝ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ተቋራጭ የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ለብር **3,768,621.77** የለውጥ ሥራዎች ተብሎ የተፈጸመው ውል የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ከተፈጸመው የመጀመሪያው ውል ብር 1,759,217.14 ጋር ሲነጻጸር 47% መሆኑ፤
- ✓ ለአማረና በጋሻው ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ለብር **496,742.31** የለውጥ ሥራዎች ተብሎ የተፈጸመው ውል የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ከተፈጸመው የመጀመሪያው ውል ብር 645,705.93 ጋር ሲነጻጸር 77% መሆኑ፤
- ✓ ለአድና ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ለብር **3,352,653.71** የለውጥ ሥራዎች ተብሎ የተፈጸመው ውል የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ከተፈጸመው የመጀመሪያው ውል ብር 1,951,159.00 ጋር ሲነጻጸር 58% መሆኑ፤

2. <u>በገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ</u>

- ✓ ኤፍ ኤ ዋይአ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እያከናወነ ያለው የህንጻ ጥገና መጋቢት 2006 ጀምሮ በስምንት ወር ውስጥ ማለቅ እንዳለበት ቢጠቀስም ግንባታው ለአንድ አመት ያህል የዘገየ ከመሆኑም በተጨማሪ ጥገናው የተቋረጠ ሲሆን፣ የሚጠገነው የቢሮ ህንጻ ተቆፋፍሮ ያለሥራ የተቀመጠ ለመሆኑ

- ✓ በመስክ ሥራ ወቅት ለመመልከት የታቸለና ምንም አይነት ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያልተደረገ መሆኑ ፤
- ✓ ለሰርቶ ማሳያ መንገድ ጥገና ብር 71,530.00 በአማካሪው ከቀረበ የክፍያ ሰርተፊኬት በላይ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ፤
- ✓ ለሰርቶ ማሳያ መንገድ ጥገና የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በውሉ መሰረት 20% ብር 538,251.52 መሰጠት ሲገባው 30% ብር 807,377.28 የተሰጠ መሆኑ፤
- ✓ ለሰርቶ ማሳያ መንገድ ጥገና የወጣው የጨረታ ዶክመንት ለኦዲት ሥራ ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፤
- ✓ ለሰርቶ ማሳያ መንገድ ጥገና ለብር 2,619,727.60 የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መንገዶች ባለሥልጣን ያጸደቀው የክፍያ ሰርተፊኬት ኦርጅናል ማስረጃው ለኦዲት ስራው ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

5.34.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ለለውጥ ሥራዎች ተብሎ ተጨማሪ ውል መፈጸም ያለበት የግዥ መመሪያውን ተከትሎ መሆን እንዳለበት፤ መመሪያውን ተከትሎ ያለመፈጸም ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ሊሆን ስለሚችልና ተጠያቂነትንም የሚያስከትል መሆኑን አሳስበናል፡፡

4.22 <u>የለውጥ ሥራ ሥምምነት ውል ከመፈጸሙ በፊት የተፈጸመ ክፍያ እና ሕጉ ከሚፈቅደው በላይ የተፈጸመ የተጨማሪ ሥራ ውል ሥምምነት ስለመገኘቱ</u>

4.22.1 <u>ግኝት</u>

በኮተቤ ለሚገነባው ጠቅላላ ሆስፒታልና የአዕምሮ ጤና ምርምር ሕንጻ ግንባታ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከሣንታ ማሪያ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ጋር ውል የፈጸመ ሲሆን፣ ክፍያዎቹ የግዥ መመሪያውን ተከትለው የተፈጸሙ እና የአመዘጋገብ ሥርዓቱም የገንዘብና

ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያን ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለኮንትራክተሩ የግንባታ ክፍያ እንዲፈጽም ለሆስፒታሉ በጻፈው ደብዳቤ መሰረትና ተያይዞ በተላከው የክፍያ ሰርተፊኬት ቁጥር 6 መሰረት የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ብር 12,541,417.01 ክፍያ ተፈጽሟል፡፡ ነገር ግን በክፍያ ሰርተፊኬቱ ላይ እስከ አሁን የተሰሩ ሥራዎች (Total Executed Work) ተብሎ በቀረበው መጠን ላይ ከውሉ በላይ የተፈጸመውን ክፍያ የሚያጠቃልል የለውጥ ሥራ ውል ለሁለተኛ ጊዜ መስከረም 2008 ዓ.ም ለብር 62,903,277.40 በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተፈርሞ ታኅሳስ 1 ቀን 2008 ዓ.ም ለሆስፒታሉ የተላከ መሆኑ ታውቋል፡፡ ሆኖም፡-

1. የብር 12,541,417.01 ክፍያ የተፈጸመው ግንቦት 28 ቀን 2007 ዓ.ም ሲሆን፣ ለክፍያው ውል የተፈረመው መስከረም 2008 ዓ.ም ክፍያው ከተፈጸመ ከሶስት ወር በኋላ መሆኑ፤

2. በግዥ መመሪያው አንቀጽ 25(3ለ) መሰረት በተጨማሪነት የሚታዘዘው የግንባታ ሥራ የገንዘብ መጠን ከመጀመሪያው ውል ጠቅላላ ዋጋ ከ30% (ሰላሳ በመቶ) የበለጠ መሆን እንደሌለበት የተመለከተ ቢሆንም ለሣንታ ማሪያ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ በጠቅላላው ለብር 81,187,004.35 የለውጥ ሥራዎች ተብሎ የተፈጸመው ውል መጀመሪያው ከተፈጸመው ውል ብር 67,660,053.56 ጋር ሲነጻጸር በ120% የጨመረ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይሄ ደግሞ የግዥ መመሪያውን ያልተከተለና የጣሰ አሰራር መሆኑ፤

3. የግንባታው ሥራ ዋና ውል ሥምምነት ሰኔ 8 ቀን 2002 ዓ.ም የተፈጸመና ግንባታው በ790 የካላንደር ቀናት የሚጠናቀቅ መሆኑ፣ እንዲሁም ለሁለት ጊዜ ያህል የተጨማሪ ሥራ ውል ሥምምነት ሲደረግ ሥራው በ360 የካላንደር ቀናት ለማጠናቀቅ ውል የተፈጸመ ቢሆንም ሥራው በጣም መዘግየት የሚታይበት መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

4.22.2 የማሻሻያ ሀሳብ

- በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት የተጨማሪ የሥራ ውል ሥምምነት ከመደረጉ በፊት ክፍያ መፈጸም ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል፤
- የግዥ መመሪያውን ሳይከተሉ የተጨማሪ ሥራ ውል ሥምምነት መፈጸም የመንግሥት ገንዘብ ያአለአግባብ እንዲወጣና ተገቢ ያልሆነ ክፍያ እንዲፈጸም ምክንያት ሊሆን እንደሚችል፤
- የግንባታ ሥራው በወቅቱ እንዲጠናቀቁ ካልተደረገና ረዘም ያለ ጊዜያት የሚወስዱ ከሆነ መንግሥትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ እንደሚችል፤
- በሆስፒታሉ የሚዘጋጀውን የሂሳብ ሪፖርት ሊያዛባው እና ተዓማኒነቱን ሊያሳጣው እንደሚችል፤
- በተጨማሪም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተጨማሪ የሥራ ውል ሥምምነት ከመፈጸሙ በፊት የክፍያ ትዕዛዝ የተሰጠበትን፣ የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ሳይከተል የተጨማሪ ሥራ ውል ሥምምነት የተፈጸመበትንና፣ የግንባታው ሥራው የዘገየበትን ምክንያት በማጣራት ተገቢውን እርምጃ መወሰድ እንዳለበት፤ በአብዛኛው በሆስፒታሎች የሚደረጉ ግንባታዎች የጨረታ ሂደትና መረጣ፣ የክፍያ ትዕዛዞች እንዲሁም የተጨማሪ ሥራ ውል ሥምምነቶች የሚፈጸሙት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በኩል በመሆኑ እነዚህ የግንባታ ሥራዎች የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትለው መፈጸም እንዳለባቸው፤ በህጉ አግባብ ለመፈጸማቸውም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገባ መሆኑን እናሳስበናል፡፡

4.23 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (Trancation Register) ላይ በወጪ ያልተመዘገቡ እና በሂሳብ መግለጫ ላይ ያልተካተቱና በብልጫ የተካተቱ ሂሳቦች

4.23.1 ግኝት

የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ወጪዎች መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ✓ የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን ግዥ ሲፈጽም ለቀነሰው የቅድሚያ ግብር (5006) ብር 692.52 እና የተጨማሪ ዕሴት ታክስ (5059) ብር 5,193.90 በድምሩ ብር 5,886.42 ደረሰኝ ቢቆርጥም በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ያልተመዘገበ፣ በሂሳብ ሪፖርቱ ውስጥ ያልተካተተና ለሚመለከተው አካል ክፍያው ያልተፈጸመ መሆኑ፤
- ✓ የቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር ከፈጸመው የአገልግሎት ክፍያ ላይ ቀንሶ ላስቀረው የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 81,768.95 እና የቅድሚያ ግብር (ዊዝሆልዲንግ) ብር 10,902.53 በድምሩ ለብር 92,671.48 ለሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ገቢ የተደረገና ምዝገባ የተከናወነ ቢሆንም ገንዘቡ ተቀናሽ ሲደረግ ግን ምንም ዓይነት ምዝገባ ያልተከናወነ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

4.23.2 የማሻሻያ ሀሳብ

በምዝገባ ላይ የታዩት ክፍተቶች ተጣርተው ተገቢው የማስተካከያ ምዝገባ እንዲከናወን መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.24 በውል ስምምነት መሰረት ያልተፈጸመ ክፍያ

4.24.1 ግኝት

ቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል እና ከሶስት ኮንስትራክሽን ድርጅቶች (ከሳንታ ማርያ፣ ከታይም ኢንጂነሪንግ እና ከሚሊቭ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር) የኤሌክትሪክ ፍጆታ ወጪ የመጋራት ውል ስምምነት ውስጥ የገቡ ሲሆን፣ በዚሁ ውል መሰረት ከህዳር 1 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ብር 19,000 (አስራ ዘጠኝ ሺ) ድረስ ያለውን የኤሌክትሪክ ፍጆታ

ወጪ ሆስፒታሉ ሊከፍል፣ ከተጠቀሰው ብር በላይ ያለውን ደግሞ በድርጅቶቹ እንዲከፈል ስምምነት ውስጥ ገብተው የነበረ ቢሆንም ሆስፒታሉ ከውሉ ስምምነቱ ውጭ በድርጅቶቹ መከፈል የነበረበትን በጥቅሉ ብር 87,831.41 ክፍያ የፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.24.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ሆስፒታሉ በውል ስምምነቱ መሰረት ከውል ተቀባዮች ተገቢውን ገንዘብ ሰብስቦ ለመንግሥት ካዝና ገቢ ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.25 <u>ተገዝተው ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው ንብረቶች</u>

4.25.1 <u>ግኝት</u>

ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የሚፈጽሟቸዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥዎች በፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን የተከተሉ መሆናቸውን፣ የተገዙትም እቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ የሚደረጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ✓ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን በብር 56,000.00 የተገዛ የውሃ ታንከር ግዥ የፈፀመ ሲሆን ዕቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፤
- ✓ የአባይ ተፋሰስ ባለስልጣን በብር 560.28 የተገዙት የጽህፈት መሳሪያዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ለመደረጋቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው መሆኑ፤
- ✓ በአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን በብር 6,100.00 ለተፈጸመው የሴቶች የባህል ልብስ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 ያልተቆረጠለት መሆኑ፤
- ✓ የምርት ገበያ ባለሥልጣን በብር 1,400.00 የፈጸመው የአገር ባህል ልብስ ግዥ በሞ/19 ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን በብር 9,629.86 የተለያዩ ዕቃዎች ግዢ የፈጸመ ሲሆን፣ ንብረቶቹ ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ያልቀረበላቸው መሆኑ፤

✓ <u>የምግብ መጠጥና ፋርማስቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት</u>

- በብር 1,421,174.88 የተገዛ ተሽከርካሪ መኪና በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፤
- በብር 2,825.17 የተገዙት የተለያዩ ዕቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ለመደረጋቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው መሆኑ፤

✓ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ለጎዴ ግብርና ኮሌጅ ከ1996 ዓ.ም እና ከዚያ በኋላ በተለያየ ጊዜ ለሥራ ማስኬጃ የላከውና በተሰብሳቢ የተያዘው ሂሳብ መወራረድ ይችል ዘንድ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አጣሪ ኮሚቴ በማቋቋም ሂሳቡ ተጣርቶ እንዲወራረድ ተደርጓል፡፡ ሆኖም የተወራረደው ሂሳብ በመረጃ የተደገፈ መሆኑ በናሙና ሲጣራ በብር 181,760.00 የተለያዩ ግዢዎች የተፈጸሙ ሲሆን፣ ንብረቶቹ ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ያልቀረበላቸው መሆኑ፤

✓ የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጁ የተለያዩ ዕቃዎች ግዢ በብር 34,145.00 የፈጸመ ቢሆንም ንብረቶቹ ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ያልቀረበ መሆኑ፤

4.25.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

- የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልቀረበ ንብረቶቹ ለመሥሪያ ቤቶቹ አገልግሎት መዋላቸውን ማረጋገጥ የማይቻል በመሆኑ፤
- የመንግሥት ገንዘብ ለታለመለት ዓለማ መዋሉንም ማረጋገጥ የማይቻል በመሆኑ፤

ዕቃዎቹ ለመሥሪያ ቤቶቹ አገልግሎት የዋሉ መሆናቸው ተጣርቶ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲቀርብላቸው አሳስበናል፡፡

4.26 ከሥራ ከለቀቁ በኋላ የተፈጸመ የደመወዝ ክፍያ

4.26.1 ግኝት

በበጀት ዓመቱ የተከፈለውን የደመወዝ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የኢትዮጵያ ዱር እንሰሳት ጥበቃ ባለሥልጣን አንድ ሰራተኛ ከሥራ ከለቀቁ በኋላ ብር 2,578.50 የደመወዝ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
2. የማዕድንና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር ስምንት ሰራተኞች ከሥራ ከለቀቁ በኋላ በድምሩ ብር 15,442.17 የደመወዝ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
3. የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት አንድ ሰራተኛ ከሥራ ከለቀቁ በኋላ ከህዳር 15 እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ ብር 12,667.99 የደመወዝ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
4. በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊንየም ሜዲካል ኮሌጅ የተለያዩ አራት ሰራተኞች ከስራ ከለቀቁ በኋላ ብር 5,007.38 ክፍያ የደመወዝ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

4.26.2 የማሻሻያ ሀሳብ

አለአግባብ የተከፈለው ደመወዝ ተመላሽ እንዲደረግ፣ ለወደፊቱ እንዲህ ዓይነቱ ክፍያ እንዳይፈጸም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.28. ከመመሪያ ዉጪ ለቅድሚያ ግብርና ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተፈጸመ ክፍያ

4.28.1 ግኝት

የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ለጎዴ ግብርና ቴ/ሙ/ት/ሥ ኮሌጅ በተለያየ ጊዜ ለሥራ ማስኬጃ ልኮለት ያወራረደው ሂሳብ ሁኔታ ሲጣራ ኮሌጁ ለፈጸመው የነዳጅ ግዥ

ከአዋጁ፣ ከደንቡና ከመመሪያ ወጪ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ብር 17,583.75 ጨምሮ የከፈለ ሲሆን፣ የቅድሚያ ግብር ክፍያ ብር 1,698.00 ቀንሶ ያስቀረ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.28.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ከህግ ውጪ ክፍያ መፈጸም፡-

- ✓ ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፣
- ✓ ተጠያቂነትን ሊያሥከትል ስለሚችል፤

ማንኛውም ግዥ ከመፈጸሙ በፊት የሚገዛው እቃም ሆነ አገልግሎት ተጨማሪ እሴት ታክስና የቅድሚያ ግብር ታክስ ሊቀነስ የሚገባው መሆን አለመሆኑን በማጣራት ግዥው መፈጸም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.29 ሳይከፈል ለሶስት ወራት ያህል በእጅ ላይ የቆየ ገንዘብ

4.29.1 ግኝት

የገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ሰኔ 30 ቀን 2007 ዓ.ም በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 374614 ለገቢዎችና ጉሙሩክ ባለሥልጣን ከመስከረም 2006 ዓ.ም ጀምሮ ከተለያዩ ግዥዎችና የአገልግሎት ክፍያዎች ላይ ተቀናሽ ያደረገውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ የቅድሚያ ግብር እንዲሁም ከኮንትራት ቅጥር ሰራተኛ የቀነሰውን የሥራ ግብር ለመክፈል ብር 3,615,045.05 ወጪ አድርጓል፡፡ ሆኖም፡-

- ✓ ቼኩ ወጪ የተደረገው ሰኔ 30/2007 ሲሆን፣ ገንዘቡ ለገቢዎችና ጉሙሩክ የተከፈለው መስከረም 28/2008 ዓ.ም መሆኑ፤
- ✓ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ የቅድሚያ ግብሩና ከሰራተኞች የተቀነሰው የሥራ ግብር በአዋጁና በደንቡ በተቀመጠው መሰረት ገቢ መደረግ ሲገባው ከመስከረም 2006 ዓ.ም ጀምሮ ክፍያው እስከተፈጸመበት መስከረም 2008 ዓ.ም ድረስ ሳይከፈል የቆየ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

4.29.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ታክሱና ግብሩ በግብር ሰብሳቢው የባንክ ሂሳብ በማዘዋወር መፈጸም ሲገባው ገንዘቡ ለሶስት ወራት ያህል ሳይከፈል በግዥ ሰራተኛዋ እጅ መቆየቱ አግባብ ስላልሆነ፣ ለወደፊቱም የሚሰበሰበው የግብርና የታክስ ሂሳብ በአዋጁና በደንቡ መሰረት ለመንግሥት ገቢ እንዲደረግ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.30 ከግዥ ሂሳብ ላይ ያልተቀነሰ ተጨማሪ እሴት ታክስና የቅድሚያ ግብር

4.30.1 ግኝት

የካቲት 8/2002 አ/ም በቁጥር ታክ/ቀ/5/102 በገገርዉ ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣዉ መመሪያ መሰረት ታክሱን የመሰብሰብ ኃላፊነት የተሰጣቸዉ የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ከመጋቢት 1 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ከብር 5,000.00 በላይ ከሚፈጸሙት ግዢ ላይ የተጨማሪ እሴት ክፍያዉን በመቀነስ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ እንዳለባቸዉ ያዛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ባለሥልጣኑ ከፈጸማቸው የዕቃና የአገልግሎት ግዥዎች ላይ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/1994 መሰረት የቅድሚያ ግብር (2%) መቀነስ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ሆኖም የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን የተለያዩ የዕቃና የአገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ከውሃ ሥራዎች እና ዲዛይን ኮንስትራክሽን ድርጅት ብር **140,730.67** የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲሁም ብር 18,764.09 ቅድሚያ ግብር በድምሩ ብር 159,494.76 ቀንሶ ለገቢዎችና ግምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ ሲገባዉ ክፍያዉን ለድርጅቶቹ የፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.30.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ያልተሰበሰበው ገንዘብ ተሰብስቦ ገቢ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የአገልግሎትና የዕቃ ግዥ ሲፈጽም በአዋጁ፣ በደንቡና

በመመሪያው መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የቅድሚያ ግብሩን በመሰብሰብ ለሚመለከተው አካል ገቢ ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

6. ንብረት

6.1 ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች ያለው የንብረት አስተዳደር ሥርዓቱ መንግሥት ባወጣው የንብረት አሰተዳደር መመሪያ መሰረት የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

6.1.1 ግኝት

1. **በቀድሞው የማዕድን ሚኒስቴር**

- ✓ የ2006 በጀት ዓመት መጨረሻ የቋሚ እቃዎች ንብረት ቆጠራ ባለመጠናቀቁ በስቶክ ካርድ ላይ ከሚገኘው ከወጪ ቀሪ ጋር የማመዛዘን ሥራ ያልተከናወነ መሆኑ፤
- ✓ ለአገልግሎት ወጪ የሚደረጉ ቋሚ ንብረቶች በተጠቃሚው ስም የሚመዘገብበት የአመዘጋገብ ሥርዓት የተጀመረ ቢሆንም ምዝገባው ተሟልቶ ያልተከናወነ መሆኑ፤
- ✓ ከመስሪያ ቤቱ ከሥራ የለቀቁ አምስት ሰራተኞች የተረከቡትን የተለያዩ ቋሚ እቃዎች ያላስረከቡ መሆኑ፤

2. **በኢትዮጵያ ዱር እንሰሳት ጥበቃ ባለሥልጣን በነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ**

- ✓ የንብረት መዝገብ ወይም ስቶክ ካርድ ያልተቋቋመና ምዝገባ ያልተከናወነ መሆኑ፤
- ✓ የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኝ (ሞ/19 እና ሞ/22) የማዘጋጀትና ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነት በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፤
- ✓ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ የመኪና ጎማዎች፣ ኮምፒተሮች፣ ታይፕ ራይተሮች፣ የወረቀት መብሻዎች፣ የማባዣ ማሽን፣ የቤት ክዳን ቆርቆሮ፣ አልጋዎች፣ ሳምሶናይቶች፣ የፋክስ ማሽን፣ ስቶቮች፣ ፍሪጆች፣ ቬንቲሌተሮች፣ የመኪና ባትሪዎችና በርሜሎች ተከማችተው የተገኙ መሆኑ፤

- ✓ የዕለት ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ለአገልግሎት ወጪ ሲደረጉና አገልግሎት ከሰጡ በኋላ ለንብረት ክፍል ገቢ ሲደረጉ የንብረት ገቢና ወጪ መቆጣጠሪያ መዝገብ (እስቶክ ካርድ) ያልተዘጋጀና ገቢና ወጪው የማይመዘገብ መሆኑ፤
- ✓ የእለት ገቢ ደረሰኝ የገቢና ወጪ ማድረግያ ደረሰኞች (በሞዴል 19 እና 22) እንዲሁም ገቢና ወጪ የተደረጉ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች (መ/ሂ/1) በአግባቡ የማይመዘገቡ መሆኑ፤

3. <u>በሕብረት ሥራ ኤጀንሲ</u>

- ✓ በሳልቫጅ ግምጃ ቤት ውስጥ ሊወገዱ የሚገባቸውና ተጠግነው አገልገሎት መስጠት የሚችሉ በርካታ አሮጌ 10 ፕሪንተር፣ 11 ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተር፣ 1 ፍሪጅ፤ 20 ዩፒኤስ ፣ 15 ካልኩሌተር ፣ 20 የአንቦ ውሃ ጠርሙስ ፣ 1 ሶኒ ቴፕ ከሁለት እስፒከር ጋር ፣ 8 ላፕቶፕ፣ 1 ዴክ፣ 4 ሳምሶናይት፣ 5 እስክሪን ኮምፒውተር፣ 5 ኤልሲዲ ፕሮጀክተር፣ 1 ጀነሬተር፣ 18 ወንበሮች፣ 1 የመኪና መስታወት፣ 1 መኪና ቲቪ ከነ እስታንዱ፣ 2 ትልቁና 4 ትንሹ እስፒከር፣ 1 የፊልም እና 1 እስክሪን ሸራ ፕሮጀክተር ፣ 1 ክሪክ እና ሌሎችም ቁሳቁሶች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ በአመቱ መጨረሻ ላይ የአላቂ፣ ቃሚ እና የሰልባጅ እቃዎች ንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም የቆጠራው ውጤት ከመዝገብ ወጪ ቀሪ ጋር ያልተገናዘበ መሆኑ፤
- ✓ ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤

4. <u>በኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ</u>

- ✓ በ2006 በጀት ዓመት መጨረሻ የአላቂና ቋሚ እቃዎች ንብረት ቆጠራ የተጀመረ ቢሆንም ቆጠራው ሳይጠናቀቅ ቀርቷል፡፡ በ2007 በጀት ዓመት መጨረሻ ደግሞ ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም በመዝገብ ወይም በስቶክ ካርድ ላይ ከሚታየው ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘን ያልተደረገ መሆኑ፤

- ✓ የአላቂና ቋሚ ንብረቶች በስቶክ ካርድ ላይ የመመዝገብ ሥራ የተጀመረ ቢሆንም ምዝገባው ተሟልቶ ያልተከናወነ መሆኑ፤
- ✓ ለቋሚ ንብረት መለያ ቁጥር ተሟልቶ ያልተሰጠ መሆኑ፤
- ✓ የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ (የቀድሞው የንብረት ክፍል ሠራተኞች ለአዲሶቹ የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲያስረክቡ) ርክክቡ ትክክለኛ ለመሆኑ ኦዲት ተደርጎ ያልተረጋገጠ መሆኑ፤
- ✓ ከቀድሞው ስፖርት ኮሚሽን የመጡ የተለያዩ የቢሮ እቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ገቢ ሳይደረጉ ቀጥታ ወጪ እየተደረጉ የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ ከዋናው ንብረት ክፍል በሞ/22 ወጪ ተደርገው ወደ ምግብ ጥሬ እቃ ግምጃ ቤት የሚገቡና ለአገልግሎት ወጪ የሚደረጉ እቃዎች ገቢና ወጪ የሚደረጉበት ቅጽና የገቢና ወጪ መቆጣጠሪያ መዝገብ ያልተቋቋመና ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፤

5. <u>በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር</u>

- ✓ ብዛት ያላቸው ዴስክ ቶፕ እና ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች የአገልሎት ጊዜያቸው ያለፈና አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ ቢታወቅም ንብረቶቹን ለማስወገድ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
- ✓ በዕርዳታ የተገዙ 13 ስማርት ቦርድ ፍላት እና 13 ፕሮጀክተሮች በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ሳይደረጉ ንብረት ክፍል የተገኙ መሆኑ፤

5.1 <u>በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል</u>

- ♦ በኦዲቱ ወቅት ሰኔ 30 ቀን 2007 ዓ.ም ፈሰስ ያልተደረጉ አላቂ ዕቃዎች ሁኔታ በናሙና ሲጣራ ብር 881,681.73 አላቂ ዕቃዎች በበጀት ዓመቱ ሥራ ላይ ያልዋሉ ሲሆን፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የውስጥ ኦዲተሮች በኩል በፈሰስ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ መሆኑ፤

- በተጠቃሚዎች እጅ ላይ ለሚገኙ ቋሚ ንብረቶች የመቆጣጠሪያ ካርድ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤
- ከመድኃኒት ማከማቻ ክፍል ወጪ ተደርገው በመድኃኒት ማሰራጫ ክፍል ውስጥ የሚገኙ መድኃኒቶች በአመቱ መጨረሻ ቆጠራና ማመዛዘን ያልተደረገ መሆኑ፤
- የመድኃኒት ማሰራጫ ክፍል የበር ቁልፎች መድሃኒቶቹን በኃላፊነት በተረከቡት ባለሙያዎች እጅ መጠበቅ ሲገባቸው በንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት ኃላፊው እጅም የመድኃኒት ቤቶቹ ቁልፎቹ የሚገኙ መሆኑ፤

6. **<u>የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት</u>**

- ✓ በኢንስቲትዩቱ በተጠቃሚዎች እጅ ላይ ለሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (UC) ያልተቋቋመላቸው መሆኑ፤
- ✓ ለቋሚ ዕቃዎች በተሟላ ሁኔታ መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤
- ✓ ከሥራ የለቀቁ አራት ሰራተኞች የተረከቧቸውን ቋሚ ዕቃዎች ያላስረከቡ መሆኑ፤
- ✓ የኢንስቲተትዩቱን ተሽከርካሪዎች የህይወት ታሪክ የሚገልጽ ማህደር በአግባቡ ያልተደራጀ መሆኑ፤
- ✓ በኬሚካልና ላብራቶሪ ግምጃ ቤት ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ የላብራቶሪ መሳሪያ ኬሚካሎች ሪኤጀንቶችና የተለያዩ ዕቃዎች የተገኙ ሲሆን ቀደም ሲል በተደረገው ኦዲት ወቅትም አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

7. **<u>በኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት</u>**

- ✓ ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ማመዛዘኛ ያልተሰራ መሆኑ፤
- ✓ ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ተሟልቶ ያልተሰጠ መሆኑ፤

- ✓ ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነት እና የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኝ (ሞ/19 እና ሞ/22) የማዘጋጀት ስራ በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፤
- ✓ አገልግሎት የማይሰጡና መወገድ ያለባቸው ንብረቶች ያልተለዩና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ ለቋሚ ንብረት ተጠቃሚዎች የንብረት ምዝገባ ካርድ (User Card) ያልተከፈተላቸው መሆኑ፤

8. **<u>የኢትዮጵያ ግብርና ኢንቨስትመንት መሬት አስተዳደር ኤጀንሲ</u>**

- ✓ ንብረት መመዝገብ፣ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እና የንብረት ወጪ ደረሰኝ ማዘጋጀት እንዲሁም የንብረት መጠበቅ ሥራ በአንድ የንብረት ሰራተኛ ኃላፊነት የሚከናወኑ መሆኑ፤
- ✓ ኤጀንሲው ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች የተሟላ መመዝገቢያና መቆጣጠሪያ የሚሆን ስቶክ ካርድ ያልቋቋመ መሆኑ፤
- ✓ ለቋሚ ንብረቶች የመለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤

9. **<u>የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን</u>**

- ✓ የቆጋ ግድብና መስኖ አውታሮች ንብረት መመዝገብ፣ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 እና የንብረት ወጪ ደረሰኝ ሞ/22 ማዘጋጀት እና የንብረት መጠበቅ ሥራ በአንድ ሰው ተደርበው የሚሰሩ መሆኑ፤

10. **<u>በቀድሞው ስፖርት ኮሚሽን</u>**

- ✓ ለቋሚ ንብረት ተጠቃሚ ሰራተኞች አልፎ አልፎ የንብረት ምዝገባ ካርድ (User Card) ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፣ የንብረት ተጠቃሚ ምዝገባ ካርድ (User Card) ለተዘጋጀላቸውም ቢሆን በተጠቃሚው እጅ የሚገኘውን ንብረት ሙሉ በሙሉ የማያሳይ መሆኑ፤
- ✓ ለቋሚ ንብረቶች የመለያ ቁጥር ተሟልቶ ያልተሰጠ መሆኑ፤

- ✓ አልፎ አልፎ ስቶክ ካርድ ያልተከፈተላቸው ንብረቶች የተገኙ መሆኑ፤

11. <u>በስምጥ ሸለቆ ተፋሰስ ባለሥልጣን</u>

- ✓ የገቢና የወጪ ሂሳብ ምዝገባ ያልተከናወነ እና የንብረት ቆጠራው ከእስቶክ ካርድ ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘን ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ በተጠቃሚዎች እጅ ላይ ለሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) ያላቋቋመ መሆኑ፤

12. <u>የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢኒስቲትዩት</u>

- ✓ ስቶክ ካርድ ያልተቋቋመላቸው አላቂና ቋሚ ንብረቶች መኖራቸው፤ ስቶክ ካርድ ለተከፈተላቸው ዕቃዎችም ቢሆንም ምዝገባ ያልተከናወነላቸው ዕቃዎች መኖራቸው፤
- ✓ የንብረት ቆጠራው ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘን ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ አልፎ አልፎ ለቋሚ ንብረቶች የመለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤
- ✓ ኢንስቲትዩቱ ቢሮዎች፣ ለከብቶች መኖ ልማት የሚውል የእርሻ መሬትና ሌሎች መናፈሻ ቦታዎች ያሉት ቢሆንም የባለቤትነት ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሌላቸው መሆኑ፤

13. <u>በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል</u>

- ✓ በተጠቃሚዎች እጅ ላይ ለሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) በተሟላ ሁኔታ ያልተሰራበት መሆኑ፤
- ✓ በቆርቆሮ በተሰራው ንብረት ክፍል ውስጥ እና ከንብረት ክፍሉ ውጭ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ ሊወገዱ አልያም ተጠግነው አገልግሎት ላይ ሊውሉ የሚገባቸው የተለያዩ የህክምና መሳሪያዎች ፣ ሲሊንደሮች፣ ፎቶ ኮፒዎች፣ የመኪና ጎማዎች፣ የመኪና ባትሪዎች፣ የመታጠቢያ ቤት ገንዳ፣ የቧንቧ ቱቦዎች፣

የታይፕ መጻፍያ ማሽኖች (ታይፕ ራይተሮች)፣ ኮምፒውተሮች፣ ሳይወገዱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

14. <u>በቀድሞው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር</u>

- ✓ ከ2006 በጀት ዓመት ጀምሮ የቋሚ ንብረት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ በሚገኙ ቋሚ ንብረቶች ላይ አልፎ አልፎ መለያ ቁጥር ያልተለጠፈ ወይም ያልተጻፈ መሆኑ፤
- ✓ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ባሉት 3 መጋዘኖች ውስጥ፡-
  - ♦ የመኪና አዲስና አሮጌ ጎማዎች ፣ ኮምፒውተሮች፣ የተለያዩ ቢሮ መገልገያ ዕቃዎች ፣ አሮጌ የስልክ ቀፎዎች፣ አሮጌ ላፕቶፖች፣ አዲስና አሮጌ የእንግዳ ወንበሮች፣ የቢሮ ጠረጴዛዎች አዳዲስ የኃላፊ ወንበሮች፣ ካሜራዎች የሚገኙ መሆኑ፤
  - ♦ ከ2001 በጀት ዓመት ጀምሮ ጥቅም ላይ ያልዋሉ በቁጥር 112 የሚሆኑ የተለያየ ቶነሮች የሚገኙ መሆኑ፤
  - ♦ በ2005 በጀት ዓመት የተገዙ የደንብ ልብሶች (ሸሚዞች እና ጫማዎች) ለተጠቃሚዎቹ ሳይታደሉ በመጋዘኖቹ ውስጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

14.1 <u>በቀድሞው ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የመንግሥት ቤቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት</u>

- ♦ በኮምፒውተሮችና በወንበሮች ላይ በከፊል የመለያ ቁጥር ያልተሰጠ (ያልተጻፈ) መሆኑ፤
- ♦ በንብረት ያዥነት የተመደቡ ሰራተኛ ዋስትና ያልያሲያዙ መሆኑ፤
- ♦ የ2007 በጀት ዓመት የቋሚ እቃዎች ቆጠራ የተካሄደ ቢሆንም በቆጠራው ላይ የመተማመኛ ፊርማ ያልተፈረመ መሆኑ፤

- የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና ስቶኮችን የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነት ለአንድ ሰራተኛ የተሰጠ መሆኑ፤

14.2 <u>በቀድሞው ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የተቀናጀ የመሬት ልማት ፕሮጀክት መረጃ ጽህፈት ቤት</u>

- የቋሚ ንብረት ቆጠራ ሲካሄድ በንብረት ክፍል የተቆጠሩት ቋሚ እቃዎች ዋጋ ያልተገለጸ መሆኑ፤
- ያልተቆጠሩ ቋሚ ንብረቶች መኖራቸው፤
- በ2007 በጀት ዓመት መጨረሻ የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ቆጠራው ከመዝገብ ወይም ከስቶክ ካርድ ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተመዛዘነ መሆኑ፤

15. <u>በብሔራዊ ሚትሪዎሎጂ ኤጀንሲ</u>

ከሐምሌ 1/2006 እስከ ሰኔ 30/2007 ዓ.ም ድረስ በስቶክ ካርድ ላይ የአላቂና የቋሚ ዕቃዎች ምዝገባ ያልተከናወነ መሆኑ፤

15.1 <u>በብሔራዊ ሚትሪዎሎጂ ኤጀንሲ የአዳማ ቅርንጫፍ ዳይሬክቶሬት</u>

- የዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊው የንብረት ወጪ ደረሰኝ ሞ/22 የሚያዘጋጅ መሆኑ፤
- አልፎ አልፎ አንዳንድ ዕቃዎች በስቶክ ካርድ ላይ ያልተመዘገቡ መሆኑ፤
- አገልግሎት የማይሰጡ የተለያዩ ዕቃዎች ሳይወገዱ በዕቃ ግምጃ ቤቱ የተገኙ መሆኑ፤

15.2 <u>በብሔራዊ ሚትሪዎሎጂ ኤጀንሲ የጅግጅጋ ቅርንጫፍ ዳይሬክቶሬት</u>

- የዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊዋ የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኝ (ሞ/19 እና ሞ/22) የሚያዘጋጁ መሆኑ፤

- ♦ አልፎ አልፎ አንዳንድ ዕቃዎች በሰቶክ ካርድ ላይ ያልተመዘገቡ መሆኑ፤
- ♦ አገልግሎት የማይሰጡ የተለያዩ ዕቃዎች ሳይወገዱ በዕቃ ግምጃ ቤቱ የተገኙ መሆኑ፤

16. **<u>በብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት</u>**

- ✓ በ2007 በጀት አመት ቋሚና አላቂ ዕቃች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ቆጠራው ከመዝገብ (ከእስቶክ) ካርድ ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘን ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ የመኪና ዕቃዎች የሚገኙ ሲሆን፣ የንብረት ክፍሉ ጣሪያ ክፍት በመሆኑ ንብረቱ ለስርቆትና ለብለሽት የተጋለጠ መሆኑ፤
- ✓ አገልግሎት የማይሰጡ ኮምፒዩተሮች፣ የብረት ጠረጴዛ ፣ ወንበሮች፣ የመኪና ጎማዎች፣ አንድ ቶዮታ ላንድ ክሩዘር፣ ሁለት ፍሪጅ፣ የፎቶግራፍ ካሜራ፣ ማጽጃ ማሽኖች ፣ የዘር መቆጣጠሪያ፣ የፎቶ ኮፒ ማሽን እና አንድ ማርቼዲስ መኪና እንዲሁም በርካታ የተለያዩ ንብረቶች ሳይወገዱ የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ ለሞባይል ካርድ እና ለነዳጅ ኩፖን ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤

17. **<u>በአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን</u>**

- ✓ በአላቂ ዕቃዎች ግምጃ ቤት እስቶክ የመያዝ፣ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፤
- ✓ በአላቂ ዕቃዎች ግምጃ በየዕቃዎች ላይ ቢን ካርድ እንዲንጠለጠል የማይደረግ መሆኑ፤
- ✓ በአላቂ ዕቃዎች ግምጃ በኮንቴነሩ ውስጥ ለሚገኙ ዕቃዎች በአብዛኛው ሼልፍ የሌላቸው መሆኑ፤

- ✓ በየቢሮ ለሚገኙ ለቋሚ ዕቃዎች (ለምሳሌ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ ኮምፒተሮች፣ ላፕቶፖች፣ ፍሪጆች ለመሳሰሉት) የመለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤
- ✓ በመለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት አገልግሎት ላይ መዋል የማይችሉ መኪኖች መለዋወጫ መሆን የማይችሉ በርካታ የመለዋወጫ ዕቃዎች ሳይወገዱ በአንድ ግምጃ ቤት ውስጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ በመለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ተቀጣጣይ የሆኑ 22 የሞተር ዘይት በርሚሎች በግምጃ ቤቱ ውሰጥ ከሌሎች ዕቃዎቹ ጋር አንድ ላይ ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ፤
- ✓ በሴንትራል ዕቃ ግምጃ ቤት በርካታ የተለያዩ ዓይነት ዕቃዎች ለረዥም ጌዜ ሳይወገዱ በግምጃ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤ (ለምሳሌ ጎማዎች፣ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎችና የመሳሰሉት)
- ✓ የሴንትራል ዕቃ ግምጃ ቤት የእሳት አደጋ መከላከያ የሌለው መሆኑ፤

17.1 <u>በአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን የናዝሬት ቅ/ጽ/ቤት</u>

- ♦ ከተፋሰስ ባለሥልጣኑ ወጪ ሆነው ወደ ቅ/ጽ/ቤ/ቱ ለሚላኩ አላቂና ቋሚ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19፣ ወጪ ሲደረጉም የንብረት ወጪ ደረሰኝ ሞ/22 የማይዘጋጅላቸው መሆኑ፣
- ♦ እስቶክ የመያዝ፣ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፤
- ♦ ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤ (ለምሳሌ ጠረጴዛዎች፣ ተሸከርካሪ ወንበሮች፣ ኮምፒተሮች እና ፕሪንተሮች ለመሳሰሉት)

17.2 በአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን የዱብቲ ቅ/ጽ/ቤት

- እስቶክ የመያዝ፣ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፤
- ለቋሚ ዕቃ መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤
- ሶስት የተበላሹ ኮምፒዊተሮች እና ሁለት ፕሪንተሮች ከዓመት በላይ ሳይጠገኑ በዕቃ ግምጃ ቤቱ ውስጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

18. በማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን

- ✓ ለቋሚ ንብረት መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤
- ✓ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ንብረቱ እንዲመዛዘን ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ስቶክ ካርድና ቢን ካርድ በተሟላ ሁኔታ እየተሠራበት ያለመሆኑ፤
- ✓ እስቶክ የመያዝ፣ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፤

19. በምርት ገበያ ባለሥልጣን

- ✓ በ2007 በጀት አመት የቋሚና አላቂ ዕቃች ቆጠራ ቢደረግም ከእስቶክ (ከመዝገብ) ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተመዛዘነ መሆኑ፤
- ✓ በዕቃ ግምጃ ቤት በሚገኙ እቃዎች ላይ ቢን ካርድ ያልተለጠፈ (ያልተንጠለጠለ) መሆኑ፤
- ✓ በርካታ የሚወገዱ ዕቃዎች (ትልልቅ የመኪና ጎማዎች፣ የሽንት ቤት መቀመጫዎች፣ የፊት መታጠቢያዎች፣ እና በርካታ ጋዜጦችና የተለያዩ ንብረቶች)ሳይወገዱ የተገኘ መሆኑ፤

20. የምግብ መጠጥና ፋርማሲቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

- ✓ በ2007 በጀት ዓመት የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ከመዝገብ (ከእስቶክ ካርድ) ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘን ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ ለቋሚ ዕቃዎች በሙሉ መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤
- ✓ በንብረት ክፍሉ ውስጥ ሊወገዱ የሚባቸው ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ የተሰባበሩ ጠረጴዛዎችና ወንበሮች፣ ኮመዲናዎች፣ የፕሪንተርና የፎቶ ኮፒ ቀለሞች ሌሎች የቢሮ ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ ለነዳጅ ኩፖን ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤

21. በኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን

- ✓ በመጋዘን ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ 14 ኮምፒውተሮች፣ 1 ላፕቶፕ፣ 8 ጠረጴዛዎች፣ 5 ወንበሮች የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ ብዛት ያላቸው የታሸጉ የኒሳን፣ የሚስትቡሽ እና የቶዮታ መኪና መለዋወጫ እቃዎች ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ በእስቶር ውስጥ ምንም አይነት አገልገሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ መሆኑ፤
- ✓ የተቀየሩ የመኪና ዕቃዎች የእቃ ገቢ ማድረጊያ ሰነድ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤
- ✓ የንብረት መጋዘኑ እጅግ ቆሸሸና እቃዎችም በአቧራ ተሸፍነው የሚታዩ መሆኑ፤

22. በአለርት ማዕከል

- ✓ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የተለያዩ የህክምና ዕቃዎች ዊልቸርና የመሳሰሉት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ከ10 ዓመት በላይ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆናቸው፤
- ✓ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የተለያዩ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች፣ ሞዴል 19 እና ሞዴል 22 እና የተለያዩ ቦክስ ፋይሎች የመሳሰሉት ብዛት ያላቸው ዕቃዎች ሳይወገዱ ከ10 አመት በላይ በመጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆናቸው፤

23. በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ

- ✓ በመደበኛ መድኃኒት እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ቢን ካርድ ማዘጋጀት የተጀመረ ቢሆንም በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ በልዩ ፋርማሲ ለሚገኙ መድኃኒቶች እስቶክ ካርድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
- ✓ በርካታ ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች በየቦታው ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ በርካታ አገልግሎት የማይሰጡ የህክምና ቋሚ ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ በኮሌጁ ሥር በሚተዳደረው በራስ እምሩ ማተሚያ ግቢ በንብረት ክፍል ውስጥ ሊወገዱ የሚገባቸው አምስት ቴሌቪዥኖች፣ ሶስት ካሜራዎች፣ ለሚዲያ የሚያገለግሉ እቃዎች አምፒሊፋይር፣ ጄነሬተር፣ መደርደሪያዎች፣ የተበላሸ አምስት ካርቶን ማስቲሽ ፣ ከአምስት አመት በላይ ሳይሰራ የቆየ መጠረዣ ማሽኖች፣ በርካታ የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ፣ የታክስ ደረሰኝና ፍሉድ የመሳሰሉ እቃዎች ሳይወገዱ የሚገኙ መሆኑ፤

24. በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ

- ✓ በበጀት ዓመቱ በተጠቃሚዎች እጅ የሚገኙ ቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ ለቋሚ እቃዎቹም መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤
- ✓ መሥሪያ ቤቱ በተጠቃሚዎች እጅ ላይ ለሚገኙ ቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) ያልተቋቋመ መሆኑ፤
- ✓ በመሥሪያ ቤቱ አሮጌ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ለረጅም ጊዜ የተከማቹ ብዛት ያላቸው ያገለገሉ የመስክ፣ የቢሮ፣ የኤሌክትሮኒክስና የሳይንቲፊክ ዕቃዎችና የመሳሰሉት በንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤

25. <u>በቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር</u>

- ✓ ሳሪስ ባለው መጋዘን የሚገኙ የሚያገለግሉና የማያገለግሉ ንብረቶች ያልተለዩ መሆኑ፤
- ✓ በሳሪስ ልዩ ልዩ የልማት ግምጃ ቤት ሰራተኛ የነበሩት በሞት የተለዩ ሲሆን፣ ርክክቡ ከዓመት በላይ ሳይደረግ የቆየ መሆኑ፤
- ✓ በርካታ ንብረቶች እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፤ (ለምሳሌ ያህል ቁጥራቸው የማይታወቅ ጎማዎች፣ ኮምፒዩተሮች፣ ፕሪንተሮችና የመሳሰሉት እቃዎች የሚገኙ መሆኑ)
- ✓ በርካታ መጽሄቶች የ2005 እትም፣ በርካታ ሌጀሮች የአዝርት ልማት ማስታወሻዎች በብዛት ከፍላጎት በላይ ታትመው አገልግሎት ሳይሰጡ በስቶር ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ ሰባት ኮንቴነር ውስጥ የተለያዩ የቋሚ እቃና የቧንቧ እቃዎች ታሽገው ያለ አገልግሎት በሳሪስ ለረጅም ዓመታት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ ሞተር ሳይክል የመጣባቸው በርካታ ብረቶች ጸሀይና ዝናብ እየተፈረረቀባቸው ሳሪስ ባለው ግቢ ውስጥ የሚገኝ መሆኑ፤
- ✓ በርካታ የመኪና መለዋወጫ እቃዎች ያለአገልግሎት የሚገኙ መሆኑ፣
- ✓ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ሰላሳ ሺ የሚሆኑ የባትሪ ድንጋዮች፣ አስራ ሶስት ጀሪካን ኬሚካል፣ አስራ ሶስት በርሜል ኬሚካል፣ እንደተገዙ አገልግሎት ላይ ሳይውሉ የመገልገያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ በስቶር ውስጥ ተከማችተው የሚገኝ መሆኑ፤
- ✓ ብዛታቸው 70 የሆኑ ባለ 25 ኪሎግራም ማዳበሪያዎች፣ በርካታ በጠርሙስና በጀሪካን የታሸጉ ኬሚካሎች ለጤና አስጊ በሆነ መልኩ በሜዳ ላይ ተዘርግፈው የሚገኙ መሆኑ፤

✓ በሳሪስ የላብራቶሪ ኬሚካል መጋዘን ውስጥ በርካታ አገልግሎት የማይሰጡ ኬሚካሎች አገልግሎት ከሚሰጡት ተለይተው እንዲቀመጡ ያልተደረጉ መሆኑ፤

25.1 <u>በቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር የቅድመ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳሬክቶሬት</u>

- በርካታ ንብረቶች እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፤ (ከ2002 ዓ.ም በፊት የነበሩ የማያገለግሉ 2,914 የገንዘብ መጠየቂያ ደረሰኞች፣ 530 የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ፣ በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች መልሶ ማቋቋሚያ የሚውል 219,860 ልዩ የቶምቦላ ትኬቶች፣ በመሥሪያ ቤቱ ስም የታተሙ 4,410 የገንዘብ መሰሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ በኤርትራ መንግሥት ጉዳት ለሚደርስባቸው ለኢትዮ ኤርትራ ተፈናቀዮች የሚውል አገልግሎት የማይሰጡ 7,715 መታወቂያ ካርድ፣)
- የማያገለግሉ 4 ፋክሶች፣ 11 ዴስክቶ ፕኮምፒዩተሮች፣ 5 ላፕቶፕ ኮሚዩተሮች ፣ 8 ፕሪንተሮች ፣ እንዲሁም ሌሌች የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- በ2005 በጀት ዓመት የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኦዲት አድርጎ አስተያየት የሰጠበት በ40 ኮንቴነር ታሽገው የሚገኙ የተለያዩ ጥቅም ሊሰጡ ከሚችሉና ከማይችሉ የቢሮ ዕቃዎችና የመኪና መለዋወጫ እቃዎች ውስጥ አስር የሚሆኑት ኮንቴነሮች ርክክብ እየተፈጸመና የማስተካከያ እርምጃ እየተወሰደባቸው ሲሆን፣ ቀሪዎቹ 30 ኮንቴነሮች ግን ምንም አይነት የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ፤
- ከስምንት አመት በላይ የመገልገያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች ለምሳሌ ያህል (Vitamin A+D) 15ml ብዛት 2000፣ የወባ መከላከያ መድኃኒት (Mosquitos Reprllent Petrollium Jelly) ብዛት 30 ካርቶን የሚገኙ መሆኑ፤

- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ የተካሄደ ቢሆንም አስቆጣሪው ያልፈረመበት እና የማመሳከር (የማመዛዘን) ሥራ ያልተሰራ መሆኑ፤

25.2 በቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል

- የድርቆሽ ሳር መጋዘኖች የእሳት ማጥፊያ የሌላቸው መሆኑ፤
- በርካታ በርሜሎችና ብረታ ብረቶች በየሜዳው ተበታትነው ዝናብና ጸሀይ እያበላሻቸው የሚገኙ መሆኑ፤
- በአላቂና ቋሚ ዕቃ መጋዘን ሊወገዱ የሚገባቸው በሮች፣ መስኮቶች እና የተለያዩ ንብረቶች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

25.3 የሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

- በቋሚ ንብረት ግምጃ ቤት አገልግሎት የማይሰጡ 47 የሂሳብ ማሽኖች ፣ 7 የስልክ ቀፎዎች፣ 9 ኮምፒውተሮች፣ 8 ፕሪንተሮች እና 10 ታይፕራይተሮች አገልግሎት ከሚሰጡት ጋር ተቀላቅለው የተቀመጡና እንዲወገዱ ለማድረግ የተደረገ ዕንቅስቃሴ የሌለ መሆኑ፤
- ባገለገሉ ዕቃዎች ግምጃ ቤት 5 የስጋ መፍጫ፣ 24 ኮምፒውተሮች፣ ጊዜ ያለፈበት ኬሚካል፣ በጣም በርካታ ትራሶች፣ በርካታ ሼልፎች፣ ጎማዎች እና ሌሎች ዕቃዎች ሳይወገዱ የሚገኙ መሆኑ፤
- በደቡብ ቤንች(ቂጤ) በሚገኘው ሰርቶ ማሳያ 40 ኩንታል የተበላሸ በቆሎ ከመኖሩም በተጨማሪ ከጤነኛው በቆሎ ጋር በአንድ ስቶር ውስጥ ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፤
- በነጭ ጋዝ የሚሰራ የዳቦ ማሽን ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ያለስራ ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፤

- የኮሌጁ ቅጽር ጊቢ በአግባቡ ያልተከለለ እና አብዛኛው ክልሉ ክፍት መሆኑ፤

25.4 የገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

- በኮሌጁ እስቶክ ካርድና ቢን ካርድ የተዘጋጀ ቢሆንም በተሟላ መልኩ ምዝገባው ያልተካሄደ መሆኑ፤ (ለምሳሌ የተማሪዎች ካፍቴሪያ የምግብ ጥሬ እቃ ግምጃ ቤት ሙሉ በሙሉ የተማሪዎች ክልኒክ የፋርማሲ ዕቃዎች፣ የሞባይል ካርድ፤ ደስታ ወረቀት)
- አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ ንብረቶች (ወደ ዘጠና የሚጠጉ የማያገለግሉ የመኪና ጎማዎችና በርካታ ብረታ ብረቶች ጸሀይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው በኮሌጁና በሰርቶ ማሳያ ግቢ ውስጥ ተበታትነው የሚገኙ መሆኑ እንዲሁም 25 ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ 30 የሚሆኑ ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች 42 የሚሆኑ ዲስክቶፕ ኮምፒዩተሮች ከነፕሮሰሰሩ እና ከኬብሎቹ ጋር እንዲሁም ቁጥሩ የማይታወቅ የተማሪ ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች) እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ወደ ስድስት የሚሆኑ ጄንሬተሮች በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- በውድ ዋጋ የተገዙ ሁለት ጄነሬተሮች ከህንጻው ግንባታ ጋር በሰንሻይን ድርጅት የተተከሉ ቢሆንም ከመጡበት ቀን ጀምሮ ያለአገልግሎት የቆሙ መሆኑ፤
- እስቶክ የመያዝ፣ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፤
- የቋሚና አላቂ እቃዎች ምዝገባ ወቅታዊ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርድና መዝገብ በተሟላ መልኩ ያልተያዘ መሆኑ፤
- በኮሌጁ የንብረት ተጠቃሚ ሰራተኞች ሥም የንብረት ምዝገባ ካርድ በተሟላ መልኩ ያልተያዘ መሆኑ፤

- በአንድ የኮሌጁ ስራተኛ ወጪ የተደረገ ቶሺባ ላፕቶፕ ኮምፒዩተር የጠፋ ሲሆን፣ መመሪያው ለኮሌጁ የበላይ ኃላፊ ሪፖርት መቅረብ እንዳለበት ቢያዝም ይህ ያልተደረገ ሲሆን፣ በተጨማሪም በጠፋው ንብረት ላይ ምንም አይነት እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፤
- ነዳጅ በንብረት መጠየቂያ የሚጠየቅ ቢሆንም የተጠየቀው ነዳጅ በንብረት ወጪ ደረሰኝ ወጪ መደረግ ሲገባው በአንድ ሰው አማካኝነት ወጪ የሚደረግ ከመሆኑም በተጨማሪ ወጪ ያደረገው ሰው ለሚመለከታቸው ሰራተኞች ለማከፋፈሉ በፊርማ ያልተረጋገጠ መሆኑ፤
- የሞባይል ካርድ በንብረት መጠየቂያ ተጠይቆ በንብረት ወጪ ደረሰኝ ወጪ መደረግ ሲገባው በአንድ ሰው አማካኝነት ወጪ የሚደረግ ከመሆኑም በተጨማሪ ወጪ ያደረገው ሰው ለሚመለከታቸው ሰራተኞች ለማከፋፈሉ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- በዕቃ ወጪ ደረሰኝ ሳይጠየቅና በሚመለከተው ኃላፊ ሳይፈቀድ ባትሪ 120A12V ለማይሰራ ትራክተር እንዲሁም፣ ዳታ ፕሮጀክተር ከዕቃ ግምጃ ቤት እንዲወጣ የተደረገ መሆኑ፤
- አንድ የኮሌጁ ስራተኛ በሞት የተለዩ ሲሆን፣ በስማቸው ያወጡት አንድ ላፕቶፕ ኮምፒዩተርና ዲጂታል ካሜራ ተመላሽ ለመደረጉ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- አንድ የኮሌጁ ስራተኛ ከሥራቸው ሲለቁ በስማቸው ያወጡትን አንድ ዲጂታል ካሜራና ላፕቶፕ ኮምፒተር ተመላሽ ለማድረጋቸው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- ለኮሌጁ ተሽከርካሪዎች አዲስ የመለዋወጫ ዕቃ ሲተካ የተቀየሩት ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተዘጋጅቶላቸው ወደ ዕቃ ግምጃ ቤት ተመላሽ ያልተደረጉ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

5.1.2 የማሻሻያ ሀሳብ

- የንብረት አስተዳደሩ አሰራር መንግሥት ባወጣው የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት የማይፈጸምና የማይስተካከል ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችል፣
- ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ካልተደረገ፤ አገልግሎት መስጠት የማይችሉት ደግሞ እንዲወገዱ ካልተደረገ ለከፋ ብልሽት ሊዳረጉና ዋጋቸው ሊቀንስ እንደሚችል፣

በአጠቃላይ በንብረት አስተዳደሩ ላይ የታዩት ክፍተቶች መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲስተካከል መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.2 የተሽከርካሪ አያያዝ፣ አጠባበቅና አጠቃቀም

5.2.1 ግኝት

በየመሥሪያ ቤቶች ውስጥ ያለው የተሽከርካሪዎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓትና መረጃ አያያዝ በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 እና በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያቁጥር 34/2004 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

1. **በኢትዮጵያ ዱር እንሰሳት ጥበቃ ባለስልጣን**

   3 ተሽከርካሪዎች የሰሌዳ ቁጥር (ኮድ 4-20065፣ 4-0262 ሞተር፣ 4-20314) የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው መሆኑ፣

2. **በኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ**

   ✓ ሁለት አውቶሞቢልና አንድ ሚኒባስ ተሽከርካሪዎች የሰሌዳ ቁጥር (ኮድ 4-02731፤ 4-02730፤ 4-02726 እና 4-20361 የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው መሆኑ፣

- ✓ አንድ ሚትሱቢሽ ተሽከርካሪ የሰሌዳ ቁጥር (ኮድ 4-20365) በግጭት አደጋ ምክንያት አገልግሎት ሳይሰጥ የቆመ መሆኑ፤

3. <u>በቀድሞው ስፖርት ኮሚሽን</u>

2 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ለኦዲት ሥራው ያልቀረበ መሆኑ፣

4. <u>በስምጥ ሸለቆ ተፋሰስ ባለሥልጣን</u>

የታርጋ ቁጥራቸው ኢት 4-20336 እና ኢት 4-19383 የሆኑ ተሽከርካሪዎች ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በህዳር ወር 2007 በእርዳታ የተገኙ ቢሆንም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊቢሬ) ሊቀርብላቸው ያልቻለ መሆኑ፣

5. <u>የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት</u>

- ✓ 14 ተሽከርካሪዎች ከ2 እስከ 8 ዓመት ድረስ ለሚሆን ጊዜ በብልሽት የቆሙ መሆኑ፣
- ✓ 15 ተሽከርካሪዎች በኢንስቲትዩቱ ስም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፣
- ✓ 7 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው መሆኑ፣
- ✓ በ2 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት መኖሩ፣

6. <u>በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል</u>

- ✓ አንድ ሱዙኪ በብልሽት የቆመ የታርጋ ቁጥር ኢአ 4625 ሞተር ሳይክል ሳይወገዱ ተቀምጦ የሚገኙ መሆኑ፣
- ✓ ለተሽከርካሪ መለዋወጫ፣ ዘይትና ቅባት ሲቀየርላቸው እና ጥገና ሲደረግላቸው ቁጥጥር እና ክትትል የሚደረግበት የአሰራር ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣

- ✓ በሆስፒታሉ ያሉ ሾፌሮች በሾፌር-መካኒክነት የተቀጠሩ ቢሆንም ከተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠባበቅ ጋር በተያያዘ እንደ ጎማ እና ዘይት መቀየር ያሉ ስራዎች በክፍያ በውጭ ሰራተኞች የሚሰሩ መሆኑ፣

8. **<u>በቀድሞው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር</u>**

- ✓ አንድ ኒሳን ባለ ደብል ጋቢና እና ሁለት ላንድሮቨሮች ታርጋ የሌላቸው መሆኑ፣
- ✓ የሰሌዳ ቁጥር 4-01134, 4-12249 እና 11-191 እና ታርጋ የሌላቸውን ስድስት መኪኖች ጨምሮ ለብዙ ጊዜ ያለበቂ መጠለያ ለዝናብና ለጸሐይ ተጋልጠው የሚገኙ እና ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣

9. **<u>በብዝሀ ህይወት ኢንስቲቱዩት</u>**

- ✓ የኢንስቲትዩቱ የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠባበቅ ሁኔታ መንግሥት ባወጣው መመሪያ መሠረት መሆኑ ኦዲት ሲደረግ ሁለት ተጎታች ጋሪዎች እና ስምንት ሞተር ብስክሌቶች በአካል በኢንሲትትዩቱ ሳይኖሩ ሊብሬያቸው ብቻ የተገኘ መሆኑ፣
- ✓ አገልግሎት የማይሰጡ ሁለት ሱዚኪ ሞተር ሳይክሎች፣ አንድ ቶዮታ ላንድ ክሩዘር እና አንድ ማርቼዲስ መኪና ሳይወገዱ የተገኙ መሆኑ፣

10. **<u>በአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን</u>**

- ✓ የተለያዩ አገልግሎት የማይሰጡ ማሽነሮች በመሥሪያ ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣ (መለያ ቁጥር 900242 ግራቭል ትሬለር፣ መለያ ቁጥር 900250 ግራቭል ትሬለር፣ መለያ ቁጥር W90-2 ሎደር ኮማትሱ፣ መለያ ቁጥር D-6 ዶዘር ኮማትሱ ፣ መለያ ቁጥር D-6 ካት፣ መለያ ቁጥር KDM CV5165-3 ስክራፒር ኮማትሱ፣ መለያ ቁጥር Hlle-Turbo ቤኔፍራ ባክ ሎደር፣ መለያ ቁጥር 908C ቤኔፍራ ኤክስካቫተር እና፣ መለያ ቁጥር 358 CTU-0358 ሎምባርዲኒ ትራክተር)

- ✓ ፓወር ፕላስ ገልባጭ አምስት መኪናዎች ማለትም የሠሌዳ ቁጥር 4-20225፣ 4-20226፣ 4-20227፣ 4-20229፣ 4-20330 የሞተር ቁጥራቸው ልጥፍ እና የሰሌዳ ቁጥር 4-20227 የሞተሩ ልጥፍ ቁጥር የጠፋ መሆኑ፣

11. <u>በአለርት ማዕከል</u>

14 ተሽከርካሪ መኪናዎች ሳይጠገኑ (ሳይወገዱ) ለረጅም አመት የቆሙ መሆኑ፣

12. <u>በቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር</u>

- ✓ አገልግሎት የማይሰጡ 32 ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ወይም እንዲወገዱ ያልተደረጉ መሆኑ፣
- ✓ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሥም የሆነ 91 ተሽከርካሪዎች የሚገኙ መሆኑ፣

12.1 <u>በቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር የቅድመ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት</u>

- ✓ ለበላይ ኃላፊዎችና ለዳይሬክተሮች ከተመደቡት ተሽከርካሪዎች በስተቀር በሌሎች በተሽከርካሪዎቹ ሁለቱም የፊት በሮች ጎን ላይ የመስሪያ ቤቱን ስም የሚያመለክት መለያ ወይም አርማ ያልተለጠፈ መሆኑ፣
- ✓ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ ዘጠኝ ተሽከርካሪዎች የሚገኙ መሆኑ፣
- ✓ በዳይሬክቶሬቱ ከቀረቡት መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው በዋናው መሥሪያ ቤት 77፣ በናዝሪት ማዕከላዊ መጋዘን 8፣ በኮምቦልቻ ማከማቻ መጋዘን 4 እንዲሁም በድሬዳዋ ማዕከላዊ መጋዘን 11 በድምሩ 100 ከባድ፣ ቀላልና መለስተኛ ተሽከርካሪዎች ከአገልግሎት ውጭ የሆኑና እንዲወገዱ ያልተደረገ ሲሆን፣ በዋናዉ መሥሪያ ቤት ከሚገኙት

ተሽከርካሪዎች ውስጥ 20 ተሽከርካሪዎች ሰነድ ያልቀረበላቸው መሆኑ፤

12.2 በቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል

- ✓ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ ከተገዛበት ወይም በእርዳታ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ የነዳጅና ቅባት ፍጆታ እንዲሁም የመለዋወጫና ጥገና ወጪ በግልጽ የሚያሳይ የግል ማህደር የሌላቸው መሆኑ፣
- ✓ 3 ትርክተሮችና 2 ሞተር ሳይክሎች በከባድና ቀላል ብልሽት ምክንያት ተበላሽተው ቆመው የሚገኙ መሆኑ፣
- ✓ 3 ትራክተሮችና 5 ሞተር ሳይክሎች ሠሌዳ ቁጥርና ሊብሬ የሌላቸው መሆኑ፣

12.3 የሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

- ♦ ለበላይ ኃላፊዎችና ለዳይሬክተሮች ከተመደቡት ተሽከርካሪዎች በስተቀር በሌሎች የኮሌጁ ተሽከርካሪዎቹ ሁለቱም የፊት በሮች ጎን ላይ የመሥሪያ ቤቱ ስም የሚያመለክት መለያ ወይም አርማ ያልተለጠፈ መሆኑ፣
- ♦ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ ከተገዛበት ወይም በእርዳታ ከተሰጡበት ጊዜ ጀምሮ የነዳጅና ቅባት ፍጆታ እንዲሁም የመለዋወጫና ጥገና ወጪ በግልጽ የሚያሳይ የግል ማህደር የሌላቸው መሆኑ፣
- ♦ ኮሌጁ የሚጠቀምበት ቤሌሩሰ ትራክተር ሠሌዳ ቁጥርና ሊብሬ የሌለው መሆኑ፣

12.4 የገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

- ♦ ለበላይ ኃላፊዎችና ለዳይሬክተሮች ከተመደቡት ተሽከርካሪዎች በስተቀር በሌሎች የኮሌጁ ተሽከርካሪዎቹ ሁለቱም የፊት በሮች ጎን ላይ የመሥሪያ ቤቱ ስም የሚያመለክት መለያ ወይም አርማ ያልተለጠፈ መሆኑ፣

- ለበላይ ኃላፊዎች እና ለኃላፊዎች ከሚመደቡ ተሸከርካሪዎች በስተቀር እያንዳንዱ ተሸከርካሪ የፈጀው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎሜትር መጠን ጋር እየተመዘገበ ተገቢዉ ሪፖርት በየወሩ የማይቀርብ መሆኑ፣

- አንድ ባልትራ ትራክተር በኮሌጁ ግቢ ውስጥ በብልሽት ምክንያት ከአንድ አመት በላይ ያአገልግሎት ጸሀይና ዝናብ እየተፈራረቀበት ቆሞ የሚገኙ መሆኑ፣

- ላንድሮቨር ታርጋ ቁጥር 21350 አ.አ እንዲሁም አራት ሞተር ሳይክሎች ታርጋ ቁጥራቸው 0197፤ 0198 ፤ 0199፤ 5232 ሊብሬ የሌላቸው መሆኑ፣

- ላንድሮቨር፣ ሚትስቡሽ ፣ጃጓር ታርጋ ቁጥር 21350 አ.አ፣24593 አ.አ 27524 አ.አ እንዲሁም የተወሰነ ክፍላቸው የቀረ ሁለት ትራክተሮች ከ5 አመት በላይ ሳይወገዱ በሰርቶ ማሳያ ግቢ ውስጥ ጸሀይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው የሚገኙ መሆኑ፣

- የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ አሥር ተሸከርካሪዎች የሚገኙ መሆኑ፣

13. <u>**በቀድሞው ማዕድን ሚኒስቴር**</u>

ቀደም ሲል በተደረገው ኦዲት ወቅት አስተያየት ተሰጥቶባቸው እርምጃ ሳይወሰድ አሁንም ባሉበት ሁኔታ የሚገኙ፡

- ✓ 8 የተለያዩ ዓይነት ተሽከርካሪዎች ከ1 ወር እስከ 10 ዓመታት ድረስ በብልሽት አገልግሎት ሳይሰጡ የቆሙ መሆኑ፣

- ✓ አንድ የሎቤድ ተሳቢ የሰሌዳ ቁጥር 4-0960 ከ20 ዓመታት በላይ በብልሽት አገልግሎት ሳይሰጥ የቆመና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌለው መሆኑ፣

14. **<u>የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ</u>**

በመስክና በማዕከል የሚገኙ ብዛታቸው ስምንት የሆኑ ተሽከርካሪዎች ጌጃቸው የማይሠራ ሲሆን ስለሁኔታው ባለፈው በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ሁኔታው ያልተስተካከለ መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

6.2.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

- ✓ በወጣው የተሽከርካሪዎች መመሪያ መሰረት ያለመፈጸም በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር እንደሚችል፣
- ✓ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶች የሆኑ ተሽከርካሪዎች የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ንብረቶች ናቸው ብሎ ለመቀበል ሊያስቸግር እንደሚችል፣
- ✓ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ካልተደረ፤ አገልግሎት መስጠት የማይችሉት ደግሞ እንዲወገዱ ካልተደረገ ለከፋ ብልሽት ሊዳረጉና ዋጋቸው ሊቀንስ እንደሚችል፣

በአጠቃላይ በተሽከርካሪዎቹ አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ ላይ የታዩት ክፍተቶች በመመሪያው መሰረት መስተካከል እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

7. <u>በጀት</u>

7.1 <u>ሥራ ላይ ያልዋለ የመደበኛና የካፒታል በጀት</u>

7.1.1 <u>ግኝት</u>

ኦዲት ለተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በ2007 በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሳብ ሲመዛዘን፡

- ✓ በሰላሳ ስምንት ሂሳብ አቅራቢ መሥሪያ ቤቶችና ለቀድሞው ግብርና፣ ለቀድሞው ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽንና ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተጠሪ በሆኑ አምስት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ከመደበኛ በጀት ከ10% በላይ ብር 180,871,275.49፣

- ✓ በአስራ አራት ሂሳብ አቅራቢ መሥሪያ ቤቶችና ለቀድሞው ግብርናና ለቀድሞው ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተጠሪ በሆኑ ስድስት መሥሪያ ቤቶች ከካፒታል በጀት ከ10% በላይ ብር 211,976,044.03፣

በድምሩ ብር 404,088,336.90 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ ታውቋል፡፡ ለዝርዝሩ አባሪ 4 ተያይዟል፡፡

7.1.2 የማሻሻያ ሀሳብ

መሥሪያ ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይችሉ ዘንድ በዕቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሠረተ በጀት ሊይዙ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

7.2 ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ ሂሳብ

7.2.1 ግኝት

ኦዲት ለተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በ2007 በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሳብ ሲመዛዘን፣

- ✓ በአሥራ አንድ ሂሳብ አቅራቢ መሥሪያ ቤቶች ከመደበኛ በጀት ብር 22,221,702.36 ለየሒሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የተደረገ መሆኑ፣
- ✓ በሁለት ሂሳብ አቅራቢ መሥሪያ ቤቶችና ለቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ በሆኑ ሶስት መሥሪያ ቤቶች ብር 6,899,917.24 ለየሒሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የተደረገ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

ለዝርዝሩ አባሪ 4 ተያይዟል፡፡

7.2.2 የማሻሻያ ሀሳብ

መሥሪያ ቤቶቹ በዕቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሠረተ በጀት ሊይዙ እንደሚገባ፤ የበጀት ዕጥረት ካጋጠማቸውም በበጀት ሕጉ መሰረት የበጀት ዝውውር መጠየቅ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

8. ልዩ ልዩ

8.1 እርምጃ ያልተወሰደባቸው በጀት ዓመታት ግኝቶች

8.1.1 የ2006 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝቶች

1. **በውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት**

- ጽህፈት ቤቱ የ15 ከተሞች የመጠጥ ውሃ ሳኒቴሽን ፕሮጀክት ግንባታ ስትራክቸሮችንና ቁሳቁሶች ለጠበቁ ጊዜያዊ የጥበቃ ሰራተኞች አገልግሎት ለሰጡባቸው ቀናቶች ክፍያ ሲፈጸም ተቀናሽ የተደረገው ብር 7,862.83 የደመወዝ ገቢ ግብር ለገቢዎችና ግምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ለመደረጉ በዚህ በጀት ዓመትም ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፣
- የ15 ከተሞችን የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የመንግሥትንና የአዉሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ ድርሻ የተጨማሪ እሴት ታክስ (የቫት) ክፍያ የሚሸፍነው የፌዴራል መንግሥት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ብር 6,147,366.49 የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያዎቹ ተቀንሰው ተገቢው ምዝገባ የተከናወነ ለመሆኑ እና ታክሱም ለሚመለከተው አካል ገቢ ለመደረጉ በዚህ ኦዲት ወቅትም ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- ጽህፈት ቤቱ በ6412 በሂሳብ መደብ ለብድር መስጠትና ማስመለስ እንዲውል ከተፈቀደለት ብር 50 ሚሊዮን ውስጥ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከተያዘው በጀት ውስጥ ተራፊው ብር 37,915,592.09 በወጪ ሒሳብ መደብ 6412 መዝግቦ ወደ ፕሮጀክት ሂሳብ እንዲዞር ያደረገ ሲሆን፣ ገንዘቡ ተመላሽ እስኪደረግ ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ እንዲመዘገብ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

2. **የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣን**

መመሪያው ከሚፈቅድው በላይ የተፈጸመው የውሎ አበል ክፍያ ብር 25,569.05 ተመላሽ ሳይደረግ የተገኘ መሆኑ፣

3. **<u>በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር</u>**

- ✓ ቀረጥ ተከፍሎባቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ካልቀረበላቸው ዕቃዎች ውስጥ ለአብዛኛዎቹ የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) የቀረበላቸው ሲሆን፣ ለቀሪዎቹ ብር 3,222,045.24 የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ያልቀረበላቸው መሆኑ፣
- ✓ ብዛት ያላቸው የማባዣ እና የፎቶ ኮፒ ማሽኖች እንዲሁም መለዋወጫ ዕቃዎች የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈና አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፣
- ✓ በእርዳታ ከገቡ መኪናዎች ጋር የመጡ የኢቬኮ መኪና መለዋወጫዎች ለረዥም አመታት ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣

4. **<u>የህብረት ሥራ ኤጀንሲ</u>**

- ✓ በቼክና በደብዳቤ ትዕዛዝ በተለያየ ጊዜያት ከባንክ ወጪ የተደረጉ ሂሳቦች ብር 17,874.74 በባንክ ስቴትመንት ላይ የሚታዩ ቢሆንም በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብና በሌጀር ላይ ስለመመዝገባቸው ማረጋገጫ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ✓ ብር 41,092.10 ዋጋ የያዙ የተለያዩ ቼኮች በሒሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ እና በሌጀር ላይ ያልተመዘገበ መሆኑ፣
- ✓ ከዜድ አካውንት ብር 256,515.06 ዋጋ የያዙ የተለያዩ ቼኮች ተዘጋጅተው በመዝገብና በሌጀር ላይ ተመዝግበው ወደ ሪፖርት ከተላለፉ በኋላ ቼኮች በልዩ ልዩ ምክንያት ቮይድ (እንዲሰረዙ) የተደረጉ ቢሆንም ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ ስለመሰራቱ ማስረጃ ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፣

5. **<u>የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ</u>**

17 ተሽከርካሪዎች ንብረትነታቸው የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ የሆኑ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ በትውስት ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ተሰጥተው የነበረና መሥሪያ ቤቱ ለኮርፖሬሽኑ

ተሽከርካሪዎቹ እንዲመለሱለት በደብዳቤ የጠየቀ ቢሆንም ተሽከርካሪዎቹ በዚህ ኦዲት ወቅትም ተመላሽ ያለመደረጋቸው የታወቀ መሆኑ፣

6. <u>የኢትዮጵያ የምግብ ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን</u>

በጆርናል ቫውቸር ቁጥር 12230/58901 ከተወራረዱት የተለያዩ ወጪዎች ብር 75,320.98 ውስጥ ለብር 51,332.63 በዚህ ኦዲት ወቅትም የወጪ ማስረጃ ያልቀረበላቸው መሆኑ፣

7. <u>የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት</u>

- ✓ በ2006 በጀት ዓመት ብር 41,189,738.68 የቀረጥ ሒሣብ ምዝገባ ተከናውኖ ዕቃዎቹ ገቢ ለመሆናቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብለት ከተገኘው ውስጥ ለብር 33,629,967.37 የንብረት ገቢ ደረሰኝ የቀረበለት ሲሆን፣ ለቀሪው ብር 7,559,771.31 ዕቃዎቹ ገቢ ለመሆናቸው በዚህ ኦዲት ወቅትም የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብለት የተገኘ መሆኑ፣
- ✓ ብር 5,152.50 ያለ አግባብ የተፈጸመው ተጨማሪ የአበል ክፍያ በዚህ ኦዲት ወቅትም ተመላሽ ሳይደረግ የተገኘ መሆኑ፣

8. <u>በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን</u>

ከሐምሌ 2005 እስከ ሰኔ 2006 ድረስ ባለው ጊዜ ያልተቀነሰው ብር 993.24 የህክምና መዋጮ እና ብር 6,300.00 ከቤት አበል ያልተቀነሰው ግብር በዚህ ኦዲት ወቅትም ያልተቀነሰ መሆኑ፣

9. <u>በአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን</u>

ከሐምሌ 2005 እስከ ሰኔ 2006 ድረስ ባለው ጊዜ ያልተቀነሰው ብር 648.00 የህክምና መዋጮ እና ብር 2,167.00 ከቤት አበል ያልተቀነሰው ግብር በዚህ ኦዲት ወቅትም ያልተቀነሰ መሆኑ፣

10. **<u>በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል</u>**

- ✓ ሆስፒታሉ በቢሾፍቱ ከተማ ለባለሙያዎች ሥልጠና ሲሰጥ የውሎ አበል ክፍያ በአዲስ አበባ ከተማ ታሪፍ መሠረት ያለአግባብ የከፈለው ብር 4,927.00 አሁንም ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ በገቢ ግብር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ከደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር ሊከፈልበት የሚገባው የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 1,601,290.49 ላይ በዚህ ኦዲት ወቅትም ግብሩ እንዲቀነስ ያልተደረገ መሆኑ፣

11. **<u>በቀድሞው የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር</u>**

መሥሪያ ቤቱን ከለቀቁ በኋላ ለሶስት ሰራተኞች ብር 2,513.00 ደመወዝ ያለአግባብ ተከፍሎአቸው የተገኘ መሆኑ፣

12. **<u>የብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት</u>**

- ✓ መወገድ የሚገባቸው የተለያዩ በርካታ ዕቃዎች፣ ጠረጴዛዎች፣ ተሽከርካሪ ወንበሮች፣ የመኪና ጎማዎች፣ ኮምፒተሮች እንዲሁም በርካታ የተለያዩ ንብረቶች በዚህ ኦዲት ወቅትም ሳይወገዱ የተገኙ መሆኑ፣
- ✓ በ2005 በጀት ዓመት የተገዙ ቋሚ ዕቃዎች ለምሳሌ (ዴል ኮምፒዩተር፣ ዩፒኤስ ወዘተ) በዚህ አዲት ወቅትም በቋሚ ዕቃ ካርድ ላይ ያልተመዘገቡ መሆኑ፣

13. **<u>በአለርት ማዕከል</u>**

- ✓ ለጌታቸው መኩሪያ አጠቃላይ ሥራ ተቋራጭ የለውጥ ሥራ ትዕዛዝ ቁጥር አንድ እና ሁለት ተብሎ የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ለተፈጸመው ብር 315,215.25 ክፍያ የተጨማሪ ሥራ ውል ሥምምነት ለመፈጸሙ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ኃላፊዎች ለመጽደቁ በዚህ ኦዲት ወቅትም ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፣

- ✓ የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያውን ተከትሎ ባለመፈጸሙ አለአግባብ የተከፈለው አበል ብር 9,207.00 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣

14. **<u>በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ</u>**

- ✓ በገቢ ደረሰኝ (ገ/ሂ/21/1) የተሰበሰበው በገቢ ሂሳብ ማጠቃለያ (ሞ64) ደረሰኝ ሲጠቃለል በብር 1,341.70 አንሶ የተገኘ ሲሆን፣ ሂሳብ እንዲተካ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣
- ✓ በብር 710,700.00 ከቶታል ኢትዮጵያ የተገዛው ነዳጅ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ለመሆኑ በዚህ ኦዲት ወቅትም ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፣
- ✓ በወጪ ለተመዘገበው ለብር 78,000.92 የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፣
- ✓ ከመደበኛው በጀት ለግል የህክምና አገልግሎት እንዲውል ከተደረገው ሂሳብ ውስጥ ቀሪው ብር 190,389.88 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ የመጋቢት ወር 2006 የደመወዝ በመዝገብና በሌጀር ሲመዘገብ ለታዩት ልዩነቶች ይኸውም፡
    - ♦ ብር 58,723.91 በዴቢት ላልተመዘገበው ሂሳብ ፣
    - ♦ ብር 44,322.48 በደቢት በመብለጥ ለተመዘገበው ሂሳብ ፣
    - ♦ ብር 32,200.75 በክሬዲት ላልተመዘገበው ሂሳብ ፣
    - ♦ ብር 17,798.62 በመብለጥ በክሬዲት ለተመዘገበው ሂሳብ ፣

      ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራለት ያልተደረገ መሆኑ፣

8.1.2 **<u>የ2005 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝቶች</u>**

1. **<u>በውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት</u>**

- ♦ ጽህፈት ቤቱ በ6214 የሂሳብ መደብ ለብድር መስጠትና ማስመለስ እንዲውል የተፈቀደለትን በጀት ብር 50,000,000.00 ወደ ፕሮጀክት ሂሳብ እንዲዞር ያደረገ ሲሆን፣ ገንዘቡ ተመላሽ እስኪደረግ ድረስ በተሰብሳቢ ሒሳብ መያዝ እንዳለበት ተገልጾ አስፈላጊው

የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

- ብር 1,883,514.72 ከዓረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት (BADEA) መሸፈን ሲገባው ከፌደራል መንግሥት በጀት ክፍያው የተፈጸመ ሲሆን፣ ገንዘቡ በተሰብሳቢ ሂሳብ ተመዝግቦ ከዕርዳታው ሰጪ ድርጅት መጠየቅ ሲገባው በወጪ ለተመዘገበው ሂሳብ ማስተካከያ ያልተሰራለት መሆኑ፣
- ጽህፈት ቤቱ የ15 ከተሞች የመጠጥ ውሃ ሳኒቴሽን ፕሮጀክት ግንባታ ስትራክቸሮችንና ቁሳቁሶችን ጥበቃ አገልግሎት ለሰጡበት ብር 339,603.20 ክፍያ ሲፈፀም ጥበቃዎቹ አገልግሎት ለሰጡባቸው ቀናቶች ስለመከፈሉና የደመወዝ ገቢ ግብሩ ለግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ገቢ ስለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘቡ በወጪ ተመዝግቦ ለተገኘው ሂሳብ ማስተካከያ ሳይሰራለት ባለበት ሁኔታ የሚገኝ መሆኑ፣

2. <u>የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣን</u>

ለውሎ አበል ለተከፈለ ብር 409.96 እና ለነዳጅ መግዣ ወጪ ለሆነው ብር 2,813.40 በድምሩ ብር 3,223.36 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሲሆን፣ በዚህ ኦዲት ወቅትም ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፣

3. <u>በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር</u>

ቀረጥ ተከፍሎባቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ካልቀረበላቸው ዕቃዎች ውስጥ ለአብዛኛዎቹ የቀረበላቸው ሲሆን፣ ለቀሪዎቹ ብር 15,842,654.97 የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ያልቀረበላቸው መሆኑ፣

4. <u>በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር</u>

- ✓ በሚመለከተው የመንግሥት አካል ሳይፈቅድ ለሰራተኞች ማበረታቻ ተብሎ የተከፈለው ብር 198,783.33 በሚመለከተው አካል እንዲፈቀድ ወይም ገንዘቡ ተመላሽ እንዲሆን ያልተደረገ መሆኑ፣

- ✓ በቢሾፍቱ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት በተዘጋጀው ስልጠና ላይ ለሰልጣኞቹ የመኝታ እና የምግብ ወጪ ብር 1,788,244.00 ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሸፈነ ቢሆንም መመሪያው ከሚፈቅደው ውጪ የተፈጸመው ተጨማሪ ክፍያ ብር 82,950.00 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣

8. <u>**በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ**</u>

- ✓ በድሪሊንግ መጋዘን አዳዲስ ማሽኖች ያለሥራ ለረጅም ጊዜ የቆሙ መሆኑ፤ የወርክ ሾፕ ማሽኖች በዚህ ኦዲት ወቅትም ያለአገልግሎት ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ ፤ እንዲሁም በመጋዘኑ ውስጥም መወገድ ያለባቸው ኬሚካሎች ለረጅም ጊዜ የጠቀመጡና እንዲወገዱ ያልተደረጉ መሆኑ፣
- ✓ ከአቶ ብርሃኑ ደጀኔ የመሥሪያ ቤቱ የንብረት ግምጃ ቤት ኃላፊ በነበሩበት ወቅት ግምቱ ብር 241,752.75 የሚሆን ንብረት በማጉደላቸው በፍርድ ቤት ከነወለዱ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ ሆኖም መሥሪያ ቤቱ በፍርድ ቤት በተወሰነባቸው መሰረት ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርጉ ለተቀጠሩበት መሥሪያ ቤት የጻፈው ደብዳቤ ወለዱን ሳይጨምር መሆኑ ተገልጾ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ማስተካከያ ሳይደረግ የተገኘ መሆኑ፣

9. <u>**በኢትዮጵያ የምግብ ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን**</u>

- ✓ ከቤት አበል ክፍያ ላይ ያልተቀነሰው ብር 23,641.00 ሥራ ግብር በዚህ ኦዲት ወቅትም ተመላሽ ሳይደረግ የተገኘ መሆኑ፣
- ✓ ከሚኒስትሮች ምክር በተላለፈው መመሪያ መሰረት ከዋና ዳይሬክተሩ እና ከምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ላይ ያልተቀነሰው 1% የህክምና አገልግሎት ብር 2,554.08 ግብር በዚህ ኦዲት ወቅትም ተመላሽ ሳይደረግ የተገኘ መሆኑ፣
- ✓ መሥሪያ ቤቱ ካወራረደው የተለያዩ ወጪዎች ሒሣብ ብር 25,843.27 ውስጥ ያለምንም የወጪ ማስረጃ በወጪ ለተመዘገበው

ሂሳብ ብር 5,406.98 በዚህ ኦዲት ወቅትም ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፣

10. <u>**በኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት**</u>

በ2005 በጀት ዓመት ብር 4,153,590.08 የቀረጥ ሒሣብ ምዝገባ ተከናውኖ ዕቃዎቹ ገቢ ለመሆናቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብለት ከተገኘው ውስጥ ለብር 1,408,130.84 የንብረት ገቢ ደረሰኝ የቀረበለት ሲሆን፣ ቀሪው ብር 2,745,459.24 ዕቃዎቹ ገቢ ለመሆናቸው በዚህ ኦዲት ወቅትም የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብለት የተገኘ መሆኑ፣

11. <u>**በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል**</u>

- ያለአግባብ የተከፈለው የውሎ አበል ብር 2,334.25 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ለሆስፒታሉ የጤና ባለሙያዎች ከሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ከተፈቀደው ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች ክፍያ ላይ ተቀናሽ ያልተደረገው ሥራ ግብር በዚህ በጀት ዓመትም ተቀናሽ ያልተደረገ መሆኑ፣

8.1.3 <u>የ2004 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝቶች</u>

1. <u>**በውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት**</u>

- ጽህፈት በ6412 የሂሳብ መደብ ለብድር መስጠትና ማስመለስ እንዲውል ከተፈቀደለት በጀት ውስጥ ብር 15,049,315.03 ወደ ፕሮጀክት ሂሳብ እንዲዞር የተደረገ ሲሆን፣ ገንዘቡ ተመላሽ እስኪደረግ ድረስ በተሰብሳቢ ሒሳብ መያዝ እንዳለበት ተገልጾ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣
- ጽህፈት ቤቱ የ15 ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ለማቲትዮሊ ጆይንት ቬንቸር (Mattioli Joint Venture) ሥራ ተቋራጭ ክፍያ ሲፈጸም ብር 328,259.52 የመያዣ ሂሳብ ፣ ብር 4,116,177.47 2% የቅድሚያ ግብር ታክስ ክፍያ፣ ብር 1,989,767.92 የቅድሚያ ክፍያ እና የማቴሪያል ኦን ሳይት ተመላሽ ሂሳብ በቀረበው የክፍያ

ምስክር ወረቀት ላይ ለቀነሰው ሂሳብ ተገቢው ማስተካከያ ያልተሰራለት መሆኑ፣

- የክብረ መንግሥት ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክት ለበርሔ ሐጎስ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ክፍያ ሲፈጽም ብር 103,533.00 የመያዣ ሂሳብ እና ብር 133,732.20 የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ ሂሳብ በቀረበው የክፍያ ምስክር ወረቀት ላይ ለተቀነሰ ሂሳብ ተገቢው የሂሳብ ምዝገባ ቢዚህ ኦዲት ውቅትም ያልተከናወነ መሆኑ፣
- ጽህፈት ቤቱ የሐረር ከተማ ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክት የቅድሚያ ክፍያ ብር 209,281.04 እና የመያዣ ሂሳብ ብር 209,281.04 በድምሩ ብር 418,562.08 ሳይቀነስ ለተቋራጩ ለጋሞን ቴቺኖ ፋብ ጆይንት ቬንቸር (GAMMON TECHNO FAB JOINT VENTURE) ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ተገልጾ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ ሳይወሰድ ባለበት ሁኔታ የሚገኝ መሆኑ፣

2. በኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣን

በ2004 በጀት ዓመት መጨረሻ በመሥሪያ ቤቱ የቆጠራ ኮሚቴ የቋሚና አላቂ እቃ ቆጠራ በተከናወነበት ወቅት፡

- ✓ አንድ ላፕቶፕ ቶሺባ ኮምፒውተር ከነቦርሳው፣
- ✓ አንድ ዲጂታል ካሜራ ከ4ጂቢ ሚሞሪ ካርድ ጋር፣
- ✓ አንድ ድንኳን እና አንድ አጉሊ የሜዳ መነፅር፣

በቆጠራ ወቅት ያልተገኙት ንብረቶች እንዲመለሱ አስፈላጊው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

3. በቀድሞው የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር

- ✓ አንድ ሰራተኛ ከሥራ ከለቀቁ በኋላ አለአግባብ የተከፈለው ደመወዝ ብር 1,145.10 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ አንድ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሰራተኛ ከሥራ ሲለቁ በእጃቸው የሚገኘውን 1 Toshiba laptop computer AR630,Toshiba laptop computer small size Intel dual እና CDMA ለማስረከባቸው

ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ ተገልጸ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

- ✓ አሚቼ በሚገኘው መጋዘን ውስጥ ያሉ ያገለገሉ ንብረቶች፣ ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ፋክሶች፣ ፍሪጆች፣ የመኪና ጎማዎች እና የመሳሰሉት ንብረቶች ሳይወገዱ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

8.1.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በድጋሚ አሳስበናል፡፡

8.2 <u>ዋስትና በሚያስፈልጋቸዉ የስራ መደቦች ላይ የተመደቡ ሰራተኞች ዋስትና (ተያዥ) እንዲያቀርቡ ያልተደረገ ስለመሆኑ</u>

8.2.1 <u>ግኝት</u>

በፌዴራል መንግሥት ሰራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003 መሰረት በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት ወይም ንብረት ያዥነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሰራተኞች ሁሉ ለተሰጣቸው ኃላፊነት የሚሆን ዋስትና ወይም ተያዥ እንዲያቀርቡ ያዛል። ሆኖም ፡

- ✓ በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አንድ የዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛ እና አንድ ዋና ገንዘብ ያዥ፣
- ✓ በኢትዮጵያ ግብርና ኢንቨስትመንት መሬት አስተዳደር ኤጀንሲ አንድ የግዥ ሰራተኛ፣
- ✓ በቀድሞው ስፖርት ኮሚሽን አንድ ገንዘብ ያዥ፣ ሁለት የግዥ ሰራተኞች እና አንድ የንብረት ያዥ ሰራተኛ፣
- ✓ በገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ በናሙና ከተመረጡት ሰራተኞች ውስጥ ሁለት ገንዘብ ያገዦች፣ ሰማኒያ ሰባት የጥበቃ ሰራተኛ እና ሶስት የእቃ ግምጃ ቤት ሰራተኞች፣

ዋስ እንዲያቀርቡ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

8.2.2 የማሻሻያ ሀሳብ

በፌዴራል መንግሥት ሰራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003 መሠረት በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት ወይም ንብረት ያዥነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች ሁሉ ለተሰጣቸው ኃላፊነት የሚሆን ዋስትና ወይም ተያዥ እንዲያቀርቡ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

8.3 ከመንግሥት ከፍተኛ ተቋማት ከተመረቁ ሰራተኞች ላይ የወጪ መጋራት ያልተሰበሰበ መሆኑ

ግኝት

ስለከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 91/1995 አንቀጽ 7 በንኡስ አንቀጽ 1 ላይ በተገለጸው መሰረት ደንቡ ተግባራዊ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የከፍተኛ ትምህርት የተከታተለን ሰው የሚቀጥር ማንኛውም አሠሪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡፡ ይኸውም፡

ሀ. ተቀጣሪው ከተማረበት ተቋም የተሰጠውን የሚፈለግበትን ክፍያ መጠን የሚገልጽ መረጃና በየወሩ ከደመወዙ እየተቀነሰ ገቢ ሊደረግ የሚገባውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ የተሰጠ ማስረጃ እንዲያቀርብ የመጠየቅ፤

ለ. የተቀጣሪዎችን ዝርዝር በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ለፌዴራል ሀገር ውስጥ ገቢዎች ባለሥልጣን በጽሁፍ የማሣወቅ፤

ሐ. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 በቀረበለት መረጃ እና በዚህ ደንብ በአንቀጽ 8(1) (ሐ) መሠረት ከተቀጣሪው ደመወዝ በየወሩ እየተቀነሰ የማስተላለፍ ግዴታ፤

እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ሆኖም

- ✓ በመንግሥት ቤቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት ለኦዲት ሥራ በናሙና ከተመረጡት የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኛ ፋይል ውስጥ በተገኘው መረጃ መሰረት አቶ ሰለሞን ተክሉ ከተባሉ የጽህፈት ቤቱ ሰራተኛ ላይ ከነሐሴ 2006 ዓ.ም ጀምሮ ብር 6,167.70 የወጪ መጋራት ክፍያ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

- ✓ ከብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል ከስድስት ሰራተኞች ላይ የወጪ መጋራት ክፍያ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

8.3.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የወጪ መጋራት የሚመለከታቸውን ሰራተኞች ፋይል ተጣርቶ እና መረጃ እንዲያቀርቡ ተደርጎ ሊሰበሰብ የሚገባው የመንግሥት ገቢ እንዲሰበሰብ መደረግ እንዳለበት እሳስበናል፡፡

8.4 <u>የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ ሆነው ግዴታቸውን ባልተወጡ መምህራኖች ላይ በገቡት ግዴታ መሰረት ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤</u>

8.4.1 <u>ግኝት</u>

በሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ለሚሰጠው የትምህርት ዕድል የግዴታ ውል የሚያስገባ፣ ዋስ የሚያስጠራ መሆኑን እና የትምህርት ዕድል ያገኙት መምህራን ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ግዴታቸውን የሚወጡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በኮሌጁ በመምህርነት ተቀጥረው ሲያገለግሉ የነበሩ 8 (ስምንት) መምህራን በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የሁለተኛ ዲግሪያቸውን እንዲማሩ የተፈቀደላቸውና ከኮሌጁም ጋር ውል የፈጸሙ ሲሆን፣ በገቡት ውል መሰረት ህጉን ካፈረሱ፡

- ✓ ለትምህርት
- ✓ ለምርምር
- ✓ በትምህርት ላይ ባሉበት ጊዜ ሲከፈላቸው የነበረውን ደሞዝ ታስቦ ተመላሽ እንዲያደርጉ ወይም ትምህርቱ የፈጀባቸውን ጊዜ እጥፍ አገልግሎት ለመስጠት ውል የገቡ እና ዋስትና ያስያዙ ቢሆንም መምህራኖቹ በውሉ መሰረት የገቡትን ግዴታ ሳይወጡ ስምንት መምህራኖች ሥራቸውን ለቀዋል፡፡ ሆኖም ኮሌጁ ግለሰቦቹ በገቡት ግዴታ መሰረት አስፈላጊውን እንዲፈጽሙ ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

8.4.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የኮሌጁ መምህራኖቹ በገቡት ውል መሰረት አገልግሎቱን እንዲሰጡ ወይንም ገንዘቡን እንዲከፍሉ ወይም ገንዘቡን ለመክፈል ፍቃደኛ ሆነው ካልተገኙም በሕግ አግባብ እንዲጠየቁ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

አባሪ. 1

<u>በደንቡና በመመሪያው መሰረት ያልተሰበሰበ (ያልተወራረደ) ሂሳብ</u>

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የሂሳብ ኮዶች							ድምር
		4201/4209	4202	4203/4208	4210/4211	4251/4253	4271/4273	4254/4274	
1	የቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር	3,227,690.29		1,482,470.25 *194,987.64	*38,587,009.67 282,918.21	* 237,169.66 1,551,760.17	76,512.27	6,637,445.61	52,277,963.77
1.1	በግብርና ሚኒስቴር ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ			210,538.09	* 56,811,021.87	*18,146,391.88 714,561.97			75,882,513.81
1.2	በቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር የቅድመ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት			6,567.34	* 1,187,677.44 27,907.86	* 2,594,253.45	13,688.00	31,984.03	3,862,078.12
1.3	የሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ				1,303,013.43	75,253.59			1,378,267.02
1.4	የግዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ			592,925.79	1,217,705.91				1,810,631.70
2	የአለርት ማዕከል							2,987.21	2,987.21
3	የእንሰሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን				11,255.57		28,029.62		39,285.19
4	የቀድሞው የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን							87,885.68	87,885.68
5	የትራንስፖርት ሚኒስቴር				*5,024.00				5,024.00
6	የቀድሞው አካባቢና ደን ሚኒስቴር			3,000.00			8,624.10		11,624.10
7	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን			27,721.88	* 2,088,284.51	*215,114.59			2,331,120.98
8	የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት				1,187.14			898.67	2,085.81
9	የጤና መድህን ኤጀንሲ			379.00	*39,355.38			264,267.73	304,002.11
	የሚዞር ድምር	3,227,690.29		2,518,589.99	101,562,360.99	23,534,505.31	126,853.99	7,025,468.93	137,995,469.50

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የሂሳብ ኮዶች							ድምር
		4201	4202/4206	4203/4208	4210/4211	4251/4253	4271/4273	4254/4274	
	የዞረ ድምር	3,227,690.29		2,518,589.99	101,562,360.99	23,534,505.31	126,853.99	7,025,468.93	137,995,469.50
10	የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	188,869.82	97,450.95	127,413.04	* 1,003,071.56	395,834.01		5,284,366.26	7,097,005.64
11	የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል		38,242.02	20,265.75	* 5,613.10 13,414.26			*1,436.94 1,758.00	80,730.07
12	የቀድሞው የውኃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር	3,705,851.11	15,039.32	11,108.65	369,767.59		286,393.98	20,754,067.05	25,142,227.70
13	የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት		39,938.29	*54,000.00	6,227.44	41,180.14			141,345.87
14	የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን						237,561.94		237,561.94
15	የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ	11,599.41							11,599.41
16	የቀድሞው ማዕድን ሚኒስቴር	1,921,951.78	82,588.30	83,736.43	21,193.72	59,824.28			2,169,294.51
17	ኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት			297,765.51	* 48,487.59 21,815.64	12,506.85		* 238.05	380,813.64
18	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	51,546.22			431,709.76				483,255.98
19	የኢትዮጲያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን			307,078.23	80,593.03 * 2,888.13	146,890.12			537,449.51
20	የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን			3,036.00			*108,373.17 1,020,187.03	* 622,717.16 975,625.31	2,729,938.67
21	የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር				400,304.78		201,637.21	5,732,684.55	6,334,626.54
22	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	214,098.99		1,007,573.04	17,649,359.70			643,404.27	19,514,436.00
23	የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት			3,652.25					3,652.25
24	የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ	720,563.23		575,738.70	* 627,997.84 173,503.08		20,710.02	289,772.31	2,408,285.18
25	የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር	124,838.56			* 26,810.89		131,096.51	7,810.51	290,556.47
26	የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን				162,720.22			82,827.62	245,547.84
27	የምግብ መጠጥና ፋርማስቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	435.00	27,303.10 * 7,540.98					49,187.31	84,466.39
	ጠቅላላ ድምር	10,167,444.41	308,102.96	5,009,957.59	122,607,839.32	24,190,740.71	2,132,813.85	41,471,364.27	205,888,263.11

* በ4206፣ 4208 ፣4209፣4210፣ 4251፣4254 እና 4271 የሚታየውን ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚያመለክት ነው፡፡

<u>ያልተከፈሉ ሂሳቦችን የሚያሣይ ዝርዝር</u>

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የሂሳብ ኮዶች							ድምር
		5001/5002	5003/5004	5006/5009	5005/ 5021	5028/5053	5035/5054	5055/5059/50 61	
1	የግብርና ሚኒስቴር	* 1,463,119.67		*628,010.73	* 18,942.68	27,977.09		*2,941,800.97	5,079,851.14
1.1	በግብርና ሚኒስቴር ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ		*20,501,328.66				* 319,978.66	2,088,639.28	22,909,946.60
1.2	በቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር የቅድመ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት			* 4,164.40 252.00	* 3,224.00	14,962.35	7,029.66	* 27,681.43	57,313.84
1.3	የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል							+ 180,457.78	180,457.78
2	የእንሰሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን			* 17,912.12		595.90		* 132,361.38	150,869.40
3	የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዮት		*492.44		*2,347.15			12,000.00	14,839.59
4	የአለርት ማዕከል	* 15,180.75						87,523.11	102,703.86
5	የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	* 4,647.50				127,536.84			132,184.34
6	የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል	* 3,773.03							3,773.03
7	የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት				16,407.90		* 53.00		16,460.90
8	የኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን		139,380.85	102,629.05	28,164.50	29,717.21	52,049.07	* 486,040.36	837,981.04
9	የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ	* 2,637,292.55					739,750.87		3,377,043.42
10	የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን	*59,375.71	1,357.65 *16,627.09						77,360.45
	ጠቅላላ ድምር	4,183,389.21	20,659,186.6 9	752,968.30	69,086.23	200,789.39	1,118,861.26	5,956,504.31	32,940,785.39

* በ5002 ፣ 5004፣ 5005፣ 5006 ፣ 5053፣ 5054 እና 5059 የሚታየውን ተከፋይ ሂሳብ የሚያመለክት ነው፡፡

\+ በ5061 የሚታየውን ተከፋይ ሂሳብ የሚያመለክት ነው፡፡

አባሪ. 3

የግዥ መመሪያውን ሳይከተል የተፈጸሙ ግዥዎች ዝርዝር

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የተፈጸመው ግዥ	ጨረታ ሳይወጣ የተፈጸመ ግዥ	ያለዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ
1	በግብርና ሚኒስቴርየቀድሞው የቅድመ ማስጠንቀቂያ ዳይሬክቶሬት	የመስተንግዶ የአገልግሎት ግዥ		58,738.09
2	የቀድሞው የውኃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር	የሆቴል አገልግሎት ግዥ	412,867.09	
3	የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት	የፎቶ ኮፒ ወረቀትና የቡናና ሻይ ቅጠል ግዥ		12,895.71
4	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	የህትመትና የቋሚ ዕቃ ግዥ		40,490.00
5	የኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን	የግሩፕ ቴብል ግዥ	181,986.35	
6	የኢትዮጵያ የጤና መድኀን ኤጀንሲ	ከኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ የመኪና ጥገና አገልግሎት ግዢ		29,806.88
7	የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	የህትመት አገልግሎት ግዥ	362,652.50	
7.1	የተቀናጀ የከተማ መሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት	ለመስተንግዶና ለመኪና ጥገና አገልግሎት ግዥ		94,287.29
8	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	ለተለያዩ ዕቃዎችና ለመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ		128,452.15
		የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ	118,527.07	
9	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ	2,972,685.64	
		የዕቃና የአገልግሎት ግዥዎች		221,350.97
	የሚዞር ድምር		4,048,718.65	586,021.09

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የተፈጸመው ግዥ	ጨረታ ሳይወጣ የተፈጸመ ግዥ	የለዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ
	የዞረ ድምር		4,048,718.65	586,021.09
10	የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ	ለመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ	587,520.40	
11	ማሪታይም ጉዳዮች ባለስልጣን	የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ		59,442.01
		ለቢሮ የሚያገለግሉ ቋሚ ዕቃዎች ግዥ	124,553.73	
12	የምርት ገበያ ባለሥልጣን	ለመስተንግዶ ግዥ		98,250.56
		በሬዲዮ ፕሮግራም ለማስተላለፍ	750,382.72	
13	የስትራተጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ	የአልሙኒዩም ፕሮፋይል ግዥ	117,399.93	
14	የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ	የመለዋወጫና የጥገና አገልግሎት ግዥ		68,406.56
15	የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን	የባለሙያ ጠረጴዛ ግዥ	179,999.84	
		ለፓርቲሽን ማሰሪያ	187,789.94	
16	የምግብ መጠጥና ፋርማስቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	የመስተንግዶ፣ የተለያዩ የአገልግሎትና የዕቃ ግዥዎች		234,980.17
		ለአልጋ፣ ለምግብና ለመሳሰሉት	238,944.59	
		ጠቅላላ ድምር	6,235,309.80	1,047,100.39

አባሪ. 4

የሒሳብ መደብ ያልጠበቀ እና በጀት ዓመቱን ሳይጠብቅ የተመዘገበ ወጪ ዝርዝር

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የተፈጸመው ግዥ	በጀት ዓመቱን ሳይጠብቅ የተመዘገበ ወጪ	በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ ወጪ
1	የቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር	ለተለያዩ ግዥዎችና አገልግሎቶች የተፈጸመ ክፍያ		318,850.00
1.1	በግብርና ሚኒስቴር ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ	ለሰልጣኞች ምሳ አበል ፣ለብሎን ቁልፍ መግዣና ለቀረጥ የተከፈለ		453,248.00
1.2	የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል	ለመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ወጪ የተደረገ		40,259.03
1.3	የግዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ	ለተለያዩ የአገልግሎት ግዥዎች የተፈጸመ ክፍያ		2,260,167.42
2	የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት	ለግለሰብ ካሳ ክፍያ፣ለሠራተኞቹ በሥልጠና ወቅት ለዉሎ አበልና ለትራንስፖርት ክፍያ		256,015.00
3	የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር	ለባንክ አገልግሎት ክፍያ		4,015.23
4	የኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን	የአገልግሎትና የዕቃ ግዥ	18,024.00	
5	የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	ለነዳጅ ግዥ ፣ለስልጠና የተከፈለ		8,539.92
		በሥልጠና ወቅት የምሳ አበል አበል ክፍያ		337,960.00
6	የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ	ለውሎ አበል፣ለትራንስፖርትና ለጥገና የተከፈለ		17,240.54
7	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	ለተሽከርካሪዎች ጥገና የተፈጸመ ክፍያ	29,659.79	
8	የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዮት	ለመኪና ዕቃ መለዋወጫ ግዥ		7,475.00
		ለደንብ ልብስ ማሰፊያ		46,660.00
9	የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን	የተለያዩ ግዥዎችና ለአገልግሎት ክፍያ የተፈጸመ		322,314.94
10	የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል	ለትርፍ ሰዓት ሥራ የተፈፀመ ክፍያ		79,086.45
የሚዞር ድምር			47,683.79	4,151,831.53

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የተፈጸመው ግዥ	በጀት ዓመቱን ሳይጠብቅ የተመዘገበ ወጪ	በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ ወጪ
		የዞረ ድምር	47,683.79	4,151,831.53
11	የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት	ለተለያዩ አገልግሎቶችና ግዥዎች፣ ለቤትና ለትራንስፖርት አበልና ለማማከር አገልግሎት		2,157,069.41
12	የቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	ለትርፍ ሰዓት፣ ለኢንተርና እና ለሥልጠና የተከፈለ		166,371.04
		ለምግብ ጥሬ ዕቃና ለቢሮ አላቂ ዕቃዎች ግዥ	291,126.30	
13	የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን	ለትራንስፖርት፣ ለኢንሹራን፣ ስለሥልጠና ለነዳጅ ግዥ		1,253,999.14
14	የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን	ለውሎ አበል፣ ለትራንስፖርትና ሰራተኞችን ለማስፈተን የተፈጸመ ክፍያ		49,202.92
		ለትርፍ ሰዓት ልዩ የሾፌሮች አበል እና ለመስተንግዶ አገልግሎት የተከፈለ	7,784.23	
15	የቀድሞው ማዕድን ሚኒስቴር	ለአገልግሎት የተፈጸመ ክፍያ	86,273.00	
16	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	ለውሎ አበልና ለመብራት አገልግሎት የተፈጸመ ክፍያ	72,640.90	
		ለተለያዩ የአገልግሎትና የዕቃ ግዥዎች የተከፈለ		15,169.12
17	የአለርት ማዕከል	ለሆስፒታሉ የሕክምና ሪኤጀንት ግዥ የተፈጸመ	60,680.78	
18	የአባይ ተፋሰስ ባለስልጣን	ለተለያዩ የወጪ ክፍያዎች		15,489.17
		የማጓጓዣ፣ የማስጫኛና የማራገፊያ ክፍያዎች		3,850.00
19	የኢትዮጵያ ግብርና ኢንቨስትመንት መሬት አስተዳደር ኤጀንሲ	ለተለያዩ አገልግሎቶች የተፈጸመ ክፍያ		48,183.10
20	የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ	ለስፖርት አሰልጣኞች የተፈጸመ ክፍያ		141,003.31
21	የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	ለልዩ ልዩ ግዥዎችና አገልግሎቶች የተፈጸመ ክፍያ		597,826.00
		ጠቅላላ ድምር	566,189.00	8,599,994.74

ያልተሰራበትን እና ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የተደረገውን የሚያሳይ ዝርዝር

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ያልተሰራበት በጀት		ለየሒሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ	
		ከመደበኛ በጀት	ከካፒታል በጀት	ከመደበኛ በጀት	ከካፒታል በጀት
1	የቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር	16,144,675.20	4,315,145.39		
1.1	በግብርና ሚኒስቴር ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ		5,084,628.84		23,978.82
1.2	የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል	7,386,829.14	5,066,703.42		
1.3	የቅደመ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት	1,309,508.53			
1.4	የሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ	* 1,919,181.86	3,616,406.25		193,473.05
1.5	የግዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ		6,229,906.90		3,828,815.26
2	የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	3,397,357.23			
2.1	በገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል	1,355,938.16			
3	የቀድሞው የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር	7,476,041.89	31,127,555.25		
4	የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	17,720,322.45	32,068,867.10		
4.1	የመንግሥት ቤቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት		9,448,730.29		
4.2	የተቀናጀ የከተማ መሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት	678,172.92	860,108.56		
5	የኢትዮጵያ መድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን	6,030,218.60	342,514.28	4,355,046.02	44,795.20
6	የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ	13,930,699.05		1,952,325.26	
7	የቀድሞው የማዕድን ሚኒስቴር	2,841,548.41	23,501,928.12		
8	የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት	462,932.99			
9	የኢትዮጵያሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢኒስቲትዮት	4,316,928.26			
	የሚዞር ድምር	84,970,354.69	121,662,494.40	6,307,371.28	4,091,062.33

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ያልተሰራበት በጀት		ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ	
		ከመደበኛ በጀት	ከካፒታል በጀት	ከመደበኛ በጀት	ከካፒታል በጀት
	የዞረ ድምር	84,970,354.69	121,662,494.40	6,307,371.28	4,091,062.33
10	ትራንስፖርት ሚኒስቴር	4,343,088.49			
11	የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	134,589.28	31,516,509.43		
12	የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢኒስቲትዩት	2,878,516.69	8,467,446.72		
13	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	7,063,084.39		1,853,811.93	
14	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	3,417,857.33	6,195,876.23		
15	የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ	2,896,962.01			
16	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	5,543,100.27 * 13,594,413.97	4,297,236.16		
17	የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን	3,84,053.44			
18	የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ	1,568,464.67		31,132.36	
19	የብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢኒስቲትዩት	4,969,094.13		5,513,857.90	
20	የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን	2,043,596.48			
21	የብሔራዊ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ አስተዳደር ጽ/ቤት	186,308.00			
22	የህብረት ሥራ ኤጀንሲ	452,265.27			
23	የቀድሞው የአካባቢና ደን ሚኒስቴር	9,576,662.77	16,531,871.70	289,570.11	2,808,854.91
24	የመንገድ ፈንድ ጽሕፈት ቤት	380,808.81			
25	የሰራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር	660,768.63		214,604.94	
26	የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን	377,694.99	303,452.08		
27	የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን	1,937,844.47	1,149,226.15		
	የሚዞር ድምር	146,995,475.34	190,124,112.87	14,210,348.52	6,899,917.24

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ያልተሰራበት በጀት		ለየሒሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ	
		ከመደበኛ በጀት	ከካፒታል በጀት	ከመደበኛ በጀት	ከካፒታል በጀት
	የዞረ ድምር	146,995,475.34	190,124,112.87	14,210,348.52	6,899,917.24
28	የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን	6,022,504.51	12,506,187.36	4,393,004.70	
29	የኢትዮጵያ ጤና መድኅን ኤጀንሲ	7,484,825.69			
30	የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል	125,120.60	9,345,743.80		
31	የአለርት ማዕከል	83,095.65			
32	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	1,457,578.43			
33	የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን	2,205,698.56			
34	የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	4,102,418.69		1,878,849.04	
35	የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ	5,291,298.02		1,627,005.20	
36	የኢትዮጵያ ግብርና ኢንቨስትመንት መሬት አስተዳደር ኤጀንሲ	3,793,913.34		112,494.90	
37	የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች ተፋሰስ ባለስልጣን	1,389,886.74			
38	የምግብ መጠጥና ፋርማስቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	1,919,459.92			
	ድምር	180,871,275.49	211,976,044.03	22,221,702.36	6,899,917.24

* ከውስጥ ገቢ የተረፈውን በጀት የሚያሳይ ነው፡

የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2007 በጀት አመት ኦዲት የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት

በዳይሬክቶሬቱ 36 መ/ቤቶች ታቅደው ሁሉም ኦዲት የተደረጉ ሲሆን የተሰጠው ኦዲት አስተያየት ነቀፌታ የሌለበት (Clean Opinion) 17 መ/ቤት ከጥቂት ስህተቶች በስተቀር አጥጋቢ በመሆኑ ነቀፌታ ያለበት (Except for opinion) 13 መ/ቤቶች የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ (Adverse opinion) 4 መ/ቤቶች አቋም ለመውሰድ ያልተቻለባቸው (Disclaimer opinion) 2 መ/ቤቶች ናቸው፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ -2/ ሀ እስከ መ ተመልክቷል/

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ

1.1. ጥሬ ገንዘብ

- በመከላከያ ሚኒስቴር
  - በሐምሌ 1 ቀን 2007 በውስጥ ኦዲተሮች በቆጠራ ከተረጋገጠው የክፍሎች የጥሬ ገንዘብና የሰነድ ቆጠራ ሰኔ 30 ቀን 2007 በክፍሎች በሪፖርት ከሚታየው ከወጪ ቀሪ ጋር ሲመዛዘን በስልጠና ዋና መምሪያ በብር 34,061.35 በልጦ ተገኝቷል፡፡ በሎጅስቲክ ዋና መምሪያ በቆጠራ የተገኘው በሪፖርት ከታየው ከወጪ ቀሪ በብር 11,957.12 አንሶ ተገኝቷል፡፡
  - ለረዥም ዓመታት ሳይተካ የቆየ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 262,990.69 ተገኝቷል፡፡

1.2 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

- በፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኤጀንሲ
  - የኤጀንሲው ዋና ገንዘብ ቤት በርና ካዝና ባልታወቀ ሁኔታ ተሰብሮ በመዘረፉ ብር 107,529.71 ጉድለት የተገኘ መሆኑን ከጥር 1 ቀን 2007 እስከ መጋቢት 30 ቀን 2007 ከቀረበው ውስጥ ኦዲት ሪፖርት መረዳት ተችሏል፡፡

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2007 የጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ በሂሳብ መደብ 4101 ብር 115,114.13 የተመለከተ ሲሆን፣ ሐምሌ 1 ቀን 2007 በውስጥ ኦዲተሮች በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረው ጥሬ ገንዘብ ብር 11,558.25 በመሆኑ በቆጠራ ያልተገኘ ብር 103,555.88 ሪፖርት ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

  በአገር መከላከያ ሚ/ር ድርጅቶቹ ሲፒኦውን ካልወሰዱ ምዝገባው መስተካከልና ሪፖርቱም ምዝገባውን መሰረት አድርጎ መዘጋጀት እንዳለበት፤ ቆጠራ ያልተደረገ ጥሬ ገንዘብ በሪፖርት ማሳያቱ አግባብ ባለመሆኑ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

  ኤጀንሲው በውስጥ ኦዲት የተገኘውን የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 107,456.71 ከሠራተኛዋ ተመላሽ ለማድረግ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ ለወደፊቱም ኤጀንሲው በሥሩ የሚጠበቀውን ጥሬ ገንዘብ ለአደጋና ለስርቆት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ጥበቃ እና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት በተጨማሪም በካዝና የሚቀመጠው የጥሬ ገንዘብ መጠን በፋይናንስ መመሪያው መሠረት ሊያስተካክል እንደሚገባና፡በብልጫ ሪፖርት የተደረገው ሪፖርቱን ስለሚያዛባ ልዩነቱ በሳጥን ጉድለት በ4202 የማስተካከያ ምዝገባ ተካሂዶ የሰኔ 30 2007 ሪፖርቱም ሊታረም እንዳለበት አሳስበናል።

  የጥ/አ/ኢ/ኦጀንሲ በጉድለት የተገኘውን ገንዘብ በተመለከተ በወቅቱ ገንዘብ ያዧ በፖሊስ ቁጥጥር ስር እንዲውሉና እንዲመረመሩ የተደረገ ስለሆነ ከዚህ ጎን ለጎን ከቦታቸው እንዲነሱ መደረጉን በአሁኑ ወቅትም የፖሊስ ምርመራ ውጤቱ በመጠናቀቁ ጉዳዩ በፍ/ቤት በመታየት ላይ መሆኑንና፤ የመጨረሻ እልባት ሲሰጠው በውሳኔው መሠረት ተገቢው እንደሚፈጸም ገልጸዋል፡፡

1.3 <u>የባንክ ሂሳብ</u>

- **<u>በፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኤጀንሲ</u>**
  - ኤጀንሲው ሚያዝያ 8 ቀን 2007 ቁጥር 1220/15-2/3 ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሰንጋ ተራ ቅርንጫፍ በፃፈው ደብዳቤ ከባንክ ሂሳብ ቁጥራቸው ብር 286,120.80 ብቻ ተቀናሽ በማድረግ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዋሳ ቅርንጫፍ በባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000070084647 ለአማ ወረቀት እና የወረቀት ማሽኒያ አምራች ኃ/የተ/የግ/ማህበር እንዲተላለፍ በጠየቀው መሰረት ገንዘቡ ለባለጥቅሙ ማስተላለፉ ቢሆንም ሂሳቡ በወጪ ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡
  - አማ የተባለው ድርጅት ለተከፈለው ብር 286,120.80 እቃውን በሙሉ ማቅረብ ባለመቻሉ ብር 178,825.50 ተመላሽ ተደርጎ የገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት ቢሆንም በባንክ ሌጀር ላይ ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡
- በኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ብር 70,332,928.12 በሂሳብ መደብ /4104/ ለረጅም ጊዜ እልባት ሳያገኝ ተገኝቷል፡፡

  በጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢኒስቲቲዩት በሌተር ኦፍ ክሬዲት የባንክ ሂሳብ /4104/ ብር 70,332,928.12 ሂሳብ መቼ ጀምሮ የተከፈተ መሆኑንና የሌተር ኦፍ ክሬዲት ሂሳብ በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉን በመግለጽ በባንክ በሌተር ኦፍ ክሬዲት የሚታየው የገንዘብ መጠን ለረጅም ጊዜ የቆየ በመሆኑ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ ሂሳቡ እልባት ሊያገኝ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

  ኤጀንሲው የበጀት ዓመቱ ሂሳብ ተሠርቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የተላከ መሆኑንና ምዝገባውን ለማስተካከል መቸገራቸውን ከአሁን በኋላ ግን በተሰጠው አስተያት መሰረት የባንክ ሂሳብና ሌጀር አመዘጋገብ ላይ ተገቢውን ጥብቅ ክትትል በማድረግ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈጸም ቁጥጥር እንደሚደረግ ገልጸዋል፡

1.4 የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ያልተሰራ

➢ በፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የሚገለገልባቸውን የባንክ ሂሳብ ቁጥሮች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30 ቀን 2007 ዓ.ም.በባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ እና በባንክ ሂሳብ ሌጀር የተመለከተውን ከወጪ ቀሪ ለማስታረቅ የባንክ ማስታረቂያ ያልተሠራ መሆኑን በመግለጽ ማስታረቂያው የባንክ ሂሳቡን ለመቆጣጠር የተዘረጋ መሆኑን በመግለጽ እንዲዘጋጅ አሳስበናል፡፡

2. ተሰብሳቢ ሂሳብ

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	የገንዘብ መጠን
1	አገር መከላከያ ሚ/ር	139,258,386.16
2	የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	7,227,176.70
3	ኢንፎረሚሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ	2,273,592.29
4	ንግድ ሚኒስቴር	1,604,015.98
5	የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ	25,053.92
6	የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚ/ር	201,875.35
7	የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮምሽን	84,611.77
8	ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ	11,859.00
9	ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት	16,115.65
10	ፍትህ ሚኒስቴር	37,668.26
11	የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠኛ ማዕከል	52,623.34
12	የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን	28,100.00
13	የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	71,943.39
14	በብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	172,191,236.99
15	በካይዘን ኢንስቲቲዩት	13,345.01
16	በፌዴራል ፖሊስ	141,284.02
17	በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት	2,876,990.56
	ድምር	**326,115,878.39**

- በአገር መከላከያ ሚኒስቴር የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሰራተኛ የሰሌዳ ቁጥሩ WMZ-2551 ባለጎማ የጦር ተሸከርካሪ (PTR) በአፋር ክልላዊ መንግስት ወረዳ

ዱብቲ ነዳጅ (ናፍጣ) የጫነ ቦቴ የሰሌዳ ቁጥር 3-15023 በመግጨቱ የተጎዳ እንሹራስ ህብረት ኢንሹራስ ካሳ ይግባኝ ጠይቆ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሹፌሩ ጥፋተኛ መሆኑን በመወሰን ለከሳሽ ህብረት ኢንሹራስ ብር 778,891.52 እና ኪሳራ ብር 71,142.10 ወለድ ብር 18,599.73 በድምሩ ብር 868,633.35 ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የባንክ ሂሳብ ተቆርጦ ለከሳሽ እንዲከፈል የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በፍ/ቤቱ መታዘዙን በመግለጽ ተቀንሶ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘው ጥፋተኛ ከሆነው ሠራተኛ እስኪተካ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው እንደ መ/ቤቱ ወጪ ብር 868,633.35 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

- በአየር ሃይል ጠቅላይ መምሪያው ከብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፕሬሽን ጋር የመማሪያ ክፍሎችን ለማስገንባት በብር 17,780,040.00 የተዋዋለ ሲሆን፣ ጠቅላይ መምሪያው ለኮርፕሬሽኑ የግንባታ ደንብና መመሪያ ከሚፈቅደው የቅድሚያ ክፍያ 30% ውጪ 50% ብር 8,890,020.00 የከፈለና በቅድሚያ ክፍያ መመዝገብ ሲገባው በቀጥታ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

  በአገር መከላከያ ሚ/ር ለረጅም አመታት ሳይሰበሰቡ የቆዩት፤ ከማን እንደሚሰበሰቡ የማይታወቁት፤ማስረጃ የሌላቸው ሂሳቦች ላይ ክትትል ተደርጎ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ከመደብሩ ጋር የተደረገው ውል ሳይታወቅና ሰነዱ ለኦዲት ሳይቀርብ ይህን ያክል ከፍተኛ ገንዘብ በተሰብሳቢ መዝግቦ መያዙ ጠቅላይ መምሪያው የመንግስትን የሂሳብ አሰራር ያልተከተለና የመንግስት ገንዘብ ለብክነት የሚደረግ በመሆኑ ሁኔታው ተጣርቶ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የምዕራብ ዕዙ በተሰብሳቢ ሂሣብ ላይ አስፈላጊውን ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ በወቅቱ ሊሰበስብና ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ሂሳቦች በመመሪያው መሰረት ውሳኔ እንዲያገኙ በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ለረጅም ዓመታት በተሰብሳቢ የሚታዩና የሚሰጠው መልስ በየበጀት ዓመቱ እየተጣራ መሆኑን ተመሳሳይ መልስ ከመስጠት ባሻገር እርምጃ ያልተወሰደባቸው በርካታ ሂሳባች ስላሉ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡ በአሰተዳደርና ፋይናንስ በሌሎችም የሚገኙት ተሰብሳቢ ሃሳቦች እንዲወራረዱ የተጠናከረ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የተገኘው ብር 55,758.00 ከ2005 ጀምሮ ሲንከባለል የመጣ ለሠራተኞች የተሰጠ የረዥም ጊዜ ብድር፤ ብር 3,750,252.07 ህዳር 02/2007ዓ.ም በድሬደዋ ሁሉ አቀፍ ማረሚያ ቤት እያሰራ ላለው የታራሚ መኖሪያ ቤት እና የአስተዳደር ህንፃ ግንባታ ቦታ ለሚነሱ ባለይዞታዎች የካሳ ክፍያ በሚል፤ ብር 3,421,166.63 የካቲት 06/2006ዓ.ም ለሰይድ ይማም አሊ አስመጪ የተለያዩ የደንብ ልብሶች ግዥ 30% ቅድመ ክፍያ ተፈጽሞ ከ1ዓመት እስከ ስምንት ወር ባላይ የቆየ ሲሆን አስተዳደሩ በሰጠው የሥራ አመራር ምላሽ የድሬደዋ ማረሚያ ቤት የካሣ ክፍያውን ባለመክፈሉ እንደተንጠለጠለ መታየቱን፤ የተለያዩ የደንብ ልብሶች ግዥ 30% ቅድመ ክፍያ በተመለከተ የመ/ቤታቸው የሕግ አገልግሎት እንደሚከታተለው መመሪያ ተሰጥቶበት ውጤቱን እየጠበቁ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የአስተዳደር መ/ቤቱ በፋይናንስ ደንቡ መሠረት ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ እዲወራረድ ተገቢው ክትትል ሊያደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3. <u>የገቢ ሂሣብ</u>

3.1 <u>በገቢ ግብር ቀረጥና የታክስ ሕግ መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ፤</u>

በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከቤት አበል ያልተቀነሰ የገቢ ግብር ብር 2,332,802.70 ፍ/ቤቱ ከቤት አበል ላይ ተቀናሽ የሚሆነውን የገቢ ግብር በግብር አዋጅ ፣ ደንብና ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባወጣው መመሪያ መሰረት እንዲፈፀም እና እስካሁንም ያልተቀነሰው የገቢ ግብር ከሚመለከታቸው ተመላሽ መደረግ እንደሚኖርበት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.2 <u>በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ ሌሎች የአሰራር ድክመቶች</u>

<u>በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት</u>

- በገቢ ደረሰኝ የተሰበሰበበው ገቢ ከ2 ቀናት እስከ 20 ቀናት ዘግይቶ ባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገ ብር 924,657.66 በመመሪያው መሠረት ገንዘቡ በተሰበሰበበት ዕለት ወይም በማግስቱ ባንክ ገቢ እንዲሆን ክትትል መደረግ እንደሚኖርበት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

ፍርድ ቤቱ በፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ውሳኔ መሠረት ያልተቀነሰ መሆኑንና አሁንም ጉዳዩ ለጉባዔው በአጀንዳነት ቀርቦ መመሪያ በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም በዕለቱ ወይም በማግስቱ ባንክ ገቢ ሳይደረግ ለመዘግየቱ ምክንያት የሆኑ ችግሮችን ለማቃለል በየምድብ ችሎቱ አቅራቢያ በሚገኙ ባንኮች ገቢ ማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ የአሰራር ሥርዓት እየዘረጉ እንደሆነና ለወደፊቱ በመመሪያው መሠረት ለመፈፀም ጥረት እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

3.3 <u>ለሚመለከተው ፈሰስ ያልተደረገ ሂሳብ</u>

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት ጽ/ቤቱ ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት አክስዮን ማሕበርና ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በጋራ በመተባበር ለታላቅ ህዳሴ ግድብ የሚውል ገቢ የማሰባሰብ ሥራ ሲሠራ የ8100 ኤ ጨዋታ በመጠናቀቁ ኢትዮ ቴሌኮም የሰበሰበው ብር 82,151,551.00 ለሚመለከተው አከል ገቢ አለመደረጉ ታውቋል፡፡እንዲሁም በኢትዮ ቴሌኮምና በኮርፖሬሽኑ በልዩነት የሚታይ ሂሳብ ብር 1,453,461.00 ተገኝቷል፡፡

በልዩነት የሚታየውን የገንዘብ መጠን ሊጣራ እንደሚገባና የተሰበሰበውም ገንዘብ ለህዳሴ ግድብ ይውል ዘንድ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡ ገቢው በጽ/ቤቱና በኢትዮ ቴሌኮም በጋራ በመነጋገር የሚፈጸም መሆኑን ፤ ያለው ሂሳብ ተጣርቶ ገንዘቡ ገቢ ለመሆኑ ክትትል በማድረግ ይህንንም በአጭር ጊዜ እንደሚተገበሩ ገልጸዋል፡፡

3.4 <u>በተፈጸሙ ግዥዎች ላይ በታክስ ህጉ መሠረት ያልተቀነሰ</u>

- የሕግ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽ/ቤት

የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT)	ብር	21,476.94
የዊዝሆልዲንግ ታክስ	ብር	<u>2,863.59</u>
በድምሩ	ብር	<u>24,340.53</u>

ጽ/ቤቱ ግዥ ፈጸሞ ከላይ የተጠቀሰውን ሳይሰበስብ ተገኝቷል፡፡

መንግስት ባወጣው የገቢ ግብር አዋጅ መሰረት ገቢዎች ሳይሰበሰቡ እንዳይቀሩ ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

4.1 <u>የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>

- ፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ብር 1,779,105.92
- የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ›› 721,940.68
- የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ›› 10,000,000.00
- በሀገር መከላከያ ምዕራብ ዕዝ ጠቅላይ መምሪያ ›› 257,587.20
- የመከላከያ ሚ/ር አየር ሃይል ጠቅላይ መመሪያ ከኢ.ፌ.ድ.ሪ ብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር በገባው ውል መሠረት ክፍያ ፈጽሞ የቀረበው የኮርፖሬሽኑ የገንዘብ መቀበያ የገቢ ደረሰኝ ብር 3,153,643.41 በወጪ የተመዘገበው ብር 3,700,704.00 በመሆኑ ፣ በድምሩ ብር 13,301,694.39 ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኤጀንሲ በአዳማ፣ በደብረዘይትና በባህርዳር ሥልጠና በሰጠበት ወቅት ሠልጣኞች ከየክልሉ እንዲሰለጥኑ የተላኩበት ደብዳቤ በማስረጃነት ለኦዲት ባለመቅረቡ ለውሎ አበል እና ለትራንስፖርት የተከፈለውን ወጪ ከማስረጃው ጋር አገናዝቦ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን በመግለጽ ኤጀንሲው ከየክልሉ ለተወጣጡ ሰልጣኞች ለከፈለው አበል ከክልሉ የተላኩ ለመሆኑ ተገቢው የሠልጣኞች ዝርዝር ማረጋገጫ በማስረጃነት ሊቀርብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በ2007 ለተካሄደው ምርጫ ለሲቪክ ማህበራት በባንክ ተልኮ ተገቢው ማስረጃ ሳይቀርብለት ሂሳቡን በወጪ መመዝገብ ለመንግስት ገንዘብ መባከን መንስዔ ሊሆን ስለሚችል ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበትና የተጠቀሰው ሂሳብ ተጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድ እንዲሁም ገንዘቡ ለታቀደለት ዓለማ ለመዋሉ መረጋገጥ እንዳለበት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.2 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ አለ አግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

- የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር ብር 75,030.40
- የሰነዶች ማረጋገጫናምዝገባ ጽ/ቤት " 16,134.50
- የኢትዮያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት " 190,577.10
- የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት " 186,547.50
- የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ›› 2,261,095.55
- በአገር መከላከያ ሚኒስቴር በተመሳሳይ ጉዞና ቀናት

  ቀናት በድጋሚ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 12,725.00

የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር ለሠራተኞቹ በትርፍ ጊዜያቸው ቢሮ ውስጥ ለሠሩ 2 ሠራተኞች ከሥራ ሰዓት በፊት ጠዋት እስከ 2፡30፣ ከሰዓት ከ11፡30 በኋላ እንዲሁም ቅዳሜና እሁድ በሹፌርነት ሰርቪስ ለሰጡ ሹፌሮች የቀን የውሎ አበል 25% በማሰብ የትርፍ ስዓት ክፍያ ወይም የምሳ አበል የተፈጸመ ክፍያ፣ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት፣ የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት በተመሳሳይ ሁኔታ ከመመሪያ ትርፍ ሰዓትና ቅዳሜ እና እሁድ ሥራ ገብተው ለሰሩበት የተፈፀመ ክፍያ፣ የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት የውሎ አበል ቅፅ ላይ በውሎ አበል ቅጾች ላይ ለሥራ የቆዩበት ጊዜ ሳይሞላ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ አሰራሩ ከመመሪያ ውጪ መሆኑን በመግለጽ እንዲታረም አሳስበናል፡፡

4.3 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተል የተፈጸሙ ግዥዎች፤

ተ.ቁ	መ/ቤት ስም	የገንዘብ መጠን
1	የአገር መከላከያ ሚ/ር	1,445,499.69
2	የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	25,961,711.36
3	የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ማህበራት ኤጀንሲ	6,807,600.00
4	የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን	4,540,740.22
5	የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽ/ቤት	121,850.00
6	በፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች	82,013.00
7	የፌዴራልማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	1,994,410.00
8	የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ	324,113.13
9	የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት	774,908.50
10	የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	20,397,758.10
11	የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት	813,653.06
12	የቀድሞው የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ	96,522.79
13	የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረሙስና ኮሚሽን	35,873.10
14	ንግድ ሚኒስቴር	729,253.33
15	የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ	15,974.11
16	የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር	179,593.77
17	የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ	162,951.07
18	የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	388,313.07
19	የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	418,596.13
20	የሕግ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽ/ቤት	83,066.22
21	የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የስልጠና ማዕከል	11,876.32
	ድምር	39,424,565.61

ከዚህ ውስጥ ከፍተኛው ግዥ ከተከናወባቸው መ/ቤቶች ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ሲሆን፤ ለ2007 አገራዊ ምርጫ የአገልግሎትና የአልባሳት ግዥ ሲፈጸም በግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት አለመፈጸሙን በመግለጽ ሕጉን ተከትሎ ግዥ እንዲፈጸም አሳስበናል፡፡ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስተሪ ልማት ኢኒስቲትዩት በግልጽ

ጨረታ ወይም ከግልጽ ጨረታ ውጭ የሌሎች የግዥ ዘዴዎችን በመጠቀም፣ የግዥ ዘዴዎችን የመረጠበትን ምክንያት እና ሁኔታዎች ሠነድ /መረጃ/ በማሟላት ግዥውን መፈጸም እንዳለበት የግዥ ደንቡ የሚያዝ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ ይህን መመሪያ ባለመከተል ግልጽ ጨረታ ያልወጣና ሌሎች የግዥ ዘዴዎችን ለመምረጡ መረጃ ሳይኖር ግዥውን ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ኢኒስቲትዩቱ የአገልግሎት ግዥ የተፈጸመባቸው ኢንስቲትዩቶች የንግድ ድርጅቶች አለመሆናቸውን የሥራዎቹ ባህሪያት ፣ ሀገራት ከሀገራት ጋር ባላቸው የትብብር ግንኙነቶች የአቅም ግናባታና የቁርኝት ሥራዎች በውል ታስሮ የሚሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡ ይሁን እንጂ ይህን የሚደግፍ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ የበጎ አድራጎትና ማህበራት ኤጀንሲ እና የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ያለውድድር የቢሮ ኪራይ መፈጸማቸው አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ ውሉ ተቋርጦ በግዥ ህጉ መሰረት እንዲፈጸም አሳስበናል፡፡ በአገር መከላከያ ሚ/ር በ2007 በተከበረው የመከላከያ በአል ለተፈጸመ ግዥ በአብዛኛው ህጉ ከሚፈቅደው ውጪ ግዥዎች የተፈጸሙ ሲሆን አሰራሩ እንዲስተካከል አሳስበናል፡፡

4.4 <u>የተለያዩ የመሰረተ ልማት ግንባታ ወጪዎች</u>

በመከላከያ ሚ/ር አየር ሃይል ጠቅላይ መምሪያ ከብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፐሬሽን ጋር የመማሪያ ክፍሎችን ለማስገንባት በብር 17,780,040.00 ተዋውሎ ጠቅላይ መምሪያው ለኮርፐሬሽኑ የግንባታ ደንብና መመሪያ ከሚፈቅደው የቅድሚያ ክፍያ 30% ውጪ 50% ብር 8,890,020.00 አየር ሃይል ጠቅላይ መምሪያው ከብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፐሬሽን ጋር የመማሪያ ክፍሎችን ለማስገንባት በብር 17,780,040.00 የተዋዋለ ሲሆን፣ ጠቅላይ መምሪያው ለኮርፐሬሽኑ የግንባታ ደንብና መመሪያ ከሚፈቅደው የቅድሚያ ክፍያ 30% ውጪ 50% ብር 8,890,020.00 የከፈለና በቅድሚያ ክፍያ መመዝገብ ሲገባው በቀጥታ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

4.5 <u>በባለስልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ</u>

- በመከላከያ ወጪውን እንዲያጸድቁ ባልተፈቀደ ላቸው ብር 676,294.80
- በፌዴራል ጥ/አ/ኢ/ልማትኤጀንሲ “ 101,850.38
- በኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ “ 122,728.01
- የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መ/ቤቶቹ “ 45,350.09

መ/ቤቶቹ የሚፈጽሟቸው ክፍያዎች ለመ/ቤቱ አገልግሎት ስለመሆኑ በሚመለከተው ኃላፊ ሊፀድቅ እንደሚገባ እሳስበናል፡፡

4.6 <u>በብልጫ የተከፈለ</u>

- የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ብር 35,000.00
  ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ግዥ መፈጸሙ
  ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበው ተወዳዳሪ ግዢ አለመፈጸሙ
  የመንግስት መመሪያን ያልተከተለ በመሆኑ አሠራሩ
  ሊታረም እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.7 <u>የወጪውን ትክክለኛነት ማጣራት ያልተቻለ ሂሳብ</u>

በአገር መከላከያ ሚኒስቴር በተለያዩ ዋና ዋና የወጪ አርዕሰቶች በወታደራዊ ዘርፍ ብር 5,822,729,792.71 በአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ብር 7,967,122.58 በድምሩ 5,830,696,915.29 ከበጀት ዓመቱ ጠቅላላ ወጪ ጋር ሲገናዘብ በመቶኛ 66.5 ወይም (66.5%) (5,830,696,915.00/8,767,277.769.00) ይሆናል፡፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ለሚኒስትሩ በተሰጠ ስልጣን በወጣው መመሪያ መሰረት ሚስጥር ናቸው በሚል ኦዲት ያልተደረገ ሂሳብ ነው ፡፡

- የመከላከያ የሲቪል ሰራተኞች ደመወዝ በመመሪያው ኦዲት እንዳይደረግ ያልተከለከለ ቢሆንም ዝርዝር ማስረጃዎች እና የደመወዝ መክፈያ ዝርዝር /Payroll/ ለኦዲት ስራ ባለመቅረቡ በድምሩ ብር 28,653,118.45 ኦዲት ማድረግ አልተቻለም፡፡

  - የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 1,110,865.88 መ/ቤቱ ለስራአመራር ሪፖርቱ በሰጠው መልስ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የ2007 በጀት ዓመት አምስት የስራ ክፍሎችን እና የማዕከል ምዝገባን ኦዲት ያደረገ ሲሆን ለኦዲት ስራ የቀረበለትንና ያልቀረበለትን ሂሳብ መደቦች በመቀላቀል፣ ኦዲት ያልተደረጉትን ክፍሎች ኦዲት እንደተደረጉ በማድረግ የተጠቃለለ ሂሳብ ሪፖርት በመውሰድ ለኦዲት ስራ ስላልቀረቡ ኦዲት ማድረግ እንዳልተቻለና ግኝት መሆኑ አግባብነት

እንደሌለው ጠቅሶ ለቀረበው ግኝት በሚከተሉት ሂሳቦች ላይ ማስረጃ እንደቀረበ ገልጸዋል፤

- በሂሳብ መደብ 6112 የሰራዊት ደሞዝ የብር መጠን 2,639,352,578.46 እና በሂሳብ መደብ 6122 የወታደራዊ አበል የብር መጠን 783,840,226.18 የተጠቃለለ ሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታየው በማዕከል ምዝገባ በየሂሳብ መደቡ ወጪ መዘርዘሪያ፤ ኦርጂናል ፔሮል ሳመሪ፤ በወጪ ማስመስከሪያ በሂሳብ መደብ 4008-01 መሰረት ለኦዲት ስራ መቅረቡን፡
- በሂሳብ መደብ 6115 የውጭ የኮንትራት ሠራተኞች ምንዳ ብር 3,999,743.52 የተጠቃለለ ሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታይ ኦዲት የተደረጉና ያልተደረጉ የስራ ክፍሎች ጠቅላላ ድምር መሆኑን፡ ለምሳሌ፡- የማዕከል ምዝገባ በዚህ ሂሳብ መደብ ለኦዲት ስራ ቀርቧል፡፡
- በሂሳብ መደብ 6132 ለወታደራዊ አባለት የመንግስት የጡረታ መዋጮ ብር 651,118,684 በማዕከል ምዝገባ ላይ የሚታይ ለኦዲት ስራ መቅረቡን፤
- በሂሳብ መደብ 6211 የሠራዊት የደንብ ልብስ የብር መጠን 452,944,233.14 ኦዲት በተደረጉና ባልተደረጉ የስራ ክፍሎች ወጪ የሆነ የድምር ውጤት ቢሆንም ኦዲት የተደረጉ ክፍሎች ግን ሰነድ ማቅረባቸውን፡
- በሂሳብ መደብ 6416 ለግለሰቦችና ተቋመት ካሳ ብር 21,341,346.05 እና በሂሳብ መደብ 6417 ለግለሰቦች ስጦታ ብር 111,602,407.53 ኦዲት የተደረጉና ኦዲት ያልተደረጉ የስራ ክፍሎች ወጪ የሆነ ድምር ሲሆን ሁሉም ሰነዶች በወቅቱ ለኦዲት ስራ መቅረባቸውን፤

በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት

በማዕከል የቀረበው ሰነድ የፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር በሂሳብ መደብ 6112፣ 6122፣ 6132 የሰራዊት ደመወዝ ለመክፈል በበጀት አመቱ የጠየቀበት ቅጾችና ማጠቃለያ ሲሆኑ ለመመሪያው መውጣት ዋናው ምክንያቶችም እነዚህን ሂሳቦች ኦዲት አድርጎ አስተያየት ለመስጠት ኦዲት በሚደረገው በጀት ዓመት አዲስ የተቀጠሩ፣ የለቀቁ፣ ጡረታ የወጡ፣ በተለያየ ምክንያት የተሰናበቱ የሰራዊት አባላት

ስም ዝርዝር አናቀርብም ሚስጥር ነው በመባሉ መሆኑን መታወቅ አለበት፡፡ በሌላ በኩል በማዕከል የቀረበው ቅጽ አባላት በደመወዝ መክፈያው ላይ የፈረሙበት የደመወዝ መክፈያ ቅጽ (payroll) አይደለም፡፡ በሂሳብ መደብ 6115 ብር 3,997,743.52 የመከላከያ ጠቅላይ መምሪያ አስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ ኦዲት ሲደረግ ሚስጥር ናቸው በሚል አስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ ባለማቅረቡ የፋይናንስ ስራ አመራር ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ መጋቢት 22 ቀን 2007 በቁጥር መ2/ለ4/1/678/07 በሚስጥር ሊያዙ /ሊጠበቁ/ የሚገባቸው መዛግብትና ሰነዶች የወጣውን መመሪያ ግልጽ ለማድረግ ተብለው በተዘረዘሩት የሂሳብ መደቦች ውስጥ ይህ የሂሳብ መደብ ባለመኖሩ በግኝት የተያዘና ኦዲት ያልተደረገ ሂሳብ ነው፡፡ መ/ቤቱ በዚህ ግኝት ላይ በሰጠው መልስ ሚስጥር መሆናቸውን ተገልጿል፡፡ 6211 የደንብ ልብስ ለልብስ ለፍራሽና አልጋ የሰራዊቱን ቁጥር ያሳያል በሚል ማስረጃ አይቀርብም፡፡ ይህ ሂሳብ በከፍተኛ ደረጃ ወጪው የሚታየው በሎጅስቲክስ ዋና መምሪያ ሲሆን በ2006 በጀት ዓመት የዋና መምሪያው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ ብር 90,229,510.22 ሚስጥር መሆኑ ተገልጾ ማስረጃው ለኦዲት አልቀረበም፡፡ ይህም በበጀት ዓመቱ ኦዲት ሪፖርት ተገልጿል፡፡ በሂሳብ መደብ 6416 እና 6417 ለሰራዊት አባላት የሚሰጥ የአገልግሎት ሽልማትን በአብዛኛው የያዘ ሲሆን ክፍያው ከወታደሩ ደመወዝ ጋር አብሮ የሚሰራ በመሆኑ ሚስጥር ነው ተብሎ ሰነዶቹ አልቀረቡም፡፡

ስለዚህ በሪፖርቱ ለኦዲት ያልቀረቡ ሂሳቦች ኦዲት አለመደረጋቸውን የሚያሳይ ዝርዝር ከመገለጹ በስተቀር የማሻያ ሃሳብና የሥራ አመራሩም ምላሽ አለመጠየቁ በሚኒስትሩ የወጣውን መመሪያ መሠረት በማድረግ መሆኑን ገልጸናል፡፡ ፌዴራል ፖሊስ ለመረጃ ግኘ መውጣቱንና ማስረጃውን ለኦዲት ማቅረብ ለሰዎቹ ደህንነት ሲባል እንደማይቻል ገልጿል፡፡

4.8 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት ፣</u>

- የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 500,000.00 የተገዙ ዕቃዎች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ መሆናቸው ሳይረጋገጥ ሂሳቡን በወጪ መመዝገብ ለመንግስት ንብረት መባከን መንስዔ በመሆኑ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.9 ፎቶ ኮፒ ማስረጃ የቀረበለት የወጪ ሂሳብ፤

- የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 745,191.12
- የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት (በኮፒ የክፍያ ሰርትፊኬት) ›› 5,719,486.45

በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽ ነዳጅ ተገዝቶ የቀረበው ሞ/19 ኮፒ፤በጠቅላይ ፍርድ ቤት ለወጪው ኮፒ የክፍያ ሰርትፊኬት በመሆኑ በዋነው ሰርትፊኬት ሌላ ክፍያ ሊፈጸም እንደሚችል በመግለጽ ያልቀረበው የንብረት ገቢ ደረሰኝና የክፍያ ሰርተፊኬት ክትትል ተደርጎ ሊቀርብ እንደሚገባና ማንኛውም የወጪ ሂሳብ ከመወራረዱ በፊት ኦሪጅናል (ዋና ቅጅ) የቀረበ መሆኑ እየተረጋገጠ ሊወራረድ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.10 የበጀት ዓመቱን ሳይጠብቅ የተከፈለ የወጪ ሂሳብ

ክፍያዎች የተፈጸሙት በጀት ዓመቱን ተከትለው ለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፣

- የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ብር 216,856.25 በ2004 እና በ2005 በጀት ዓመት ከኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን የማስታወቂያ አገልግሎት ያገኘበት ከ2ና ከ3 ዓመታት በኋላ በ2007 በጀት ዓመት ክፍያዎች ሲፈጸሙ በጀት ዓመቱን ጠብቀው መሆን እንዳለባቸው በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.11 በድጋሚ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ

- የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በ2006 በጀት ዓመት በወጪ ብር 80,335.61 የመዘገበውን ሂሳብ በድጋሚ በ2007 በጀት ዓመት በወጪ መዝግቦ ተገኝቷል፡፡ በ2006 በጀት አመት ገንዘቡ ወጪ አለመደረጉ ከተረጋገጠ በመመሪያው መሰረት በተከፋይ ሂሳብ መያዝ እንደነበረበትና ሁለት ጊዜ በወጪ ለተመዘገበው ሂሳብ ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስባለን፡፡

3.6 መደቡን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ

➢ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ	ብር	6,730,783.42
➢ የኢትየጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ	“	76,957.69
➢ የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉደዮች ሚኒስቴር	“	872,289.59
➢ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	“	24,377.62
➢ ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ	“	89,945.00
➢ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን	“	54,622,967.67
➢ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት		4,417,274.66
ድምር	ብር	66,834,595.65

የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ ተመዝግቦ ተገኘቷል። በመሆኑም በፌደራል መንግሥት የሂሣብ አያያዝ መሠረት ክፍያዎች እንዲፈጸሙ ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚባ አሳስበናል፡፡

5. የተከፋይ ሂሣብ

5.1 ለረጅም አመታት በተከፋይ የተያዙ

➢ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ	ብር	264,212.10
➢ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን	“	18,340.00
➢ የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የስልጠና ማዕከል	“	517,704.39
➢ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ማህበራት ኤጀንሲ	“	29,170,083.93
➢ የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት(2007)	“	659,961.36
➢ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት (2007)	“	20,738.63
➢ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር	“	140,672,253.79

ከዚህ ውስጥ ከፍተኛው የመከላከያ ሚ/ር እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ሲሆን፤ ኦጀንሲው ከፈረሱ ማህበራት በአደራ የተቀመጠና የማጥራት ሥራው ረዘም ያለ ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በአገር መከላከያ ሚ/ር ካለፉት ዓመታት ጀምሮ በተሰብሳቢ የሚታዩት ሃሳቦች እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ እሳስበናል፡፡

5.2 በተከፋይ ሂሳብ ላይ የታዩ የሂሳብ አያያዝ ችግሮች

በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሂሳብ መደብ 5052 የመያዣ /የዋስትና ሂሳብ/ ብር 4,911,997.97 ማስረጃ ባለመቅረቡ ሁኔታውን ለማወቅ አልተቻለም ፡፡

በዋስትና ሂሳቦች ላይ መ/ቤቱ ሁኔታውን አጣርቶ እርምጃ መውሰድ እንደሚገባው በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

6. የበጀት አጠቃቀም

6.1 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት

በ2007 በጀት ዓመት የተመደበው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲገናዘብ ከ10% በላይ ያለውን ብቻ በመውሰድ ያልተሠራበት በጀት፤

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	መደበኛ	ካፒታል
1	የጨ/ጨ/ኢ/ል/ኢንስቲትዩት	5,495,168.92	
2	የሕገጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽ/ቤት	1,001,366.44	
3	የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ	597,470.75	
4	የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የስልጠና ማዕከል	748,580.80	
5	የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን	10,523,715.66	
6	የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ	15,114,867.25	
7	የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም	1,243,670.43	
8	የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን	91,886,238.87	
9	የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት	22,278,862.50	
10	የፍትህና የህግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲቲዩት	1,761,406.81	
11	የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	12,318,235.04	96,960,245.13
12	ኢንፎረሜሽን መረብ ደህንንት ኤጀንሲ	50,944,597.96	
13	ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ	5,368,980.16	
14	የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ	3,799,600.97	
15	የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ	4,223,670.17	
16	የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል	11,689,373.00	
	ድምር	223,880,938.48	96,960,245.13

6.2 ከበጀት በላይ የወጣ

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	መደበኛ	ካፒታል
1	የጨ/ጨ/ኢ/ል/ኢንስቲትዩት		138,375.59
2	የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም	829,044.34	
3	የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን	123,560,176.47	
4	የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል	1,073,233.67	
5	ንግድ ሚኒስቴር	1,111,392.75	93,326.61
	ድምር	125,462,454.48	231,702.20

አገሪቱ ያላትን ውስን በጀት በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ በበቂ ዕቅድ ላይ የተመሰረተ በጀት አዘጋጅቶ በማስፈቀድ የተፈቀደለትን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል እንደሚገባና የበጀት እጥረት ሲያጋጥም የበጀት ዝውውር በመጠየቅ ክፍያ መፈፀም እንዳለበትና ለወደፊቱ በበጀት ጥያቄና አጠቃቀም ላይ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ አሳስበናል፡፡

የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር በላከው የሥራ አመራር ሪፖርት ምላሽ አብዛኛውን በጀት የሚገለገሉበት በዋ/መ/ቤት ሥር የሚገኙ ማዕከላት መሆናቸውን፣ በሥራ ማስኬጃ መልክ ከወሰዱ በኋላ የበጀት ዓመቱ ሲደርስባቸው ስለሚመልሱት ተርፎ መታየቱን፣ ካፒታል በጀትን በተመለከተ ክፍያ የሚፈጽመው ማንኛውም ኮንትራክተር የክፍያ ማዘዣ ሰርተፊኬት ሲያቀርቡላቸው ብቻ በመሆኑ ወቅቱን ስለማይጠብቁ ተርፎ መታየቱን፣ ለቀጣይ ክፍያዎች በወቅቱ እንዲጠቃለሉ ማድረግ እንዳለባቸው ታምኖ ያም ካልሆነ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እያመለከቱ ለሌላ ክፍያ እንዲያውለው ማድረግ እንዳለባቸው ማመናቸውን ገልጸዋል፡፡

የጨ/ጨ/ኢ/ል/ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን መደበኛ በጀት ሲሆን መ/ቤቶቹም በጀት ሲጠይቁ የተመደበውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ ሥራ ላይ የማይውል በጀት በመጠየቅ የሌላውን መ/ቤት መሠረታዊ መርሀ ግብር እንዳይደናቀፉ በዕቅድና በጥናት ላይ የተመሠረተ በጀት ሊዘጋጅ እንደሚገባ ፡- ከበጀት በላይ ለወጣውም የተፈቀደው በጀት ሊሰራ ለታቀደው ዓላማ የማይበቃ ከሆነም የበጀት ዝውውር አድረጎ መጠቀም የሚቻል በመሆኑ ማስፈቀድ ስለሚቻል ለወደፊቱ የበጀት ሕግ ተጠብቆ ሊሠራ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

እንዲሁም ከበጀት በላይ የወጣውን በተመለከተ ንግድ ሚኒስቴርም ከበጀት በላይ የተቀመጠውን አስተያየት ለወደፊቱ በትምህርትነት እንደሚወሰድና አቅጣጫ እንደሚያስቀምጥ ገልጿል፡፡

7. <u>የዕቃና ንብረት አስተዳደር</u>

7.1 <u>የቋሚና አላቂ ዕቃ ቆጠራ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ (ከእስቶክ ካርድ) ያልተገናዘበ</u>

- የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት
- የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር
- የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮምሽን

የሚቀርበውም ሪፖርት የተቋቋመው ኮሚቴ የፈረመበት ሠነድ ሲሆንና ተጠያቂነትን ያገናዘበ አግባብ ባለው ሁኔታ ሊዘጋጅና ሊቀርብ እንደሚገባ፡፡እንዲሁም ለቋሚ ዕቃዎች ተከታታይ መለያ ቁጥር ለሁሉም ሊሠጣቸው እንደሚገባ አሰስበናል፡፡

በፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት ቆጠራ ከመዝገብ ወጪ ቀሪ ጋር ተገናዝቦ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ሊቀርብ መቅረብ እንዳለበት አሳስበናል።

7.2 <u>ለቋሚ ንብረት መዝገብ ያልተቋቋመባቸው/ያልተመዘገቡ/ቤቶች</u>

ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ

7.3 <u>የቋሚ ዕቃዎች ምዝገባ ያልተከናወነባቸው መ/ቤቶች</u>

- የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

7.4 <u>ለእያንዳንዱ ቋሚ ንብረት የራሱ የሆነ መለያ ቁጥር ያልተሰጠው ፤</u>

- የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር
- የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ
- የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮምሽን

በፌዴራል መንግሥት የንብረት አያያዝና አጠባበቅ መመሪያ መሠረት ቋሚ ንብረቶች የመለያ ቁጥር ተሰጥቷቸውና ተመዝግበው መያዛቸው ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

7.5 ሌሎች የንብረት አያያዝ ድክመቶች

የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል/19 እና የንብረት ወጪ ደረሰኝ ሞዴል/22 የሚዘጋጀውና የዕቃ ግምጃ ቤት ሰራተኛ (ጠባቂ) የሚከናወነው በአንድ ሰራተኛ ሆኖ የተገኘ፤

- የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል
- የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ
- የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት
- ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ

በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር9/2003 መሠረት ንብረት ተረክቦ ገቢና ወጪ ማድረግ እና የንብረት መዝገብ መያዝ ኃላፊነቶች በአንድ ሠራተኛ መያዝ እንደሌለበት ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ኤጀንሲው መመሪያውን ተግባራዊ ሊያደርግ አሳስበናል፡፡

- **የሕግ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽ/ቤት**

  የቋሚ እና የአላቂ ዕቃዎች በሞ/19 እና ሞ/22 ገቢና ወጪ ቢደረጉም መዝገብ ያልተቋቋመ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

- **የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት**

  ወደ ዕቃ ግ/ቤት ለሚገቡ ዕቃዎች በዕቃ ግ/ቤት የሚያዝ ቢን ካርድ የተቋቋመላቸው ቢሆንም ቢን ካርዶቹ በዕቃው ዓይነት ከወጪ ቀሪያቸውን በሚያሳይ መልኩ አልተቀመጠም፡፡

  በተጠቃሚዎች የሚገኙ ቋሚ ዕቃዎች መንግስት ቋሚ ንብረት አስተዳደር ማንዋል (ጎፋም) በሚያዘው መሠረት መቆጣጠርያ ካርድ የተቋቋመላቸው ቢሆንም በተጠቃሚውና በንብረት ክፍል የተያዘው ካርድ መለያ ቁጥር አልተሰጠም፡፡

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ኮሚቴ ተቋቁሞ ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ያልተመዛዘነ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በስፖንሰርሽፕ ድጋፍ የተገኙ ዕቃዎች የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኝ ቢቁረጥላቸው ምዝገባ ሳይከናወን ተገኝቷል፡፡

- **<u>የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የስልጠና ማዕከል</u>**

የዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛ የንብረት መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ በሞ/19 እና በሞ/22 ገቢና ወጪ የሚመዘገብ ቢሆንም የዕቃውን ከወጪ ቀሪ የማያሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከሕዳር 2007 ጀምሮ የንብረት ምዝገባ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡
የተገኙት የንብረት አያያዝና ድክመቶች እንዲስተካከሉ አሳስበናል፡፡

- **<u>በብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት</u>**
  - ❖ ንብረት ከዋናው መ/ቤት ሣሪስ ወደሚገኘው ማሰልጠኛ ጣቢያ ገቢ ሲሆን የዕቃ ገቢ ደረሰኝ የማይዘጋጅ መሆኑና እቃው ለአገልግሎት ሲፈለግ በጽ/ቤቱ በተዘጋጀ ቅጽ (ቅጽ1)ላይ በማስፈረም እንደሚወስዱ ታውቋል፡፡
  - ❖ ከማሠልጠኛው ጣቢያው ንብረቶች ወጪ ሲደረጉ የዕቃ መጠየቂያ (ሞዴል/20) የማይዘጋጅ መሆኑ፤
  - ❖ የንብረት ሠራተኞች የሥራ ክፍፍል አለመኖር፤
  - ❖ በንብረት ክፍል ውስጥ በነሀሴ 11/2006 እና በጥቅምት 11/2007 ዓ.ም በብር 157,500.00 ከተገዙ13 የህትመት ቀለሞች ውስጥ 3 አገልግሎታቸው እንደ ግሪጎሪያን አቆጣጠር ከ2009 በፊት የሆነ ፣ 1 ከ2008 በፊት እና 9 የጊዜ ገደብ (Expire Date) ያልተገለጸባቸው የህትመት ቀለሞች (ፕሊት) መገኘታቸው፤

ንብረቶች ገቢ ሲሆኑም ሆነ ተጠይቀው ወጪም ሲደረግ በመንግስት የንብረት አስተዳደር ላይ በተገለጹት ሞዴሎች (ሞ/19 ፣ሞ/20እና ሞ/22) ገቢና ወጪ ሊደረግ እንደሚገባ እንዲሁም የህትመት ቀለሙ አገልግሎት የሚሠጠውና የማይሰጠው ተለይቶ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

- <u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት</u>

  - ❖ በንብረት ክፍል ውስጥ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ የተለያዩ ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ተሽከርካሪ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች ተገኝተዋል፡፡

    አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በመመሪያው መሰረት መወገድ እንደሚኖርባቸው በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7.6 <u>የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠቃቀም</u>

<u>ሊብሬ ቁጥር የሌላቸው ተሽከርካሪዎች</u>

- በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሥር ከሚገኙ ተሽከርካሪ መኪናዎች የሰሌዳ ቁጥር 4 02087 አይሱዙ ተሽከርካሪ፤ የሰሌዳ ቁጥር 4-04168 ሚስት ቡሽ እና የሰሌዳ ቁጥር 4-14973 ቶዮታ ያሪስ ተሽከርካሪዎች ሊብሬአቸው ለኦዲት ሊቀርብ አልቻለም፡፡

<u>ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ</u>

- የሠሌዳ ቁጥር 20053, 17575, 17922, 20454, 18086, ለሆኑ ተሽከርካሪዎች ሊብሬአቸው ለኦዲት አልቀረበም፡፡
- በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ስለተሽከርካሪዎች ሁኔታ የሚገልጽ ፋይል (ማህደር) ባለመገኘቱ የተሽከርካሪዎችን የሕይወት ታሪክ ለማወቅ አልተቻለም፣
- በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ 4 ተሽከርካሪዎች (የሠሌዳ ቁጥር 4-07951፣ ኮድ 4-04696፣ ኮድ 4-01980፣ ኮድ 4-05526) በሜዳ ላይ ለፀሐይና ለዝናብ የተጋለጡ መሆኑ፤

<u>የባለቤትነት ደብተር /ሊብሬ የሌላቸው</u>

- የሕግ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽ/ቤት 2 ተሽከርካሪዎች
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት 1 ተሽከርካሪና አንድ ሞተር ሳይክል
- የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የስልጠና ማዕከል 1 ተሽከርካሪ
- ፍትህ ሚ/ር ሊብሬ ያልቀረበለት ተሽከርካሪ ለድሬዳዋ ፍ/ፅ/ቤት መሰጠቱ የተገለጸ ቢሆንም ለመላኩ ማረጋገጫ ያልቀረበለት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት የኢንስቲትዩቱ በላከው በሥራ አመራር ሪፖርት ምላሽ የ2007 አመታዊ የቴክኒክና ክላውዶ ማስደረግ ሊብሬዎቹ ሲፈለጉ የሶስት ተሽከርካሪዎች ሊብሬ ከተቀመጡበት ቦታ የጠፉ በመሆኑ አስቀድሞ ይሄንኑ ለአቃቂ ቃሊቲ ፖሊስ መምሪያና ለአዲስ አበባ ትራንስፖርት ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በወቅቱ ከማሳወቅ በተጨማሪ በጠፉ ሊብሬዎች ምትክ እንዲሰጣቸው መጠየቁን ገልጿል፡፡ እንዲሁም ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ ተሽከርካሪዎች የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ያልደረሰ በመሆኑ ምክንያት ሊብሬው በመንገድ ትራንስፖርት የተያዘባቸው መሆኑንና በሚቀጥለው በጀት ዓመት የሚወጣላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የተጠቀሱት ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ /ሊብሬ/ እንዲቀርብ አስፈላጊው ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡በብልሽት የቆሙት ተሽከርካሪዎች በመመሪያው መሰረት እንዲወገዱ ወይም ለሚመለከተው አካል ርክክብ እንዲደረግ አስፈላጊው ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡ተሽከርካሪዎቹ የመ/ቤቶች ለመሆናቸው ማረጋገጥ እንዲያስችል የተሽከርካሪ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ ሊኖር እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

8. ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ

❖ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

- በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ለፕሬዝዳንቱ ጽ/ቤት አገልግሎት የሚውል ወንበር ለሰበር ዳኞች ጠረጴዛ ግዥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ደጋፊ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 88,250.00 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ ሂሳብ ብር 34,122.11 ተገኝቷል ፡፡
- የፎቶ ኮፒ ማሽን መለዋወጫ ዕቃዎች በመዝገብ ሳይመዘገብ ተገኝቷል ፡፡
- በፍ/ቤቱ ስር የሚገኙ ተሽከርካሪ መኪናዎች ሰባት የባለቤትነት መታወቂያ (ሊብሬ) የሌላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡
- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የወጪ ማስመስከሪያ እና ደጋፊ ማስረጃዎች የ16 የክፍያ ቫውቸሮች በተደጋጋሚ ተጠይቆ ባለመቅረባቸው የብር 1,779,873.81 የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፡፡

- የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰኔ 30,2005 በቀረበው የሂሳብ ሚዛን ሪፖርት የባንክ ተቀማጭ (Deposit in transit) በሚል የተመለከተው ብር 31,663,784.76 በሰኔ 30/2005 የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ መሠረት የተመለከተ ብር 30,050,597.13 ሲገናዘብ በልዩነት የታየው ብር 1,613,187.63 ባንክ ገቢ የሆነበት የባንክ ክሬዲት አድቫይስ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ባለመቻሉ በ2006 በጀት ዓመት የተወሰደ እርምጃ ሲጣራ ለኦዲት በማስረጃነት የቀረቡት የባንክ ክሬዲት አድቫይሶች ብር1,735,122.20 ብሄራዊ ባንክ በማዕከላዊ ግምጃ ቤት በተለያዩ ቼኮች ገቢ መደረጉን አድቫይሶቹ ቢያሳዩም ከማን እንደተሰበሰቡ ገቢ የተደረጉበት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች (መሂ/1) ዝርዝር፣ በገቢና በወጪ ስለመመዝገባቸው፣ በሰኔ 2005 እና በሐምሌ 2005 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ አለመታየታቸው የቀረቡት ክሬዲት አድቫይሶች ድምር ብር 1,735,123.20 በግኝቱ ከተገለጸው በብር 121,934.57 በመብለጡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉን ።
- በከፍተኛ ፍርድ ቤት በ2005 ኦዲት በተሰጠው አስተያየት ማስረጃ ያልቀረበለት ብር 31,755.00 ወጪው ለፍርድ ቤቱ አገልግሎት መዋሉንና ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሳብ መገኘቱን፡፡
- በከፍተኛ ፍርድ ቤት ብር 1,070,340.84 ያዘጋጀውም ሆነ ያፀደቀው ስምና ፊርማ ሳይኖረው በኃላፊ ሳይፀድቅ ማስተካከያው ተመዝግቦ መገኘቱን ፡፡

❖ <u>የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት</u>

- የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይኖር እንዲሁም ክፍያ እንዲፈጸም የታዘዘበት የማዘዣ ደብዳቤ፣ ለየትኛው ምርጫ የተሰጠ ድጎማ እንደሆነ የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖር በሂሳብ መደብ 6231 ብር 7,553.956.83 ክፍያው ተፈጽሞ መገኘቱ፡፡

❖ <u>ንግድ ሚኒስቴር</u>

በሞ/64 ገቢ ያልተደረገና ባንክ ገቢ ለመደረጉ የባንክ ክሬዲት አድቫይስ ያልቀረበለት የገቢ ሂሳብ ብር 20,306.00 ማስረጃ አልቀረበም፡፡

❖ **<u>የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ</u>**

2005 በጀት ዓመት በኦዲት ሪፖርት በቀረበው መሰረት ኤጀንሲው ብር 161,451.43 ለመኪና ጥገና ወጪ አድርጎ ለሥራና ቤቶች ሚ/ር መ/ቤቱ ክፍያ ለመፈፀሙ በፀረ ሙስና በመታየት ላይ ያለና እልባት ያላገኘ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በኦዲት ሪፖርቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት መ/ቤቶቹ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰዱ በድጋሚ አሳስበናል፡፡

➢ **<u>የአገር መከላከያ ሚኒስቴር</u>** የ2006 በጀት ዓመትና ከዚያ በፊት ሂሣብ ኦዲት ተደርጎ በተሰጠው አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደ፣ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣

- በሂሳብ መደብ 4201 ቅድሚያ ክፍያ ከብር 18,820,181.82 ውስጥ ብር 11,593,098.46 በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት፣ ብር 1,376,502.39 በምስራቅ ዕዝ፣ ብር 845,430.78 በምዕራብ ዕዝ እና ቀሪው ብር 5,005,150.19 በተለያዩ መምሪያዎች እና ዕዞች በተሰብሳቢ ተመዝግቦ ባለፉት ዓመታት በኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው ለረጅም ዓመታት የቆዩና ከማን እንደሚፈለግ ማስረጃ የሌለው መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 4202 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ከተያዘው ብር 262,684.90 ብር 200,187.27 በሎጅስቲክ ዋና መምሪያ የቀድሞ ገንዘብ ያዥ ያልተተካ እና ቀሪው ብር 62,497.62 በተለያዩ መምሪያዎች እና ዕዞች ለረጅም ጊዜ በተሰብሳቢ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 4210 የሌሎች መ/ቤቶች ቅድሚያ ክፍያ ከተያዘው ብር 107,940,925.36 ውስጥ በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ብር 10,966,546.00 በምዕራብ ዕዝ ብር 7,348,792.87፣ በምስራቅ ዕዝ ብር 1,320,386.97፣ በሎጅስቲክ ዋና መምሪያ ብር 986,222.51 እና ቀሪው ብር 42,318,977.01 በተለያዩ መምሪያዎችና ዕዞች ለረጅም ጊዜ በተሰብሳቢ የተመዝገበ መሆኑ፣

- በሂሳብ መደብ 4251 የሥራ ተቋራጭ ቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በሪፖርት ከተመለከተው ብር 38,527,406.54 ውስጥ ብር 15,173,225.79 በመከላከያ ቤቶች አስተዳደር ዋና ዳይሬክቶሬት፣ ብር 512,628.84 በሎጅስቲክ ዋና መምሪያ፣ ብር 94,987.48 በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት እና ቀሪው ብር 22,746,564.43 በተለያዩ መምሪያዎችና ዕዞች ለረጅም ጊዜ በተሰብሳቢ የተያዘ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 4253 ለዕቃ አቀራቢዎች ቅድሚያ ክፍያ ውስጥ ብር 33,992,953.51 በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ሲሆን ብር 1,968,921.02 በ1998 ለዕቃ አቅራቢዎች እና ብር 24,367,855.38 በ2003 ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት የተከፈለ እና ቀሪው ብር 2,985,285.63 በተለያዩ መምሪያዎችና ዕዞች ለረጅም ጊዜ በተሰብሳቢ የተያዘ መሆኑ፣ በአጠቃላይ ከላይ የተገለጹት ሂሳቦ ማስረጃ የሌላቸው እና ለረጅም ዓመታት በተሰብሳቢ የተያዙ መሆኑ ታውቋል፡፡

የተሰብሳቢ ሂሳቦች በበቂ ማስረጃ የተደገፉ መሆናቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ዳይሬክቶሬቱ በሰኔ 30/2006 በሂሳብ መደብ 4251 የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ኦዲት ሲደረግ፣ ዳይሬክቶሬቱ ሚሊተሪ ፖሊስ እየተባለ በሚጠራው ግቢ ውስጥ መዝገብ ቤት ለማስገንባት በብር 11,704,195.79 ከመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ጋር በታህሳስ 15 ቀን 2006 ዓ.ም. (24 December 2013) በተፈረመ ውል በቀን 24/08/06 በባንክ የወጪ ማዘዣ ቁጥር 83405 ብር 3,511,258.74 ቅድሚያ ክፍያ እና ኮንስትራክሽን ድርጅቱ ግንባታው በምን ደረጃ ላይ እንዳለ እና የተሰራውን ስራ (Executed Amount/Payment Certificate) ሳይቀርብ ተቆጣጣሪ ድርጅቱም ሳያውቅ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በቀን 27/10/06 በባንክ የወጪ ማዘዣ ቁጥር 647484 ብር 11,586,202.42 ከኮንስትራክሽን የክፍያ ህግና ሂደት ውጪ ተከፍሎ በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ መገኘቱን፡፡ ለተከፈለው ሂሳብ ኢንተርፕራይዙ ገንዘቡን ለመቀበሉ ማስረጃ አለማቅረቡ፤ እንዲሁም በውሉ ላይ የስራው ጠቅላላ ዋጋ ብር 11,704,195.79 ሆኖ ሳለ ከላይ በተጠቀሱት የወጪ ማዘዣ

ቁጥሮች በድምሩ ብር 15,097,461.16 ክፍያ ሲፈጸም በብልጫ ብር 3,393,265.37 ለኮንስትራክሽን ድርጅቱ ተከፍሎ መገኘቱን፤ በብልጫ ሊከፈል የቻለው በምን ምክንያት እንደሆነ የቀረበ ማስረጃና በአማካሪው መሐንዲስ በኩል የተሰጠ ማረጋገጫ የሌለው ሆኖ መገኘቱን፤ በሌላ በኩል በግንባታ ውል ስምምነቱ ላይ ስራው ተሰርቶ የሚጠናቀቅበት ጊዜ ውሉ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ 150 ካላንደር ቀን የሚል ሲሆን ይህም ግንቦት 15 ቀን 2006 ዓ.ም. መጠናቀቅ እንደነበረበት ይሁን እንጂ እስከ ሰኔ 30/2006 ዓ.ም. ስለስራው ደረጃ የሚገልጽ ማስረጃ አለመገኘቱን የግንባታ ስራው አለመጠናቀቁን፤ የጉዳት ካሣም አለመጠየቁ፤

<u>የተከፋይ ሂሳብ</u>

- በሂሳብ መደብ 5021 ለሠራተኞች ተከፋይ ሂሳቦች ከተያዘው ብር 1,831,070.50 በወቅቱ ሳይከፈል በመቅረቱ በተከፋይ ተይዞ መገኘቱ፣
- በሂሳብ መደብ 5028 በመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ከተያዘው ብር 2,716,915.38 በወቅቱ ሳይከፈል ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ተይዞ መገኘቱ፤
- በሂሳብ መደብ 5054 ሌሎች የመያዣ ሂሳቦች ከተያዘው ብር 79,093,658.24 ውስጥ ብር 10,460,092.58 በማዕከል ምዝገባ፣ ብር 1,493974.87 በመከላከያ ቤቶች አስተዳደር ዋና ዳይሬክቶሬት፣ ብር 7,690,523.89 በሎጅስቲክ ዋና መምሪያ፣ ብር 2,473,383.98 በምዕራብ ዕዝ፣ ብር 8,541,716.61 በምስራቅ ዕዝ እና ቀሪው ብር 48,493,966.31 በተለያዩ መምሪያዎችና ዕዞች በወቅቱ ሳይከፈል ለረጅም ጊዜ በተከፋይ ተይዞ መገኘቱን፤

የአገር መከላከያ ሚኒስቴር በኦዲቱ ወቅት በ2006 በጀት ዓመት ኦዲት በተሰጠው አስተያየት መሰረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ለፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በጽሁፍ ጠይቀን የተሰጠው መልስ በእያንዳንዱ ሂሳብ ላይ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ባለመሆኑ ተስተካክሎ እንዲቀርብ ተጠይቆ ኦዲቱ እስኪጠናቀቅ የካቲት

22 ቀን 2008 ዓ.ም በእያንዳንዱ ግኝት ላይ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

የፌደራል መ/ቤቶች ከ2002 እስከ 2006 በጀት ዓመት በመ/ቤታችን ኦዲት ተደርገው በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት በግኝቶቹ ላይ እርምጃ ለመወሰዱ በመ/ቤቶቹ የውስጥ ኦዲት ተጣርቶ እንዲደርሰው የጠየቀው ለሌላ ስራ በሌላ ክፍል ሲሆን የመ/ቤቱን የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሲያደርግ በ2006 በጀት ዓመት በተሰጠው አስተያየት መሠረት የተወሰደውን እርምጃ የማጣራቱ ስራ የ2007 በጀት ዓመት ኦዲት አካል በመሆኑ ለኦዲት ቡድኑ ተገቢውን ምላሽ መስጠት እና በመልሱ መሠረት የተወሰደውን እርምጃ ሰነዶችን በመመርመር የማረጋገጥ ሥራ የሚሰራበት በመሆኑ መልሱ አለመሰጠቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመውጫ ስብሰባ ወቅት የፋይናንስ ዳይሬክተሯ ምላሽ ነው ብለው ስብሰባው ላይ የሰጡን ሰነድ የኦዲት ቡድኑ ለጠየቀው የተዘጋጀ አይደለም፡፡ ስለዚህ መ/ቤቱ በመ/ቤታችን በተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች እርምጃ ሊወሰድና ይህንንም ለማረጋገጥ በሚደረገው ኦዲት ሊተባበርና ክትትልም ማድረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት የ2007 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች

1. የወጪ ግኝቶች

1.1 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዥዎች

- አገልግሎቱ ለመስተንግዶ የግዥ መመሪያውን ሳይከተል ያለ ዋጋ ማወዳደሪያ ግዥ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ብር 1,997,937.58

1.2 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

ለኦዲት በተፈቀዱት የሂሳብ መደቦች በወጪ የተመዘገበው የቀረጥ ሂሳብ ብር 512,484,298.25 በማስረጃ የተደገፈ መሆኑ ሲጣራ የዕቃ ማሳወቂያ ቅጽ መጫኛ

ሰነድ /ፓኪንግ ሊስት/ እና እቃዎቹ ገቢ ለመሆናቸው ሞዴል 19 ያልቀረቡ በመሆናቸው የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ግዥዎች በግዥ አዋጁ መሰረት እንዲፈጸም ያለማስረጃ የተመዘገቡት ማስረጃዎቹ እንዲሟሉ አሳስበናል፡፡ አገልግሎቱ በላከው መልስ የሆቴል አገልግሎት ግዥው ከመስሪያ ቤቱ የስራ ባህሪ አንጻር ሚስጥር መሆኑንና ምን ያህል ሰው እንደሚመጣ የማይታወቅ በመሆኑ በቅድሚያ ፕሮፎርማ መሰብሰብ እንደማይችሉ ገልጸዋል፡፡

1.3 <u>ደንብና መመሪያን ሳይከተል የተፈጸመ ክፍያ</u>

- በብር 98,547.03 የተለያዩ የጽዳት አገልገሎት የሚውል ግዢ ሲፈጽም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚሰጠው የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ድርጅቱ ስለመኖሩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያልቀረበ ተገኝቷል፡፡
- የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 በክፍል 2 አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፅ 5 በበጀት ዓመቱ በአንድ ጊዜ የክፍያ መጠናቸው ከብር 50,000.00 በላይ የሆኑ ወጪዎች ወደ ባለመብቱ የባንክ ሒሳብ በማስተላለፍ መፈጸም እንዳለበት ያዛል፤፡ ሆኖም አገልግሎቱ በ6 የተለያዩ ክፍያዎች በድምሩ ብር 594,165.66 በቼክ ክፍያ መፈጸሙን በመግለጽ ክፍያዎች በመመሪያው መሰረት እንዲፈጸም አሳስበናል፡፡

1.4 <u>በኦዲቱ ያልተሸፈነ ሂሳብ</u>

- በአገልግሎቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 804/2005 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 2(ሠ) ለዋና ዳይሬክተሩ በተሰጠ ስልጣን መሰረት ብር 433,892,583.33 ወይም 39.42% ሚስጥር በመሆኑ በኦዲቱ አልታየም፡፡

2 <u>በጀት</u>

- በ2007 በጀት ዓመት የተፈቀደው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት ከዚህ በታች በተመለከቱት ሶስት ዋና መምሪያዎች በድምሩ ብር 31,228,432.44 ተገኝቷል፡፡

  ዝርዝሩም፤

  - በድጋፍና አገልግሎት ዋና መምሪያ ብር 47,192.47 (27.77%)
  - በኢምግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ የካፒታል በጀት ብር 26,474,044.02 (52 %)

- የውጭ መረጃ ዋና መምሪያ 4,707,195.95 (22.77 %)

የበጀት ዝግጅቱ በዕቅድ እንዲከናወን አሳስበናል፡፡

3. <u>የክትትል ኦዲት፤</u>

- በ2006 በጀት ብር 513,487.03 ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰብ መገኘቱን በመግለጽ እንዲሰበሰብ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ብር 445,628.02 አሁንም ሳይወራረድ መገኘቱን በመግለጽ ሂሳቡ እንዲወራረድ አሳስበናል፡፡

<u>የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የ2007 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሪፖርት</u>

1. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

1.1 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዥዎች ብር 8,461,585.15

በቀጥታ የግዥ ዘዴ ለመፈጸም የሚጠይቀው ዝርዝር ሁኔታ ሳይሟላ ከአንድ አቅራቢ የተገዛ፣ የዋጋ ማቅረቢያ ፕሮፎርማ በፍሉድ በማጥፋትና በመደለዝ፣

በፕሮፎርማ መገዛት ሲገባው ከአንድ አቅራቢ ግዥው መፈጸሙ የግዥ ህጉን የተከተለ አለመሆኑን በመግለጽ አሰራሩ እንዲታረም፤ እንዲሁም መስሪያ ቤቱ በሰጠው መልስ የግዥ ኤጀንሲ የፈቀደው በጨረታ መገዛት የሚገባውን በፕሮፎርማ ቢያንስ ሁለት አቅራቢዎችን በማወዳደር ወይም በለቀማ እንዲፈጸም የፈቀደ ሲሆን በዚህ መንገድ ግዥውን ለመፈጸም ካልተቻለ ምክንያታቸውን በጽሁፍ ለሚመለከተው ሃላፊ አቅርበው በቀጥታ መፈጸም ሲገባ ኤጀንሲው የሰጠውን መመሪያ አለአግባብ በመተርጎም የተፈጸመው ግዥ መሆኑን፣ የመኪናው ኪራይም ቢሆን ለአንድ ዓመት ውል የተገባ ሲሆን ክፍያው ግን ውሉ ካለቀ በኋላ አዲስ ውል በመግባት የተፈጸመው ክፍያ አግባብ አለመሆኑን አሳስበናል፡፡

መ/ቤቱም በላከው መልስ ለግንቦት 20 በዓል አስቸኳይ እንዲገዛ በመወሰኑ ከአንድ አቅራቢ እንዲገዛ የፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲን ጠይቀው በተፈቀደው መሰረት መሆኑን እንዲሁም ከአሴቅ መኪና ኪራይ ጋር በተያያዘ መስከረም 16 ቀን 2006 ዓ.ም. በወጣው ግልጽ ጨረታ

አሸናፊ በመሆኑ ከሚንስቴር መ/ቤታችን ጋር ለበጀት ዓመቱ ለሚያስፈልገው የመኪና ኪራይ የተደረገ የቀጥታ ግዢ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

1.2 ምንም የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ ብር 1,362,779.26

በተለያዩ ክፍያዎች ማሽረጃ ሳይቀርብ ለውሎ አበል፣ ለመስተንግዶ ክፍያ፣ የደሞዝ ክፍያ ማስረጃዎች ያልቀረቡና ከፊሉ ደግሞ ኮፒ የክፍያ ማስረጃ የቀረቡ በመሆናቸው የተያዙ ወጪዎች ሲሆኑ እነዚህ ሂሳቦች ማስረጃ እንዲቀርብላቸው አሳስበናል፡፡

1.3 ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለአግባብ የተከፈሉ ክፍያዎች ብር 46,044.87

የፕሪቶሪያ ኢ.ፌዲሪ ኤምባሲ በተለያዩ ወቅቶች ከአገር ቤት የመጡ እንግዶች ለመቀበል እና ለመሸኘት የሚያግዙ የኤርፖርት የፕሮቶኮል ሰራተኞች እና በተለያዩ ጊዜያት ስብሰባ ሲደረግ አገልግሎት ለሰጡ ዲፕሎማቲክ ፀጥታ ጠባቂ ፖሊሶች ጉርሻ በሚል ብር 44,034.87 (ራንድ 20,015.85) በወጪ ሂሳብ የተመዘገበ ሲሆን ጉርሻውም በትክክል ለመስጠቱ ማረጋገጥ ያልተቻለ እንዲሁም በመንግስት የውጭ ሃገር ጉዞ የውሎ አበል መመሪያ መሰረት ወደ ውጭ ሲሄድ ለመልካም አገልግሎት ዶላር 50.00 እንደሚከፈል የሚፈቅድ ሲሆን የዋሽንግተን ኤንባሲ አንዱ ሰራተኛ ውሎ ገብ ኒዮርክ ሁለት ጊዜ ለተመላለሰበት 100 የአሜሪካ ዶላር የተከፈለበት ከመመሪያ ውጭ መሆኑን እንዲታረም አሳስበናል፡፡

1.4 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ ብር 35,200.00

በኢ.ፌድሪ የፕሪቶሪያ ኤምባሲ የብሄር ብሄረሰቦች ቀን ለማክበር ለምግብ አገልግሎት ለሰጡበት በሚል አጥጋቢ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ሂሳብ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪ አገልግሎቱን ለመግኘት በሚመለከተው ሰራተኛ ወይም ሀላፊ ሁኔታው ተገልጾ የቀረበ የፀደቀ መስታወሻ አልቀረበም፣ አገልግሎት የሰጠው ድርጅት (ሆቴል) እንዴት እንደተመረጠ ማስረጃ የለም፣

1.5 በብልጫ የተከፈለ ብር 42,398.55

የኢ.ፌዲሪ ኤምባሲ ብራሰልስ በቀረበው የትኬት ማስረጃ ላይ ዮሮ 490 ፊት በእጅ አንድ ቁጥር በመጨመር 1490 ዮሮ በዚህም 1000 ዩሮ ወይም ብር

28,000 አለአግባብ በወጪ የተመዘገበ እና ብር 14,398.55 ከቀረበው ማስጃ በላይ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ ነው፡፡

1.6 የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሳብ ብር 27,280,735.00

ለሰነዓ ፎረም መዋጮ የተከፈለ ሲሆን በሚመለከታቸው ሃላፊዎች የፀደቀ ውሳኔ እና የኢትዮጵያ ድርሻ ምን ያህል እንደሆነ የሚገልጽ ምንም ዓይነት ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ ነው፡፡

1.7 የሒሳብ መደቡን ያልጠበቁ ወጪዎች ብር 1,852,424.99

በፌዴራል መንግስት የሂሳብ አወቃቀር መሰረት በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ ሲሆን አሰራሩ እንዲስተካል የማሻሻያ ሃሳብ ሰጥተናል፡፡

2. <u>ተሰብሳቢ</u>

2.1 <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

2.1.1 በሰኔ 30/2007 በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርቶች ብር 52,255,447.77 የታየ ሲሆን የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ በዕድሜ ተተንትኖ እና ደጋፊ ማስረጃዎች አባሪ ተደርገው እንዲቀርቡ ቢጠየቅም ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ሆኖም የኦዲት ሪፖርቱ ከተላከ በኋላ በዕድሜ ተተንትኖና የተወሰኑ ማስረጃዎች የተወራረዱ መሆኑን እንዲሁም ማስረጃ እንዳላቸው በመግለጻቸው የመውጪያ ስብሰባ ከመካሄዱ በፊትና በኋላ በተደረገው ኦዲት የሂሳብ ትክክለኛነት ባይረጋገጥም በ2007 በጀት ዓመት ወጪ የተደረጉ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 12,284,778.73 ማስረጃ እንዳለው ታውቋል፡፡ በዚሁም መሰረት ልዩነቱ ብር 39,970,669.04 ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ ብር 21,240,449.42 የ2005 በጀት ዓመት ውዝፍ ሲሆን 11,987,842.90 እና ቀሪው የዘመኑ 18,730,219.52 በድምሩ ብር 30,718,062.42 ማስረጃ የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

2.1.2 በ2005 በጀት ዓመት ከነበረው 189,610,276.93 ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ብር 21,240,449.42 በ ሰኔ 30,2007 በሪፖርት ከተገለጸው ተሰብቢ ሂሳብ ብር 52,255,447.77 ውስጥ ይገኛል፡፡ የዚህ ሂሳብ ዝርዝር ሁኔታ፤

- ብር 1,846,214.94 በተለያዩ ሚሲዮኖች በቤት ኪራይ እና ሌሎች እንደ መብራት፣ ኢንተርኔት እና ጋራዥ የመሳሰሉ መያዣዎች የተከፈለ መሆኑን የቀረበ ቢሆንም በሚሲዮኖቹ የአገልግሎቱ ውል በየወቅቱ የታደሰ መሆኑን ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

- በተለያዩ የመ/ቤቱ ሰራተኞች ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ተብሎ ከተጠቀሰው ሂሳብ ብር 2,454,542.04 ውስጥ ብር 1,914,653.81 የተሟላ ማስረጃ የሌለው እና ከማን እንደሚፈለግ ለኦዲት የቀረበው ሰነድ የማያመለክት መሆኑ፤

- ከ10 ዓመት በላይ የቆዩ እና ሂሳቡን ከመዝገብ ለማሰረዝ በክትትል ላይ ያለ ተብሎ ከተጠቀሰው ሂሳብ ብር 973,077.78 ውስጥ ብር 267,917.65 ገንዘቡ ለማን እንደተከፈለ እና ከማን እንደሚፈለግ ማስረጃ ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ፤

- ከግብርና ሚኒስቴር ብር 1,468,044.71፣ ከሶማሌ ክልል ብር 1,770,743.25 ከኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን ብር 1,986,671.90 በድምሩ 5,225,459.86 ከመ/ቤቶቹ እንደሚፈለግ እና መ/ቤቶቹ ተጠይቀው ገንዘቡን ገቢ ባለመድረጋቸው ምክንያት ለረጅም ዓመታት የቆየ መሆኑ፤

- ብር 9,805,271.44 ሂሳቡ ከማን እንደሚፈለግ እና ማስረጃው ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

2.2 በወጪ ማስመስከሪያ ላይ ሰራተኛው ሳይፈረም ተመዝግቦ የተገኘ የግዥ ቅ/ክፍያ ብር 42,250.00

የቤጂንግ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ለመኖሪያ ቤት የጽዳት ቁሳቁስ ግዥ በቅድመ ክፍያ ብር 42,250.00 የወሰደው ሰራተኛ ስለመውሰዱ በወጪ ማስመስከሪያው ላይ ሳይፈርም ተገኝቷል ፡፡

3. <u>ተከፋይ ሂሳብ</u>

3.1 በሰኔ 30/2007 በተከፋይ የሂሳብ ሪፖርት ብር 53,599,028.31 የተከፋይ ሂሳብ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ዝርዝሩም በዕድሜ ተተንትኖ እና ደጋፊ ማስረጃዎች

በአባሪነት እንዲቀርቡ ቢጠየቁም ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ሆኖም የኦዲት ሪፖርቱ ከተላከ በኋላ በዕድሜ ተተንትኖና የተወሰኑ ማስረጃዎች የተወራረዱ መሆኑን እንዲሁም ማስረጃ እንዳላቸው በመግለጻቸው የመውጫ ስብሰባ ከመካሄዱ በፊትና በኋላ በተደረገው ኦዲት የሂሳቡ ትክክለኛነት ባይረጋገጥም በ2007 በጀት ዓመት ብር 2,,853,716.64 ማስረጃ የቀረበለት ሂሳብ ተገኝቷል ቀሪው ብር 50,745,311.67 ማስረጃ የለውም፡፡

4. <u>የክትትል ኦዲት</u>

በ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት እርምጃ መወሰዱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

4.1 <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

በ2005 በጀት መጨረሻ በሂሳብ ሪፖርት የተመለከተው የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 189,610,276.93 ውስጥ ብር 168,369,827.51 መወራረዱን በኦዲቱ ወቅት መግለጫ ተሰጥቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ተወራረደ የተባለው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

4.1.1 ብር 27,411,285.24 የተሰብሳቢ ሂሳቦችን ክሬዲት እና የተጣራ ሀብት ዴቢት በማድረግ ከመዝገብ ለተሰረዙት ሂሳቦች መሰረት የሆኑት ሰነዶችና ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው ተወራረደ የተባለውን ሂሣብ አግባብ አለመሆኑን ተረጋግጧል፡፡

4.1.2 ብር 36,716,650.83 የተሰብሳቢ ሂሳቦችን ክሬዲት እና የተከፋይ ሂሳቦችን ዴቢት በማድረግ ከመዝገብ የተሰረዙት ሂሳቦች ለማጣፋት መሰረት የሆኑትን ሰነዶች፣ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

4.1.3 በ2005 በጀት ዓመት መጨረሻ በተሰብሳቢ ከተመለከተው ሂሳብ ውስጥ ብር 168,369,827.51 መወራረዱ በተገለጸው መሠረት ከፍ ብሎ በቁጥር 4.1.1 እና 4.1.2 በተገለጸው ሁኔታ የተወራረዱት ተወራረደ የተባለው ተሰበሰሳቢ ሂሳብ ሲቀነስ ለብር 82,368,644.21 ተሰብሳቢ ሂሳቦች ምንም ማስረጃ ያልቀረበላቸው በመዝገብ የሌሉ በሂሳብ ሪፖርትም ያልተገለፁ ተገኝተዋል፡፡

4.1.4 በ2005 በጀት ዓመት መጨረሻ በሂሳብ ሪፖርት የተመለከተው የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 189,610,276.93 ውስጥ እስከ ሰኔ 30/2006 ድረስ ያልተወራረደ እና በሪፖርት የተመለከተ ሂሳብ በድምሩብር 21,240,449.42 ኦዲት ሲደረግ ፤

- ብር 1,846,214.94 በተለያዩ ሚሲዮኖች በቤት ኪራይ እና ሌሎች እንደ መብራት፣ ኢንተርኔት እና ጋራዥ የመሳሰሉ መያዣዎች የተከፈለ መሆኑን የቀረበ ቢሆንም በሚሲዮኖቹ የአገልግሎቱ ውል በየወቅቱ የታደሰ መሆኑን ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- በተለያዩ የመ/ቤቱ ሰራተኞች ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ተብሎ ከተጠቀሰው ሂሳብ ብር 2,454,542.04 ውስጥ ብር 1,914,653.81 የተሟላ ማስረጃ የሌለው እና ከማን እንደሚፈለግ ለኦዲት የቀረበው ሰነድ የማያመለክት መሆኑ፤
- ከ10 ዓመት በላይ የቆዩ እና ሂሳቡን ከመዝገብ ለማሰረዝ በክትትል ላይ ያለ ተብሎ ከተጠቀሰው ሂሳብ ብር 973,077.78 ውስጥ ብር 267,917.65 ገንዘቡ ለማን እንደተከፈለ እና ከማን እንደሚፈለግ ማስረጃ ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ፤
- ከግብርና ሚኒስቴር ብር 1,468,044.71፣ ከሶማሌ ክልል ብር 1,770,743.25 ከኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን ብር 1,986,671.90 በድምሩ 5,225,459.86 ከመ/ቤቶቹ እንደሚፈለግ እና መ/ቤቶቹ ተጠይቀው ገንዘቡን ገቢ ባለመድረጋቸው ምክንያት ለረጅም ዓመታት የቆየ መሆኑ፤
- ብር 9,805,271.44 ሂሳቡ ከማን እንደሚፈለግ እና ማስረጃው ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.2 <u>ተከፋይ ሂሳብ</u>

በ2005 በጀት ዓመት መጨረሻ በሂሳብ ሪፖርት በተመለከተው የተከፋይ ሂሳብ ብር 179,361,280.26 ብር 168,369,827.51 መወራረዱ በኦዲቱ ወቅት ኦዲት አስደራጊዎች በሰጡን መግለጫ መሰረት ትክክለኝነቱ ሲጣራ፤

4.2.1 ተከፋይና ተሰብሳቢ ሂሣብን በማጣፋት ከመዝገበ የተሰረዘ (የተወራረደ) የተከፋይ ሂሣብ ብር 64,344,349.54 ሚ/ር መ/ቤቱ ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር ባለው የስራ ግንኙነት ሠራተኞች ያለባቸውን ተከፋይ ሂሣብ በስማቸው ከተያዘው ተሰብሳቢ ሂሣብ ጋር አንድ ሚስዮን ከሌላው ሚሲዮን የሚፈለገውንና እዳውን ፣ ሌላው ሚሲዮን በአንዱ ሚሲዮን ሥም በተከፋይ የያዘውንና በበጀትና በቪዛ መካከል የተመዘገበውን ከተከፋይ ሂሳብና ከተሰብሳቢ ወ.ዘ.ተ በማገዳደል ከሂሳብ አሰራር ውጭና በማስረጃ ሳይደገፍ ብር 64,344,349.54 ተወራርዶ ተገኝቷል፡፡

መ/ቤቱ ከሀገር መከላከያ ሚ/ር ጋር ባለው የስራ ግንኙነት በመከላከያ ሚ/ር ሥም በተከፋይ የተያዘውን በተሰብሳቢ ጋር በማጣፋት/በማገደደል/ከመንግሥት የሂሣብ አሠራር ውጭ በድምሩ ብር 2,434,111.67 ከመዝገበ እንዲሰረዙ የተደረጉና ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የተሟ ማስረጃ የሌላቸው ተገኝቷል፡፡

4.2.2 ሰኔ 30 ቀን 2005 በተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ላይ ከሚታየው ሂሳብ ውስጥ በሰኔ 30 ቀን 2006 በተዘጋጀው የሂሣብ ሪፖርቶች በተከፋይ ያልተያዘና ለመወራረዳቸው ምንም አይነት ማስረጃ ያልቀረበላቸው ብር 57,141,453.08 እናየተሟላ ማስረጃ ያልቀረበላቸው ብር 18,438,902.38 ተገኝቷል፡፡

4.2.3 ሰኔ 2005 ዋናው መ/ቤት ለሚስዮኖች ባስተላለፈው የፋክስ መልዕክት ለካፒታል ፕሮጀክት በጀት የሚላክላቸው ሚሲዮኖች የበጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት በተለያዩ ምክንያቶች መክፈል ካልተቻለ የበጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት የወጪው ምዝገባ በበጀት ዓመቱ እንዲከናወን በሂሳብ መደብ 5001 በችሮታ ጊዜ በተከፋይ ተመዝግቦ ክፍያው ከሀምሌ 30/2005 በፊት እንዲፈጸም ባስተላለፈው ትዕዛዝ መሰረት በፓሪስ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ለኦዲት የቀረቡት ማስረጃዎች ሲታዩ በተደረገው የአመዘጋገብ ችግር ከ6244 የሂሳብ መደብ ብር 27,536,784.42 አለግባብ ተቀንሶ ተገኝቷል፡፡

4.2.4 ተከፋይ ከተጣራ ሀብት ጋር በማጣጣት ከመዝገብ ለተሰረዘ የተከፋይ ሂሳብ ብር 5,216,996.40 የገንዘብ ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ፈሰስ መደረግ የሚገባው ወደ ተጣራ ሀብት ተመዝግቦ ተገኝቷል ማስረጃም ያልቀረበለት ተገኝቷል፡፡

4.2.5 በአራት ሚሲዮኖች በተከፋይ በክሬዲት ተመዝግቦ የነበረውን ብር 688,645.96 በየሀገሩ የውጭ ምንዛሬ ባንክ ሂሳብ ቁጥሮች 4102-03-05 ክሬዲት በማድረግ ተከፋዩ እንዲጣፋ ሲደረግ በቂ ማስረጃ ሳይቀርብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

4.2.6 በተለያዩ የተከፋይ የሂሳብ መደቦች በሰባት ኤምባሲዎች በተከፋይ የተያዘውን በድምሩ ብር 296,209.50 በፌዴራል መንግስት የሂሳብ አወቃቀር በማይታወቅ በሚኒስተር መ/ቤቱ ሪፖርቱም ባልተገለጸ የሂሳብ መደብ ቁጥር 1485 ክሬዲት ተደርጎ እንዲጣፋ ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

በተደረገው ማጣራት ማስረጃዎች እንዲቀርቡ የተወሰደ እርምጃ እንዲገለጽልን በኦዲት ወቅት ቢጠየቅም መልስ ባለማግኘታችን የስራ አመራር ሪፖርት ተልኮ ለዚህም በወቅቱ መልስ ባለመስጠታቸው መጋቢት 23/2008 ኦዲት ሪፖርቱ ከተላከ በኋላ በሰጡት መልስና ከመውጫ ስብሰባ በኋላ ሚያዚያ 24/2008 በሰጡት መልስ ማስረጃ ሳይኖረው ከመዝገብ ስለተሰረዘው ብር 82,365,644.21 ውስጥ ብር 39,940,068.48፤ ከ 27,411,285.24 ተሰብሳ ሂሳብ ውስጥ 7,737,442.44 እንዲሁም 36,716,650.83 ውስጥ 5,266,902.41 ማስረጃ ማዘጋጀታቸውን ገልጸዋል ይሁን እንጂ ማስረጃው የዘገየ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ይሁን እንጂ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ክቡር ዋና ኦዲተሩ ይህን ሂሳብ በተመለከተ መ/ቤቱ ማስረጃዎቹን አሟልቶ እንዲያዘጋጅና ኦዲቱን አንድ የተለየ ቡድን መድበው እንደሚሰራ ማሳሰቢያ ሰጥተዋል፡፡

1. የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶችኦዲት ዳይሬክቶሬት ዕቅድና ክንውን

1.1 የኦዲት ዕቅድና ክንውን በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና በበጀት አንፃር

ተ.ቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	ፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	10/3/08	401,374,534.42	603,827,322.07	1,005,201,856.49
2	የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር	19/04/08	43,605,541.00		43,605,541.00
3	የሰነዶች ምዝገባና መረጋገጫ ጽ/ቤት	2/2/08	66,774,290.00	-	66,774,290.00
4	የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ	14/1/08	20,384,038.14		20,384,038.00
5	የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኤጀንሲ	15/2/08	50,780,782.13		50,780,782.13
6	የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ	26/1/08	446,056,932.00		446,056,932.00
7	ንግድ ሚኒስቴር	25/4/08	65,413,676.25	26,561,320.0	91,974,996.00
8	የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	6/1/2008	34,113,984.00	70,153,300.0	104,267,282.00
9	የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	12/1/2008	24,146,649.00	35,000,000.0	59,146,649.00
10	የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ	29/3/08	22,643,130.00	-	22,643,130.00
11	የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት	12/02/08	20,992,939.00		20,992,939.00
12	የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል	7/3/2008	15,204,200.00	-	15,204,200.00
13	የፌዴራል የከተማ መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ	7/4/08	14,523.090.00	-	14,523.090.00
14	የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን	1/2/08	43,663,592.00		43,663,592.00
15	የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት	03/02/08	1,046,179,954.90	54,596,170.00	1100776124.90
16	ፍትህ ሚኒስቴር	05/01/08	102,213,172.00	16,235,788.00	118,448,960
17	የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት	06/3/08	8,809,880.00	-	8,809,880.00

ተ.ቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
18	የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት	12/04/08	26,256,920.00	25,000,000.00	51,256,920.00
19	የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	21/03/08	33,488,870.00	120,000,000.00	153,488,870.00
20	የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከል	06/12/07	12,857,520.00	-	12,857,520.00
21	የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት	01/02/08	11,993,384.89	795,580.00	12,788,964.89
22	የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን	04/01/08	21,876,379.00	-	21,876,379.00
23	የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ	16/03/08	27,616,760.00	-	27,616,760.00
24	የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ	09/03/08	25,510,430.00	-	25,510,430.00
25	የህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት	13/12/07	7,221,920.00	-	7,221,920.00
26	የህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽ/ቤት	01/12/07	5,758,170.00	-	5,758,170.00
27	የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	4/2/2008	339,165,255.40		
28	የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን	20/3/2008	2,114,207,951.13	300,000,000.0	2,414,207,951.1
29	የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት	23/3/2008	180,906,708.13	5,367,690.00	186,274,398.13
30	የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን	11/12/07	50,130,282.69		
31	የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲቲዩት	25/12/07	9,758,212.86		
32	የቀድሞው የፕራይቬይታዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ	3/03/2008	27,715,537.52		
33	የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም	15/2/2008	41,568,975.42		
34	የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲቲዩት	4/2/2008	18,917,362.20		
35	የአገር መከላከያ ሚኒስቴር	28/1/2008	2,936,580,854.00 (33.5)	0.00	2,936,580,854.00 (33.5)
36	የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	27/1/2008	1,335,249,620.08	0.00	1,335,249,620.08